፮ ፤ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ቤታ።
፯ ፤ ወርእሱ ፡ ይጐድዕ ፡ ሰማየ ።
፰ ፤ ወኵሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ።
፱ ፤ ነገሥትኒ ፡ ወጳጳሳት ፡ ይቀውሙ ፡ ዓውዶ ።
፲ ፤ መንፈቆሙ ፡ ይሰግዱ ፡ ሎቱ ።
፲፩ ፤ ወመንፈቆሙ ፡ ያሰምኩ ፡ ቦቱ ።
፲፪ ፤ ወበመልዕልቴሁ ፡ ንቡራን ፡ አዕዋፍ ፡ ብዙኃን ።
፲፫ ፤ ጸዓድኢዳን ፡ ወቀይሐን ።
፲፬ ፤ ወቦ ፡ ዘአመድ ።
፲፭ ፤ ወቦ ፡ ኮሳኩሳን ።
፲፮ ፤ ወእንዘ ፡ ትሬኢ ፡ ዘንተ ፡ ከልሐ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ በውስተ ፡ ንዋሙ ።
፲፯ ፤ ወአሕደጋ ፡ ራእያ ፡ ወነቅሐት ።
፲፰ ፤ ወአንቅሐቶ ፡ ሎቱኒ ።
፲፱ ፤ ወትቤሎ ፡ በእንተ ፡ ምንት ፡ ትኬልሃ ፤
፳ ፤ ወይቤላ ፡ ዕጹበ ፡ ራእየ ፡ ርኢኩ ።
፳፩ ፤ ወትቤሉ ፡ ምንትኑ ፡ ነገሩ ፡
፳፪ ፤ ወይቤላ ፡ ናሁ ፡ ፀሐይ ፡ ብሩህ ፡ ወፅአ ፡ እምታኅተ ፡ ፒለስ ።
፳፫ ፤ ወብዙኃን ፡ ከዋክብት ፡ ብሩሃን ፡ ኢይትኌለቍ ፡ ኀዙላን ፡ በክንፉ ።
፳፬ ፤ ወአብርሃ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ።
፳፭ ፤ ወእምብዙኃ ፡ ብርሃኑ ፡ ዋከየት ፡ ሀገር ።
፳፮ ፡ ወዘንተ ፡ ራእየ ፡ ርእዩየ ፡ ደንገፀኩ ፡ ወበከይኩ ።
፳፯ ፤ ወትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ዕጹብ ፡ ውእቱ፡ ዝነገር ፡ ወመኑ ፡ ይክል ፡ ሰሚዖቶ ።
፳፰ ፤ ወአነሂ ፡ ከማከ ፡ ርኢኩ ፡ ራእየ፡መድምመ።
፳፱ ፤ ወነገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘርእየት ።
፴ ፤ ወሰሚዖ ፡ አንከረ ፡ ውእቱኒ ።
፴፩ ፤ ወተናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ፡ ምንትኑ ፡ ዘይከውን ፡ ላዕሌነ ፡ በዝ፡መዋዕል።
፴፪ ፤ ወእንዘ ፡ ይትበሀሉ ፡ ዘንተ ፡ በበይናቲሆሙ ኖሙ ።

ዐሥራ ፡ አራት ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በተገናኙ ፡ በነጋው ፡ በመጋቢት ፡ በሃያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ የሚያጥንበትን ቀን ፡ ጨርሶ ፡ ወደቤቱ ፡ ገባ ።
፪ ፤ በዚችም ፡ ሌሊት ፡ በሃያ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ከሚስቱ ፡ ተገናኘ ።
፫ ፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተፀነሱ ።
፬ ፤ አንድነት ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ እግዚእ ፡ ሐረያ፡ ራእይ ፡ አየች ።
፭ ፤ ራእዩም ፡ እንዲህ ፡ ነው ።
፮ ፤ የብርሃን ፡ ምሰሶ ፡ ከቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ቁሞ ።
፯ ፤ የምሰሶው ፡ ራስ ፡ ከሰማይ ፡ ደርሶ ።
፰ ፤ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ።
፱ ፤ ነገሥታቱም ፡ ጳጳሳቱም ፡ በዙሪያው ፡ ቁመው ።
፲ ፤ እኩሌቶቹም ፡ ይሰግዱለታል ።
፲፩ ፤ እኩሌቶቹም ፡ እሱን ፡ ጽግ ፡ አድርገው ፡ ይቀመጣሉ ።
፲፪ ፤ በሱም፡ ላይ፡ ብዙ፡ አዕዋፍ፡ ተቀምጠባታል ።
፲፫ ፤ እኩሌቶቹ ፡ ነጫጮች እኩሌቶቹም ቀያዮች ።
፲፬ ፤ እኩሌቶቹ ፡ አመድ ፡ አመድ ፡ ይመስላሉ።
፲፭ ፤ ዝጉርጉርም ፡ ናቸው ።
፲፮ ፤ ይህን ፡ ስታይ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ በዕንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ተናገረ ።
፲፯ ፤ ሕልም ፡ ማየቷን ፡ አስተዋት ፡ ነቃች ።
፲፰ ፤ እሱንም ፡ አነቃቸው ።
፲፱ ፤ ለምን ፡ ትጮህለህ ፡ አለችው ።
፳ ፤ ድንቅ ፡ ሕልም ፡ አየሁ ፡ አላት ።
፳፩ ፤ እንደምንድነው ፡ አለችው ።
፳፪ ፤ ከምንተኛበት ፡ አኅበሩ ፡ ሥር ፡ ፀሐይ ፡ ሲወጣ ።
፳፫ ፤ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ብሩሃን ፡ ከዋክብት ፡ በክንፉ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ።
፳፬ ፤ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ሲያበሩ ።
፳፭ ፤ ከብርሃኑም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሀገሩ ፡ ሁሉ አበራ ።
፳፮ ፤ ይህን ፡ ራእይ ፡ ዓይቼ ፡ ደንግጬ ፡ አለቀስኩ ፡ አላት ።
፳፯ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ማንም ፡ ሊሰማው፡አይቻል ።
፳፰ ፤ ኔኤም ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ ድንቅ ፡ ሕልም ፡ አየሁ ፡ አለችው ።
፳፱ ፤ ያየችውን ፡ ራእይ ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ።
፴ ፤ እሱም ፡ ሰምቶ ፡ አደነቀ ።
፴፩ ፤ በዚህ ፡ ወራት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ይደረግ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጨዋወቱት ።
፴፪ ፤ ይህን ፡ ሲነጋገሩ ፡ ለእየራሳቸው ፡ ተኙ ።

፴፫ ፤ ወአስተርአያ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ በውስተ ፡ ንዋማ ።

፴፬ ፤ ወይቤላ ፡ ዮም ፡ ተፀንሰ ፡ በውስተ ፡ ማኅፀንኪ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ዘነገርኩኪ ፡ ቅድመ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ሀሎ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔኪ ።

፴፭ ፤ ይእዜ ፡ ዘነገርኩኪ ፡ ተፀንሰ ፡ በማኅፀንኪ ፡ ፍቁር ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበኀበ ፡ ማርያም ፡ እሙ ።

፴፮ ፤ በኀበ ፡ መላእክትኒ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ጥቀ።

፴፯ ፤ ወኢይከውን ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ መጠ፡ አሐቲ ፡ እምትሩፋት ፡ ገድሉ ።

፴፰ ፤ ወዘንተ ፡ እምድኅረ ፡ ይቤላ ፡ ተሰወረ ፡ እምኔሃ ።

፴፱ ፤ ወከማሁ ፡ አስተርአዮ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ በከመ ፡ ይቤላ ።

፵ ፤ ወበጽባሕ ፡ ተንሥአ ፡ ወይቤላ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ምንተ ፡ ርኢኪ ፡ በዳግማይ ፡ ንዋምኪ ።

፵፩ ፤ ወትቤሎ ፡ አስተርአየኒ ፡ ሚካኤል ፡ ወነገረኒ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤላ ።

፵፪ ፤ ወውእቱኒ ፡ ይቤላ ፡ ሊተኒ ፡ ከማኪ ፡ ይቤለኒ ።

፵፫ ፤ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ያስተዓፅቡ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሆሙ ።

፵፬ ፤ ወውእቱሰ ፡ አልባሳተ ፡ ሰርጕ ፡ ዘአምጽአት ፡ እምነ ፡ ዳሞት ።

፵፭ ፤ ሤጡ ፡ ወወሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን፡ ወኢተርፈ፡ ውስተ ፡ ቤ ሙ ፡ ወኢምንትኒ።

፵፮ ፤ እስመ ፡ አዘዛ ፡ ቅድመ ፡ ለእግዚእ፡ ሐረያ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አመ ፡ ሜጣ ፡ እምጼዋዌ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኀቢ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ፡ አልባሰ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕሌኪ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ።

፵፯ ፤ በከመ ፡ ነገራ ፡ ለክሙሰ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርእየክሙ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየኀጥአክሙ ።

መዝ ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፵፰ ፤ ወውእቶሙኒ ፡ ገብሩ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ።

፵፱ ፤ ወኢያንተጉ ፡ እምቃሉ ፡ ወኢአሐተ ።

፶ ፤ ወውእቱሂ፡ ኢያኅጥአሙ ፡ እምዘፈቀዱ ።

መዝ ፡ ፴፯ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ።

፶፩ ፤ እስመ ፡ ኢያስተኄንስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሰ ፡ ጻድቅት ።

፶፪ ፤ ወገቢረ ፡ በዓሉሰ ፡ ለሚካኤልአፈድፈዱ፡ እምዘ ፡ ቀዳሚ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ እምድኅረ ፡ ፱ ፡ አውራኀ ፡ አመ፡ ፳ ፡ ወ፬ ፡ ለታኅሣሥ ፡ ተወልደ ።

፴፫ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ ተኝታ ፡ ሳለች ፡ቅዱስ ሚካኤል ፡ ታያት ፡ ተነጋገራት ።

፴፬ ፤ ቀድሞ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልጃለሽ ፡ ብዬ የነገርኩሽ ፡ የተመረጠ ፡ ልጅ ፡ ዛሬ ፡ በማኅፀንሽ ፡ ተፀነሰ ፡ አላት ።

፴፭ ፤ በእግዚአብሔር ፡ በእመቤታችንም፡ዘንድ የተወደደ ፡ ነው ።

፴፮ ፤ በመላእክትም ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ነው ።

፴፯ ፤ ከብዙ ፡ ሥራው፡ ላንዲቱ ፡ ሰማይና ፡ ምድር መጠኑ ፡ አይሆንም ።

፴፰ ፤ ይህን ፡ ከነገራት ፡ በኋላ ፡ ተሰወራት ።

፴፱ ፤ ለጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ለሷ ፡ እንደነገራት ፡ ነገረው ።

፵ ፤ ዳግመኛ ፡ በተኛሽ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አየሽ ፡ አላት ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ።

፵፩ ፤ ሚካኤል ፡ ታየኝ ፡ ተነጋገረኝ ፡ አለችው ፡ የነገራትን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ።

፵፪ ፤ እሱም ፡ ለኔም ፡ እንጂ ፡ እንዳንቺ ፡ ነገረኝ አላት ።

፵፫ ፤ እግዚአብሔር ፡የሠራላቸውን ፡ ሥራ ፡ እያደነቁ ፡ ተቀመጡ ።

፵፬ ፤ እነሱም ፡ ከዳሞት ፡ ያመጣችውንም ፡ የጌጧን ፡ ልብስ ።

፵፭ ፤ ሸጠው ፡ ከቤታቸው ፡ ምንም ፡ ሳያስቀሩ ፡ ለደኀ ፡ ሰጡት ።

፵፮ ፤ ቀድሞ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለእግዚእ ሐረያ ፡ከምርኮ ፡ በመለሳት ፡ ጊዜ ፡ ይህን፡ ሁሉ ፡ የወርቅ ፡ ልብስ ፡ ጌጥሽን ፡ ለደሀ ፡ ስጭው ፡ ብሎ ፡ ነግሯት ፡ ነበርና ፡ እንደ ነገራት ።

፵፯ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቃችኋል ፡ የሚያሳጣችሁ ፡ የለም ።

መዝሙር ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፵፰ ፤ እነሱም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ።

፵፱ ፤ ከአዘዛቸው ፡ አንዲት ፡ ስንኳ፡አላስቀሩም ።

፶ ፤ እሱም ፡ ያሻቸውን ፡ ሁሉ ፡ አላሳጣቸውም።

መዝሙር ፡ ፴፯ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ።

፶፩ ፤ እግዚአብሔር ወዳጆቹን ፡ አያስቸግርምና ።

፶፪ ፤ የቅዱስ ፡ ሚካኤልንም ፡ በዓል ፡ ማዘከር፡ ግን ፡ ከቀድሟቸው ፡ ይልቅ ፡ እያበዙ ፡ ያዘክሩ ፡ ጀመር ።

ዐሥራ ፡ አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ከዘጠኝ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በታኅሣሥ ፡ በሃያ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ፍሥሐ ጽዮን ተወለደ ።

፪ ፤ ወኮነ ፡ ዓቢይ ፡ ፍሥሐ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ በውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡፡
፫ ፤ እስመ ፡ መካን ፡ ብእሲቱ ፡ ወለደት ፡ ወልደ ፡፡
፬ ፤ ወራእዩኒ ፡ መንክር ፡ ጥቀ ፡ ጸዓዳ ፡ ከመ ፡ አስሐትያ ፡፡
፭ ፤ ወቀይሁ ፡ ከመ ፡ ጽጌረዳ ፡፡
፮ ፤ ወገብሩ ፡ ምሳሐ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡፡
፯ ፤ ወለሰብአ ፡ ሀገርኒ ፡ በበሥርዓቶሙ ፡፡
፰ ፤ ወእምድኅረ ፡ ፍሥሓሆሙ ፡ አተው ፡ እንዘ ያነክሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠናያተ ፡ ዘገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወለብእሲቱ ፡፡
፱ ፤ ወበሣልስት ፡ ዕለት ፡ እምዘ ፡ ተወልደ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ በእምርት ፡ ዕለት ፡፡
፲ ፤ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዝካረ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ለመድኃኒነ ፡፡
፲፩ ፤ ጊዜ ፡ ፫ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ አንሥአ ፡ እደዊሁ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ወአንቃዕደወ ፡ ላዕለ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ከልሐ ፡፡
፲፪ ፤ ወባረኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡፡
፲፫ ፤ ፩ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ውእቱ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡
፲፬ ፤ እስመ ፡ በይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ይወርድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ኅበ ፡ ፈቀደ ፡፡
፲፭ ፤ ወሕፃንኒ ፡ ርእየ ፡ ርደተ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ አቅረበ ፡ ዘንተ ፡ ፫ ፡ ቅዳሴያተ ፡፡
፲፮ ፤ ለአምላኩ ፡ እንዘ ፡ ይገኒ ፡ በከመ ፡ መሐሮ ፡ ለሊሁ ፡፡
፲፯ ፤ ወሰሚዓ ፡ እሙ ፡ ነገረ ፡ ጽኑዓ ፡ እምአፈ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ አስተዐፀበት ፡ በልባ ፡፡
፲፰ ፤ ወትቤሎ ፡ አ ፡ ፍሡሕ ፡ ወልድ ፡ ምንተ ፡ ትብል ፡፡
፲፱ ፤ ዝሰ ፡ ቃል ፡ ግብረ ፡ አቡከ ፡ ውእቱ ፡፡
፳ ፤ ወለከሰ ፡ ጠቢወ ፡ አጥባት ፡፡
፳፩ ፤ ወሶበ ፡ አተወ ፡ ምታ ፡ ነገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘከመ ፡ ይቤ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡፡
፳፪ ፤ ወሰሚዖ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ አንከረ ፡ ወይቤ ፡፡
፳፫ ፤ ወይቤ ፡ ሕይወኒ ፡ ወልድየ ፡ ለነዋህ ፡ እም ፡፡
፳፬ ፤ ከመ ፡ እርአይ ፡ ኪያከ ፡ እንዘ ፡ ትቄድስ ፡ ከመዝ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

፪ ፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ በጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ፡፡
፫ ፤ መካን ፡ የነበረች ፡ ሚስቱ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወልዳለችና ፡፡
፬ ፤ መልኩም ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ እንደመስታወት ፡ የሚያንጸባርቅ ፡ ነው ፡፡
፭ ፤ ቅላቱም ፡ እንደጽጌረዳ ፡ ነው ፡፡
፮ ፤ ለነዳያንም ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ ዋሉ ፡፡
፯ ፤ ለሀገራቸውም ፡ ሰዎች ፡ እንደማዕርጋቸው ፡ ምሳ ፡ አደረጉላቸው ፡፡
፰ ፤ በዓሉንም ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያና ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገላቸውን ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ እያደነቁ ፡ ወደቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ፡፡
፱ ፤ ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠው ፡ ልጅ በተወለደ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡፡
፲ ፤ ይህችም ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የትንሣኤው ፡ መታሰቢያ ፡ በምትሆን ፡ በታወቀች ፡ ቀን ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡፡
፲፩ ፤ ከመዓልቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ይህ ፡ ብላቴና ፡ እጆቹን ፡ አንሥቶ ፡ ወደሰማይ ፡ ተመልክቶ ፡ ጮሆ ፡ ተናገረ ፡፡
፲፪ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አመሰገነ ፡፡
፲፫ ፤ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ አብ በአካል ፡ በስም ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና አንድ ፡ የሚሆን ፡ ወልድ ፡ በአካል ፡ በስም ልዩ ፡ ነው ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአካል ፡ በስም ፡ ልዩ ፡ ነው ፡፡
፲፬ ፤ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ወደደበት ፡ ይወርዳልና ፡፡
፲፭ ፤ ሕፃኑም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲወርድ ፡ አይቶ ፡፡
፲፮ ፤ ይህን ፡ ሦስት ፡ ምስጋና ፡ አቀረበ ፡ እሱ ፡ እንዳስተማረው ፡ ለፈጣሪው ፡ እየተገዛ ፡፡
፲፯ ፤ እናቱም ፡ ከተመረጠ ፡ ልጅዋ ፡ ይህን ፡ ጽኑ ነገር ፡ ሰምታ ፡ በልቡናዋ ፡ አደነቀች ፡፡
፲፰ ፤ ልጄ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ አለችው ፡፡
፲፱ ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ ያባትህ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡፡
፳ ፤ ላንተ ፡ ግን ፡ የሚገባህ ፡ ጡት ፡ መጥባት ፡ ነው ፡፡
፳፩ ፤ ባሏ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ተመልሶ ፡ ወደቤቱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ፡፡
፳፪ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ አደነቀ ፡፡
፳፫ ፤ ልጄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳድግህ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ያኑርህ ፡፡
፳፬ ፤ በቤተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ እያልክ ስትቀድስ ፡ ዓይህ ፡ ዘንድ ፡፡

፳፭ ፡ ወለዝንቱሰ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ይሜግብዎ ፡
መላእክት ፡ ዘልፈ ፡ እንዘ ፡ ይጼልሉ ፡ አክ
ናፊሆሙ ፡መልዕልቴሁ ።
፳፮ ፤ ወውእቱኒ ፡ ይትለሐይ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ዕበ ፡ ይሬእዮሙ ፡ ሰፊሆሙ ፡ አክናፈ ።
፳፯ ፤ ወይስሕቅ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ።
፳፰ ፤ ወአልቦ ፡ አመ ፡ ይበኪ ፡ በከመ ፡ ይበ
ክዩ ፡ ሕፃናት ።
፳፱ ፤ እስመ ፡ አፈ ፡ ራትዓን ፡ ይመልእ ፡ ሰሐቀ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ፤ ወአመ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ንጽሕ ፡ ዘው
እቱ ፡ ፵ ፡ ዕለት ።
፪ ፡ ወሰድዎ ፡ ለሕፃን ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ።
፫ የሐብዎ ፡ ስመ ።
፬ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ህየ ፡ አጥመቅዎ ፡ ወሰመይዎ ፡
ስሞ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።

፭ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ፍሥሐሃ ፡ ለጽዮን ።

፮ ፤ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ያስተፍስሐ ፡ ለቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ በቃለ ፡ ምሕሮሁ ፡ ሐዋዝ ።

፯ ፤ ወያስተናሥእ ፡ ጥቅማ ፡ በሃይማኖቱ፡ጽኑዕ።

፰ ፤ ወአቲዎሙ ፡ ቤቶሙ ፡ አስተርአዮ ፡ ቅዱስ
ሚካኤል ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ በንዋሙ ።

፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ዘአብ
ሠርኩከ ፡ ቅድመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡
ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሐቌከ ።
፲ ፤ ወስሙኒ ፡ ኢኮነ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።
፲፩ ፤ ካልዕ ፡ ውእቱ ፡ ስሙ ፡ ወስውር ፡ ውእቱ፡
ንምኔከ ።
፲፪ ፤ ወሀሎ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሕተ ፡ አክናፊሁ ፡ ለእ
ግዚእ ፡ መናፍስት ።
፲፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ፀጋ ፡ ዘአብ ፡ ንግረኒ ፡ እግዚእየ ፡
መኑ ፡ ውእቱ ፡ ስሙ ።
፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ስምሰ ፡ እን
ግርከ ፡ ኢተፈኖኩ ።
፲፭ ፤ ወባሕቱ ፡ ራእየ ፡ ዘርኢክሙ ፡ አንተ ፡ ወብ
እሲትከ ፡ አመ ፡ ፅንሰቱ፡ ለወልድከ ፡ ኅሩይ
አፈክር ፡ ለክሙ ፡ ተፈኖኩ ።
፲፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ፀጋ ፡ ዘአብ ፡ በልኬ ፡ ፈክር፡
ሊተ ፡ ንግዚእየ ።
፲፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ሚካኤል ፡ ፀሐይ ፡ እንዘ ፡ ይሠ
ርቅ ፡ እቤትከ ፡ ዘርኢከ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
ወልድከ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምሐቌከ ።
፲፰ ፤ ዘበብርሃኑ ፡ ይሰድድ ፡ ጽልመተ ፡ ጌጋይ ፡
ንምላዕለ ፡ መሃይምናን ።
፲፱ ፤ ወከዋክብት ፡ ብሩሃን ፡ ተኀቤሎሙ ፡ በአ
ክናፊሁ ፡ ዘርኢከ ፡ ደቂቁ ፡ እሙንቱ ፡ እለ

፳፭ ፤ ይህንም ፡ ብላቴና ፡ መላእክት ፡ ክንፋቸውን፡
እየጋረዱ ፡ ዘወትር ፡ ይመግቡት ፡ ነበር ።

፳፮ ፤ እሱም ፡ ክንፋቸውን ፡ ሲጋርዱት ፡ ባያቸው ፡
ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ይጫወት ፡ ነበር ።
፳፯ ፤ ሁልጊዜ ፡ ይስቅ ፡ ነበር ።
፳፰ ፤ ሕፃናት ፡ እንደሚያለቅሱ ፡ አያለቅ
ስም ፡ ነበር ።
፳፱ ፤ ቅኖች ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ ደስ ፡ ይላቸ
ዋልና ።

ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከ፫ሥሕ ፡ የሚነጹበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡
ጊዜ ፡ ባርባው ፡ ቀን ።
፪ ፤ በአሪት ፡ እንደተጻፈው ፡ ሕፃኑን ፡ ወደቤተ
መቅደስ ፡ ወሰዱት ።
፫ ፤ ስም ፡ ያወጡለት ፡ ዘንድ ።
፬ ፤ ከቤተ ፡ መቅደስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አጥ
ምቀው ፡ ስሙንም ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡
አሉት ።
፭ ፤ ትርጓሜውም ፡ የጽዮን ፡ ደስታዋ ፡ ነው ፡
ማለት ፡ ነው ፡
፮ ፤ ባማረ ፡ በተወደደ ፡ ትምህርቱ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያንን ፡ (ምእመናንን)ደስ ፡ ያሰኛት
ዘንድ ፡ አለውና ።
፯ ፤ በጽኑም ፡ ሃይማኖቱ ፡ ሥራዋን ፡ ያጸና ፡
ዘንድ ።
፰ ፤ ወደቤታቸውም ፡ ተመልሰው ፡ ከገቡ ፡
በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡
በሕልሙ ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ።
፱ ፤ ቀድሞ ፡ የተመረጸ ፡ ልጅ ፡ በአብራክህ ፡
አለ ፡ ብየ ፡ የነገርኩህ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲ ፤ ስሙም ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ አይደለም ።
፲፩ ፤ ስሙ ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ካንተ ፡ የተሰወረ፡ነው።

፲፪ ፤ በልበ ፡ ሥላሴ ፡ ታውቆ ፡ ያለ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ጌታዬ ፡ ስሙ ፡ ማነው ፡
ንገረኝ ፡ አለው ።
፲፬ ፤ ስሙን ፡ ልነግርህ ፡ አልተላኩም ።

፲፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ብላቴና ፡ በተፀነሰ ፡ ጊዜ፡
አንተም ፡ ሚስትህም ፡ ያያችሁትን ፡ ህልም
ልተረጕምላችሁ ፡ ታዝዣለሁ ፡ እንጂ።
፲፮ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ በል ፡ ጌታዬ ፡ ተርጕምልኝ
አለው ።
፲፯ ፤ ፀሐይ ፡ ከቤትህ ፡ ሲመጣ ፡ ያየኸው፡ ከአ
ብራክህ ፡ የተከፈለ ፡ ይህ ፡ ልጅህ ፡ ነው።
፲፰ ፤ በብርሃኑ ፡ ከምእመናን ፡ ላይ ፡ የኃጢአት
ጨለማን ፡ የሚያርቅ ።
፲፱ ፤ በክንፋም ፡ ላይ ፡ ታዝለው ፡ ያየሃቸው ፡
ከዋክብት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይወለዱ፡

ሀለዎሙ፡ይትወለዱ፡ሎቱ፡እመንፈስ፡ቅዱስ ።
፳ ፤ ብእሲትከኒ ፡ ዘርእየት ፡ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡
ቀዊሞ ፡ በመልዕልተ፡ ቤትከሙ ፡ ወርእሱ ፡
ይጐድዕ ፡ ሰማየ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ፡ወልድከ።
፳፩ ፤ ነገሥተ ፡ ምድር ፡ ጳጳሳትኒ ፡ ዘርእየት ፡
እንዘ ፡ ይገንዩ ፡ ሎቱ ፡ በአማን ፡ ይሰግዱ ፡
ነገሥተ ፡ ምድር ።
፳፪ ፤ ወይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ አሕዛብ ።
፳፫ ፤ ወይከውን ፡ ምስማከ ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ።
፳፬ ፤ ውስተ ፡ አርእስተ ፡ አድባር ።
፳፭ ፤ ወይነውሕ ፡ እምአርዝ ፡ ፍሬሁ ።

፳፮ ፤ ወይበቍል ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ሣዕረ ፡
ምድር ።
፳፯ ፤ ወይከውን ፡ ቡሩከ ፡ ስሙ ፡ ለዓለም ።
መዝ ፡ ፸ ፡ ቍ ፡ ፲፯
፳፰ ፤ ወበከመ ፡ ይትሌዐል ፡ ሰማይ ፡ እምድር ፡
ከማሁ ፡ ይትሌዓል ፡ ዝክረ ፡ ስሙ ፡ እምእለ
ከማሁ ።
፳፱ ፤ ዝውእቱ ፡ ፍካሬ ፡ ሕልምክሙ ።
፴ ፤ ወምስለዝ ፡ ብሂለ ፡ ቃል ፡ ተሰወረ ፡ መል
አክ ፡ እምኔሁ ።
፴፩ ፤ ወተንሢአ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ይቤላ ፡ ለብእሲቱ
አ ፡ እኅትየ ፡ መርዓት ፡ ምንተ ፡ ርኢኪ ፡
በዛቲ ፡ ሌሊት ፤

፴፪ ፤ ወትቤሎ ፡ አልቦ ፡ ዘርኢኩ ።
፴፫ ፤ ወባሕቱ ፡ በክቡድ ፡ ንዋም ፡ ኀደርኩ ፡
ኵሎ ፡ ኑኃ ፡ ሌሊት ።
፴፬ ፤ ወይቤላ ፡ ግሩመ ፡ ራእየ ፡ ርኢኩ ፡ አንሰ ።
፴፭ ፤ ውእተ ፡ ራእየ ፡ ዘርኢነ ፡ ቅድመ ፡ እመ ፡
ዕንስቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ፈከረ ፡ ሊተ
ሚካኤል ።

፴፮ ፤ ወነገራ ፡ ኵሎ ፡ ዘከመ ፡ ይቤሎ ።
፴፯ ፤ ወሰሚዓ ፡ አንከረት ፡ ወተደመት ።
፴፰ ፤ ወተበሃሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ምንትኑ ፡ ዘይ
ከውን ፡ እምዝንቱ ፡ ሕፃን ።
፴፱ ፤ እስመ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩ ፤ ወአመ ፡ ኮነ ፡ ለፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ፩ ፡ ዓመተ
ወ፫ተ ፡ አውራኃ ፡ ኮነ ፡ ዓቢይ ፡ ረኃብ ፡
ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ሸዋ ።
፪ ፤ ወፈድፋደሰ ፡ በምድረ ፡ ዞረሬ ።
፫ ፤ ወትቤሎ ፡ እግዚእ፡ሐረያ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡
ናሁ ፡ በዓሉ ፡ ለሚካኤል ፡ አልጸቀ ፡ ምንተ ፡
ንገብር ፡ ዘአልብነ ፡ ምንትኒ ፡ ውስተ፡እዴነ።

፬ ፤ ነሐድግኑ ፡ ገቢረ ፡ በዓሉ ፡ ለሚካኤል ፡
ዘእንበለ ፡ ንሙት ፤
፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ነዓ ፡ ሑር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፡ ወግበር ፡ ጸሎተ ፡ በህየ ።

ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ ልጆቹ ፡ ናቸው ።
፳ ፤ ሚስትህም ፡ በቤታችሁ ፡ ላይ ፡ የብርሃን ፡
ምሰሶ ፡ ቆሞ ፡ ራሱ ፡ ከሰማይ ፡ ደርሶ ፡
ያየችው ፡ ይህ ፡ ልጅህ ፡ ነው ።
፳፩ ፤ ነገሥታቱ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሲገዙለት ፡ ያየችውም ፡
በውነት ፡ ነገሥታቱ ፡ ይሰግዱለታል ።

፳፪ ፤ አሕዛብም ፡ ይገዙለታል ።
፳፫ ፤ ለሁሉም ፡ መጸጊያ ፡ ይሆናል ።
፳፬ ፤ ከነገሥታቱ ፡ በላይ ፡ ሁኖ ፡ ይኖራል ።
፳፭ ፤ ተአምራቱ ፡ ከዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ይበዛል ፡ ሥፍር ፡
ቍጥር ፡ የለውም ።
፳፮ ፤ እንደሣዕረ ፡ ምድር ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

፳፯ ፤ ስሙም ፡ ለዘላለም ፡ ሲመሰገን ፡ ይኖራል ።

፳፰ ፤ ሰማይ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ እንደሆነ ፡ የሱም
ስም ፡ አጠራሩ ፡ እንደሱ ፡ ካሉ ፡ ከቅዱ
ሳን ፡ ምእመናን ፡ በላይ ፡ ሁኖ ፡ ይኖራል ።
፳፱ ፤ የሕልማችሁ ፡ ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ ነው፡አለው።
፴ ፤ ይህን ፡ ከነገረው ፡ በኋላ ፡ መልአኩ ፡ ከሱ ፡
ተሰወረ ።
፴፩ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ከዕንቅልፉ ፡ ተነሥቶ ፡
ሚስቱን ፡ እኅቴ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡
ምን ፡ አየሽ ፡ አላት ።

፴፪ ፤ ያየሁት ፡ የለም ።
፴፫ ፤ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ዕንቅልፍ ፡ ጸንቶብኝ
አደርኩ ፡ እንጂ ፡ አለችው ።
፴፬ ፤ እኔስ ፡ ግሩም ፡ ህልም ፡ አየሁ ፡ አላት ።
፴፭ ፤ ቀድሞ ፡ ይህ ፡ ብላቴና ፡ በተፀነስ ፡ ጊዜ ፡
ያን ፡ ያየነውን ፡ ህልም ፡ ሚካኤል ፡ ተር
ጕሞ ፡ ነገረኝ ፡ ብሎ ።

፴፮ ፤ የነገረውን ፡ ሁሉ ፡ ነገራት ።
፴፯ ፤ ሰምታ ፡ አደነቀች ።
፴፰ ፤ ከዚህ ፡ ከብላቴና ፡ የተነሣ ፡ የሚደረገው ፡
ምን ፡ ይሆን ፡ ተባባሉ ።
፴፱ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አድሮበታልና ።

ዐሥራ ፡ ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡
ወር ፡ ከሆነው ፡ በኋላ ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡
ሁሉ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ።
፪ ፤ ይልቁንም ፡ በዞረሬ ፡ አውራጃ ፡ ጸና ።
፫ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ እንዲህ ፡
አለችው ፡ እነሆ፡ የሚካኤል ፡ በዓል ፡ ደረሰ
በጃችን ፡ ምንም ፡ የሌለን ፡ ምን ፡ እናደርጋ
ለን ፡ አለችው ።
፬ ፤ ወይንስ ፡ ሳንሞት ፡ በዓሉን ፡ እንተዋለን ።

፭ ፤ አሁንም ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሂደህ ፡ ወደ
እግዚአብሔር ፡ አመልክት ።

፮ ፤ ከመ ፡ ያእምረነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግብረ ፡ ዘንገብር ።
፯ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ያንጸፈጽፍ ፡ አንብዕ ፡ እምአዕይንቲሃ ።
፰ ፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ጸጋዘአብ ፡ እንዘ ፡ ትበኪ ፡ ብእሲቱ ፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ በዓሉ ፡ ለሚካኤል ።
፱ ፤ ኀዘነ ፡ ፈድፋደ ፡ ወተሰብረ ፡ ልቡ ።
፲ ፤ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወቦአ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአድነነ ፡ መልዕልተ ፡ መንበረ ፡ ታቦት ፡ ወአንጠብጠበ ፡ አንብዖ ።
፲፩ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሚ ፡ እግበር ፡ እግዚእ ፡ናሁ ፡ ገቢረ ፡ በዓሉ ፡ ለሚካኤል ፡ ተጸርዓ ፡ እምኔየ ፡ ወአልብየ ፡ ምንትኒ ፡ ውስተ ፡ ቅዴየ ።
፲፪ ፤ ፍትነኒ ፡ ወአመክር ፡ ልብየ ።
፲፫ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥየ ፡ ወአምላኪየ ።
፲፬ ፤ ኀቤከ ፡ አንቀዓዱ ፡ አዕይንትየ ፡ አመ ፡ ምንዳቤየ ።
፲፭ ፤ ወቅድሚከ ፡ እክው ፡ ስእለትየ ።
፲፮ ፤ ለከ ፡ እነግር ፡ ኃዘንየ ፡ ወለከ ፡ አየድዕ ፡ ትካዝየ ።
፲፯ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘሴሰይኮሙ ፡ መና ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ በእደ ፡ ሚካኤል ፡ መልአክከ ።
፲፰ ፤ እምሐቅለ ፡ ሲና ፡ እስከ ፡ ቃዴስ ፡ በርኔ ።
፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ አንተ ፡ አምረኒ ፡ ፍኖተ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ እገብር ።
፳ ፤ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ ይጼሊ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ።
፳፩ ፤ ወብእሲቱ ፡ ትበኪ ፡ ፈድፋደ ፡ ነቢራ ፡ በዴዴ ፡ አንቀጸ ፡ ቤታ ።
፳፪ ፤ ወሶበ ፡ ርእያ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ እንዘ ፡ ትበኪ ፡ ኀሙ ፡ ገሠሠ ፡ አናብኢሃ ፡ በአፃብዒሁ ።
፳፫ ፤ ወትቤሎ ፡ ምንተ ፡ ይብል ፡ ዝ ፡ ሕፃን ፡ እስመ ፡ ዘኢየአምር ፡ ከመ ፡ ይጸራዕ ፡ ገቢረ ፡ በዓሉ ፡ ለሚካኤል ፡ ወአፍአመቶ ፡ አጥባቲሃ ።
፳፬ ፤ ወዐበየ ፡ ጠቢወ ፡ ጥበ ፡ ቀጸባ ፡ መንገለ ፡ ቤት ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ አብእኒ ።
፳፭ ፤ ይእቲሰ ፡ ኢያእመረት ።
፳፮ ፤ ወከልሐ ፡ ወአንብዓ ፡ እንዘ ፡ ይኤምር ፡ ገቢአ ፡ መንገለ ፡ ቤት ።
፳፯ ፤ ወሶበ ፡ አእመረቶ ፡ እሙ ፡ ትቤ ፡ ምንት ፡ ብየ ፡ በጊዜ ፡ በዊእ ፡ ውስተ ፡ ቤት ።
፳፰ ፤ ወቦአት ፡ በእንተ ፡ ብካየ ፡ ወልዳ ።
፳፱ ፤ ወሀሎ ፡ ውስተ ፡ አስፈሬድ ፡ ሐሪጸ ፡ ሥርናይ ፡ ንስቲት ፡ ዘየአክል ፡ መጠነ ፡ መሥፈርተ ፡ ቃቡ ።

፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ የምናደርገውን ፡ ያመለክተን ፡ ዘንድ ።
፯ ፤ ይህንንም ፡ ስትናገረው ፡ ዕንባዋን ፡ እያፈሰሰች ፡ ነው ።
፰ ፤ የሚካኤል ፡ በዓሉ ፡ ታጐሎብኝ ፡ ብላ ፡ ሚስቱ ፡ ስታለቅስ ፡ በየ ፡ ጊዜ ።
፱ ፤ ልቡ ፡ ስብርብር ፡ ብሎ ፡ አዘነ ።
፲ ፤ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔዶ ፡ ከመቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ከመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ።
፲፩ ፤ በጂ ፡ ምንም ፡ የለኝ ፡ የሚካኤል ፡ በዓል ፡ ታጐለብኝ ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ምን ፡ ላድርግ እያለ ፡ አለቀሰ ።
፲፪ ፤ ልቡናዬን ፡ መርምረው ።
፲፫ ፤ ፈጣሪዬን ፡ ንጉሤም ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፲፬ ፤ ወዳንተ ፡ አንጋጥጣለሁ ።
፲፭ ፤ ልመናዬን ፡ ወዳንተ ፡ አቀርባለሁ ።
፲፮ ፤ ችግሬን ፡ ሐሳቤን ፡ ላንተ ፡ እነግራለሁ ።
፲፯ ፤ በባለሟልህ ፡ በሚካኤል ፡ እጅ ፡ እስራኤልን መና ፡ የመገብካቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፲፰ ፤ ከሲና ፡ ዱር ፡ ጀምረህ ፡ እስከ ፡ ቃዴስ ፡ በርኔ ፡ ድረስ ።
፲፱ ፤ ዛሬም ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ እንደማደርገው ፡ ነገር ፡ አመልክተኝ ።
፳ ፤ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ሲለምን ።
፳፩ ፤ ሚስቱም ፡ በቤቷ ፡ ደጃፍ ፡ ተቀምጣ ፡ ብዙ ታለቅስ ፡ ነበር ።
፳፪ ፤ የተመረጠ ፡ ልጅዋም ፡ ስታለቅስ ፡ አይቶ ፡ ዕንባዋን ፡ በጣቱ ፡ ጠረገላት ።
፳፫ ፤ የሚካኤል ፡ በዓል ፡ እንዲታጐል ፡ አያውቅ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ይለኛል ፡ ብላ ፡ ጡቷን ፡ አጎረሰችው ።
፳፬ ፤ መጥባቱን ፡ ትቶ ፡ ወደቤት ፡ አግቢኝ ፡ እንደሚል ፡ ወደቤት ፡ ጠቅሶ ፡ አሳያት ።
፳፭ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ አላወቀችም ።
፳፮ ፤ ወደቤት ፡ ለመግባት ፡ እያመለከተ ፡ ጮኾ ፡ አለቀሰ ።
፳፯ ፤ እናቱ ፡ ወደቤት ፡ አግቢኝ ፡ ማለቱን ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ብትገባ ፡ ከቤት ፡ ምን ፡ አለኝ ፡ አለች ።
፳፰ ፤ ልጅዋ ፡ ስላለቀሰ ፡ ይዛው ፡ ገባች ።
፳፱ ፤ ጥቂት ፡ የሥንዴ ፡ ዱቄት ፡ በዕንቅብ ፡ ውስጥ አንድ ፡ ድርጎ ፡ የሚሆን ፡ ነበረ ።

፴ ፤ ወቀጸባ ፡ ሕፃን ፡ ለእሙ ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ መጥውኒ ፡ ውእተ ፡ አስፈሬዳ ።
፴፩ ፤ አምጽአት ፡ ሎቱ ፡ ወመጠወቶ ።
፴፪ ፤ ወደየ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለውእቱ ፡ ሐሪጸ ፡ ሥርናይ ።
፴፫ ፤ ወበጊዜሃ ፡ መልአ ፡ ውስተ ፡ አስፈሬዳ ፡ ወተክዕወ ፡ ዘተርፈ ።
፴፬ ፤ ወርእያ ፡ እሙ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ደንገፀት ፡ ፈድፋደ ።
፴፭ ፤ ወካዕበ ፡ ቀጸባ ፡ ወልድ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ከመ ፡ ታምጽእ ፡ ሎቱ ፡ ካልአ ፡ አስፈሬዳ ፡ ወአምጽአት ፡ ሎቱ ።
፴፮ ፤ ወወደየ ፡ ንስቲተ ፡ ሐሪጸ ፡ ውእቱ ፡ ከ መ ፡ ዘይትለሐይ ፡ ወመልአ ፡ ህየኒ ።
፴፯ ፤ ወአምጽአት ፡ ሎቱ ፡ ሣልሰቲ ፡ ወመልአ ፡ ከማሁ ።
፴፰ ፤ ወሶበ ፡ ደክመት ፡ ጸውዓታ ፡ ለዓመታ ከመ ፡ ትርድአ ።
፴፱ ፤ ወአምጽአት ፡ ፱ተ ፡ አስፈሬዳተ ፡ ወመልአ ፡ ውስቴቶሙኒ ።
፵ ፤ ወኮነ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ።
፵፩ ፤ ወወረደ ፡ በረከተ ፡ እግዚአብሔር፡ በይእቲ ዕለት ፡ ለአለ ፡ ቤቱ ። ለጸጋ ፡ ዘአብ ።
፵፪ ፤ ወወልድስ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ኮነ ፡ ያንፈር ዕድ ፡ ሶበ ፡ ይሬኢ ፡ በረከተ ፡ እንዘ ፡ ይወ ርድ ፡ እምሰማይ ፡ ከመ ፡ ጠል ።
፵፫ ፤ ወሀለየት ፡ እሙ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ዝንቱ ፡ ወልድየ ፡ ከሃሊ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ አምላኩ።
፵፬ ፤ ወአምጽአት ፡ ልሁክትምተ ፡ ዘቅብዕ ፡ ዘቦቱ ንስቲተ ፡ ቅብዕ ።
፵፭ ፤ ወወደየት ፡ እዴሁ ፡ ውስቴቱ ፡ አማዕቲባ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ።
፵፮ ፤ ወፈልሐ ፡ ከመ ፡ ዘአርሰንዎ ፡ በእሳት ፡ ወመ ልአ ፡ ፍጡነ ።
፵፯ ፤ ወአምጽአት ። አመታ ፡ ዐቢየነ ፡ ቅሱታተ ፡ ወቀድሐት ፡ እምውእቱ ፡ ቅብዕ ፡ ውስቴ ቶሙ ፡ ወመልኡ ፡ ኵሎሙ ።
፵፰ ፤ ወአምጽአት ፡ ሙዳየ ፡ ጌው ፡ ወወደየት ፡ እዴሁ ፡ ለሕፃን ፡ ዲቤሁ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ አማዕቲባ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ።
፵፱ ፤ ወመልአ ፡ ፍጡነ ፡ ወአገሐሰት ፡ እምኔሁ ፡ ውስተ ፡ ዓቢይ ፡ ጽሕርት ፡ ወመልአ፡ከማሁ።
፶ ፤ ወአምጽአት ፡ ካዕበ ፡ ገና ፡ ወልጉነ ፡ ወወ ደየት ፡ ውስቴቶሙ ፡ እምውእቱ ፡ ጌው ፡ ወመልኡ ።
፶፩ ፤ ወቅብዓ ፡ መለዓርኒ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትገበር ፡ ለጸብሐ ፡ ተረክቡ ፡ ምሉአኒሆሙ ፡ በበመካ ኖሙ ።
፶፪ ፤ ወአልቦ ፡ ዘተረክበ ፡ እራቁ ፡ እምንዋየ ፡ ቤት ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ።
፶፫ ፤ ወእግዚእ ፡ ሐረያስ ፡ ኮነት ፡ መንክርተ ፡ እምዝንቱ ፡ ግብር ።

፴ ፤ ይህን ፡ ዕንቅቡን ፡ ስጭኝ ፡ እንደሚል ጠቅሶ ፡ አሳያት ።
፴፩ ፤ አምጥታ ፡ ሰጠችው ።
፴፪ ፤ እጁን ፡ ከዱቄቱ ፡ ላይ ፡ ጨመረው ።
፴፫ ፤ ወዲያው ፡ መልቶ ፡ ፈሰሰ ።
፴፬ ፤ ይህን ፡ ሥራ ፡ ዓይታ ፡ አደነቀች ።
፴፭ ፤ ዳግመኛም ፡ ልጅዋ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ሁለ ተኛውን ፡ ዕንቅብ ፡ አምጭ ፡ ብሎ ፡ ጠቀ ሳት ፡ አቀረበችለት ።
፴፮ ፤ እንደመጫወት ፡ ጥቂት ፡ ዱቄት ፡ ዘግኖ ፡ ጨመረበት ፡ ከዚያም ፡ መላ ።
፴፯ ፤ ሦስተኛውንም ፡ ዕንቅብ ፡ አመጣችለት ፡ እንደቀድሞው ፡ መላ ።
፴፰ ፤ እሷን ፡ ቢደክማት ፡ ገረዷን ፡ እርጅኝ ፡ ብላ ጠራቻት ።
፴፱ ፤ ዘጠኝ ፡ ዕንቅብ ፡ አመጣች ፡ በነሱ ፡ ሁሉ ፡ መላ ።
፵ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ እንቅብ ፡ ሆነ ።
፵፩ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ በፀጋ ፡ ዘአብ ፡ ቤት የእግዚአብሔር፡ በረከት ፡ መላ ።
፵፪ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ግን ፡ በረከት ፡ በሰማይ ፡ እንደዝናም ፡ ሲወርድ ፡ እያየ ፡ ደስ ፡ ብሎት ልዝለል ፡ ልዝለል ፡ አለ ።
፵፫ ፤ ይህ ፡ ልጄ ፡ እንደ ፡ ፈጣሪው ፡ ሁሉ ፡ የሚ ቻለው ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አሰበች ።
፵፬ ፤ ጥቂት ፡ ቅቤ ፡ ያለበት ፡ የቅቤ ፡ ማሰሮ አመጣች ።
፵፭ ፤ እጁን ፡ እንደመስቀል ፡ አማትባ ፡ ከውስጡ ፡ ጨመረችው ።
፵፮ ፤ በእሳት ፡ እንዳፈሉት ፡ ፈልቶ ፡ ፈጥኖ፡መላ።
፵፯ ፤ ገረዲ ፡ ታላቅ ፡ እንስራ ፡ አምጥታ ፡ ከቅቤው ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እየቀዳች ፡ ከውስጡ ፡ ጨመረችው ፡ ሁሉም ፡ መሉ ።
፵፰ ፤ የጨው ፡ ሙዳይም ፡ አምጥታ ፡ እንደቀ ድሞዋ ፡ አማትባ ፡ የሕፃኑን ፡ እጅ ፡ ከው ስጡ ፡ ጨመረችው ።
፵፱ ፤ ፈጥኖ ፡ መላ ። ከሱም ፡ ቀድታ ፡ በታላቅ ፡ እንስራ ፡ ጨመረች ፡ እንደዚያው ፡ መላ ።
፶ ፤ ዳግመኛም ፡ ጋን ፡ ምንቸት ፡ አቀረበች ፡ ከጨው ፡ እየዘገነች ፡ ከውስጣቸው ፡ ጨመ ረ ችው ፡ ጋኑም ፡ ምንቸቱም ፡ መላ ።
፶፩ ፤ የኑግ ፡ ቅባኑግም ፡ ለወጥ ፡ የሚሠራም ፡ ሁሉ ፡ በየቦታቸው ፡ መልተው ፡ ተገኙ ።
፶፪ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ ከቤት ፡ ዕቃ ፡ ባዶውን ፡ የተገኘ ፡ የለም ።
፶፫ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ታአምራት ፡ አይታ ፡ አደነቀች ።

፶፬ ፤ ወአዘዘታ ፡ ለአመታ ፡ ታስተዳሉ ፡ መባልዕተ ፡ ለበዓለ ፡ ሚካኤል ።

፶፭ ፤ ዝውእቱ ፡ እመ ፡ ፲ ፡ ወ፪ ፡ ለመጋቢት ፡ በካልዓይ ፡ ዓመት ፡ እምዘተጼወወት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ።

፶፮ ፤ ወሶበ ፡ አተወ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነገረቶ ፡ ብእሲቱ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ እምወልዶሙ ፡ ኅሩይ ።

፶፯ ፤ ወሰሚዖ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ባረኮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፶፰ ፤ ወይቤ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ እስራኤል ፡ ዘተሣሀለነ ፡ ወገብረ ፡ መድኀኒተ ፡ ለሕዝበ ፡ ዚአሁ ።

ዘካርያስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፶፱ ፤ ነፍስየ ፡ ትባርኮ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፷ ፤ ወትገኒ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ።
፷፩ ፤ ምንተኑ ፡ አዐስየከ ፡ እግዚኦ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብርከ ፡ ሊተ ፡ ዘኢድልወትየ ፡ ለኃጥእ ።

መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።

፷፪ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ነሥአ ፡ ለሕፃን ፡ ሐቀፎ ፡ ወሰዓሞ ።
፷፫ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሕይወኒ ፡ ወልድየ ፡ ለብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ ወለጕንዱይ ፡ ዓመታት ።
፷፬ ፤ ከመ ፡ ትኩነነ ፡ ጽጋበ ፡ በዘመነ ፡ ረኃብ ።
፷፭ ፤ ወስቴ ፡ በዘመነ ፡ ጽምዕ ።
፷፮ ፤ ልብስ ፡ በዘመነ ፡ ዕርቃን ።
፷፯ ፤ ወብዕል ፡ በዘመነ ፡ ተጽናስ ።
፷፰ ፤ ፍሥሐ ፡ በዘመነ ፡ ኀዘን ።
፷፱ ፤ ወምስካየ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤ ።

፸ ፤ ዘከመዝ ፡ ወልድ ፡ ሕይወኒ ፡ ብዙኃ ፤

፸፩ ፤ ወነበበ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ ፡ አንሰ ፡ አሐዩ ብዙኃ ፡ ወአንተ ፡ ትመውት፡እምቅድሜየ ።

፸፪ ፤ ወአልብከ ፡ ካልዕ ፡ ዘርዕ ፡ ዘእንበሌየ ።
፸፫ ፤ እመኒ ፡ ሞትከ ፡ ርቡሕ ፡ ለከ ፡ ይጸንሐከ ፡ ዕሤትከ ፡ አክሊለ ፡ ምዝጋና ፡ ድልው ።

፸፬ ፤ በእንተ ፡ ክህነትከ ፡ ንጹሕ ።
፸፭ ፤ ወበእንተ ፡ ዕጣንከ ፡ ስጡው ።
፸፮ ፤ ወበእንተ ፡ ምጽዋትከ ፡ ወኩፍ ።

ጢሞ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፮ ።

፸፯ ፤ አንሰ ፡ እትረፍ ፡ ለተቃትሎ ፡ ጽኑዕ ።
፸፰ ፤ እስመ ፡ ቀትልየኒ ፡ ኢኮነ ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ፡ ወደም ።

፶፬ ፤ ገረዷን ፡ ጠርታ ፡ ለሚካኤል ፡ በዓል ፡ የሚሆነውን ፡ ምግብ ፡ አዘጋጁ ፡ አለቻት ።

፶፭ ፤ ይኸውም ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ በተማረከች ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በመጋቢት ፡ በ፲፪ ፡ ቀን ፡ ነው ።

፶፮ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተመልሶ ፡ ወደቤቱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ የተመረጠ ፡ ልጃቸው ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ።

፶፯ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ሰምቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፤

፶፰ ፤ እኛን ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ ለወገኖቹ ፡ ድኅነትን ያደረገ ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ዘካርያስ ፡ ፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፶፱ ፤ ሰውነቴ ፡ እግዚአብሔርን፡ ታመሰግነዋለች።
፷ ፤ ለክቡር ፡ ስሙም ፡ ትገዛለች ።
፷፩ ፤ ለኔ ፡ ለኃጥእ ፡ የማይገባኝ ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስላደረግህልኝ ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ምን ፡ ወሮታ ፡ እከፍልሃለሁ ።

መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።

፷፪ ፤ ይህን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ልጁን ፡ አንሥቶ ፡ ታቅፎ ፡ ሳመው ።
፷፫ ፤ ልጄ ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ኑርልኝ ፡ እያለ ።

፷፬ ፤ በረኃብ ፡ ጊዜም ፡ ጽጋብ ።
፷፭ ፤ በጽም ፡ ጊዜ ፡ መጠጥ ።
፷፮ ፤ በታረዝን ፡ ጊዜ ፡ ልብስ ።
፷፯ ፤ በችጋር ፡ ጊዜ ፡ ብዕል ፤
፷፰ ፤ በኀዘን ፡ ጊዜ ፡ ደስታ ።
፷፱ ፤ በመከራ ፡ ጊዜም ፡ መጠጊያ ፡ ትሆነን ፤ ዘንድ ።
፸ ፤ እንደዚህ ፡ ያለህ ፡ ልጄ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኑርልኝ ፡ አለ ።
፸፩ ፤ እኔስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እኖራለሁ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ አስቀደሞ ፡ ትሞታለህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
፸፪ ፤ ያለኔም ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ የለህም ።
፸፫ ፤ ብትሞትም ፡ የተዘጋጀ ፡ ተመስግነህ ፡ የምትቀበለው ፡ ዋጋህ ፡ ይቆይሃል ።

፸፬ ፤ ስለንጹሕ ፡ ክህነትህ ።
፸፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለሚቀበለው ፡ ዕጣንህ ።
፸፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለሚቀበለው፡ ምጽዋትህ።

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ፡ ፮፡ ጢሞ ፡

፸፯ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለጽኑዕ ፡ ሙጋት ፡ እቀራለሁ ።
፸፰ ፤ የምዋጋውም ፡ ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አይደለም ።

፸፱ ፤ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ መኳንንት ፡ እለ ፡ ይመ
ልኩ ፡ ዓለመ ፡ ጽልመት ፡ ዘውእቶሙ ፡
መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ እለ ፡ መትሕተ ፡
ሰማይ ።

ኤፌ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቊ ፡ ፲፪ ።

፹ ፤ ወአንተሰ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ትወርድ ፡ ውስተ ፡
ዓለመ ፡ አበዊከ ።
፹፩ ፤ አንተ ፡ ይእቲ ፡ መቃብር ፡ እመ ፡ ኵሉ ።
፹፪ ፤ ወዘንተ ፡ ሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ወልዱ ፡ ደንገፀ ፡
ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወፈርሃ ፡ ጥቀ ።
፹፫ ፤ ወባሕቱ ፡ አዕኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ
ይብል ።
፹፬ ፤ አእኵተከ ፡ አባ ፡ እግዚኦ ፡ ሰማያት ፡
ወምድር ።
፹፭ ፤ እስመ ፡ ሰወርኮ ፡ ለዝንቱ ፡ እምጠቢባን ፡
ወእምለባውያን ፡ ወከሠትኮ ፡ ለሕፃናት ።
፹፮ ፤ እወ ፡ አባ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ሥምረትከ ።
፹፯ ፤ በአማን ፡ ጠቢበ ፡ ጠቢባን ፡ አንተ ።
፹፰ ፤ ነገረ ፡ ቃልከ ፡ ያበርሀ ፡ ወያጠብብ ፡ ሕፃናተ ።

መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ቊ ፡ ፻፴ ።

፹፱ ፤ አኮ ፡ ድልወትየ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ታርእየኒ ፡
ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ መንክራተ ፡ ዘትገብር ፡ በላ
ዕለ ፡ ዝወልድ ፡ ዘኀረይኮ ፡ አንተ ።
፺ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ኵሉ ፡ አዕኰቶ ።
፺፩ ፤ ይቤሎ ፡ ለወልዱ ።
፺፪ ፤ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዘወሀበከ ፡
ታእምር ፡ ሕጎ ፡ ወሥርዓቶ ።
፺፫ ፤ ወእምዝ ፡ አስተዳለወ ፡ መባልዕተ ፡ ብዙኃ ፡
ወገብሩ ፡ በዓለ ፡ ዓቢየ ፡ በእንተ ፡ ሚካኤል
፺፬ ፤ እመ፲ወ፪ ፡ ለመጋቢት ።
፺፭ ፤ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ።
፺፮ ፤ ወለ[illegible]ጽንዖ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ።
፺፯ ፤ ወለኵሉ ፡ ጽኑሳን ፡ ለአዝማዲሆሙኒ ፡
ለሰብአ ፡ ሀገርኒ ፡ ገብሩ ፡ ምሳሐ ፡ ዓቢየ ።
፺፰ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ሰብእ ፡ ያነክሩ ፡ እንዘ
ይብሉ ፡ በአይቴ ፡ ረከቡ ፡ እሉ ፡ ዘመጠ
ነዝ ፡ ማዕደ ፡ በዝ ፡ ዘመን ፡ ዐጸባ ።
፺፱ ፤ ወአልቦ ፡ እክል ፡ ውስተ ፡ ሀገርነ ።
፻ ፤ ንሕነሂ ፡ ሶበ ፡ ንገብር ፡ በዓለ ፡ ሚካኤል ፡
እምረከብነኑ ፡ ከመዝ ።
፻፩ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ እምአመ ፡ ተወልደ ፡
ወልዶሙ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ብዕሉ ፡ ጥቀ ።

፸፱ ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ዓለመ ፡ ጽልመትን ፡
ከሚገዙ ፡ ከአጋንንት ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቊ ፡ ፲፪ ፡ ኤፌ ።

፹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አባቴ ፡ ወደ ፡ አባቶችህ ፡
መኖሪያ ፡ ትሔዳለህ ።
፹፩ ፤ ይችውም ፡ የሁሉ ፡ መገኛ ፡ መቃብር ፡ ናት
፹፪ ፤ ልጁ ፡ ይህን ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ
እጅግ ፡ ፈራ ፡ ደነገጠ ።
፹፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ አመሰገነ ።
፹፬ ፤ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠርህ ፡ ጌታ ፡ አመ
ሰግንሃለሁ ።
፹፭ ፤ ይህንን ፡ ዐዋቆች ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሰውረህ ፡
ለሕፃናት ፡ ገልጸኸዋልና ።
፹፮ ፤ አዎን ፡ አባቴ ፡ ካዋቂ ፡ መሰወር ፡ ላላዋቂ ፡
መግለጽ ፡ ልማድህ ፡ ነው ።
፹፯ ፤ በውነት ፡ አንተ ፡ ዐዋቆች ፡ የምታደርጋ
ቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፹፰ ፤ ነገርህ ፡ ሕፃናትን ፡ ያራቅቃል ።

መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ቊ ፡ ፻፴ ።

፹፱ ፤ አንተ ፡ በመረጥከው ፡ በዚህ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡
የምታደርገውን ፡ ተአምራት ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡
ልትገልጽልኝ ፡ አይገባኝም ።
፺ ፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ አመሰገነ ።
፺፩ ፤ ልጁንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ።
፺፪ ፤ ሕጉን ፡ ሥርዓቱን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡
ዕውቀቱን ፡ ለሰጠህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።
፺፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ አዘጋጅተው ፡
በሚካኤል ፡ ስም ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።
፺፬ ፤ በመጋቢት ፡ በ፲፪ ፡ ቀን ።
፺፭ ፤ ለድኻው ፡ ሁሉ ።
፺፮ ፤ እናት ፡ አባት ፡ የሌላውን ፡ ለማጽናናት ።
፺፯ ፤ ለተቸገሩት ፡ ሁሉ ፡ ለዘመዶቻቸውም ፡
ለሀገሩም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ምሳ ፡ አደረጉ ።
፺፰ ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ በረ
ኃብ ፡ ዘመን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ምግብ ፡
ከየት ፡ አገኙ ፡ እያሉ ፡ አደነቁ ።
፺፱ ፤ በሀገራችን ፡ እህል ፡ የለ ።
፻ ፤ እኛም ፡ የሚካኤልን ፡ ዝክር ፡ ብናዘክር ፡
እንዲህ ፡ ባገኘን ፡ ነበር ፡ አሉ ።
፻፩ ፤ ልጃቸው ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ከተወለደ ፡
ወዲህ ፡ እጅግ ፡ ከበሩ ፡ ያሉም ፡ አሉ ።

፶፪ ፤ ወእንዘ ፡ ይትበሃሉ ፡ ዘንተ፡ጸጊቦሙ፡አተው
ብሔሮሙ ።
፶፫ ፤ ወጸጋ ፡ ዘአብሰ ፡ ወእግዚእ ፡ ሐረያ ፡
ነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይሴስዩ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብአ ፡
ሀገር ፡ እስከ ፡ አመ ፡ የኃልፍ ፡ ዘመነ ፡
ረኃብ ።
፶፬ ፤ ወኢሃልቀ ፡ ውእቱ ፡ ሐሪጽ ፡ ሥርናይ ፡ እስከ
ብዙኅ ፡ መዋዕል ።
አኮ ፡ ሐሪጽ ፡ ሥርናይ ፡ ባሕቲቱ ።
ዓዲ ፡ ቅብዕኒ ፡ ወጼውኒ ፡ ወኵሉ ፡ መፍቅ
ዳተ ፡ ቤት ፡ ዘተባረኩ ፡ በእደ ፡ ወልዶሙ
ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ኢኀልቀ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡
ሞቶሙ ፡ ወነበሩ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወእግዚእ
ሐረያ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሰላም ፡ እንዘ ፡ ይሴብ
ሕዎ ፡ ወየአኵትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ።
በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሎሙ ፡ በእደ ፡
ወልዶሙ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ዳግመ ፡ ገብረት ፡ እግዚአብሔር ፡
ዓቢየ ፡ ኃይለ ፡ በእደ ፡ ወልዳ ፡ ፍሥሐ ፡
ጽዮን ።
፪ ፤ ወመጽአ ፡ ኀቤሃ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ መኰንነ ፡
ሀገር ።
፫ ፤ እንዘ ፡ የኃልፍ ፡ ይእተ ፡ ፍኖተ ።
፬ ፤ ወይቤላ ፡ ሀብኒ ፡ ምሳሐ ፡ እስመ ፡ ርኅብኩ
ፈድፋደ ።
፭ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅድስት ፡ ምሳሐሰ ፡ እምሀብኩከ
ወባሕቱ ፡ ምዝር ፡ አልብየ ።
፮ ፤ ወይቤላ ፡ ሶበሰ ፡ ተረክበ ፡ ምዝር ፡ እምኮነ ፡
ሠናይ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘብኪ ፡ ሀብኒ ።
፯ ፤ ወቦአት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ውስተ ፡ ቤታ ፡
እንዘ ፡ ተኀዝን ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ ዘአል
ባቲ ፡ ምዝር ።
፰ ፤ ወትብል ፡ በልባ ፡ አምላኩ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ
ኅሩይ ፡ ግበር ፡ ሊተ ፡ ተአምረ ፡ በከመ ፡
ልማድከ ።
፱ ፤ ወአዘዘታ ፡ ለዓመታ ፡ ትሥራዕ ፡ ማዕዳተ ፡
ብዙኃ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለመኰንን ።
፲ ፤ ወሀለየት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ በዝንቱ ፡ ወል
ደየ ፡ ሀሎ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡
እዴሁ ።
፲፩ ፤ ቀዳሚኒ ፡ አተውኩ ፡ እምጼዋዌ፡በእንቲአሁ።
፲፪ ፤ ወዳግመ ፡ ድኅንኩ ፡ እሞተ ፡ ረኃብ ፡ በእ
ዴሁ ።
፲፫ ፤ ወእስከ ፡ ይእዜ ፡ ሀሎኩ ፡ በጸጋሁ ።
፲፬ ፤ ወይእዜኒ ፡ ይገብር ፡ ሊተ ፡ አምላኪየ ፡
ኃይለ ፡ ቦቱ ።
፲፭ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትሄሊ ፡ ነሥአቶ ፡ ለወ
ልዳ ፡ ወወሰደቶ ፡ ምስሌሃ ።
፲፮ ፤ ወበጺሐ ፡ ኀበ ፡ ቀሡተ ፡ ማይ ፡ ምሉእ ፡
ዘሀሎ ፡ በጥቃ ፡ ቤት ።

፶፪ ፤ በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ፡ይህን፡እየተባባሉ
ወደየሀገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ።
፶፫ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያና ፡ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ የረኃቡ ፡
ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ለሀገሩ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ይህን ፡ እየመገቡ ፡ ተቀመጡ ።
፶፬ ፤ ይህም ፡ የሥንዴ ፡ ዱቄት ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ አልተፈጸመም ።
የአንዱ ፡ ዱቄት ፡ ብቻ ፡ አይደል ።
ለቤት ፡ የሚፈለጉ ፡ በልጃቸው ፡ እጅ ፡ የተ
ባረከው ፡ ሁሉ ፡ ጨውም ፡ ቅቤውም ፡ እስኪ
ሞቱ ፡ ድረስ ፡ አልተፈጸመም ።
እግዚእ ፡ ሐረያና ፡ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ደስ ፡
ብሏቸው ፡ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ ተቀመጡ ።
በልጃቸው ፡ በፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ እጅ ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ ስለተደረገላቸው ።

ዐሥራ ፡ ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡
በልጁ ፡ በፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ እጅ ፡ ታላቅ ፡
ታላቅ ፡ ተአምራት ፡ አደረገች ።
፪ ፤ አንድ ፡ ሀገረ ፡ ገዥ ፡ ሰውም ፡ መጣ ።
፫ ፤ በዚያች ፡ ጐዳና ፡ ሲያልፍ ።
፬ ፤ እጅግ ፡ ተርቤያለሁና ፡ ምሳ ፡ አብሊኝ ፡
አላት ።
፭ ፤ መጠጥ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ ምሳ ፡ በሰጡሁህ
ነበር ፡ አለችው ።
፮ ፤ መጠጥ ፡ በተገኘ ፡ ደግ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ያለሽን ፡ ስጭኝ ፡ አላት ።
፯ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ መጠጥ ፡ ስለሌላት ፡
እጅግ ፡ እያዘነች ፡ ወደቤት ፡ ገባች ።
፰ ፤ በልቡናዋ ፡ የተመረጠ ፡ የዚህ ፡ ልጅ ፡
ፈጣሪ ፡ እንደልማድህ ፡ ተአምራት ፡ አድ
ርግልኝ ፡ ትላለች ።
፱ ፤ ለጌታ ፡ የሚሆን ፡ ገበታ ፡ ሥሪ ፡ ብላ ፡ አዘዘ
ቻት ።
፲ ፤ በዚህ ፡ በልጅ ፡ እጅ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አድሮበታል ፡ እያለች ፡ አሰበች ።
፲፩ ፤ ቀድሞም ፡ ስለሱ ፡ ከምርኮ ፡ ተመለስኩ ።
፲፪ ፤ ዳግመኛም ፡ በረኃብ ፡ ከመሞት ፡ በሱ ፡
እጅ ፡ ዳንኩ ።
፲፫ ፤ እስካሁንም ፡ በቸርነቱ ፡ አለሁ ።
፲፬ ፤ ዛሬም ፡ ፈጣሪዬ ፡ በሱ ፡ ተአምራት ፡ ያደ
ርግልኛል ።
፲፭ ፤ ይህን ፡ እያለች ፡ ልጁን ፡ ከእሷ ፡ ጋራ ፡
ይዛው ፡ ሄደች ።
፲፮ ፤ በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የውኃው ፡ ዕቃ ፡ ካለ
በት ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ።

፲፯ ፤ ነሥአት ፡ እደ ፡ ወልዳ ፡ ወባረከት ፡ ውእተ ፡
ማየ ፡ አማዕቲባ ፡ በትእምርተ ፡ **መስቀል ።**
፲፰ ፤ ወኮነ ፡ ምዝረ ፡ ጥዑመ ፡ ዘነከራ ።
፲፱ ፤ ወጸውዓታ ፡ ለዓመታ ፡ ወትቤላ ፡ ቅድሒ ፡
ምዝረ ፡ በኒባል ፡ እምዝንቱ ፡ ቀሡት ።

፳ ፤ ወቀድሐት ፡ ወመልአ ፡ ወተርፈ ።
፳፩ ፤ ወቀድሐት ፡ ካዕበ ፡ በብዙኃ ፡ ኔባላት ፡ ወኢ
ተወድዓ ።
፳፪ ፤ ውንደገት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ይጽንሐኒ ፡
ለድኅር ።
፳፫ ፤ ወአዘዘት ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ ይጸውዕዎ ፡
ለመኰንን ፡ ወያብዕዎ ፡ ውስተ ፡ ካልዕ ፡
ቤት ።
፳፬ ፤ ወአቅረበት ፡ ሎቱ ፡ ብዙኃ ፡ መባልዕተ ፡
ወስቴያተ ፡ በከመ ፡ ይትፈቀድ ።
፳፭ ፤ ወአንከረ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ እንዘ ፡ ይብል
በአይቴ ፡ ረከበት ፡ ግብተ ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡
ዘመጠንዝ ፡ ማዕደ ።

፳፮ ፤ ኀድጉሰ ፡ ሊተ ፡ ዝሰ፡ ለንጉሥኒ ፡ እምአከለ።
፳፯ ፤ ወእንዘ ፡ ይትበሃሉ ፡ ከመዝ ፡ ምስለ ፡ እለ
ምስሌሁ ፡ በልዑ ፡ ወጸግቡ ።
፳፰ ፤ ወአትረፉ ፡ ለሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወይቤ ፡ መኰ
ንን ፡ ጸውዕዋ ፡ **ለእግዚእ ፡ ሐረያ ።**

፳፱ ፤ ወሶበ ፡ በጽሐት ፡ ኀቤሁ ፡ ይቤላ ፡ ዘመጠ
ነዝኑ ፡ ምዝረ ፡ ጥዑመ ፡ አንቢረኪ ፡ ትቤ
ልኒ ፡ አልብየ ፡ ምዝር ።
፴ አማንየ ፡ ዕብለኪ ፡ በቤተ ፡ ነገሥትኒ ፡
ኢይትረከብ ፡ ዘከመዝ ፡ ምዝር ።

፴፩ ወትቤሎ ፡ ቅድስት ፡ አንሰ ፡ ኢያእመርኩ ፡
ወኢ ፡ አክዎ ፡ ቅድመ ፡ ለዝንቱ ፡ ምዝር ።
፴፪ ፤ ወባሕቱ ፡ እምድኅረ ፡ ኃለፍኩ ፡ እምኔከ ፡
ወኃበንዮ ፡ አምላክከ ።

፴፫ ፤ ወይቤላ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ይባርክ ፡ ላዕሌኪ
ወኵሎ ፡ ዘአጥረይኪ ።
፴፬ ፤ ወእምድኅረ ፡ ባረካ ፡ ሖረ ፡ መኰንን፡ፍኖቶ።

፴፭ ፤ ወውእቱ ፡ ማየ ፡ ቀሱት ፡ ዘኮነ ፡ ምዝረ ፡
ነበረ ፡ መጠነ ፡ ፴ ፡ መዋዕል ፡ እንዘ ፡ ይሰ
ትይዎ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ።
፴፮ ፡ ወኢይከውን መ ጸጸ ።
፴፯ ፤ አላ ፡ ለለጌሠሙ ፡ ይትረከብ ፡ ጻዕፈ ፡ ኬዊኖ።
፴፰ ፤ ወዝንቱሰ ፡ ወልድ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን**
አመ ፡ ይትሌተት ፡ በግዕዘ ፡ ሕፃናት ።

፴፱ ፤ ወቦ ፡ አመ ፡ ይነብብ ፡ በነገር ፡ ጽኑዕ ፡
ከመ ፡ ወሬዛ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ።
፵ ፤ ወለእሙኒ ፡ ብዙኃ ፡ ተአምር ፡ ተገብረ ፡
ላቲ ፡ በባርኮ ፡ እዴሁ ።
፵፩ ፤ ወይእቲኒ ፡ ትረከብ ፡ ኵሎ ፡ ዘኃሠሠት ።
፵፪ ፤ ወከመዝ ፡ ልህቀ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡
በአርእዮ ፡ ኃይል ፡ ወዕበይ ።

፲፯ ፤ የልጅዋን ፡ እጅ ፡ ይዛ ፡ አማትባ ፡ ውኃውን ፡
ባረከችው ።
፲፰ ፤ የተደነቀ ፡ ጠላ ፡ ሆነ ።
፲፱ ፤ ገረዷን ፡ ጠርታ ፡ ጠላውን ፡ በገምቦ ፡ ከማ
ድጋው ፡ ቅጅው ፡ አለቻት ።

፳ ፤ ቀድታው ፡ መልቶ ፡ ተረፈ ።
፳፩ ፤ ዳግመኛም ፡ በብዙ ፡ ገምቦ ፡ ቀዳችው ፡
አልተፈጸመም ።
፳፪ ፤ ለኋላ ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ ተወችው ።

፳፫ ፤ **እግዚእ ፡ ሐረያም ፡** ጠርታችሁ ፡ ከሁለተ
ኛው ፡ ቤት ፡ አግቡት ፡ ብላ ፡ አዘዘች ።

፳፬ ፤ እንደሚሻው ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ብዙ ፡ መጠጥ
አቀረበችለት ።
፳፭ ፤ ይህም ፡ መኰንን ፡ ይች ፡ ሴት ፡ ድንገት ፡
ይህን ፡ ያህል ፡ ምግብ ፡ ከየት ፡ አገኘች ፡
እያለ ፡ አደነቀ ።

፳፮ ፤ ለኔስ ፡ ይቅርና ፡ ለንጉሡም ፡ በበቃ ፡ ነበረ ።
፳፯ ፤ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ከሱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡
እየተባባሉ ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ።
፳፰ ፤ በሀገር ፡ ላሉም ፡ ሰዎች ፡ አተረፉ ፡ ይህም ፡
መኰንን ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያን ፡** ጥሯት ፡ አለ ።

፳፱ ፤ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ
ያማረ ፡ መጠጥ ፡ እያለሽ ፡ የለኝም ፡ ትይ
ኛለሽ ፡ አላት ።
፴ ፤ በውነት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስንኳ ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ መጠጥ ፡ አይገኝም ፡ አላት ።

፴፩ ፤ **እግዚእ ፡ ሐረያም ፡** እኔ ፡ እንዳለም ፡ አላወ
ቅሁ ፡ ቀድሞም ፡ አላየሁት ፡ አለችው ።
፴፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ከሄድኩ ፡ በኋላ
ፈጣሪህ ፡ ሰጠኝ ፡ አለችው ።

፴፫ ፤ አንቺንም ፡ ገንዘብሽንም ፡ ሁሉ ፡ **እግዚአ
ብሔር ፡** ይባርክልሽ ፡ ብሎ ፡ መረቃት ።
፴፬ ፤ ይህም ፡ መኰንን ፡ መርቋት ፡ ተነሥቶ ፡
ሄደ ።

፴፭ ፤ ይህም ፡ ጠላ ፡ የሆነው ፡ የማድጋ ፡ ውኃ ፡
ያገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየጠጣው ፡ እስከ ፡
አርባ ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ።
፴፮ ፤ ሳይኮመጥጥ ።
፴፯ ፤ እየነጋ ፡ አፍለኛ ፡ ሁኖ ፡ ይገኛል ፡ እንጂ ።
፴፰ ፤ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡** ግን ፡ እንደሕፃናት ፡ አፉን
ያልፈታ ፡ ሁኖ ፡ የሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ አለ።

፴፱ ፤ እንደ ፡ ሃያ ፡ ዘመን ፡ ጕልማሳም ፡ ሁኖ ፡
በጽኑዕ ፡ ነገር ፡ የሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።
፵ ፤ ለናቱም ፡ በሱ ፡ እጅ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡
ተደረገላት ።
፵፩ ፤ እሷም ፡ የፈለገችውን ፡ ሁሉ ፡ ታገኝ ፡ ነበር ።
፵፪ ፤ ይህም ፡ የተመረጠ ፡ ልጅ ፡ እንደዚህ ፡
ብዙ ፡ ተአምራት ፡ እያደረገ ፡ አደገ ።

ዘ ሰ ሉ ስ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ እምድኅረ ፡ ኮኖ ፡ ፯ ፡ ዓመተ ፡ ተምህረ ፡ እምአቡሁ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ።
፪ ፤ ወኵሎ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብሉየ ፡ ወሐዲሰ ፡ ዘምስለ ፡ ዓቂበ ፡ ሕጎሙ።
፫ ፤ ወሶበሂ ፡ ይትማሀር ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ተምህረ ።
፬ ፤ ወያጸንዕ ፡ ፍጡነ ፡ ዘነገርዎ ።
፭ ፤ እስመ ፡ እንተ ፡ ውስቴ ፡ ኅዱር ፡ ክርስቶስ ።
፮ ፤ ውእቱኬ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘመርዔት ፡ ዘይሜህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ጥበበ ።
፯ ፤ ወኮነ ፡ ስርግወ ፡ በኵሉ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቅኑየ ፡ ለትእዛዙ ።
፰ ፤ ወይትፌቀር ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእዮ ፡ ወዘሰምዖ ።
፱ ፤ ወወጠነ ፡ ከመ ፡ ይጹም ፡ ጾመ ፡ ቅድስተ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እመ ፡ ኵሉ ፡ ምግባራት ።
፲ ፤ ወአትለወ ፡ ጸሎተ ፡ ውስቴታ ።
፲፩ ፤ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ሐገፋ ፡ እምእለ ፡ ይትቃተልዎ ፡ አጋንንት ።
፲፪ ፤ ወወሰከ ፡ ዓዲ ፡ ትዕግሥተ ።
፲፫ ፤ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኮነቶ ፡ ሐመረ ፡ እስከ ፡ አዕረገቶ ፡ እምድር ፡ ሰማያተ ።
፲፬ ፤ ወረሰዮቶ ፡ ልዑለ ፡ እምኵሉ ።
፲፭ ፤ ወአመ ፡ ኮኖ ፡ ፍጹመ ፡ ፲ ፡ ወ፮ ፡ ዓመተ ፡ ነሥአ ፡ አቡሁ ፡ ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ።
፲፮ ፤ እንዘ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ብንያሚ ፡ ወዓዲሁ ፡ ጳጳስ ፡ ሀሎ ፡ በምድረ ፡ አምሐራ ።
፲፯ ፤ ወእምቅድመ ፡ ይብጽሑ ፡ ህየ ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለአባ ፡ ጌርሎስ ፡ ጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ።
፲፰ ፤ ወይቤሎ ፡ ጌሠመ ፡ ይመጽእ ፡ ኀቤከ ፡ ብእሲ ፡ ቀይሕ ፡ ወመዓድም ፡ ገጹ ።
፲፱ ፤ ወይሰግድ ፡ ለከ ፡ እምርሁቅ ።
፳ ፤ ወቦቱ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ዘይበቁዕ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ።
፳፩ ፤ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር።
፳፪ ፤ ወኢይከውን ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ መጠነ፡ አሐቲ ፡ ስእርተ ፡ ርእሱ ።
፳፫ ፤ ወስሙ ፡ ጽሑፍ ፡ በአክናፈ ፡ ሥላሴ ።
፳፬ ፤ ዘመጠንዝ ፡ ወልደ ፡ አምጽኦኩ ፡ ለከ ፡ ወሲሞ ፍጡነ ፡ ሲመተ ፡ ዲቁና ።
፳፭ ፤ ወፈነዎ ፡ በሰላም ፡ ብሔሮ ።

ዐሥራ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከሆነው ፡ በኋላ ፡ ካባቱ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊት ፡ ተማረ ።
፪ ፤ ሕጋቸውንም ፡ ከመጠበቅ ፡ ጋራ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚነበብ ፡ መጻሕፍትን ፡ ሁሉ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ አጠና ።
፫ ፤ ሲማርም ፡ ቀድሞ ፡ የተማረው ፡ ይመስላል ።
፬ ፤ የነገሩትንም ፡ ፈጥኖ ፡ ያጠና ፡ ነበር ።
፭ ፤ በልቡናው ፡ ክርስቶስ ፡ አድሮበታልና ።
፮ ፤ ይኸውም ፡ ለሰው ፡ ዕውቀትን ፡ የሚገልጽ ፡ በምእመናን ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።
፯ ፤ ሕጉን ፡ በመጠበቅ ፡ የጸና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በማምለክ ፡ የተጌጸ ፡ ሆነ ።
፰ ፤ ነገሩን ፡ በሰማው ፡ መልኩንም ፡ ባየው ፡ ሁሉ ፡ ይወደድ ፡ ነበር ።
፱ ፤ የሥራው ፡ ሁሉ ፡ መገኛ ፡ የምትሆን ፡ ጾምን ፡ መጾም ፡ ጀመረ ።
፲ ፤ ጸሎትን ፡ አብዝቶ ፡ ከመጸለይ ፡ ጋራ ።
፲፩ ፤ ከሚዋጉት ፡ አጋንንት ፡ ጋሻ ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ።
፲፪ ፤ ትዕግሥትንም ፡ አጽንቶ ፡ ያዘ ።
፲፫ ፤ ከምድር ፡ ወደሰማይ ፡ ለመውጣት ፡ መርከብ ፡ መሰላል ፡ ሆናዋለችና ።
፲፬ ፤ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ አክብራዋለችና ።
፲፭ ፤ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመትም ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ይዞ ፡ ወደጳጳሱ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ወሰደው ።
፲፮ ፤ አባ ፡ ብንያም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በአማራ ፡ አውራጃ ፡ ጳጳስ ፡ ገና ፡ መምጣቱ ፡ ነበርና ።
፲፯ ፤ ከዚያ ፡ ሳያደርሱ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አባ ፡ ጌርሎስን ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ።
፲፰ ፤ ነገ ፡ ወዳንተ ፡ መልኩ ፡ ያማረ ፡ ቀይ ፡ ሰው ይመጣል ።
፲፱ ፤ እርቆ ፡ እጅ ፡ ይነሣሃል ።
፳ ፤ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበቃ ፡ የተመረጠ ፡ ልጅ ፡ ይዞ ።
፳፩ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ የከበረ ነው ።
፳፪ ፤ ከራስ ፡ ጸጉሩ ፡ ላንዲቱ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ዋጋዋ ፡ አይሆንም ።
፳፫ ፤ ስሙም ፡ በልበ ፡ ሥላሴ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ።
፳፬ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ አምጥቼልሃለሁና ፡ ፈጥነህ ፡ ዲቁና ፡ ሹመው ፡ አለው ።
፳፭ ፤ በፍቅር ፡ ተቀብለህ ፡ በፍቅር ፡ ሸኘው ፡ አለው ።

፷፮ ፤ ወእምድኅረ ፡ ይቤሎ ፡ ዘንተ ፡ ተሰወረ ፡ እምኔሁ ።
፷፯ ፤ ወሰሚዖ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ መልአክ ፡ አንከረ ።
፷፰ ፤ ወኀደረ ፡ ኵላ ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ያስተዐፅብ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።
፷፱ ፤ ወጸቢሆ ፡ ወፅአ ፡ አፍአ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ ዘአስተርአዮ ፡ መልአክ ።

፸ ፤ ወወእተ ፡ ጊዜ ፡ በጽሐ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወቆመ ፡ እምርኁቅ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ።
፸፩ ፤ ወአእመረ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ከመ ፡ እሙን፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ መልአክ ፡ ዘአስተርአዮ ፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ።
፸፪ ፤ ወቆሙ ፡ ካህናት ፡ እምየማኑ ፡ ወእምፀጋሙ ፡ በከመ ፡ ሕግ ፡ ዘልማድ ።
፸፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ለጸ ፡ እምኔሆሙ ፡ አምጽእ፡ ለብእሲ ፡ ቀይሕ ፡ ዘሀሎ ፡ ይቀውም ፡ ቅድሜየ ።
፸፬ ፤ ወጸውዖ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወአምጽኦ ።
፸፭ ፤ ወበጺሖ ፡ ኀቤሁ ፡ ሰገደ ፡ ቅድሜሁ ።

፸፮ ፤ ወተባረከ ፡ እምኔሁ ።
፸፯ ፤ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ አይቴ ፡ ሀሎ፡ ወልድከ ፡ ፍሡሕ ፡ ወቅቡዐ ፡ እመንፈስ፡ ቅዱስ ።
፸፰ ፤ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ እምኔየ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወመላእክቲሁ ።
፸፱ ፤ ወልዑል ፡ ውእቱ ፡ እምእለ ፡ ከማሁ ።

፹ ፤ ወበእንቲአሁ ፡ ይትወሀብ ፡ ሙኣተ ፡ ፀር፡ ለነገሥት ።
፹፩ ፤ ወቅብዓ ፡ ሜሮን ፡ ለካህናት ፡ ፍትሐ ፡ ኢያድልዎ ፡ ለመኳንንት ።
፹፪ ፤ ወኃይለ ፡ ግርማ ፡ ለመሣፍንት ።
፹፫ ፤ ዕቅበተ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ።
፹፬ ፤ ወጽንዓ ፡ ሃይማኖት ፡ ለመሃይምናን ፡ ወመሃይምንት ።
፹፭ ፤ ወሰሚዖ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ዘንተ ነገረ ፡ እምአፈ ፡ አቡነ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ቆመ ፡ ነዋኀ ፡ ሰዓተ ፡ እንዘ ፡ ያነክር፡ እምቃሉ ።
፹፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ጳጳስ ፡ ምንተ ፡ ታነክር ፡ እምቃልየ ፡ ኢሀሎኑ ፡ ወልድከ ፡ ዝየ ።
፹፯ ፤ ወያቤሎ ፡ እወ ፡ ሀሎ ፡ አቡየ ።
፹፰ ፤ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ እንከሰ ፡ ሑር፡ አምጽኦ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ እቀድሶ ፡ በከመ፡ አዘዘኒ ፡ እግዚአብሔር ።
፹፱ ፤ ወአኮ ፡ ኪያሁ ፡ ዘእቄድስ ፡ አላ ፡ ኃጥአ ።

፺ ፤ አላ ፡ ውእቱ ፡ ይቄድሰኒ ፡ በቅድስና ፡ ዘሀሎ፡ ላዕሌሁ ።

፷፮ ፤ ይህን ፡ ከነገረው ፡ በኋላ ፡ ከሱ ፡ ተሰወረ።
፷፯ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ ይህን ፡ የመልአኩን ፡ ቃል፡ ሰምቶ፡ አደነቀ ።
፷፰ ፤ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ፡ ሲያደንቅ ፡ አደረ ።
፷፱ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡ የነገረው ፡ነገር፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ወደደጅ፡ ወጣ ።

፸ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ደረሰ ፡ ከሩቅ ፡ ሁኖ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።
፸፩ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ መልአኩ ፡ የነገረው ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ ዐውቆ ፡ ተመልሶ ፡ ከማዕርጉ ፡ ቦታ፡ ተቀመጠ ።
፸፪ ፤ ካህናቱም ፡ እንደልማዳቸው ፡ በግራ፡ በቀኝ፡ ቆሙ ።
፸፫ ፤ ከነሱ ፡ አንዱን ፡ ያን ፡ የቆመ ፡ ቀይ ፡ ሰው፡ ጠርተህ ፡ አምጣው ፡ አለው ።

፸፬ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብንም ፡ ጠርቶ ፡ አቀረበው ።
፸፭ ፤ ከጳጳሱም ፡ ዘንድ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።
፸፮ ፤ በረከት ፡ ተቀበለ ።
፸፯ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የከበረ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ልጅህ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ አለው ።

፸፰ ፤ በመላእክትና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ነው ።
፸፱ ፤ እንደሱ ፡ ካሉ ፡ ምእመናንም ፡ ይልቅ፡ የከበረ ፡ ነው ።
፹ ፤ በሱ ፡ ምክንያት ፡ ለነገሥታት ፡ ጠላትን፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ ይሰጣል ።
፹፩ ፤ ለካህናትም ፡ በልጅነት ፡ ማክበር ፡ ይሰጣል፡ ለመኳንንትም ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ።

፹፪ ፤ ለመሳፍንቱም ፡ የግርማ ፡ ኃይል ።
፹፫ ፤ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ መጠበቅ ።
፹፬ ፤ ለሴቶችና ፡ ለወንዶች ፡ ምእመናን ፡ የሃይማኖት ፡ ጽናት ፡ ይሰጣል ።
፹፭ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ከአባ ፡ ጌርሎስ ፡ ቃል ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እያደነቀ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ቆሞ ፡ ቆየ ።

፹፮ ፤ ጳጳሱም ፡ ምን ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ ታደንቃለህ ልጅህ ፡ ከዚህ፡ የለምን ፡ አለው ።
፹፯ ፤ አባቴ ፡ አዎን ፡ አለ ፡ አለው ።
፹፰ ፤ ጳጳሱም፡ እንኪያስ ፡ ሂድ ፡ ፈጥነህ ፡ አምጣው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘኝ ፡ አከብረው ፡ ዘንድ ።
፹፱ ፤ እኔ ፡ ኃጥኡ ፡ እሱን ፡ የማከብረው ፡ አይደለም ።
፺ ፤ እሱ ፡ በተሰጠው ፡ ክብር ፡ ያከብረኛል ፡ እንጂ ።

፶፩ ፤ ወሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ዘንተ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ አምጽአ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ለወልዱ ፡ ፍሥሐ ጽዮን ፡ ወዓቀሞ ፡ ቅድመ ፡ ጳጳስ ።

፶፪ ፤ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ተንሥአ ፡ ፍጡነ ፡ እመንበሩ ፡ ወሐቀፎ ፡ ክሣዶ ፡ ወሰዓሞ ።

፶፫ ፤ ወደንገፁ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ ተንሥአ ፡ ጳጳስ ፡ ወሰዓሞ ፡ ለሕፃን ።

፶፬ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ምንተ ፡ ርኢከ ፡ አቡነ ፡ ከመ፡ ትትነሣእ ፡ ጳጳስ ፡ ለዘመጠነዝ፡ ሕፃን።

፶፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ዘአእመርኩ፡ አነ ፡ ኢያእመርክሙ ፡ አንትሙ ።

፶፮ ፤ ዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ወፍቁር ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ ማርያም ፡ እሙ ።

፶፯ ፤ ወኢሀሎ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ሚካኤልኒ ፡ የሐውር ፡ ቅድሜሁ ፡ እንዘ ፡ ያጸንዕ ፡ ሰይፈ ፡ እሳት ።

፶፰ ፤ አንትሙ ፡ ትሬእዩ ፡ ናእሰ ፡ አካሉ ።

፶፱ ፤ ወአነ ፡ እሬኢ ፡ ዕበየ ፡ ጸጋሁ ።

፷ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ነሥአ ፡ ለፍሥሐ ፡ ጽዮን ወአንበሮ ፡ ታሕቴሁ ፡ እንዘ ፡ ይከድኖ ፡ እምአልባሲሁ ፡ ወለአቡሁኒ ፡ ተወክፎ ፡ ሠናየ ፡ በእንቲአሁ ።

፷፩ ፤ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ያኀድርዎ ፡ ኀበ ፡ ሠናይ፡ ማኀደር ።

፷፪ ፤ ወለሊቱሰ ፡ አኀደሮ ፡ ምስሌሁ ።

፷፫ ፤ ወበሳኒታ ፡ ገብረ ፡ ቅዳሴ ፡ ክህነት ፡ በከመ አዘዞ ፡ መልአክ ።

፷፬ ፤ ወአብአ ፡ ለፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ምስሌሁ ፡ ወሤሞ ፡ ዲያቆነ ።

፷፭ ፤ ወፈጺሞ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ወፅአ ፡ አባ፡ ጌርሎስ ፡ ኀበ ፡ ማኀደሩ ።

፷፮ ፤ ወይቤ ፡ አምጽእዎ ፡ ለፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ኀቤየ ።

፷፯ ፤ ወሶበ ፡ አምጽእዎ ፡ አንበሮ ፡ ኀቤሁ ፡ እምጣነ ፡ ፫ ፡ ሱባኤ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈልጦ ፡ እምኔሁ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

፷፰ ፤ ወጥቀ ፡ አፍቀሮ ።

፷፱ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ባረኮ ፡ በኵሉ ፡ በረከተ፡ መንፈሳዊት ።

፸ ፤ ወፈነዎ ፡ በሰላም ፡ ብሔሮ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩ ፤ ወእንዘ ፡ የሐውር ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ለገቢእ ፡ ሀገሮሙ ፡ እምብሔረ ፡ አምሐራ ፡ በጽሑ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ።

፪ ፤ ወይቤሎ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ለወልዱ ።

፫ ፤ አኹሰ ፡ አኃዝን ፡ ብዙኃ ፡ በእንቲአከ ፡ ወበእንቲአየ ።

፶፩ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ ይህን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ልጁ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮንን ፡ ከጳጳሱ ፡ ፊት ፡ አቀረበው ።

፶፪ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ከማዕርግ፡ ቦታው ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሥቶ ፡ አንገቱን ፡ አቅፎ ፡ ሳመው ።

፶፫ ፤ ሕዝቡም ፡ ጳጳሱ ፡ ተነሥቶ፡ ሕፃኑን ፡ ሲስመው ፡ አይተው ፡ ደነገጡ ።

፶፬ ፤ አባታችን ፡ አንተ ፡ ጳጳሱ ፡ ለዚህ ፡ ሕፃን፡ እጅ ፡ መንሣትህ ፡ ምን ፡ አይተህ ፡ ነው ፡ አሉት ።

፶፭ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ እኔ ፡ ያወቅሁትን ፡ እናንት ፡ አላወቃችሁትም ፡ አላቸው ።

፶፮ ፤ ይህ ፡ ልጅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ፡ የከበረ ፡ ነው፡ በናቱ፡ በእመቤታችን፡ በማርያምም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነው ፡

፶፯ ፤ የሚሄደውም ፡ ብቻውን ፡ አይደለም ፡ ሚካኤልም ፡ የእሳት ፡ ሰይፍ ፡ ይዞ ፡ እፊት ፡ እፊቱ ፡ አብሮት ፡ ይሄዳል ፡ እንጂ ።

፶፰ ፤ እናንተ ፡ የአካሉን ፡ ትንሽነት፡ ታያላችሁ።

፶፱ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የተሰጠውን ፡ ክብር ፡ አያለሁ።

፷ ፤ ይህን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮንን ይዞ ፡ ካጠገቡ ፡ አስቀመጠው ፡ ከልብሱም አለበሰው ፡ አባቱንም ፡ ስለልጁ ፡ ደግነት ፡ አክብሮ ፡ ተቀበለው ።

፷፩ ፤ ከደህና ፡ ቦታ ፡ አሳድሩት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፷፪ ፤ ልጁን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አሳደረው ።

፷፫ ፤ በነጋው ፡ መልአኩ ፡ እንዳዘዘው ፡ ቅዳሴ ፡ ሠራ ።

፷፬ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይዞ ፡ ገብቶ ፡ ዲቁና ፡ ሾመው ።

፷፭ ፤ አባ ፡ ጌርሎስም ፡ የቅዳሴውን ፡ ሥርዓት ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ወደቤቱ ፡ ሄደ ።

፷፮ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንን ፡ ወደኔ ፡ አምጡት ፡ አለ።

፷፯ ፤ ከመጣም ፡ በኋላ ፡ ሌትም ፡ ቀንም ፡ ከሱ፡ ሳይለይ ፡ ሦስት ፡ ሱባኤ ፡ አስነበተው ።

፷፰ ፤ እጅግ ፡ ወደደው ።

፷፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ መንፈሳዊ ፡ ክብር አከበረው ።

፸ ፤ ወደሀገሩ ፡ በፍቅር ፡ ሸኘው ።

ሃያኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ካማራ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ለመመለስ ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ ሲሄዱ ፡ ካንዲት ፡ አገር ፡ ደረሱ ።

፪ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ልጁን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

፫ ፤ ስላንተና ፡ ስለኔ ፡ ብዙ ፡ አዝናለሁ ።

፩ ፡ ስንቅንሂ ፡ ኅልቀ ፡ እስመ ፡ ኢንክል ፡
ሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ ዘእንበለ ፡ መብልዕ ።
፪ ፡ አንተ ፡ ሕፃን ፡ ወአነ ፡ አረጋዊ ።
፫ ፡ እስመ ፡ ይከምን ፡ በፍኖት ፡ መኑ ፡ ያነሥአነ ።
፬ ፡ ወሰብአ ፡ ሀገርሂ ፡ እኩያን ፡ እሙንቱ ፡
ወኢይትዌከፉ ፡ ነግደ ።
፭ ፡ ኅድግሰ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ሲሳየ ፡ ውስተ ፡
ቤትሂ ፡ ጥቀ ፡ ኢያበውኡ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተ
ኀየሉሙ ።
፮ ፡ ወይቤሎ ፡ ወልዱ ፡ ለምንት ፡ ተኃዝን ፡ አባ
እንዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ምስሌነ ።
፯ ፡ ኢትዜክርኑ ፡ ቃሎ ፡ ዘይቤ ።
ማቴ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ።
፰ ኢተሐልዩኬ ፡ ወኢትትከዙ ፡ እንዘ ፡ ትብሉ
ምንተ ፡ ንበልዕ ፡ ወምንተ ፡ ንሰቲ ፡ ወምንተ
ንትከደን ።
፱ ፡ እስመ ፡ ዘንተሰ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ አፍአ ፡
የኃሥሥዎ ።
፲ ፡ አንትሙሰ ፡ ሕሡ ፡ መቅድመ ፡ መንግሥተ
ዚአሁ ፡ ወጽድቆ ።
፲፩ ፡ ወዝንቱስ ፡ ኵሉ ፡ ይትዌሰከክሙ ።

፲፪ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ወልድ ፡ ኀሩይ ፡ አኅደጎ
ኀዘነ ።
፲፫ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡሁ ፡ ሕየወኒ ፡ ወልድየ ፡
ለነዋሁ ፡ ዓለም ።
፲፬ ፡ አንሰ ፡ እትአመኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ
ይረድአኒ ፡ በእንቲአከ ።
፲፭ ፡ በዝ ፡ ነገር ፡ ወበዘይመስሎ ፡ እንዘ ፡ ይዛውዑ
ወዓሉ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ።
፲፮ ፡ ወሰበ ፡ መስየ ፡ ይቤሎ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡
አይቴ ፡ ነኃድር ፡ አቡየ ።
፲፯ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡሁ ፡ ኢይቤለከኑ ፡ ወልድየ ፡
ኢይትዌከፉ ፡ ነግደ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡
ውስተ ፡ ቤትሂ ፡ ጥቀ ፡ ኢያበውኡ ።
፲፰ ፡ ወይቤሎ ፡ ወልዱ ፡ ነአ ፡ እስኩ ፡ ናመክሮሙ
ለሰብእ ፡ እለ ፡ ሀለው ፡ አንጻሪነ ።
፲፱ ፡ ወይቤሎ ፡ በልኬ ፡ ንሑር ፡ ወልድየ ።
፳ ፡ ወሐዊሮሙ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡
ይነብሩ ፡ በዴዴ ፡ ቤቶሙ ።
፳፩ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ሰላም ፡ ለሰ
ብእ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ።
፳፪ ፡ እመበ ፡ ዝየ ፡ ውሉደ ፡ ሰላም ፡ ያዕርፍ ፡
ሰላመ ፡ አምላክ ፡ ላዕሌሁ ።
፳፫ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይሰወጥ ፡ ሰላምየ ፡ ሊተ ።
ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።
፳፬ ፡ ወሰሚዖሙ ፡ ቃሎ ፡ ተምዑ ፡ ላዕሌሁ ።
ወይቤልዎ ፡ እስመ ፡ ሰላመ ፡ የሀባ ፡ ለእምክ
ከመ ፡ ትኀድርኑ ፡ ኀቤነ ፡ መጻእከ ።
፳፭ ፡ ወተንሥኡ ፡ ፭ ፡ ብእሲ ፡ እምእለ ፡ ይነብሩ ፡
ህየ ፡ ወዘበጠ ፡ ለቅዱስ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።
፳፮ ፡ ወበከየ ፡ ቅዱስ ፡ ወአንብዓ ፡ ብዙኃ ።

፩ ፡ ስንቃችን ፡ አለቀ ፡ ያለምግብ ፡ መንገድ ፡
መሄድ ፡ አይቻለንምና ።
፪ ፡ አንተ ፡ ሕፃን ፡ ነህ ፡ እኔ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ።
፫ ፡ በጐዳና ፡ ብንወድቅ ፡ ማን ፡ ያነሣናል ።
፬ ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ክፉዎች ፡ ናቸው ፡ እንግዳም
አይቀበሉም ።
፭ ፡ ስንኳን ፡ ምግብ ፡ ሊሰጡ ፡ ከቤት ፡ ስንኳ ፡
አያስገቡም ፡ በግድ ፡ እንጅ ፡ ወደው ፡ አያ
ስገቡም ።
፮ ፡ አባቴ ፡ ለምን ፡ ታዝናለህ ፡ ፈጣሪያችን ፡
ከኛ ፡ ጋር ፡ ሳለ ።
፯ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ የተናገረውን ፡ አታስብምን
ማቴ ፡ ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ።
፰ ፡ ምን ፡ እንበላለን ፡ ምን ፡ እንጠጣለን ፡ ምን
እንለብሳለን ፡ ብላችሁ ፡ አታስቡ ፡ ያለውን ።

፱ ፡ ይህንስ ፡ ሁሉ ፡ ከሃይማኖት ፡ በአፍአ ፡ ያሉ
አሕዛብ ፡ ያደርጉታልና ።
፲ ፡ እናንተስ ፡ አስቀድማችሁ ፡ መንግሥት ፡
ሰማያትን ፡ ልጅነትን ፡ ፈልጉ ።
፲፩ ፡ ይህስ ፡ ሁሉ ፡ ጻረጎት ፡ ሆኖ ፡ ይጨመርላ
ችኋል ።
፲፪ ፡ የተመረጠ ፡ ልጁ ፡ ይህን ፡ ብሎ ፡ ኀዘኑን ፡
አስተወው ።
፲፫ ፡ አባቱም ፡ ልጄ ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ኑርልኝ ፡
አለው ።
፲፬ ፡ ስለአንተ ፡ እንዲረዳኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አምነዋለሁ ።
፲፭ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁሉ ፡
በጐዳና ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ዋሉ ።
፲፮ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ አባቴ ፡
ወዴት ፡ እናድራለን ፡ አለው ።
፲፯ ፡ ልጄ ፡ የዚህ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ እንግዳ ፡ አይቀበ
ሉም ፡ ከቤትም ፡ አያስገቡ ፡ አላልኩህምን ።

፲፰ ፡ ልጁም ፡ እስኪ ፡ ና ፡ ከፊታችን ፡ ያሉትን ፡
ሰዎች ፡ እንፈትናቸው ፡ አለው ።
፲፱ ፡ ልጄ ፡ በል ፡ እንሂድ ፡ አለው ።
፳ ፡ ሄደው ፡ ከቤታቸው ፡ በር ፡ ከተቀመጡ ፡
ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ደረሱ ።
፳፩ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ቸር ፡ ዋላችሁ ፡ ቸር ፡
አደራችሁ ፡ አላቸው ።
፳፪ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ የፈጣሪያችን ፡ ፍቅር
ይደርበት ።
፳፫ ፡ እንደሌለም ፡ ሰላምታዬ ፡ ወደኔ ፡ ይመለስ ።
ማቴ ፡ ፀሥረኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።
፳፬ ፡ ነገሩን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተቆጥተው ፡ እናት
ህን ፡ ፍቅር ፡ ይስጣት ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ልታ
ድር ፡ መጣህ ፡ አሉት ።
፳፭ ፡ ከዚያ ፡ ከተቀመጡበት ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡
ፍሥሐ ፡ ጽዮንን ፡ መታው ።
፳፮ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ብዙ ፡ አለቀሰ ።

፴ ፤ ወይቤሎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ለምንት ፡ ትገብር ፡ ዘንተ ፡ ህየንተ ፡ ሰላምኑ ፡ ተዓስየኒ ፡ ግፍአ ፡ ወህየንተ ፡ ተወክፎ ፡ ዝብጠተ ።

፴፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ አ ፡ ሚካኤል ፡ መልአከ ፡ ኃይሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢትሬኢኑ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ግፍዓ ፡ ዘገብረ ፡ ላዕሌየ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ።

፴፪ ፤ አርእየኒ ፡ ኃይለ ፡ ረድኤትከ ፡ አ ፡ ቅዱሱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፴፫ ፤ ወዘእንበለ ፡ ይትፈጸም ፡ ቃል ፡ እምአፉሁ ለቅዱስ ።

፴፬ ፤ ተሰቅለ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘዘበጦ ፡ መልዕልተ ፡ አየር ፡ ቍልቍሊተ ፡ እንዘ ፡ ይሬእዩ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ።

፴፭ ፤ ወኮነ ፡ ይትቀሠፍ ፡ ብዙኃ ፡ ወኢይትአመር ዘይቀሥፎ ።

፴፮ ፤ ወባሕቱ ፡ ይሰማዕ ፡ ድምፁ ፡ ከመ፡ ድምፀ ፡ ነፋስ ፡ ዓውሎ ።

፴፯ ፤ ወየዓወዩ ፡ ወይብል ፡ አ ፡ ሰብእ ፡ ኄራን፡ መሐሩኒ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ።

፴፰ ፤ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ርእዮም ፡ ዘንተ ።

፴፱ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ኪያነሂ ፡ መሐሩነ ፡ እስመ በኢያእምሮ ፡ ተዓወርናከሙ ።

፵ ፤ ወእምስልዎሙ ፡ ከመ ፡ መሠርያን ፡ እሙንቱ ።

፵፩ ፤ ወአስተብቍዕዎሙ ፡ ብዙኃ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ መሐሩነ ።

፵፪ ፤ ወስቊልሰ ፡ ዓዲሁ ፡ የአወዩ ፡ ወይኬልህ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ መሐረኒ ፡ አንተ ፡ ሕፃን ፡ በእንተ ፡ አምላክከ ፡ ከሃሊ ።

፵፫ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ንኡስ ፡ በአካል ፡ ወምግባርከሰ ፡ እምሰማያት ፡ ይትሌዓል ።

፵፬ ፤ አንሰ ፡ ተአበይኩ ፡ ላዕሌከ ፡ በኢያእምሮትየ ፡ በከመ ፡ ልማድየ ።

፵፭ ፤ ወባሕቱ ፡ አርአይከ ፡ ኃይለከ ፡ በላዕሌየ ።

፵፮ ፤ ወእምይእዜሰ ፡ ኢይገብእ ፡ ኀበ ፡ ዝ ፡ ግብር መሐረኒ ።

፵፯ ፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ከመ ፡ አምነ ፡ ኃጢአቶ ፡ ይቤሎ ፡ ለውእቱ ስቁል ፡ እእመርከኑ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕንበይነ ፡ ግፉዓን ፡ ከመ ፡ ይትበቀል ፡ ሎሙ ፡ ፍጡነ ።

፵፰ ፤ ወይቤ ፡ እወ ፡ አእመርኩ ፡ እግዚእየ ።

፵፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ዘሰቀለከ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ያውርድከ ።

፶ ፤ ወሶቤሃ ፡ አጽነነ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ለወሪድ፡ በበሕቅ ፡ ሕቀ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ምድረ።

፶፩ ፤ ወአስተርአየ ፡ ትምህርተ ፡ ቅሥፈት ፡ ውስተ ፡ ዘባኑ ፡ ከመ ፡ ዘአውዓይዋ ፡ በእሳት

፴ ፤ ይህን ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋለህ ፡ ሰላምታ ፡ ብሰጥህ ፡ ግፍ ፡ ትሰጠኛለህ ፡ እንደመቀበል ፡ ትመታኛለህ ፡ አለው።

፴፩ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሉ ፡ ሚካኤል ፡ ይህ ሰው ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ያደረገው ፡ ግፍ ፡ ሁሉ፡ አታይምን ።

፴፪ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟል ፡ አንተ ፡ የረዳትንትህን ፡ ኃይል ፡ አሳየኝ ።

፴፫ ፤ ክቡር ፡ የሆነ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ይህን ፡ ሲናገር ።

፴፬ ፤ ይህ ፡ የመታው ፡ ሰው ፡ የአገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያየው ፡ ወደሰማይ ፡ ወጥቶ፡ ተዘዝቆ ፡ ተሰቀለ ።

፴፭ ፤ ብዙ ፡ ይገረፋል፡ የሚገርፈው፡ አይታይም።

፴፮ ፤ ድምፁ ፡ እንደጥልቅ ፡ ነፋስ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ፡ እንጂ ።

፴፯ ፤ እናንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉኝ፡ እያለ ፡ ይጮሃል ።

፴፰ ፤ ያገሩም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ አይተው፡ ደነገጡ ።

፴፱ ፤ እኛም ፡ ባለማወቅ ፡ ቸል ፡ ብለናችኋልና፡ እኛንም ፡ ይቅር ፡ በሉን ፡ አሏቸው ።

፵ ፤ እንደጠንቋይ ፡ መስለዋቸው ፡ ነበር ።

፵፩ ፤ ይቅር ፡ በሉን ፡ እያሉ ፡ ብዙ፡ ማለዷቸው።

፵፪ ፤ አንተ ፡ ብላቴና ፡ ሁሉ ፡ ስለሚቻለው ፡ ስለ ፈጣሪህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እያለ ፡ ገና ፡ ይጮህ ፡ ነበር ።

፵፫ ፤ አካልህ ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ ሥራህ ፡ ግን ፡ ከሰማያት ፡ ይበልጣል ።

፵፬ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ባለማወቄ ፡ እንደልማዴ ፡ የትዕቢት ፡ ሥራ ፡ ሠራሁብህ ።

፵፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ላይ፡ ኃይልህን፡ ገለጽህ።

፵፮ ፤ እንግዲህስ ፡ ዳግመኛ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ መሥራት ፡ አልመለስምና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፵፯ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱን እንዳመነ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰዎች ፡ የሚፈርደውን ፡ ፍርድ ፈጥኖም ፡ እንዲበቀልላቸው ፡ ዐወቅህን ፡ አለው ።

፵፰ ፤ ጌታዬ ፡ አዎን ፡ ዐወቅሁ ፡ አለ ።

፵፱ ፤ የሰቀለህ ፡ አምላክ ፡ እሱ ፡ ያውርድህ ፡ አለው ።

፶ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ እስኪደርስ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያለ ፡ ወደታች፡ ወረደ ።

፶፩ ፤ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ እንደተቃጠለ፡ ሁኖ ፡ የግርፋት ፡ ምልክት ፡ ታየ ።

፶፪ ፤ ወቆመ ፡ ቅድሜሆሙ ፡ ወሰገደ ፡ ሎሙ ።

አሪ ፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፶፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አጋእዝትየ ፡ ገሀሡ ፡ ኀበ፡ ገብርክሙ ፡ ባኡ ፡ ቤትየ ፡ ወኀድሩ ፡ አግብርተ ፡ **እግዚአብሔር** ።

፶፬ ፤ ወአኮ ፡ እም ፡ ልቡ ፡ ዘይቤ ፡ ዘንተ ፡ አላ ፡ እምአፉሁ ።

፶፭ ፤ ወእንተ ፡ ውስጡሰ፡ ይመስልዎ፡ መሠርያን ።

፶፮ ፤ ወሰብአ ፡ ሀገርሂ ፡ ተብሃሉ ፡ በበይናቲሆሙ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አነ ፡ አኀድሮሙ ፡ አነ ፡ አኀድሮሙ ።

፶፯ ፤ ወአእመሮሙ ፡ ቅዱስ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን፡** እከየ ፡ ልቦሙ ፡ ዘይሄልዩ ።

፶፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ኢኮነ ፡ ንሕነ ፡ በከመ ፡ ትትሔዘቡነ ፡ አንትሙ ።

፶፱ ፤ አላ ፡ አግብርቲሁ ፡ **ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** ንሕነ ።

ግብ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

፷ ፤ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ንገብር ፡ ኃይለ ።

፷፩ ፤ ወውእቱ ፡ የኃሥሮሙ ፡ ለእለ፡ይሣቅዩነ ።

መዝ ፡ ፶፱ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።

፷፪ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ንሕነሰ፡ ንብል ፡ አማልክት ፡ ተመሲሎሙ ፡ ሰብአ መጽኡ ፡ ኀቤነ ።

ግብ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፲፩ ።

፷፫ ፤ ወይሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ኢትበሉ ፡ ከመዝ ፡ አግብርተ ፡ አምላክ ፡ ንሕነ ።

፷፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ አኀድአሙ ፡ እምእከዮሙ ፡

፷፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ቅዱስ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።**

፷፮ ፤ በእንተ ፡ ማኅደርነሂ ፡ ኢትትበአሱ ፡ ኀበ ዘተሰቅለ ፡ ብእሲ ፡ ነኀድር ።

፷፯ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሠለጠ ፡ በመቅሠፍት ፡ ኃጢአቶ ።

፷፰ ፤ ወይቤ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ አማን ፡ አነ ፡ ተሰቀልኩ ፡ ቤዛ ፡ ዙሎሙ ፡ ርቱዕ ፡ ፍትሕከ ፡ እግዚእየ ።

፷፱ ፤ ወነሥአሙ ፡ በፍሥሐ ፡ ወአብአሙ ፡ ውስተ ቤቱ ።

፸ ፤ ወሠርዓ ፡ ማዕደ ፡ ወዓቅረበ ፡ ሎሙ ።

፸፩ ፤ ወበልዑ ፡ ወጸግቡ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ምስሌሆሙ ።

፸፪ ፤ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወአምጽአ ፡ ማየ ፡ ወሐፀበ ፡ እገሪሆሙ ።

፸፫ ፤ ወሀለወት ፡ ብእሲቱ ፡ ሕምምት ፡ ጥቀ ።

፶፪ ፤ ከፊታቸው ፡ ወድቆ ፡ ሰገደ ።

አሪ ፡ ዘፍ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንተኛ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፶፫ ፤ **የእግዚአብሔር፡** ተገዥዎች ፡ ጌቶቼ፡ ከቤቴ ገብታችሁ ፡ እደሩልኝ ፡ አላቸው ።

፶፬ ፤ ይህንም ፡ ማለቱ ፡ ከልቡ ፡ አምኖ ፡ አይደለም ፡ ባፉ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፶፭ ፤ ውስጡ ፡ ግን ፡ ጠንቋዮች ፡ መስለውት ፡ ነው ።

፶፮ ፤ የሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ እስበሳቸው ፡ እኔ ፡ አሳድራቸዋለሁ ፡ እኔ ፡ አሳድራቸዋለሁ ፡ ተባባሉ ።

፶፯ ፤ **ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡** የልባቸውን ፡ ክፋት፡ ዐውቆ ።

፶፰ ፤ የ ዚህ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ እኛ ፡ እናንተ ፡እንደምትጠራጠሩን ፡ አይደለንም ።

፶፱ ፤ እኛ ፡ **የክርስቶስ ፡** አገልጋዮች፡ነን ፡ እንጂ ።

ግብ ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

፷ ፤ በሱ ፡ ስም ፡ አምነን ፡ ሥራ፡እንሠራለንና።

፷፩ ፤ እሱም ፡ መከራ ፡ የሚያጸኑብንን ፡ እንዲህ፡ ያደርጋቸዋል ።

ሃምሳ ፡ ዘጠኝ ፡ መዝ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።

፷፪ ፤ እኛስ ፡ አማልክት ፡ ሰው ፡ መስለው ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጡ ፡ እንላለን ።

ግብ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፲፩ ።

፷፫ ፡ **ፍሥሐ፡ጽዮንም ፡** እንደዚህ ፡ አትበሉ ። እኛስ ፡ የፈጣሪ ፡ አገልጋዮች ፡ ነን ፡ አላቸው ።

፷፬ ፤ ይህን ፡ ብሎ ፡ ከክፋታቸው ፡ መለሳቸው።

፷፭ ፤ ዳግመኛም ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡** እንዲህ ፡ አላቸው ።

፷፮ ፤ ስለ ፡ ማደሪያችንም ፡ አትጣሉ ፡ ከተሰቀለው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ እናድራለን ፡ አላቸው።

፷፯ ፤ የኃጢአቱን ፡ ፍዳ ፡ ተቀብሏልና ።

፷፰ ፤ ይህም፡ሰው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ ተሰቀልኩ ፡ ጌታዬ ፡ ፍርድህ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ።

፷፱ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይዟቸው ፡ ገባ።

፸ ፤ ማዕድ ፡ ሠርቶ ፡ አቀረበላቸው ።

፸፩ ፤ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በልተው ፡ ጸገቡ ።

፸፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ውኃ ፡ አምጥቶ እግራቸውን ፡ አጠበ ።

፸፫ ፤ ሚስቱ ፡ በጭንቅ ፡ ታማ ፡ ነበር ።

፭፬ ፤ ወወልዱኒ ፡ መጻጉዕ ።
፭፭ ፤ ወነሥአ ፡ ምሕፃበ ፡ እገሪሆሙ ፡ ወረቀዮሙ በአሚን ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አምላኮሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ዘቦኡ ፡ ቤትየ ፡ ያጥኢክሙዮም ።
፭፮ ፤ ወሐይው ፡ በጊዜሃ ፡ ወቆሙ ፡ ርቱዓ ፡ ከመ ዘኢለከፎሙ ፡ ምንትኒ ።
፭፯ ፤ ወተፈሥሐ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወሰገደ ፡ ቅድሜሆሙ ።
፭፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ፈነወክሙ ፡ ኀቤየ ፡ ለሕይወት ።

፭፱ ፤ ናሁ ፡ ብእሲትየ ፡ ሕምምት ፡ ወወልድየ ፡ መጻጉዕ ፡ ተንሥኡ ፡ እምስካቦሙ ፡ ሶበ ለከፎሙ ፡ ጸበለ ፡ እገሪክሙ ።
፷ ፤ ወይቤሎ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡** አኮ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘተፈወሱ ፡ ብእሲትከ ፡ ወወልድከ ። አላ ፡ ሃይማኖትከ ።
፷፩ ፤ እስመ ፡ ዘየአምን ፡ **በክርስቶስ ፡** ኵሉ ፡ ይትገበር ፡ ሎቱ ።

ማርቆስ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፵፫ ።

፷፪ ፤ ወበጽባሕ ፡ ተንሥኡ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ፍኖቶሙ ።
፷፫ ፤ ወተጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሰሚዖሙ ፡ ከመ ፡ ፈወሱ ፡ ዱያነ ፡ ወሰገዱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሆሙ ።
፷፬ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ስረዩ ፡ ለነ ፡ በእንተ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ኵሎ ፡ ዘአበስነ ፡ ለክሙ ።
፷፭ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ይስረይ ፡ ለክሙ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ኵሎ ፡ አበሳክሙ ።

፷፮ ፤ ወእምይእዜሰ ፡ ኢትግበሩ ፡ ከመዝ ።
፷ ፤ ተፋቀሩ ፡ በበይናቲክሙ ።
፷፰ ፤ እስመ ፡ ተፋቅሮ ፡ ይደፍኖን ፡ ለኵሎን ፡ ኃጣውእ ።

ጴጥ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፷፱ ፤ ወአፍቅሩ ፡ ነግደ ፡ በምልአ ፡ ልብክሙ ።

፸ ፤ እንዘ ፡ ኢታስተ ዐፅቡ ።

፸፩ ፤ ወነ መ ፡ ይቤለክሙ ፡ እግዚእ ፡ ርኁብኩ ፡ ወኢያብላዕክሙኒ ፡ ጸማዕኩ ፡ ወኢያስተይክሙኒ ፡ ነግደ ፡ ኮንኩ ፡ ወኢተወከፍክሙኒ ፡ ንሎንተ ፡ ወዘመትልወ ፡ ቃላት ፡ ሶበ ፡ ይትዎቀሰክሙ ፡ በዓውደ ፡ ፍትሕ ፡ ምንተ ፡ ታገብኡ ፡ ሎቱ ።

ማቴ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

፸፪ ፤ ወዳግመ ፡ አዘዘ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አጽግቦ ፡ ለርኁብ ፡ እምእክልከ ።

፭፬ ፤ ልጃም ፡ ጐባጣ ፡ ነበር ።
፭፭ ፤ ዛሬ ፡ ከቤቴ ፡ የገቡ ፡ የሊህ ፡ የቅዱሳን ፡ ፈጣሪ ፡ ያድናችሁ ፡ ብሎ ፡ የእግራቸውን እጣቢ ፡ አምኖ ፡ ረጫቸው ።

፭፮ ፤ ፈጥነው ፡ ዳኑ ፡ ምንም ፡ እንዳላገኛቸው ፡ ሁነው ፡ ተነሥተው ፡ ቆሙ ።
፭፯ ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በፊታቸው ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።
፭፰ ፤ **እግዚአብሔር ፡** እኔን ፡ ለማዳን ፡ ወደኔ ፡ ሰደዳችሁ ።

፭፱ ፤ ታማ ፡ የነበረች ፡ ሚስቴ ፡ መጻጉዕም ፡ የሆነ ልጄ ፡ የእግራችሁ ፡ እጣቢ ፡ በነካቸው ፡ ጊዜ ፡ ከየመኝታቸው ፡ ፈጥነው ፡ ተነሡ ።
፷ ፤ **ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡** ሚስትህና ፡ ልጅህ ፡ ስለኛ ፡ የዳኑ ፡ አይደለም ፡ ሃይማኖትህ ፡ አዳናቸው ፡ እንጂ ።
፷፩ ፤ **በክርስቶስ ፡** ላመነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይደረግለታልና ።

ማርቆስ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፵፫

፷፪ ፤ በነጋው ፡ ጐዳናቸውን ፡ ሊሄዱ ፡ ተነሡ ።

፷፫ ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የታመሙትን ፡ እንዳዳኗቸው ፡ ሰምተው ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ከእግራቸው ፡ ላይ ፡ ወደቁ ።
፷፬ ፤ የበደልናችሁን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ **እግዚአብሔር** ብላችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉን ፡ አሏቸው ።
፷፭ ፤ **እግዚአብሔር ፡** ኃጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡ ይበላችሁ ፡ አሏቸው ።

፷፮ ፤ ዳግመኛ ፡ እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ አታድርጉ ።
፷፯ ፤ እስበሳችሁ ፡ ተፋቀሩ ።
፷፰ ፤ ፍቅር ፡ ኃጢአቶችን ፡ እንዳይሠሩ ፡ ያደርጋቸዋልና ፡ በሠሩም ፡ እንዲሰረዩ ፡ ያደርጋቸዋልና ።

ጴጥ ፡ አራተኛ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፷፱ ፤ በፍጹም ፡ ልቡናችሁ ፡ እንግዳ ፡ መቀበልን ውደዱ ።
፸ ፤ ዕጹብ ፡ ዕጹብ ፡ ሳትሉ ፡ ማለት ፡ ዛሬ ፡ በኔ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ የጭራሮ ፡ ጎጆ ፡ ያለኔ ያቆመው ፡ የለም ፡ ሳትሉ ።
፸፩ ፤ ጌታችን ፡ ብራብ ፡ ኣላበላችሁኝም ፡ ብጸማ ፡ ኣላጠጣችሁኝም ፡ እንግዳ ፡ ብሆን ፡ አልተቀበላችሁኝም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውንም በፍርድ ፡ ዐደባባይ ፡ በወቀሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ትመልሳላችሁ ፡ አላቸው ።

ማቴ ፡ ሃያ ፡ አምስተኛ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

፸፪ ፤ ዳግመኛም ፡ ለተራበው ፡ ከእህልህ ፡ ስጥ ፡ ብሎ ፡ አዝዟል ።

፲፫ ፤ ወአንድሮ ፡ ለነዳይ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎተ ፡ ቤትከ ።
፲፬ ፤ ወእመ ፡ ርኢከ ፡ ዕሩቀ ፡ ክድኖ ፡ እምዘብከ ።
፲፭ ፤ ወኢትትዓወር ፡ እምዘርዓ ፡ ቤትከ ።
፲፮ ፤ ወዘንተ ፡ ሶበ ፡ ትገብር ፡ አኮ ፡ በከ ፡ ኢየኀድገከ ፡ አምላክከ ።
፲፯ ፤ አላ ፡ ጊዜ ፡ ጸዋዕኮ ፡ ነየ ፡ ሀሎኩ ፡ ይብለከ ።
፲፰ ፤ ወይሰምዐከ ፡ ጽራኀከ ።
፲፱ ፤ ወአንከሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ሞገሰ ፡ ቃሉ ፡ ወጣዕመ ፡ ነገሩ ፡ ወሣዕሣዐ ፡ አፉሁ ።
፳ ፤ ወአስተፋነውዎሙ ፡ በሰላም ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አምላክከ ፡ ያኅድር ፡ በልብነ ፡ ኵሎ ፡ ዘተቤለነ ።
፳፩ ፤ ወኀለፉ ፡ እምህየ ፡ ወሀለዉ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ፳ወ፬ ፡ እደው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩ ፤ ወመስዮ ፡ ብሔር ፡ አሚሃኒ ፡ ኢረከቡ ፡ ኅበ ፡ የኀድሩ ።
፪ ፤ ወስንቅኒ ፡ አልቦሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ንስቲት ፡ ጣህል ፡ ዘሀሎ ፡ ጽፍነት ።
፫ ፤ ዘየአክል ፡ መጠነ ፡ መሥፈርተ ፡ ቃሉ ።
፬ ፤ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ጸላዕት ፡ ከመ ፡ ይኅድሩ ፡ ህየ ።
፭ ፤ ወኢረከቡ ፡ ማየ ፡ ዘይሰትዩ ።
፮ ፤ ወተመንደቡ ፡ ጥቀ ፡ በጽማዕ ፡ ማይ ።
፯ ፤ ወተአተተ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ እምኔሆሙ ፡ ሕቀ ፡ ጸለየ ።
፰ ፤ ወይቤ ፡ እግዚኦ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘሰማዕከኒ ፡ ትማልም ፡ በእንተ ፡ ውኁዙ ፡ ብእሲ ፡ ከማሁ ፡ ዮምኒ ፡ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ በበይነ ፡ ማይኒ ።
፱ ፤ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዘአውፃእከ ፡ ማየ ፡ እምኰኵሕ ፡ ልሙድ ፡ አመ ፡ ጸምዑ ፡ ሕዝብከ እስራኤል ።
፲ ፤ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ዘንተ ፡ በከየ ፡ ወወረደ ፡ አንብዑ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።
፲፩ ፤ ወእምኀበ ፡ ወረደ ፡ አንብዑ ፡ ነቅዓ ፡ ማይ ፡ ጸዓዳ ።
፲፪ ፤ ወጣዕሙ ፡ ከመ ፡ አያየተ ፡ መዓር ።
፲፫ ፤ ሰትየ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ነፍሱ ።
፲፬ ፤ ወአዕኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፲፭ ፤ ወጸውዖሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንዑ ስትዩ ፡ እስመ ፡ ረከብኩ ፡ ማየ ።
፲፮ ፤ ወይቤልዎ ፡ እምአይቴ ፡ ረከብከ ፡ አ ፡ ወልድ ፡ ኄሩይ ፡
፲፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ኀበ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ።
፲፰ ፤ መርሆሙ ፡ ወሰትዩ ፡ ወረወዩ ።
፲፱ ፤ እሙንቱሰ ፡ ኢያእመሩ ፡ ከመ ፡ በጸሎቱ ፡ ቅዱስ ፡ ወፅአ ፡ ማይ ።

፲፫ ፤ ድኃውንም ፡ ከቤትህ ፡ አሳድር ።
፲፬ ፤ የታረዘም ፡ ብታይ ፡ ካለህ ፡ ሰጥተህ ፡ አልብሰው ።
፲፭ ፤ ከቤትህም ፡ ዘር ፡ ቸል ፡ አትበል ።
፲፮ ፤ ይህንን ፡ ባደረግህ ፡ ጊዜ ፡ ፈጣሪ ፡ በብላሽ ፡ አይጥልህም ።
፲፯ ፤ በጠራኸው ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡ ይልሐል ፡ እንጂ ።
፲፰ ፤ የለመንከውን ፡ ይሰማሃል ፡ እንጂ ።
፲፱ ፤ ከዚያ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አከናውኖ ፡ መናገሩን ፡ የነገሩን ፡ ጣዕም ፡ የቃሉን ፡ መወደድ ፡ አደነቁ ።
፳ ፤ የነገርከንን ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪህ ፡ በልቡናችን ፡ ያሳድርብን ፡ ብለው ፡ በፍቅር ፡ ሸኝዋቸው ።
፳፩ ፤ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ሄዱ ፡ ከነሱም ፡ ጋራ ሃያ ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ሃያ ፡ አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጊዜውም ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳድራቸው ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ አላገኙም ።
፪ ፤ ስንቅም ፡ አልቀባቸው ፡ ነበር ፡ ባቁማዳ ፡ ጥቂት ፡ ዱቄት ፡ ነበረች ፡ እንጂ ።
፫ ፤ አንድ ፡ ድርጎ ፡ የሚሆን ።
፬ ፤ ከዋሻ ፡ ውስጥ ፡ እንደር ፡ ብለው ፡ ገቡ ።
፭ ፤ እሚጠጡትም ፡ ውኃ ፡ አላገኙም ።
፮ ፤ በውኃ ፡ ጥም ፡ እጅግ ፡ ተጨነቁ ።
፯ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀ ፡ ብሎ ፡ ይለምን ፡ ጀመር ።
፰ ፤ ትናንት ፡ ስለዚያ ፡ ሰው ፡ የሰማኸኝ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዛሬም ፡ ስለ ውኃው ፡ ስማኝ ።
፱ ፤ ወገኖችህ ፡ እስራኤል ፡ በተጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ከደረቅ ፡ ደንጊያ ፡ ውኃ ፡ ያወጣህላቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፲ ፤ እንዲህ ፡ እያለ ፡ እየለመነ ፡ አለቀሰ ፡ ዕንባውም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ወረደ ።
፲፩ ፤ ዕንባው ፡ ከፈሰሰበት ፡ ቦታ ፡ ጽሩ ፡ ውኃ ፡ ወጣ ።
፲፪ ፤ ጣዕሙ ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ወለላ ፡ የሆነ ።
፲፫ ፤ ጠጥቶ ፡ ደስ ፡ አለው ።
፲፬ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነ ።
፲፭ ፤ ሕዝቡንም ፡ ጠርቶ ፡ ውኃ ፡ አግኝቻለሁና ፡ ኑ ፡ ጠጡ ፡ አላቸው ።
፲፮ ፤ አንተ ፡ የተመረጥህ ፡ ልጅ ፡ ከየት ፡ አገኘህ ፡ አሉት ።
፲፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ ካዘዘበት ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።
፲፰ ፤ ወስዶ ፡ አሳያቸው ፡ ጠጥተው ፡ ጠገቡ ።
፲፱ ፤ እነሱ ፡ ግን ፡ ውኃው ፡ የወጣው ፡ በሱ ፡ ጸሎት ፡ እንደሆነ ፡ አላወቁም ።

፳ ፤ ቀድሑ ፡ በአግባሪሆሙ ፡ ወበሐምሐሞሙ ፡ ወወሰዱ ።
፳፩ ፤ ወነሥአ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን** እምውእቱ ፡ ማይ ፡ ወረቀየ ፡ ለውእቱ ፡ ጣህን ፡ እንዘ ፡ የአትብ ፡ በስመ ፡ **ሥላሴ** ።
፳፪ ፤ ወይብል ፡ ምላእ ፡ እግዚኦ ፡ በረከተከ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ጣህን ።
፳፫ ፤ ስንቅነ ፡ ከመ ፡ ኢየሀልቅ ፡ ብነ ።
፳፬ ፤ ወመልአ ፡ ውእቱ ፡ ጣህን ፡ ውስተ ፡ ጽፍንት ፡ ዘሀለወ ፡ ቦቱ ፡ ፍጡነ ፡ በከመ ፡ ቃሉ።
፳፭ ፤ ወአሠነዩ ፡ እምውስቴቱ ፡ በልዐ ፡ ወጸግቡ ።
፳፮ ፤ ወአእኰትዎ ፡ **ለእግዚአብሔር** ።
፳፯ ፤ ወበሳኒታ ፡ ሖረ ፡ ቅዱስ ፤ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ማይ ፡ ወይቤሎ ፡ ኅዳዕ ፡ በቃለ ፡ አምላኪየ ኃያል ።
፳፰ ፤ ወበጊዜሃ ፡ የብሰ ።
፳፱ ፤ ወሖሩ ፡ ፍኖቶሙ ፡ ወውእተሂ ፡ ስንቅ ፡ ኢኀልቀ ፡ እንዘ ፡ ይመስሑ ፡ ወይዴረሩ ፡ እምኔሁ ፡ ፳ወ፮ቱ ፡ እደው ።
፴ ፤ ወተበሃሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ሚመጠነ ፡ ኃይለ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ይተልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ።
፴፩ ፤ ነጽሩ ፡ ዘንተ ፡ ጣህነ ፡ ኢይውህድ ፡ እምእለ ይበልዕዎ ፡ ወኢይከብደሂ ፡ ለእለ ፡ ይጾውርዎ ።
፴፪ ፤ ወበዝንቱ ፡ ነከራ ፡ አተው ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ፡ ዞረሬ ።
፴፫ ፤ ወተቀበለቶሙ ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ በፍሥሐ እንዘ ፡ ትትሐሠይ ።
፴፬ ፤ በእንተ ፡ ዘአተወ ፡ ምታ ፡ ዳኅነ ፡ ወበእንተ፡ ዘኮነ ፡ ወልዳ ፡ ዲያቆነ ።
፴፭ ፤ ወነገራ ፡ **ጸጋ ፡ ዘአብ** ፡ ዘከመ ፡ አፍቀሮ ፡ ጳጳስ ፡ ለወልዳ ፡ ወዘከመ ፡ ኮና ፡ ሎቱ ፡ተአምራት ፡ ብዙኃን ፡ በፍኖት ።
፴፮ ፤ ወሰሚዓ ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ ሰብሐቶ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ በእንቲአሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ ፤ ወልሀቀ ፡ ወልድ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን** ፡ ወወርዘወ ፡ **በመንፈስ ፡ ቅዱስ** ።
፪ ፤ ወተምህረ ፡ ተጽዕኖ ፡ ፈረስ ፡ ወንዒወ ፡ ኦራዊት ፡ ወነጺፈ፡ ቀስት ፡ ወዘሎ ፡ ንዋየ ሐቅል ።
፫ ፤ ሶበሂ ፡ ይጼዓን ፡ ፈረሰ ፡ ይርሕጹ ፡ አፍራስ፡ እምጽንዓ ፡ ኃይሉ ።
፬ ፤ ወሶበሂ ፡ ይዌስክ ፡ ቀስተ ፡ ይረክብ፡ዘሐለየ።
፭ ፤ ቀስቱኒ ፡ ኢትገብእ ፡ ዕራቃ ፡ ዘእንበለ ፡ ትትቀባዕ ፡ ደመ ።

ነገሥት ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

፳ ፤ በየቅላቸው ፡ በየጠርሙሳቸው ፡ ቀድተው ፡ ወሰዱ ።
፳፩ ፤ **ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ በሥላሴ** ፡ ስም ፡ አማትቦ ፡ ከወኀው ፡ ዘግኖ ፡ ዱቄቱን፡ረጨው።
፳፪ ፤ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ዱቄት ፡ አበርክተው እያለ ።
፳፫ ፤ ስንቃችን ፡ እንዳያልቅብን ።
፳፬ ፤ ይህም ፡ ዱቄት ፡ በስልቻቸው ፡ እንዳቃሉ፡ ፈጥኖ ፡ መላ ።
፳፭ ፤ ከሱ ፡ ምግባቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ በልተው ጸገቡ ።
፳፮ ፤ ይህን ፡ የሰጠኸን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ክብር ይግባህ ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ።
፳፯ ፤ በነጋው ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን** ፡ ውኀው ፡ ካለበት ፡ ሄዶ ፡ ኃያል ፡ በሚሆን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ቃል ፡ ጸጥ ፡ በል ፡ አለው ።
፳፰ ፤ ፈጥኖ ፡ ደረቀ ፡ ጕዳናቸውን ፡ ይዘው ፡ሄዱ ።
፳፱ ፤ ይህም ፡ ስንቅ ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ እየተመገቡት ፡ አላለቀም ።
፴ ፤ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለዚህ ፡ ብላቴና ፡ ምን ያህል ፡ ተአምራት ፡ ይደረግለታል ፡ ተባባሉ ።
፴፩ ፤ ይህን ፡ ዱቄት ፡ ተመልከቱ፡ ለሚበሉት ፡ አያልቅባቸውም ፡ ለሚሸከሙትም ፡ አይከብዳቸውም ።
፴፪ ፤ እንዲህ ፡ እያደነቁ ፤ አገራቸው ፡ ዞረሬ ፡ ገቡ ።
፴፫ ፤ **እግዚእ ፡ ሐረያም** ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ወጥታ ፡ ተቀበለቻቸው ።
፴፬ ፤ ልጅዋ ፡ ዲቁና ፡ ስለተቀበለ ፡ ባሏም ፡ ደህና ስለገባ ።
፴፭ ፤ **ጸጋ ፡ ዘአብም** ፡ ጳጳሱ ፡ ልጅዋን ፡ እንደ ፡ ወደደው ፡ በጕዳናም ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ እንደተደረገለት ፡ ነገራት ።
፴፮ ፤ **እግዚእ ፡ ሐረያም** ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ ሰምታ ፡ **እግዚአብሔርን** ፡ አመሰገነች ።

ካያ ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ **ፍሥሐ ፡ ጽዮንም** ፡ ተጽናንቶ ፡ አደገ ፡ **በመንፈስ ፡ ቅዱስም** ፡ ጐለመሰ ።
፪ ፤ ፈረስ ፡ መቀመጥን ፡ አውሬ ፡ ማደንን ፡ በቀስት ፡ መንደፍን ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ሁሉ ፡ ዐወቀ ።
፫ ፤ ፈረስም ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ከኃይሉ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ፈረሶቹ ፡ ይወዙ ፡ ነበር ።
፬ ፤ ጦርም ፡ በወረወረ ፡ ጊዜ ፡ ያሰበውን ፡ ያገኛል ።
፭ ፤ ጦሩም ፡ ደም ፡ ሳትቀባ ፡ ባዶዋን ፡ አትመለስም ።

ነገሥት ፡ አንደኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

፮ ፤ ወኮነ ፡ ጽኑዕ ፡ ጥቀ ፡ በቃሉ ፡ ወበምግባሩ ።

፯ ፤ መልክኡኒ ፡ አደመ ፡ ወሐየሰ ፡ እምኵሎሙ ፡ ወራዙት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ።

፰ ፤ ወሐጸዩ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ አበዊሁ ፡ ወእሙ ፡ ወለተ ፡ ፩ዱ ፡ እምዐበይተ ፡ ሀገር ።

፱ ፤ ወአዕሚሮ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ይቤሎሙ ፡ ለምንት ፡ ተሐጽዩ ፡ ሊተ ፡ ብእሲተ ።

፲ ፤ አንሰ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ላቲ ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ፈኃርኩ ፡ ርእስየ ፡ ለ፩ ፡ ምት ፡ ንጹሕ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፲፪ ፤ ይቤሎ ፡ አቡሁ ፡ ለምንት ፡ ትብል ፡ ከመዝ ወልድየ ።

፲፫ ፤ ሕግ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቤለነ ፡ ለሊሁ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልእዋ ፡ ለምድር ።

አሪ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።

፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ለአቡሁ ፡ ሚመጠን ፡ መንክራት ፡ እለ ፡ ሐፀዩ ፡ ርእሶሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዓቀቡ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ታቦተ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲፭ ፤ ወሚመጠን ፡ ሕፃናት ፡ እለ ፡ ይመውቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይልህቁ ።

፲፮ ፤ ይውህድኑ ፡ ዘርዓ ፡ አዳም ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወበእንቲአየኒ ።

፲፯ ፤ ምንትኒ ፡ ኢይውህድ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ አበዮ ፡ ለአቡሁ ።

፲፰ ፤ ወአምጽአ ፡ ሎቱ ፡ ይእተ ፡ ወለተ ፡ ዘእንበለ ፈቃዱ ፡ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ብእሲተ ።

፲፱ ፤ ወውእቱሰ ፡ ኢያእመራ ።

፳ ፤ እስመ ፡ ኀተም ፡ በድንግልና ፡ ወሰርግው ፡ በቅድስና ።

፳፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ እምዘአ ብእዋ ፡ ሞተት ፡ ይእቲ ፡ ወለት ።

፳፪ ፤ ወተፈሥሐ ፡ ቅዱስ ።

፳፫ ፤ እስመ ፡ ኮነቶ ፡ ዕቅፍተ ፡ በዓይኑ ።

፳፬ ፤ ወነበረ ፡ በንጽሕ ፡ ወበቅድስና ፡ ወኢተአ ሰረ ፡ በኀብለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ።

፳፭ ፤ ወተሰርገወት ፡ ነፍሱ ፡ በፈሪሃ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወበአእምሮ ፡ ጽድቅ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩ ፤ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ ከመዝ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ።

፪ ፤ ወነገሮ ፡ ከመ ፡ ወለጡ ፡ ሰብአ ፡ ሸዋ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሃይማኖተ ፡ ሐዋርያት ።

፫ ፤ ወከመ ፡ ያጥምቁ ፡ ሕፃናተ ፡ እምቅድመ ፡ ይግዝሩ ።

፬ ፤ ወሰሚዖ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ባረኮ ፡ ወአዕ ኰቶ ።

፮ ፤ በተናገረው ፡ ነገር ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የጸና ፡ ሆነ ።

፯ ፤ መልኩም ፡ በሀገሩ ፡ ካሉ ፡ ጐልማሶች ፡ ይልቅ ፡ እያማረ ፡ እየበለጠ ፡ ሄደ ።

፰ ፤ እናት ፡ አባቱም ፡ ከሀገር ፡ ሽማግሎች ፡ ያንዱን ፡ ልጅ ፡ አጨዑለት ።

፱ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ዐውቆ ፡ ለኔ ፡ ሚስት ፡ ማጨታችሁ ፡ ለምንድነው ።

፲ ፤ እኔ ፡ እሷን ፡ አልሻም ፡ አላገባም ።

፲፩ ፤ እኔ ፡ ራሴን ፡ ላንድ ፡ ለንጹሕ ፡ ባል ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጭቻለሁ ፡ አላቸው ።

፲፪ ፤ አባቱም ፡ ልጄ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ።

፲፫ ፤ ውለዱ ፡ ተዋለዱ ፡ ምድርን ፡ ምሏት ፡ ብሎ ጌታ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ አለው ።

አሪ ፡ አንደኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።

፲፬ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ አባቱን ፡ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ራሳቸውን ፡ ያጩ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ያደረጉ ፡ መነኰሳት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ናቸው ።

፲፭ ፤ ተወልደው ፡ ሳያድጉ ፡ የሚሞቱ ፡ ሕፃናት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ አለው ።

፲፮ ፤ ስለኔና ፡ ስለነሱ ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ ያንሳልን ።

፲፯ ፤ ምንም ፡ አያንስ ፡ ይህን ፡ ብሎ ፡ አባቱን ፡ አይሆንም ፡ አለው ።

፲፰ ፤ ያለፈቃዱ ፡ ያችን ፡ ብላቴና ፡ ሚስት ፡ ትሁነው ፡ ብሎ ፡ አመጣለት ።

፲፱ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ በግብር ፡ ዐላወቃትም ።

፳ ፤ በድንግልና ፡ የታተመ ፡ በቅድስና ፡ የተሸለመ ፡ ነውና ።

፳፩ ፤ ባመጧት ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይች ፡ ብላቴና ፡ ሞተች ።

፳፪ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ደስ ፡ አለው ።

፳፫ ፤ ላይኑ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሁናው ፡ ነበርና ።

፳፬ ፤ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ፍቅር ፡ ገመድ ፡ አልተያዘም ።

፳፭ ፤ ሰውነቱ ፡ እውነትን ፡ ነገር ፡ በመውደድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በማምለክ ፡ የተጌጸች ፡ ሆነች ።

ኻያ ፡ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ እንደዚህ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ሄደ ።

፪ ፤ የሸዋ ፡ ሰዎች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥርዓት ፡ እንዳፈረሱ ፡ የሐዋርያትንም ፡ ትምህርት ፡ እንደለወጡ ።

፫ ፤ ሕፃናትን ፡ ሳይገዝሩ ፡ እንደሚያጠምቁ ፡ ነገረው ።

፬ ፤ አባ ፡ ጌርሎስን ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ መረቀው ፡ አመሰገነው ።

፭ ፤ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ቀናዕከ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ከመ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢየ ፡ እስራኤል ።
፮ ፤ ናሁ ፡ አንተ ፡ ትከውን ፡ ሐዋርያ ፡ ሐዲስ ።
፯ ፤ ትሥዕር ፡ ጣዖተ ፡ ወትቄድስ ፡ ታቦተ ።
፰ ፤ ወትሠይም ፡ ቀሳውስተ ፡ ወዲያቆናተ ።
፱ ፤ ወይሰደዱ ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ በቃልከ ፡ እምኵሉ ፡ በሐውርት ።
፲ ፤ ወትመይጦሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እምአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ውስተ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘኀደረ ፡ ላዕሌከ ።
፲፩ ፤ ወወሀቦ ፡ ሢመተ ፡ ቅስና ፡ ዐሜሞ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አድያማተ ፡ ሸዋ ።
፲፪ ፤ ወአያደ ፡ ዐዋዴ ፡ ዘይብል ።
፲፫ ፤ ናሁአ ፡ ሜምክዎ ፡ ለፍሥሐ ፡ ጽዮንአ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርተ ፡ ሸዋአ ።
፲፬ ፤ ከመ ፡ ይኩንአ ፡ እምታሕቴየአ ፤
፲፭ ፤ ዘአሰረአ ፡ ይኩንአ ፡ እሱርአ ።
፲፮ ፤ ወዘፈትሐአ ፡ ይኩንአ ፡ ፍቱሐአ ።
፲፯ ፤ በሥልጣነ ፡ መባሕትአ ፡ ዘወሀቡኒአ ፡ አበውየ ፡ ሐዋርያትአ ፡ አነሂአ ፡ አባሕኩአ ፡ሎቱአ ።
፲፰ ፤ ወፈነዎ ፡ በክብር ፡ ወበሰላም ፡ ውስተ ፡ ብሔሩ ።
፲፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይሰይሞ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ በምድረ ፡ አምሐራ ፡ አስተርአያ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡
፳ ፤ ወይቤላ ፡ ዮም ፡ ተአትበ ፡ ራዕይኪ ፡ ዘቀዳሚ ።
፳፩ ፤ ወልድኪ ፡ ኮነ ፡ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ወአዕዋፍ ፡ ብዙኃን ፡ ነቢሮሙ ፡ ዲቤሁ ፡ ዘርኢኪ ፡ ደቂቁ ፡ እሙንቱ፡እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይትወለዱ ፡ ሎቱ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፳፪ ፤ ወበከመ ፡ ርኢኪ ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ኅብሮሙ ፡ ከማሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ጽድቆሙ ።
፳፫ ፤ ወባሕቱ ፡ አልቦ ፡ ዘይትሃጎል ፡ ፩ሂ ፡ እምኔሆሙ ።
፳፬ ፤ ወውእቱሂ ፡ ዕልው ፡ ዘጼወወኪ ፡ ዓቢየ ፡ ክርስቲያን ፡ ይከውን ፡ በገጸሁ ።
፳፭ ፤ ወእምእንባዜ ፡ ልቡሂ ፡ ይትፌወስ ፡ በጸሎቱ ።
፳፮ ፤ ወእለ ፡ ሞቱ ፡ ሰብእ ፡ እምግርማ ፡ መብረቅአመ ፡ መሰጥኮ ፡ ኪያኪ ፡ ይትነሥኡ ፡ በአስተብቍዖቱ ።
፳፯ ፤ ወይከውን ፡ አበ ፡ ቅዱሳን ።
፳፰ ፤ ወይትቀደስ ፡ ቦቱ ፡ አምላከ ፡ ቅዱሳን ።
፳፱ ፤ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ከሠትኩ ፡ ለኪ ፡ በእንተ ፡ ዘአፍቀርክኒ ፡ ወገበርኪ ፡ ተዝካርየ ።
፴ ፤ ወተሰወረ ፡ መልአክ ፡ እምኔሃ ፡ ምስለዝ ፡ ብሂለ ፡ ቃል ።

፭ ፤ እንደ ፡ እስራኤል ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀንተሃልና ።
፮ ፤ እንደ ፡ ሐዲስ ፡ ሐዋርያ ፡ ትሆናለህ ፡ አለው ።
፯ ፤ ጣዖትን ፡ ታጠፋለህ ፡ ታቦትን ፡ ትባርካለህ
፰ ፤ ቅስና ፡ ዲቁና ፡ ትሾማለህ ።
፱ ፤ አጋንንትም ፡ ባንተ ፡ ቃል ፡ ከየሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ይርቃሉ ።
፲ ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በተሰጠህ ፡ ሐዋርያነት ፡ ብዙዎችን ፡ ሰዎች ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትመልሳቸዋለህ ።
፲፩ ፤ ቅስና ፡ ሰጥቶ ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ።
፲፪ ፤ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ተናገረ ።
፲፫ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንን በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አድርጌ ፡ እነሆ ፡ ሾሜዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ አናገረ ።
፲፬ ፤ ሹመቱ ፡ ከኔ ፡ በታች ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።
፲፭ ፤ በምድር ፡ ያሰረው ፡ በሰማይ ፡ የታሰረ ፡ ይሁን ።
፲፮ ፤ በምድር ፡ የፈታው ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።
፲፯ ፤ አባቶቼ ፡ ሐዋርያት ፡ በሰጡኝ ፡ ሥልጣን ፡ እኔም ፡ ሾሜዋለሁ ፡ ብሎ ፡ አናገረ ።
፲፰ ፤ በፍቅር ፡ አክብሮ ፡ ሾሞ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ሰደደው ።
፲፱ ፤ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ ሲሾመው ፡ ባማራ ፡ አውራጃ ፡ ሳለ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ታያት ፡ ተነጋገራት ።
፳ ፤ ቀድሞ ፡ ያየሽው ፡ ራዕይ ፡ ዛሬ ፡ ተፈጸመ አላት ።
፳፩ ፤ ልጅሽ ፡ በውነት ፡ የብርሃን ፡ ምሰሶ ፡ ሆነ ፤ በሱም ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ያየሻቸው ፡ ብዙ ፡ አዕዋፍ ፡ ልጆቹ ፡ ናቸው ። የመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፳፪ ፤ መልካቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኖ ፡ እንዳየሽው ፡ ሥራቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ።
፳፫ ፤ ከነሱም ፡ አንዱ ፡ስንኳ ፡ የሚጐዳ ፡ የለም ።
፳፬ ፤ ያም ፡ የማረከሽ ፡ ከሃዲ ፡ በሱ ፡ እጅ ፡ ደግ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሆናል ።
፳፭ ፤ አእምሮውንም ፡ ከማጣት ፡ በሱ ፡ ልመና ፡ ይድናል ።
፳፮ ፤ አንችን ፡ ነጥቄ ፡ ባመጣሁሽ ፡ ጊዜ ፡ በመብረቅ ፡ ድንጋጤ ፡ የሞቱትም ፡ ሰዎች ፡ በሱ ልመና ፡ ይነሣሉ ።
፳፯ ፤ የቅዱሳን ፡ አባት ፡ ይሆናል ።
፳፰ ፤ የቅዱሳን ፡ ፈጣሪም ፡ በሱ ፡ ይመሰገናል ።
፳፱ ፤ እኔን ፡ ስለወደድሽና ፡ ዝክሬን ፡ ስለዘከርሽ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገለጽኩልሽ ፡ አላት ።
፴ ፤ መልአኩም ፡ ይህን ፡ ከነገራት ፡ በኋላ ፡ ተሰወረ ።

፴፩ ፤ ወነገረቶ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ለምታ ፡ ዘከመ ፡
አስተርአያ ፡ መልአክ ፡ ወዘከመ ፡ ይቤላ ።
፴፪ ፤ ወይቤላ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ነሀብ ፡ ስብሐተ ፡
ለዘወሀበነ ፡ ዘንተ ፡ ወልደ ።
፴፫ ፤ ወአተወ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ኀቤሆሙ ፡ በሞ
ገስ ፡ ወክብር ፡ እምኀበ ፡ ጳጳስ ፡ ነሢኦ ፡
ሢመተ ፡ ክህነት ፡ ከዊና ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ።
፴፬ ፤ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ተፈሥሑ
ጥቀ ።
፴፭ ፤ ወገብሩ ፡ በዓለ ፡ ዓቢየ ፡ በከመ ፡ ልማዶሙ ፡
ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወለኵሎሙ ፡
ሰብአ ፡ ሀገር ።
፴፮ ፤ ወትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ለወልዳ ፡
ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ማዕዜ ፡ ተሰየምከ ፡
ሢመተ ፡ ክህነት ።
፴፯ ፤ ወነገራ ፡ ዕለቶ ፡ ዘተሰይመ ፡ ቦቱ ።
፴፰ ፤ ወትቤሎ ፡ አነሂ ፡ በውእቱ ፡ አእመርኩ ፡
ዘንተ ፡ እስመ ፡ አስተርአየኒ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካ
ኤል፡ ወከመዝ ፡ ይቤለኒ ።
፴፱ ፤ ወነገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤላ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ በዘመነ ፡ ስብከቱ ፡
ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፪ ፤ እምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ ዓመታት ፡ እምዘ ፡ ተሐ
ይደት ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለእስራኤል ፡ እም
እዴሆሙ ፡ ለድልነዓድ ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ፻ ፡ ፴ ፡
ወ፫ቱ ፡ ዓመታት ።
፫ ፤ አመ ፡ ፯ ፡ ለሐምሌ ፡ አግብዓ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ መንግሥተ ፡ እምነገደ ፡ ሂጳጳ ፡ ለይ
ኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስራኤላዊ ፡ በጸሎቱ ፡
ለቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፬ ፤ በዝየ ፡ ንጽሕፍ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘርሙ ፡ ብዕለ ፡
ነገሥታት ።
፭ ፤ ዘተረክበ ፡ በእደ ፡ አቡነ ፡ ክቡረ ፡ ስም ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፮ ፤ ዘወገ ፡ መላእክት ፡ ወትሩፈ ፡ ምግባራት ።
፯ ፤ ዘኢያጽነንዎ ፡ መንገለ ፡ ሐኬት ፡ እኩያን ፡
ልማድ ፡ መናፍስት ።
፰ ፤ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሀሉ ፡ ስምሌነ ።
፱ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።
፲ ፤ ወነበረ ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይሠመይ ፡ ዘእልመ
ክኑን ።
፲፩ ፤ ዘውእቱ ፡ ይትባረክ ፡ ወልዱ ፡ ለጸድቅ ፡
ንጉሥ ፡ ላሊበላ ።
፲፪ ፤ ወ፩ ፡ ውእቱ ፡ እምነገሥተ ፡ ዛጔ ።
፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ተምዓ ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕለ ፡ ቤተ
ዳዊት ።

፴፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ለባሏ ፡ መልአኩ ፡ እንደ
ታያትና ፡ እንዳላት ፡ ነገረችው ።
፴፪ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ይህንን ፡ ልጅ ፡ ለሰጠን ፡
ለፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ፡ አላት ።
፴፫ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ከጳጳሳት ፡ ዘንድ ፡ ቅስና
ተቀብሎ ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ ተሾሞ ፡ በብዙ
ክብር ፡ ባለሟልነት ፡ ወደነሱ ፡ ተመልሶ ፡
ገባ ።
፴፬ ፤ እናት ፡ አባቱም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡
ደስ ፡ አላቸው ።
፴፭ ፤ እንደልማዳቸው ፡ ለድኀውም ፡ ለሀገሩም ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።
፴፮ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ልጇ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡
ቅስና ፡ የተሾምከው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ አለችው ።
፴፯ ፤ የተሾመበትን ፡ ቀን ፡ ነገራት ።
፴፰ ፤ እኔም ፡ ይህን ፡ ዐወቅሁ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል
እንደዚሁ ፡ ብሎ ፡ ነግሮኛልና ።
፴፱ ፤ የነገራትን ፡ ሁሉ ፡ ለሱም ፡ ነገረችው ።

ኻያ ፡ አራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሚያስተ
ምርበት ፡ ዘመን ፡ በዚያ ፡ ወራት ።
፪ ፤ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡
ያህል ፡ ከድልነዓድ ፡ እጅ ፡ የእስራኤል ፡
መንግሥት ፡ ከሄደች ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡
በኋላ ።
፫ ፤ በሐምሌ ፡ በሰባት ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡
በአባታችን ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልመና ፡
መንግሥትን ፡ ከዛጔ ፡ ወገን ፡ የእስራኤል ፡
ወገን ፡ ለሚሆን ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡
መለሰ ።
፬ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የነገሥታትን ፡ ታሪክ ፡
እንጽፋለን ።
፭ ፤ ስሙ ፡ በከበረ ፡ በአባታችን ፡ በተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ እጅ ፡ የተገኘ ።
፮ ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የመላእ
ክት ፡ ወገን ፡ የሚሆን ።
፯ ፤ በክፉ ፡ ነገር ፡ የጸኑ ፡ አጋንንት ፡ እሱን ፡
ሊዋጉት ፡ የማይቻላቸው ።
፰ ፤ ልመናው ፡ በረከቱ ፡ ከሁላችን ፡ ጋር ፡
ይሁን ።
፱ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።
፲ ፤ እልመክኑን ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡
ነበረ ።
፲፩ ፤ ይኸውም ፡ የጻድቁ ፡ ንጉሥ ፡ የላሊበላ ፡
ልጅ ፡ ይትባረክ ፡ ነው ።
፲፪ ፤ ይኸውም ፡ ከዛጔ ፡ ወገን ፡ ነገሥታት ፡
አንዱ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፲፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዳዊት ፡ ወገኖች ፡ በተቆጣ
ጊዜ ።

፲፬ ፤ ወወሀቦሙ ፡ መንግሥተ ፡ ዳዊት ፡ ለእሉ ፡ ነገሥታተ ፡ ዛጔ ።

፲፭ ፤ ወእንዘ ፡ ሀለወ ፡ በመንግሥቱ ፡ ዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእልመክኑን ።

፲፮ ፤ ተንሥአ ፡ ዶርሆ ፡ ወነቀወ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፤

፲፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዘበልዓ ፡ ርእስየ ፡ ይነግሥ ፡ ወይወርስ ፡ መንግሥተ ፡ ዳዊት ።

፲፰ ፤ ወይነግሥ ፡ በዓለም ፡ ወኢይፈልስ ፡ መንግሥቱ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ።

፲፱ ፤ ወከመዝ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡ ይነቁ ፡ መጠነ ፡ ፫ ፡ አውራኅ ።

፳ ፤ ወፍካሬሁ ፡ ለንቅወት ፡ ዶርሆ ፡ አልቦ ፡ ዘየአምር ።

፳፩ ፤ ወኢእሙኳንንቲሁ ፡ ወኢእመሳፍንቲሁ ።

፳፪ ፤ ወኢእምፍቁራኒሁ ፡ ካህናት ።

፳፫ ፤ ወኢእማእምራነ ፡ መጻሕፍት ።

፳፬ ፤ እንበለ ፡ ንጉሥ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእልመክኑን ።

፳፭ ፤ ወእኅዞ ፡ ፍርሃት ፡ ወረዓድ ።

፳፮ ፤ ወእንዘ ፡ ከመዝ ፡ ይፈርህ ፡ መጽአ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ትእይንቱ ፡ በግርማ ፡ ዓቢይ ።

፳፯ ፤ ወነገርዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ምጽአቶ ፡ አቡነ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፳፰ ፤ ወይቤልዎ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ትእይንትከ ፡ ፩ ፡ መነኮስ ፡ ዘዓቢይ ፡ ሞገሱ ፡ ወመፍርሀ ፡ ገጹ ፡ ወመርዐድ ፡ ኵለንታሁ ፡ ከመ ፡ ትንግሮ ፡ ኵሎ ፡ ኀ ከዘ ፡ ልብከ ።

፳፱ ፤ ወዘንተ ፡ ነገረ ፡ ሶበ ፡ ይቤልዎ ፡ ውእቱኒ ፡ ተሰጥዎሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለሰብአ ፡ ቤቱ ፡ መንገለ ፡ አይቴ ፡ ሀሎ ፡ ዝኩ ፡ መነኮስ ፡ ዘትብሉኒ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ትእይንትከ ።

፴ ፤ ወአውሥኡ ፡ ወይቤልዎ ፡ ናሁ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መልአከ ፡ ኃይልከ ።

፴፩ ፤ ወሰሚዖ ፡ ተሰጥዎተ ፡ ነገረ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ተንሥአ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእልመክኑን ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወመኳንንቲሁ ፡ ወመሣፍንቲሁ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፴፪ ፤ ወወድቀ ፡ በቅድሜሁ ፡ ወተሳለመ ፡ እደዊሁ ወእገሪሁ ።

፴፫ ፤ ወወእቱኒ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተንሥአ ፡ ፍጡነ ፡ ወአንሥኦ ።

፴፬ ፤ ወተቀበሎ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሐሤት ፡ ወነበሩ ፡ ኅቡረ ።

፴፭ ፤ ወአግሐሡ ፡ ሰብአ ፡ እምቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ ከመ ፡ ይዚያነው ፡ ነገራቲሆሙ ።

፴፮ ፤ ወአይድኦ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእልመክኑን ፡ ነገረ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ ወፍካሬ ፡ ቃሉ ።

፴፯ ፤ ወይቤሎ ፡ አንሰ ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ስኩበ ውስተ ፡ አራትየ ፡ ጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ወነቃሕኩ ፡ ሶቤሃ ፡ እምንዋም ።

፲፬ ፤ የዳዊትን ፡ መንግሥት ፡ ለኒህ ፡ ለዛጔ ፡ ልጆች ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ ይህ ፡ እልመክኑን ፡ ንግሥ ፡ ሳለ ።

፲፮ ፤ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ዶሮ ፡ ተነሥቶ ፡ ጮኸ ።

፲፯ ፤ የኔን ፡ ራስ ፡ የበላ ፡ ይነግሣል ፡ የዳዊትን ፤ መንግሥት ፡ ይወርሳል ።

፲፰ ፤ በዓለም ፡ ነግሦ ፡ ይኖራል ፡ መንግሥቱም ፡ ወደሌላ ፡ አይሄድም ፡ እያለ ።

፲፱ ፤ ሦስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ሲጮህ ፡ ሰነበተ ።

፳ ፤ የዶሮውን ፡ ጩኸት ፡ ትርጓሜ ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ።

፳፩ ፤ ከመኳንንቱም ፡ ከመሣፍንቱም ።

፳፪ ፤ ከወዳጆቹም ፡ ከካህናት ።

፳፫ ፤ ከመጽሐፍ ፡ ዐዋቂዎችም ።

፳፬ ፤ ንጉሡ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከንጉሡ ፡ በቀር ።

፳፭ ፤ ንጉሡን ፡ ፍርሃት ፡ እንቅጥቅጥ ፡ አደረበት

፳፮ ፤ እንዲህ ፡ እየፈራ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መጥቶ ፡ በታላቅ ግርማ ፡ ከከተማው ፡ ገባ ።

፳፯ ፤ ለንጉሡ ፡ የአባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መምጣት፡ ቤተሰቡ ፡ ነገሩት ።

፳፰ ፤ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ሁለንተናው ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያስፈራ ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ ከከተማህ ፡ ገብቷል ፡ የልቡናህን ፡ ኀዘን ፡ ሁሉ ፡ ንገረው ፡ አሉት ።

፳፱ ፤ ይህን ፡ በነገሩት ፡ ጊዜ ፡ እሱም ፡ ከከተማህ ፡ ገብቷል ፡ የምትሉኝ ፡ መነኩሴ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፡ አላቸው ።

፴ ፤ ከሠራዊትህ ፡ አበጋዝ ፡ ቤት ፡ አለ ፡ አሉት ።

፴፩ ፤ ንጉሡም ፡ ዘእልመክኑን ፡ ቤተሰቡ ፡ የነገሩትን ፡ መልስ ፡ ሰምቶ ፡ ሠራዊቱን ፡ መኳንንቱን ፡ መሳፍንቱን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ አባታችን ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሄደ ።

፴፪ ፤ ከፊቱ ፡ ወድቆ ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ሳመ ።

፴፫ ፤ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ከወደቀበት ፡ አነሣው ።

፴፬ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ አክብሮ ፡ ተቀበለው ፡ ባንድነት ፡ ተቀመጡ ።

፴፭ ፤ ነገራቸውን ፡ ይነጋገሩ ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ከፊታቸው ፡ አስወገዱ ።

፴፮ ፤ ንጉሡም ፡ እልመክኑን ፡ የዶሮውን ጩኸት ፡ ነገር ፡ የነገሩንም ፡ ትርጓሜ ፡ ነገረው ።

፴፯ ፤ እኔ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ከዕንቅልፌ ፡ ነቃሁ ።

፴፰ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ ምስለ ፡
ፍካሬሁ ።
፴፱ ፤ ወካልዓነስ ፡ ኢሰምዑ ።
፵ ፤ አ ፡ አቡየ ፡ ኢይድአኒ ፡ ዘነጋቲሁ ፡ ለዝንቱ
ነገር ።
፵፩ ፤ አንስ ፡ ስእንኩ ፡ ተርጕሞቶ ፡ ወጠይቆቶ ፡
ለዝንቱ ፡ ነገር ።
፵፪ ፤ ምንትኑ ፡ ምክንያቱ ፡ ወምንት ፡ ምክንያቱ ፡
ጾታ ፡ ነገሩ ።
፵፫ ፤ ሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ለእልመክኑን ፡ ንጉሥ ፡
በቃለ ፡ ግናይ ።
፵፬ ፤ አውሥአ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ወይ
ቤሎ ፡ ዕጹብ ፡ ነገረ ፡ ተስእልከኒ ፡ ዘኢኮነ ፡
እምቅድመዝ ፡ ወኢይከውንኒ ፡ እምድኅረዝ።
፵፭ ፤ ወአርመመ ፡ ነዋህ ፡ ሰዓተ ፡ በተደሞ ፡ ወበ
አንክሮ ።
፵፮ ፤ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ስማዕ ፡ እን
ግርከ ፡ ዘትቤለኒ ፡ ነገረ ።
፵፯ ፤ ተንሥአ ፡ ወአኀዘ ፡ ለውእቱ ፡ ዶርሆ ፡
ጎርድ ፡ ወብላዕ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ንባበ ፡ ቃሉ ፡
ለዝኩ ፡ ዶርሆ ፡ ዘይቤ ፡ ዘበልዓ ፡ ርእስየ ፡
ኢይፈልስ ፡ መንግሥት ፡ እምነ ፡ ቤቱ ፡
ወይነግሥ ፡ ለዓለም ።
፵፰ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእል
መክኑን ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መንግ
ሥት ፡ ወጸውዓ ፡ ለዓመቱ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡
ደሊላዊት ።
፵፱ ፤ ወክብርት ፡ ይእቲ ፡ እምአዕማቲሁ ።
፶ ፤ ወይቤላ ፡ ተንሥኢ ፡ ወአኀዚዮ ፡ ለዝንቱ ፡
ዶርሆ ፡ ወጎርዲዮ ፡ ለዘይነቀውዕ ፡ ዶርሆ ፡
ውስተ ፡ ቤትየ ፡ ወትረ ፡ ከመ ፡ እብልዖ ፡
ፍጡነ ፡ በኢጕንድዮ ።
፶፩ ፤ ወኢይቅረባ ፡ ካልዓት ፡ አንስት ፡ ዘእንበ
ሌኪ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ዶርሆ ።
፶፪ ፤ ዳዕሙ ፡ ግበሪዮ ፡ በኅቡእ ።
፶፫ ፤ ወኢትከሥቲዮ ፡ እስመ ፡ ኅቡእ ፡ ምሥ
ጢሩ ።
፶፬ ፤ ወዘንተ ፡ ነገራ ፡ ሶበ ፡ ይቤላ ፡ ተንሥአት ፡
ፍጡነ ፡ አኀዘቶ ፡ ወኀረደቶ ።
፶፭ ፤ ወወደየት ፡ ውስቴቱ ፡ ብዙኃተ ፡ አቃቢ
ራተ ፡ ከመ ፡ ታምእዞ ፡ ለውእቱ ፡ ዶርሆ ።
፶፮ ፤ ወለርእሰ ፡ ዶርሆሰ ፡ ገደፈቶ ፡ ወኀደገቶ ፡
ውስተ ፡ ምንዳደ ፡ ቤታ ።
፶፯ ፤ እምጣነ ፡ ባቲ ፡ ልማድ ።

ክፍል ።

፶፰ ፤ ወበውእቱ ፡ ዘመን ፡ ነበረ ፡ ፩ ፡ ወልድ ፡
ዘስሙ ፡ ይኩኖ ፡ እምላክ ፡ ዘተኃርየ ፡ እም
ከርሠ ፡ እሙ ፡ ወዘይወርስ ፡ መንበረ ፡
ዳዊት ፡ አቡሁ ።

፴፰ ፤ የዶሮውን ፡ ጩኸት ፡ ከነትርጓሜው ፡
ሰማሁ ።
፴፱ ፤ ሌሎቹ ፡ ግን ፡ አያውቁትም ።
፵ ፤ አባቴ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ አኳኋን ፡ ንገረኝ ፡
አለው ።
፵፩ ፤ እኔስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ መረዳት ፡
አልተቻለኝም ።
፵፪ ፤ ምክንያቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ የነገሩስ ፡
ስልት ፡ አኳኋን ፡ ምንድር ፡ ነው ።
፵፫ ፤ ንጉሥ ፡ እልመክኑን ፡ በልመና ፡ ቃል ፡
እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ።
፵፬ ፤ ከዚህ ፡ ቀደሞ ፡ ያልተደረገ ፡ ወደፊትም ፡
የማይደረግ ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ነገር ፡ ጠየ
ቅከኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።
፵፭ ፤ በማድነቅ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ቆየ ።
፵፮ ፤ የምትለኝን ፡ ነገር ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡ ብሎ
ነገር ፡ ጀመረ ።
፵፯ ፤ ያ ፡ ዶሮ ፡ የኔን ፡ ራስ ፡ የበላ ፡ መንግሥት ፡
ከወገኑ ፡ አይወጣም ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡
ይነግሣል ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ተነሥ
ተህ ፡ ዶሮውን ፡ ይዘህ ፡ አርደህ ፡ ራሱን ፡
ብላው ፡ አለው ።
፵፰ ፤ ንጉሡም ፡ ዘእልመክኑን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ወደቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብቶ ፡ ደሊ
ላዊት ፡ የምትባል ፡ ገረዱን ፡ ጠራት ።
፵፱ ፤ ይቺውም ፡ ከባሮቹ ፡ ሁሉ ፡ የከበረች ፡ ናት ።
፶ ፤ ከቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ዘወትር ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡
የሚጮኸውን ፡ ዶሮ ፡ ይዘሽ ፡ አርደሽ ፡ ፈጥ
ነሽ ፡ አዘጋጅው ፡ እንድመገበው ፡ አላት ።
፶፩ ፤ ከዚህ ፡ ከዶሮ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ አንቺ ፡ ሌላ
ሴት ፡ አይቅረብ ።
፶፪ ፤ ተሰውረሽ ፡ አድርጊው ፡ እንጂ ።
፶፫ ፤ ምሥጢሩ ፡ ረቂቅ ፡ ነውና ፡ ለማንም ፡
አትግለጭ ፡ አላት ።
፶፬ ፤ ይህንን ፡ በነገራት ፡ ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ ተነሥታ
ይዛ ፡ አረደችው ።
፶፭ ፤ ታጣፍጠው ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ቅመም ፡
ጨመረችበት ።
፶፮ ፤ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ ግን ፡ ከምድጃው ፡ ዳር ፡
ጣለችው ።
፶፯ ፤ ልማዷ ፡ ነውና ።

ክፍል ።

፶፰ ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በናቱ ፡ ማኅፀን ፡ የተመረጠ
ያባቱ ፡ የዳዊትን ፡ መንግሥት ፡ የሚወርስ ፡
ይኩኖ ፡ እምላክ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡
ነበረ ።

፶፱ ፤ ወተዘከረ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላሁ ፡ ዘመ
ሐለ ፡ ለዳዊት ፡ ዘይቤሎ ፡ ወአሐንጽ ፡ ለት
ውልደ ፡ ትውልድ ፡ መንበረከ ።

መዝ ፡ ፹፰ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፳ ፤ እመስ ፡ ኀደጉ ፡ ደቂቁ ፡ ሕግየ ።
፳፩ ፤ ወኢሖሩ ፡ በኵነኔየ ።
፳፪ ፤ እዋኅያ ፡ በበትር ፡ ለኃጢአቶሙ ።
፳፫ ፤ ወበመቅሠፍት ፡ ለአበሳሆሙ ።

፳፬ ፤ ወሣህልየሰ ፡ ኢይከልዕ ፡ እምኔሆሙ ።
፳፭ ፤ ወኢይኤምፃ ፡ በጽድቅየ ።

፳፮ ፤ ምዕረ ፡ መሐልኩ ፡ በቅዱስየ ፡ ከመ ፡ ለዳ
ዊት ፡ ኢይኤስዎ ።

፳፯ ፤ ወዘርዑሂ ፡ ለዓለም ፡ ይሄሉ ።
፳፰ ፤ ወመንበሩሂ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ በቅድሜየ ።

፳፱ ፤ ወሥሩዕ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡ ለዓለም ።
፴ ፤ ወመትልወ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአፈ ፡ ዳዊት ።
፴፩ ፤ ወአልዓልኩ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ።
፴፪ ፤ ወረከብክዎ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርየ ።
፴፫ ፤ ወቀባዕክዎ ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱስ ።
፴፬ ፤ እስመ ፡ እዴየ ፡ ትረድኦ ፡ ወመዝራዕትየ ፡
ታጸንዖ ።
፴፭ ፤ ወኢይበቍዕ ፡ ጸላዒ ፡ በላዕሌሁ ።
፴፮ ፤ ወውሉደ ፡ ዓመፃ ፡ ኢይደግም ፡ አሕምሞቶ።
፴፯ ፤ ወእመትሮሙ ፡ ለፀሩ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።
፴፰ ፤ ወአኀሥሮሙ ፡ ለጸላዕቱ ።
፴፱ ፤ ሣህልየሰ ፡ ወጽድቅየ ፡ ምስሌሁ ።

፵ ፤ ወበስምየ ፡ ይትሌዓል ፡ ቀርኑ ።
፵፩ ፤ ወእሠይም ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ እዴሁ ።
፵፪ ፤ ወውስተ ፡ አፍላግ ፡ የማኖ ፡ ውእቱ ፡ ይብ
ለኒ ፡ አቡየ ፡ አንተ ።
፵፫ ፤ አምላኪየ ፡ ረዳእየ ፡ ወመድኃንየ ።
፵፬ ፤ ወአነሂ ፡ በኵርየ ፡ እሬስዮ ።
፵፭ ፤ ወልዑል ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር ፡ ወለዓለም
እዓቅብ ፡ ሎቱ ፡ ሣህልየ ።
፵፮ ፤ ወምእመን ፡ ውእቱ ፡ ለኪዳንየ ።
፵፯ ፤ ወእሬሲ ፡ ዘርዖ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
፵፰ ፤ ወመንበሩሂ ፡ ከመ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

፩ ፤ ንግባዕኬ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ነገር ፡ ወውእቱሰ ፡
ወልድ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡
ይትቀነይ ፡ ለንጉሥ ፡ ዘእልመክኑን ።
፪ ፤ ወተቀንዮቱሂ ፡ ቦ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ የዓጽድ ፡
ማዕረ ፡ ለአብቅልተ ፡ ንጉሥ ።
፫ ፤ ወቦ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ያበልዕ ፡ እክለ ፡ ለአፍራሰ
ንጉሥ ።

፶፱ ፤ መንበረ ፡ መንግሥትህ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አን
ጽልሐለሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት
የተናገረውን ፡ ነገር ፡ አሰበ ።

መዝ ፡ ፹፰ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፳ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ልጆቹ ፡ ሕጌን ፡ ቢያፈርሱ ።
፳፩ ፤ በሕጌ ፡ ጸንተው ፡ ባይኖሩ ።
፳፪ ፤ ጥቃቅን ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠሩ ፡ በበትር ።
፳፫ ፤ ደጋግ ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠሩ ፡ በጨንገር ፡ እቀ
ጣቸዋለሁ ።
፳፬ ፤ ይቅርታዬንም ፡ ከነሱ ፡ አላርቅም ።
፳፭ ፤ የተናገርኩትንም ፡ ነገር ፡ አላስቀርባቸ
ውም ።
፳፮ ፤ ለዳዊት ፡ የተናገርኩትን ፡ ነገር ፡ እንዳላ
ስቀር ፡ ሕያውየ ፡ አማንየ ፡ ብዬ ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ ተናግሬያለሁ ፡ ምያለሁ ።
፳፯ ፤ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል።
፳፰ ፤ መንበረ ፡ መንግሥቱም ፡ ፀሐይ ፡ ሳያልፍ ፡
አያልፍም ።
፳፱ ፤ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።
፴ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ዳግመኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
በዳዊት ፡ አድሮ ፡ ተናገረ ።
፴፩ ፤ ከወገኖቼ ፡ ይልቅ ፡ ዳዊትን ፡ መረጥኩ ።
፴፪ ፤ ባለሟሌ ፡ ዳዊትን ፡ አገኘሁ ።
፴፫ ፤ ቀብቼ ፡ አነገሥኩት ።
፴፬ ፤ ሥልጣኔ ፡ ትረዳዋለች ፡ ታጸናዋለች ።

፴፭ ፤ ጠላቱ ፡ አይሠለጥንበትም ።
፴፮ ፤ ዳግመኛ ፡ ጠላት ፡ መከራ ፡ አያመጣበትም ።
፴፯ ፤ ጠላቶቹን ፡ ከፊቱ ፡ አጠፋቸዋለሁ ።
፴፰ ፤ ጠላቶቹን ፡ አጐሳቍላቸዋለሁ ።
፴፱ ፤ ይቅርታዬ ፡ ቸርነቴ ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡
ጸንቶ ፡ ይኖራል ።
፵ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ ሥልጣኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ይላል ።
፵፩ ፤ ሥልጣኑ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ፍኖራል ።
፵፪ ፤ ሥልጣኑም ፡ በነገሥታቱ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፡
እሱም ፡ አባቴ ፡ ይለኛል ።
፵፫ ፤ ፈጣሪዬ ፡ ረዳቴ ፡ መድኃኒቴ ፡ ይለኛል ።
፵፬ ፤ እኔም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አደርገዋለሁ ።
፵፭ ፤ ከነገሥታት ፡ በላይ ፡ ይሆናል ፡ ይቅርታዬን
ለዘላለሙ ፡ አጸናለታለሁ ።
፵፮ ፤ ለቃል ፡ ኪዳኔም ፡ የታመነ ፡ ነው ።
፵፯ ፤ የልጅ ፡ ልጁን ፡ ለዘላለም ፡ አጸናዋለሁ ።
፵፰ ፤ መንበረ ፡ መንግሥቱም ፡ ሰማይ ፡ ሳያልፍ ፡
አያልፍም ።

ኻያ ፡ አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ይህም ፡ ልጅ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ለንጉሡ ፡
ለእልመክኑን ፡ ሲያገለግል ፡ ኖረ ።

፪ ፤ ሲያገለግልም ፡ ለንጉሡ ፡ በቅሎች ፡ ሣር ፡
የሚያጭድበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።
፫ ፤ ለፈረሶቹም ፡ እህል ፡ የሚያበላበት ፡ ጊዜ ፡
አለ ።

፬ ፤ ወቦጊዜ ፡ እንዘ ፡ ይጸውር ፡ ሰይፈ ፡ ወኲናተ ፡ ወወልታ ፡ በቅድመ ፡ ንጉሥ ።
፭ ፤ ወለርእሰ ፡ ዶርሆሂ ፡ ዘኀደገቶ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ምንዳድ ፡ ረከበ ፡ ውእቱ ወልድ ፡ ይኩኖ ፡ እምላከ ፡ ነሥአ ፡ ወበልዓ ፡ ወመልአ ፡ ከርሦ ።
፮ ፤ ወረሰዮ ፡ ልዑለ ፡ ወኃያለ ፡ እስከ ፡ ተለዓለ ፡ መልዕልተ ፡ ኵሎሙ ፡ ኃያላን ።
፯ ፤ ወአብርሃ ፡ ገጹ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ።
፰ ፤ ወገረሞሙ ፡ ግርማሁ ፡ ለኵሎሙ ፡ አግብርተ ፡ ንጉሥ ።
፱ ፤ ወፈርህዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወአንከርዎ ።
፲ ፤ ወአፍቀርዎ ፡ ጥቀ ፡ ወወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ።
፲፩ ፤ ወአእመሩ ፡ ከመ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ።
፲፪ ፤ ወይቤሉ ፡ ምንትኑ ፡ ነገር ፡ ዘይከውን ፡ ላዕለ እደ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩ ፤ ካዕበ ፡ ንትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ነገረ ፡ ዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘአልመክኑን ።
፪ ፤ ወሶበ ፡ ኢረከበ ፡ ለዝንቱ ፡ ርእሰ ፡ ዶርሆ ፡ እምውስተ ፡ ጸሀል ፡ ደንገፀ ፡ ወተከዘ ፡ ወተሐውከ ።
፫ ፤ ወበከየ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአንገርገረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።
፬ ፤ ተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፭ ፤ ወተራከቡ ፡ በበይናቲሆሙ ።
፮ ፤ ወአግሐሡ ፡ ሰብአ ፡ እምቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ።
፯ ፤ ወተርፉ ፡ ባሕቲቶሙ ።
፰ ፤ ወነገሮ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ኵነተ ፡ ርእሰ ፡ ዶርሆ ።
፱ ፤ ወይቤሎ ፡ አንሰ ፡ ገበርኩ ፡ በከመ ፡ አዘዝከኒ ፡ ወአመክርከኒ ።
፲ ፤ ወብእሲትሰ ፡ አጥፍአቶ ፡ ለርእሰ ፡ ዶርሆ ፡ ወኢረከበቶ ፡ ኀበ ፡ ወገረቶ ።
፲፩ ፤ እስመ ፡ መሰላ ፡ ከመ ፡ ኢይበልዕ ፡ አነ ፡ ርእሰ ፡ ዶርሆ ፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ አነሂ ፡ ተከዝኩ ፡ ወደንገፅኩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወመጻእኩ ፡ ኀቤከ ፡ ከመ ፡ እንግርከ ፡ ወእዜኑከ ።
፲፪ ፤ ናሁ ፡ ምክንያተ ፡ ጥፍዓቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ርእሰ ፡ ዶርሆ ፡ እ ፡ አቡየ ፡ በዘይትከሃለከ ፡ ተራድአኒ ፡ ወአመክረኒ ፡ እስመ ፡ ብከ ፡ ሀሎ ፡ ሥልጣን ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ።
፲፫ ፤ እስመ ፡ ጸሎትከኒ ፡ ትክል ፡ ወታሠልጥ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ እኁወ ፡ እግዚእነ ።

፬ ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ሰይፍ ፡ ዣግሬ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬ ፡ እየሆነ ፡ ነው ።
፭ ፤ ይህች ፡ ሴት ፡ ከማጀት ፡ እምድጃ ፡ የጣለችውን ፡ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ ይኩኖ ፡ እምላክ ፡ አግኝቶ ፡ አንሥቶ ፡ በላው ፡ ፈጥኖ ፡ ጠገበ ።
፮ ፤ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡ ኃይለኛ ፡ አደረገው ።
፯ ፤ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ብሩህ ፡ ሆነ ።
፰ ፤ ግርማው ፡ የንጉሡን ፡ ባሮች ፡ ሁሉ ፡ አስፈራቸው ።
፱ ፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፈሩ ፡ አደነቁ ።
፲ ፤ እጅግ ፡ ወደዱት ፡ ነገሩን ፡ በልቡናቸው ፡ አስተዋሉት ።
፲፩ ፤ ሀብተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳደረበት ፡ ዐወቁ ።
፲፪ ፤ በዚህ ፡ ብላቴና ፡ እጅ ፡ የሚደረገው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ አሉ ።

ኻያ ፡ ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዘአልመክኑን ፡ ነገር ፡ እንመለስ ።
፪ ፤ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ ከሳህኑ ፡ ላይ ፡ ባጣው ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ አዘነ ፡ ልቡናው ፡ ተሸበረ ።
፫ ፤ አጽንቶ ፡ አለቀሰ ፡ ተፍገምግሞ ፡ ወደቀ ።
፬ ፤ ተነሥቶ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አባታችን ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ።
፭ ፤ ተገናኙ ።
፮ ፤ እንደቀድሞው ፡ ሰውን ፡ ከፊታቸው ፡ አስወግደው ።
፯ ፤ በቀይታ ፡ ተነጋገሩ ።
፰ ፤ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ አኳኋን ፡ ለአባታችን ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነገረው ።
፱ ፤ እኔስ ፡ እንዳዘዝከኝ ፡ እንደመከርከኝ ፡ አደረግሁ ።
፲ ፤ ሴቲቱ ፡ ግን ፡ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ አጠፋችው ከጣለችበትም ፡ ቦታ ፡ ብትፈልገው ፡ አጣችው ።
፲፩ ፤ የዶሮውን ፡ ራስ ፡ የማልበላ ፡ መስሏት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አዘንኩ ፡ ብዙ ፡ ደነገጥኩ ፡ ይህን ፡ ልነግርህ ፡ መጣሁ ።
፲፪ ፤ የዚህ ፡ የዶሮ ፡ ራስ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። አባቴ ፡ በተቻለህ ፡ ርዳኝ ፡ ምከረኝ ፡ በሰማይ ፡ በምድርም ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶሀልና ።
፲፫ ፤ ጸሎትህም ፡ ግዳጅ ፡ ትፈጽማለችና ፡ የጌታችን ፡ ወንድም ፡ ሐዋርያው ፡ ያዕቆብ ፡ እንደተናገረ ።

፲፬ ፤ ወሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ዘንተ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእልመ
ክኑን ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፲፭ ፤ ወውእቱሂ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ብፁዓዊ ፡ ወኃያል ፡ ያርብሓዊ ፡ ሰሚዖ ፡
ዘንተ ፡ ነገረ ፡ እምአፈ ፡ ንጉሥ ፡ ተንሥአ ፡
ወአውተረ ፡ ጸልዮ ፡ ወአንቃዕደወ ፡ ገጾ ፡
መንገለ ፡ ሰማይ ።
፲፮ ፤ ወይቤ ፡ አ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ አማል
ክት ፡ ወእግዚአ ፡ አጋዕዝት ፡ ወንጉሠ ፡
ነገሥት ፡ ስምዓኒ ፡ ጸሎትየ ፡ ወስእለትየ ፡
አ ፡ ዘሰማዕከ ፡ ጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡
ወሐዋርያት፡ጻድቃን ፡ ወሰማዕት ፡ ደናግል ፡
ወመነኰሳት፡ጸሎተ፡ትጉሃን፡መላእክት ። ወበ
ጸሎተ ፡ እግዝእተ ፡ ኵልነ ፡ ማርያም ። ኃጥ
እተ ፡ አምሳል ፡ እምነ ፡ እምሳላት ፡ ወመ
ዳየ ፡ ስእለታት ።
ወሊተኒ ፡ ለኃጥእ ፡ ገብርከ ፡ ኢትትኃየየኒ ፡
በእንተ ፡ አበሳየ ።
ወክሥት ፡ ሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ ጥፍ
ዓተ ፡ ርእሰ ፡ ዝንቱ ፡ ዶርሆ ።
ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ሶበ ፡ ጸለየ ፡ አቡነ ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መጽአ ፡ መልአክ ፡
ኀቤሁ ፡ እምሰማይ ። ወይቤሎ ፡ መልአከ ፡
እግዚአብሔር ፡ ኢትጸሊ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡
ንጉሠ ፡ ዛጌ ።
የአክሎ ፡ ዘወሀብክዎ ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡
መጠነ ፡ ፫፻፴ ፡ ወ፫ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡
ኢይደልዎ ።
ይቤለከ ፡ ዘንተ፡ እግዚአብሔር ፡ኀድግ፡ኢት
ጸሊ ።ወዮምሰ ፡ ባሕቱ ፡ አግባዕኩ ፡ ለከ ፡
መንግሥተ ፡ እግዚኡ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡
ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ወለዘርዑ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።
ወኢግብኦቱ ፡ ሎቱ ፡ አኮ ፡ መንግሥት ፡
ባሕቲቶ ። አላ ፡ ምስለ ፡ ቀርነ ፡ ቅብዕ ፡
ከመ ፡ ሥርዓተ ፡ አበዊሁ ፡ ነገሥታት ፡
ወአስማተ ፡ ዕፍረታትኒ ።
ዘውእቱ ፡ ስሂን ።
ዕንጎታት ፡ ወማየ ፡ ከርካዕ ፡ ኮል ፡ ምስለ ፡
ፍሬ ፡ ወይን ። እሎንታቱ ፡ ገቢረከ ፡ ወአ
ኀቢረከ ፡ ውስተ ፡ ፩ ፡ ጽዋዕ ፡ ደዮ ።
ወአንተኒ ፡ ነሢአከ ፡ ዕጣነ ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡
ሕፍን ፡ ባእ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ወዕጥን ፡ ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግ
አብሔር ፡ መጠነ ፡ ፫ ፡ ሱባዔ ፡ ዕለታተ ።
ሶበኒ ፡ ትወፅእ ፡ እምዝንቱ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፡ ንሣእ ፡ ኅራሬ ፡ ዕጣን ፡ በእዴከ ፡
ወአስተዋሕዶ ፡ ምስለ ፡ ማይ ፡ ወደዮ ፡
ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡ ዕፍረታተ ፡ ወድ
ግም ፡ ቦቱ ፡ እምቃለ ፡ ዳዊት ።
ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ መዝ ፡ ፪
እግዚኦ ፡ ሚበዝኁ ፡ መዝ ፡ ፫ ።
ሶበ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ መዝ ፡ ፬ ።

፲፬ ፤ ንጉሡ ፡ ዘእልመክኑን ፡ ለአባታችን ፡ ለተ
ክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይህን ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ።
፲፭ ፤ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ መንፈሳዊ ፡ አርበኛ ፡ አባ
ታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የንጉሡን ፡
ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ይጸልይ ፡ ጀመር ፡ ወደሰማይ
አቅንቶ ፡ ተመለከተ ።

፲፮ ፤ የአማልክት ፡ ፈጣሪ ፡ የአጋእዝት ፡ ጌታ ፡
የነገሥታት ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልመ
ናዬን ፡ ስማኝ ፡ አለ ። የትጉሃን ፡ መላእ
ክት ፡ የደናግል ፡ የመነኰሳት ። የነቢያት ፡
የሐዋርያትን ፡ ልመና ፡ የምትሰማ ። የል
መና ፡ መገኛ ፡ ምሳሌ ፡ የሌላት ፡ የሁላችን፡
እመቤት ፡ የምትሆን ፡ የእመቤታችንን ፡
ልመና ፡ የሰማህ ።
ኃጥእ ፡ እኔንም ፡ ባሪያህን ፡ ስለኃጢአቴ ፡
ቸል ፡ አትበለኝ ።
የዶሮውንም ፡ ራስ ፡ ጥፋት ፡ ለዚህ ፡ ለን
ጉሥ ፡ ግለጽለት ። አባታችን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡እንዲህ ፡ እያለ ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡
መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ታዞ ፡ መጣ ።
መልአኩም ፡ ለዛጌ ፡ ወገን ፡ ለሚሆን ፡
ለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ አትጸልይለት ።
የማይገባው ፡ ሲሆን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ
ሦስት ፡ ዘመን ፡ የሰጠሁት ፡ ይበቃዋል ።
እግዚአብሔር ፡ አትጸልይ ፡ ብሎሃል ፡
አለው ።
ዛሬስ ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ
የጌታውን ፡ መንግሥት ፡ መልሼለታለሁ ፡
የልጅ ፡ ልጁ ፡ ይገዛል ።
የመለስኩለትም ፡ መንግሥቱን ፡ ብቻ ፡
አይደለም ።
እንዳባቶቹ ፡ እንደነገሥታት ፡ ሥርዓት ፡
ቀርነ ፡ ቅብዕንም ፡ ነው ፡ እንጂ ።
የሽቶዎችም ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።
ሥሂን ፡ ወሚዓ ፡ ቀንሞስ ፡ ወቀናንሞስ ፡
ጽስጥቂስ ፡ ዕንጐታት ፡ ወማየ ፡ ከርካዕ ፡
ኮል ፡ ምስለ ፡ ፍሬ ፡ ወይን ፡ ናቸው ።
እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ባንድ ፡
ጽዋ ፡ ጨምረው ።
አንተም ፡ ሦስት ፡ ዕፍኝ ፡ ያህል ፡ ዕጣን ፡
ይዘህ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተህ ፡ ታቦ
ቱን ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ቀን ፡ ዕጠን ።
ከቤተ ፡ መቅደስም ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ ኅራሪ ፡
ዕጣኑን ፡ በጅህ ፡ ይዘህ ፡ በውኃ ፡ ለውሰህ ፡
ሽቱ ፡ ካለበት ፡ ጽዋ ፡ ጨምረው ።
ከዳዊት ፡ ቃል ፡ ድገምበት ።
ለምንት ፡ አንገለጉን ፡ መዝ ፡ ፪ ።
እግዚኦ ፡ ሚበዙኁን ፡ መዝ ፡ ፫ ።
ሶበ ፡ ጸዋዕክዎን ፡ መዝ ፡ ፬ ።

ይስማዕከ ፡ መዝ ፡ ፲፱ ።
እግዚኦ ፡ በኃይልከ ፡ መዝ ፡ ፳ ።
ግፍዖሙ ፡ መዝ ፡ ፴፬ ።
እግዚኦ ፡ ሰማዕነ ፡ መዝ ፡ ፵፫ ።
ጐሥዓ ፡ መዝ ፡ ፵፬ ።
ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ሣህልከ ፡ መዝ ፡ ፶ ።
ይትነሣእ ፡ መዝ ፡ ፷፯ ።
እግዚኦ ፡ ነጸርከ ፡ መዝ ፡ ፷፱ ።
ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ መዝ ፡ ፸ ።
እግዚኦ ፡ ኰነኔከ ፡ ሀቦ ፡ ለንጉሥ ፡ መዝ ፡ ፸፩ ።
ተሣሃልከ ፡ መዝ ፡ ፹፬ ።
አጽምዕ ፡ እግዚኦ ፡ እዝነከ ፡ መዝ ፡ ፹፭ ።
ምሕረተከ ፡ እሴብሕ ፡ መዝ ፡ ፹፰ ።
እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ ደንገፁ ፡ አሕዛብ፡ መዝ ፡ ፺፰ ።
ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ፡ መዝ ፡ ፻፩።
አሌዕለከ ፡ መዝ ፡ ፻፵፬ ።
ወእምነቢያት፡ጸሎተ፡ሐና ፡ መሐልይ ፡ ፬ ።
ጸሎተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ፲፫ ።
ጸሎተ ፡ ዘካርያስ ፡ መሐ ፡ ፲፬ ።
ወመሐልይ ፡ ፰ ።
ውዳሴ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ምስለ፡ አንቀጸ ፡ ብርሃን ።
ወጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ ፳ወ፩ ፡ እሎንተ ፡ ጸሎታተ ፡ሶበ ፡ ጸለይከ ፡ አንተ ።
ፍጡነ ፡ ይፈልህ ፡ ለከ ፡ ዝንቱ ፡ ቅብዓ ፡ ነገሥታት ፡ አሜሃ ፡ ንሥእ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ወቅብዖ ፡ አንተ ፡ በእዴከ ።
ከመ ፡ ይኩን ፡ ንጉሠ ፡ መልዕልተ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥታት ፡ ወይመልክ ፡ ባሕቲቱ ፡ ኵሎ ፡ ኢትዮጵያ ።
ወለዝንቱስ ፡ ቅብዕ ፡ አኮ ፡ ዘይትቀበልዎ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥታት ፡ እለ ፡ ነግሡ ፡ እምድኅሬሁ ።
እንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጻድቅ። ወዓዲ ፡ ዘይትነሣእ ፡ እምድኅረ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ንጉሥ ።
በመዋዕል ፡ ብዙኅ ፡ ፳፻፡ወ፪፻፡ወ፳፡ወ፪ቱ ፡ ወዓመት ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለ፪ ፡ ነገሥታት ዘይነግሡ ፡ በዝቅብዕ ።
መጠነ ፡ ፺ ፡ ወ፪ቱ ፡ ዓመታት ።
ወለከኒ ፡ የሀብከ ፡ እምነገሥት ፡ ዚአሁ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ፩ደ ፡ እደ ፡ ወይኩን ፡ ለከ ፡ ወልዶ ፡ እመቦ ፡ ዘተሀበለ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግከ ፡ ወመንግሥትከ ፡ ይትዋረስ ፡ መርገመ ።
ወናሁ ፡ ከሠትኩ ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ ኅቡኣቲሁ፡ ለእግዚአብሔር ።

ይስማዕከን ፡ መዝ ፡ ፲፱ ።
እግዚኦ ፡ በኃይልከን ፡ መዝ ፡ ፳ ።
ግፍዖሙን ፡ መዝ ፡ ፴፬ ።
እግዚኦ ፡ ሰማዕነን ፡ መዝ ፡ ፵፫ ።
ጐሥዓን ፡ መዝ ፡ ፵፬ ።
ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ሣህልከን ፡ መዝ ፡ ፶ ።
ይትነሣእን ፡ መዝ ፡ ፷፯ ።
እግዚኦ ፡ ነጸርን ፡ መዝ ፡ ፷፱ ።
ኪያከ ፡ ተወከልኩን ፡ መዝ ፡ ፸ ።
እግዚኦ ፡ ኰነኔከ ፡ ሀቦ ፡ ለንጉሥን ፡ መዝ ፡ ፸፩ ።
ተሣሃልከን ፡ መዝ ፡ ፹፬ ።
አጽምዕ ፡ እግዚኦ ፡ እዝነከን ፡ መዝ፡ ፹፭፡
ምሕረተከ ፡ እሴብሕን ፡ መዝ ፡ ፹፰ ።
እግዚአብሔር ፡ነግሠ ፡ ደንገፁ ፡ አሕዛብን ፡ መዝ ፡ ፺፰ ።
ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየን ፡ መዝ፡፻፩ ።
አሌዕለከን ፡ መዝ ፡ ፻፵፬ ።
ከነቢያት ፡ ጸሎተ ፡ ሐናን ፡ መሐልይ፡፬ ።
ጸሎተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያምን ፡ ፲፫ ።
ጸሎተ ፡ ዘካርያስን ፡ መሐልይ ፡ ፲፬።
መሐልይ ፡ አምስቱን ፡
ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ አንቀጸ ፡ ብርሃን ፡
ጸሎተ፡ ወንጌል ፡ እሊህን ፡ ሃያ ፡ አንዱን፡ ጸሎታት ፡ አንተ ፡ በጸለይክ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቅብዓ ፡ መንግሥት ፡ ፈጥኖ ፡ ይፈላሃል ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ አንተ ፡ በጅህ ፡ ይዘህ ፡ ቅባው ።
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።
ኢትዮጵያን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ።
ይህንም ፡ ቅብዓ ፡ መንግሥት፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚነግሡ ፡ ነገሥታት ፡ የሚቀበሉት አይደለም ።
ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ዳግመኛ ፡ ከዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በኋላ ፡ የሚነሣው ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ከሰባት ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዚህም ፡ ቅብዓ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ የሚነግሡ ፡ የሁለቱ፡ ነገሥታት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ።
አርባ ፡ ሁለት ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ዘመን ፡ ነው ።
ይኩኖ ፡ አምላክም ፡ ከመንግሥቱም፡ሲሶ ። አንድ ፡ እጅ ፡ ይሰጥህ ።
እሱም ፡ ላንተ ፡ ልጅ ፡ ይሁንህ ፡ አለው ።
ይህን ፡ መንግሥትና ፡ ሥርዓትህን ፡ ደፍሮ ያፈረሰ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ መርገመ ፡ ጌባልን ፡ ይወርሳል ።

ወእንተኒ ፡ ኢታትርፎ ፡ ዳዕሙ ፡ ቅብዖ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላከ ።
ወዘንተ ፡ ነገረ ፡ ተናገሮ ፡ አርገ ፡ መልአከ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ።
ወአቡነሂ ፡ ክቡረ ፡ ስም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰሚዖ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ እምአፈ ፡ መልአክ ፡ ቀብዖ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ።
ወፈነዎ ፡ ውስተ ፡ ጸብዕ ፡ ከመ ፡ ይጻባዕ ፡ ምስለ ፡ ዝኩ ፡ ንጉሥ ።
ወሞአ ፡ ወቀተሎ ።
ወነግሠ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸሎቱ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
ርእዩኬ ፡ ኃይሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘይገብር ፡ በጸሎተ ፡ ቅዱሳኒሁ ።
ወሶበ ፡ ነግሠ ፡ ኮነ ፡ ሰላም ፡ ወዛኅን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ።

ክፍል ።

በዝየኒ ፡ ንኄልቍ ፡ ተረፈ ፡ ልደቶሙ ፡ ለእለ ፡ ተኀይደት ፡ መንግሥቶሙ ።
ወዝውእቱ ።
ድልነአድ ፡ ወለዶ ፡ ለማኀበረ ፡ ውድም ።
ወማኀበረ ፡ ውድም ፡ ወለዶ ፡ ለአግብአ ፡ ጽዮን ።
ወአግብአ ፡ ጽዮን ፡ ወለዶ ፡ ለጽንፈ ፡ አርእድ ።
ወጽንፈ ፡ አርእድ ፡ ወለዶ ፡ ለነጋሽ ፡ ዛሬ ።
ወነጋሽ ፡ ዛሬ ፡ ወለዶ ፡ ለአስፋሐ ።
ወአስፋሐ ፡ ወለዶ ፡ ለያዕቆብ ።
ወያዕቆብ ፡ ወለዶ ፡ ለባሕረ ፡ አሰገድ ።
ትውልድ ፡ ፪ወ፲ ።
ወባሕረ ፡ አሰገድ ፡ ወለዶ ፡ ለእድም ፡ አሰገድ ።
ወእድም ፡ አሰገድ ፡ ወለዶ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡
ዘሜጠ ፡ መንግሥተ ፡ እምነ ፡ ዛጔ ፡ ትውልድ ፡ ፻፲ ፡ ወ፪ ፡ እምነ ፡ አዳም ።
ወእምእብነ ፡ ሐኪም ፡ ትውልድ ፡ ፸ወ፲።
ወዘነበሩ ፡ በስደት ፡ እሉ ፡ ትውልድ፡ ፲፡ እንዘ ፡ የአይሉ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወገዳም ፡ ወይትፋለሱ ፡ እምሀገር ፡ ለሀገር ፡ ወይትኃብኡ ፡ ውስተ ፡ በአታት ፡ ወግበበ ፡ ምድር ።

እስከ ፡ መንግሥቱ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ።
ወሶበ ፡ ነግሠ ፡ ኮነ ፡ ሰላም ፡ ወዛኅን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ።
ወከመዝ ፡ ገብረ ፡ ሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በኃይለ ፡ አምላኩ ፡ ኅጡአ ፡ ተስእኖ ።

እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሥጢሩን ፡ ሁሉ ፡ ገልጬ ፡ ነገርኩህ ።
አንተም ፡ የነገርኩህን ፡ ሳታስቀር ፡ ይኩኖ አምላክን ፡ ቅባው ፡ እንጂ ።
ይህን ፡ ከነገረው ፡ በኋላ ፡ መልአኩ ፡ ወደ፡ ሰማይ ፡ አረገ ።
ስሙ ፡ የከበረ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ከመልአኩ ፡ ቃል ፡ ይህን፡ነገር፡ ሰምቶ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ቀብቶ ፡ አነገሠው ።
ንጉሡን ፡ ውጋ ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ።
ድል ፡ አደረገው ፡ ገደለው ፡
በአባታችን ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸሎት፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነገሠ ።
እግዚአብሔር ፡ በወዳጆቹ ፡ አድሮ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ አስተውሉ ።
በነገሠም ፡ ጊዜ ፡ በየሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥታ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ሆነ ።

ክፍል ።

መንግሥት ፡ የሄደችባቸውንም ፡ ሰዎች፡ የልደታቸውን ፡ ቍጥር ፡ በዚህ ፡ እንናገራለን ።
ቍጥራቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ።
ድልነአድም ፡ ማኀበረ ፡ ውድምን ፡ ወለደ። ማኀበረ ፡ ውድምም ፡ አግብአ ፡ ጽዮንን፡ ወለደ ፡ አግብአ ፡ ጽዮንም ፡ ጽንፈ ፡ አርእድን ፡ ወለደ ።
ጽንፈ ፡ አርእድም ፡ ነጋሽ ፡ ዛሬን ፡ ወለደ ።
ነጋሽ ፡ ዛሬም ፡ አስፋሕን ፡ ወለደ ።
አስፋሕም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ።
ያዕቆብም ፡ ባሕረ ፡ አሰገድን ፡ ወለደ ።
መቶ ፡ ዐሥር ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
ባሕረ ፡ አሰገድም ፡ እድም ፡ አሰገድን ፡ ወለደ ።
እድም ፡ አሰገድም ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ወለደ ።
ከዛጔ ፡ ልጆች ፡ መንግሥትን ፡ የመለሰ ።
ከአዳም ፡ ፫ ሞሮ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ትውልድ ።
ከእብነ ፡ ሐኪም ፡ ፳ምሮ ፡ ሰባ ፡ ሰባት ።
በስደት ፡ የኖሩም ፡ እሊህ ፡ የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ዐሥር ፡ ናቸው ፡ ዱር ፡ ለዱር ፡ ሲዞሩ ።
ከሀገር ፡ ወደሀገር ፡ ሲሰደዱ ።
በየዋሻው ፡ በየፍርኩታው ፡ ሲሸሽጉ ።
ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ነገሠ፡ ድረስ ፡ እሱም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ በየሀገሩ ፡ ሁሉ ። ጸጥታ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ሆነ ።
ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሁሉ ፡ በሚቻለው ፡ በፈጣሪው ፡ ኃይል ፡ እንደዚህ ፡ አደረገላቸው ።

አ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ምንተኑ ፡ ዕሤተ፡ ተዓሥይዎ ፡ ወዓይኑ ፡ ፍዳ ፡ ትፈድይዎ ።
ለዘመጠንነዝ ፡ አቡክሙ ፡ ዘአግብአ ፡ ለክሙ ዘንተ ፡ ዐቢየ ፡ ርስተ ፡ ዘውእቱ ፡ መንግሥተ
ወባሕቱ ፡ አጽንዑ ፡ ኪዳኖ ።
ወዕቀቡ ፡ መሐላሁ ፡ ዘተካየደ ፡ ወተመሐለ ፡ ምስለ ፡ አቡክሙ ።
ይኩኖ ፡ አምላክ ።
ወ፪ሆሙ ፡ አጽንዑ ፡ ኪዳነ ፡ ወመሐላ ።
በደብረ ፡ ሊባኖስ ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳፯ ።

፩ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ በ፫ ፡ ፻፴ ፡ ወ፫ ፡ ዓመት ።
፪ ፤ አመ ፡ ፮ ፡ ለሐምሌ ፡ አግብአ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥተ ፡ እምነገደ ፡ ሂጳጳ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስራኤላዊ ።
፫ ፤ ወኮነ ፡ ሰላም ፡ ወዛኅን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ።
፬ ፤ ወእምድኅረ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ አዕረፈት ፡ እሙ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ፡ ለወርኃ ፡ ነሐሴ ።
፭ ፤ ወእምድኅሬሃ ፡ በሐሙስ ፡ መዋዕል ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ ፡ ለውእቱ ፡ ወርኅ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሁ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ።
፮ ፤ በረከተ ፡ ፪ሆሙ ፡ አርጋብ ።
፯ ፤ ወበረከተ ፡ ወልዶሙ ፡ ጠቢብ ፡ በላዕሌነ ፡ ትርብብ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።
፰ ፤ ወበከየ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ በእንተ ዘኮነ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ።
፱ ፤ ወባሕቱ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አጽንዖ ።
፲ ፤ ወኮነ ፡ ከሃሌ ፡ በቃሉ ፡ ወበምግባሩ ።
፲፩ ፤ ወመፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር ።
፲፪ ፤ ወጥቀ ፡ ይፀመድ ፡ ጸሎተ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።
፲፫ ፤ ወይትግህ ፡ ከመ ፡ መላእክት ።
፲፬ ፤ ወይሰግድ ፡ ከመ ፡ መንኰራኵር ።
፲፭ ፤ ወይዜምር ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ በበ፯ ፡ ጊዜ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ።
፲፮ ፤ ወያነብብ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ወሐዋርያት ።
፲፯ ፤ ወእማንቱ ፡ አጽንእሁ ፡ ልቦ ።
፲፰ ፤ ወወሀባሁ ፡ ያፈቅራ ፡ ለጥበብ ።
፲፱ ፡ ወጸንአ ፡ ጥቀ ፡ ለፍካሬሆን ።
፳ ፤ ወዓቀበ ፡ ግብረ ፡ ክህነቱ ፡ በጥንቃቄ ።
፳፩ ፤ ወነበረ ፡ ከመዝ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ በቤተ አቡሁ ፡ ወእሙ ።
፳፪ ፤ ወኮነ ፡ ፈድፋደ ፡ ብዑለ ፡ ጸጋ ።

እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ ትሰጡታላችሁ ።
እንዴት ፡ ያለ ፡ ብድራት ፡ ትከፍሉታላችሁ።
ታላቅ ፡ ርስት ፡ መንግሥታችሁን ፡ ለመለሰላችሁ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አባታችሁ ፡ ምን ፡ ወሮታ ፡ ታደርጉለታላችሁ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ አጽኑ ።
ከአባታችሁ ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጋራ ፡ የተማማለውንም ፡ መሐላ ፡ ጠብቁ ።
ሁለቱም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የተማማሉትን ፡ መሐላ ፡ አጽንተው ፡ ኖሩ ።

ኻያ ፡ ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ሦስት ፡ ዘመን ።
፪ ፤ በሐምሌ ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥትን ፡ ከዛጔ ፡ ወገን ፡ የእስራኤል ወገን ፡ ለሚሆን ፡ ለይኩኖ፡ አምላክ፡ መለሰ።
፫ ፤ በየሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥታ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ሆነ ።
፬ ፤ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እናቱ ፡ እግዚእ፡ ሐረያ ፡ በነሐሴ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ዐረፈች ።
፭ ፤ እሷም ፡ በሞተች ፡ በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ በነሐሴ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ አባቱ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ዐረፈ ።
፮ ፤ የሁለቱ ፡ ሽማግሎች ፡ በረከት ።
፯ ፤ ብልህ ፡ አዋቂ ፡ የሚሆን ፡ የልጃቸውም ፡ በረከት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ትደር ፤
ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።
፰ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ እናት ፡ አባቱ ፡ ስለሞቱበት ፡ አለቀሰ ።
፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አጸናው ።
፲ ፤ በሚናገረው ፡ ነገር ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የሚቻለው ፡ ሆነ ።
፲፩ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚያገለግል ፡ ሆነ ።
፲፪ ፤ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በጸሎት ፡ የተፀመደ ፡ ሆኖ ።
፲፫ ፤ እንደ ፡ መላእክት ፡ ትጉህ ፡ ሆነ ።
፲፬ ፤ እንደ ፡ ሠረገላ ፡ እየተፋጠነ ፡ ይሰግዳል ።
፲፭ ፤ ባንዲት ፡ ቀን ፡ በሰባቱ ፡ ጊዜያት ፡ ሰባት፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ያደርስ ፡ ነበር ።
፲፮ ፤ ብሉያትንም ፡ ሐዲሳትንም ፡ ይደግም ፡ ነበረ ።
፲፯ ፤ እነዚህ ፡ ልቡናውን ፡ አጸኑለት ።
፲፰ ፤ ዕውቀትን ፡ እንዲወድ ፡ አደረጉት ።
፲፱ ፤ ትርጓሜያቸውንም ፡ ፈጽሞ ፡ ተረዳ ።
፳ ፤ የክህነቱንም ፡ ሥራ ፡ ጠንቅቆ ፡ ጠበቀ ።
፳፩ ፤ በናት ፡ ባባቱ ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ዓመት እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ ተቀመጠ ።
፳፪ ፤ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ሆነ ።

፷፫ ፤ ወበ፩ ፡ እመዋዕል ፡ ወፅአ ፡ ገዳመ ፡ ከመ ፡ ይንአው ፡ ኃየላተ ፡ ምስለ ፡ ብዙኀ ፡ ሰብእ ።
፷፬ ፤ ወተፈልጠ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ያስተሐይድ ።
፷፭ ፤ ወከዊኖ ፡ ቀትረ ፡ መዓልት ፡ አስተርአዮ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ በአልባሰ ፡ ግርማ ።
፷፮ ፤ ወሶበ ፡ ነጸሮ ፡ ቅዱስ ፡ ወድቀ ፡ በገጹ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ በድን ።
፷፯ ፤ ወአንሥኦ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወአተበ ፡ ላዕሌሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ።
፷፰ ፤ ወአዕተተ ፡ ፍርሃተ ፡ እምላዕሌሁ ።
፷፱ ፤ ወርእዮ ፡ ገፃዶ ፡ ለመልአክ ።
፸ ፤ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚእየ ፡ ዘአሬእየከ ፡ በዘመጠነዝ ፡ ዕበይ ።
፸፩ ፤ ወይቤሎ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ሚካኤል ፡ መልአከ ፡ ኃይሉ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፸፪ ፤ ዘዘልፈ ፡ አዓቅበከ ፡ ወኢይትፈለጥ ፡ እምኔከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።
፸፫ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘአውፃእክዎ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እምከርሠ ፡ ማይ ፡ በእንቲአከ ።
፸፬ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘሜጥክዋ ፡ እምጼዋዌ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ በእንቲአከ ።
፸፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ለምንት ፡ ኮንከ ፡ ነዓዌ ፡ አራዊት ።
፸፮ ፤ እስመዝ ፡ ግብር ፡ ኢይደሉ ፡ ለካህናት ፡ ዘእንበለ ፡ ለአሕዛብ ።
፸፯ ፤ ለካህናትሰ ፡ ግብሮሙ ፡ ምሕሮ ፡ ሃይማኖት ፡ ወገሥጾ ፡ ሕዝብ ።
፸፰ ፤ እምይእዜሰ ፡ ኢትኩን ፡ ነዓዌ ፡ አራዊት ።
፸፱ ፤ ወኢመስተጽእነ ፡ ፈረስ ።
፹ ፤ አላ ፡ ኩን ፡ ነዓዌ ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብእ ፡ ለመንግለ ፡ እግዚአብሔር ።
፹፩ ፤ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ መክፈልተ ፡ ለቤቱ ።
፹፪ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ጸገወከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓቢየ ፡ ሥልጣነ ።
፹፫ ፤ ታንሥእ ፡ ሙታነ ፡ ወትፌውስ ፡ ዱያነ ።
፹፬ ፤ ወትስድድ ፡ መናፍስተ ፡ ርኩሳነ ፡ እምሀገር ፡ ወእምገዳም ።
፹፭ ፤ ወትመውእ ፡ ለሰይጣን ።
፹፮ ፤ ወኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ይነፍጹ ፡ እምግርማከ ።
፹፯ ፤ ወኢይኩን ፡ ስምከ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።
፹፰ ፤ አላ ፡ ይኩን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፹፱ ፤ ዘበትርጓሜሁ ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሂል ።
፺ ፤ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ ይትናገሮ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አስተርአዮ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነቢሮ ፡ መልዕልተ ፡ አክናፊሁ ፡

፷፫ ፤ ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ቀን ፡ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ዋሊያ ፡ ሊያድን ፡ ወደዱር ፡ ሄደ ።
፷፬ ፤ ሲመለከት ፡ ከነሱ ፡ ተለይቶ ፡ ሄደ ።
፷፭ ፤ ቀትር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ታየው ።
፷፮ ፤ ክቡር ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮንም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ደንግጾ ፡ እንደ ፡ በድን ፡ ሆነ ።
፷፯ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ አማትቦ ፡ አሥነሣው ።
፷፰ ፤ ፍርሃቱን ፡ አራቀለት ።
፷፱ ፤ መልአኩን ፡ ተገልጾለት ፡ አየው ።
፸ ፤ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግናንነት ፡ የማይህ ፡ ጌታዬ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አለው ።
፸፩ ፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ እኔ ፡ ሚካኤል ፡ ነኝ ፡ አለው ።
፸፪ ፤ ዘወትር ፡ የምጠብቅህ ፡ ካንተ ፡ የማልለይ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፸፫ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ ስላንተ ፡ ከውኀ ፡ ውስጥ ፡ ያወጣሁት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፸፬ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያንም ፡ ስላንተ ፡ ከተማረከችበት ፡ የመለስኋት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፸፭ ፤ አውሬ ፡ አዳኝ ፡ ለምን ፡ ትሆናለህ ።
፸፮ ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከሃይማኖት ፡ በአፍአ ፡ ላሉ ፡ ለአሕዛብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለካህናት ፡ አይገባምና ።
፸፯ ፤ ለካህናትስ ፡ ሥራቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ማስተማር ፡ ሕዝቡን ፡ መምከር ፡ ነው ።
፸፰ ፤ እንግዲህስ ፡ አውሬ ፡ አዳኝ ፡ አትሁን ።
፸፱ ፤ ፈረሰኛም ፡ አትሁን ።
፹ ፤ ሰውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመመለስ ፡ ሰውን ፡ በትምህርት ፡ የምታድን ፡ ሁን ፡ እንጂ ።
፹፩ ፤ ለቤቱ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ለማያት ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ።
፹፪ ፤ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽኑዕ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶሀልና ።
፹፫ ፤ ሙት ፡ ታሥነሣ ፡ ዘንድ ፡ ድውይ ፡ ትፈውስ ፡ ዘንድ ።
፹፬ ፤ ርኩሳን ፡ አጋንንትን ፡ ከሀገርም ፡ ከምድረ በዳም ፡ ታርቃቸው ፡ ዘንድ ።
፹፭ ፤ ዲያብሎስንም ፡ ድል ፡ ትነሣዋለህ ።
፹፮ ፤ ሠራዊቱ ፡ አጋንንትም ፡ አንተን ፡ በመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ይሸሻሉ ።
፹፯ ፤ ስምህም ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ አይሁን ።
፹፰ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።
፹፱ ፤ ትርጓሜውም ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡
፺ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ይህን ፡ ሲነጋገረው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሚካኤል ፡

በአምሳለ ፡ ወሬዛ ፡ ዘሠናይ ፡ ርእየቶ ፡ ገጹ ።

፶፩ በከመ ፡ ኮነ ፡ በሥጋ ፡ ምስለ ፡ አርዳኢሁ ፡

፶፪ ፤ ወርእዮ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አን
ክረ ፡ ፈድፋደ ።

፶፫ ፤ እስመ ፡ እምቅድመ ፡ አሜሃ ፡ ኢርእዮ ፡
ለመልአክ ፡ ወኢነጸሮ ፡ ለአምላክ ፡ ገሃደ።

፶፬ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ ሰላም ፡ ለከ አ ፡
ፍቁርየ ።

፶፭ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚእየ ።

፶፮ ፤ ወይቤሎ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ መድ
ኅነ ፡ ዓለም ።

፶፯ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘፈጠርኩከ ፡ እምከርሠ ፡
እምከ ፡ ዘቀደስኩከ ።

፶፰ ፤ ወመክፈልተ ፡ ዚአየ ፡ ዘረሰይኩከ ።

፶፱ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘወደይኩ ፡ መንፈስ ፡ ስብ
ሐት ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ ከመ ፡ ትቀድስኒ ፡
በ፫ ፡ ቅዳሴያት ፡ እምአመ ፡ ተወለድከ ፡
በሣልስት ፡ ዕለት ።

፷ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘወደይኩ ፡ መንፈስ ፡ በረ
ከት ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ከመ ፡ ይምላእ ፡
በቤተ ፡ አቡከ ፡ ወእምከ ፡ ሐሪጽ ፡ ሥርናይ ፡
ወቅብዕ ፡ ወኵሎ ፡ መፍቅዳተ ፡ ቤት ፡ አመ
መዋዕለ ፡ ረኅብ ።

፷፩ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘሰቀልክዎ ፡ ለብእሲ ፡ መል
ዕልተ ፡ ነፋሳት ፡ ወቀሠፍክዎ ፡ በመዓትየ ፡
ሶበ ፡ አኀሠመ ፡ ላዕሌከ ።

፷፪ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘአንቃዕኩ ፡ ለከ ፡ ማየ ፡
ጥዑመ ፡ እምድር ፡ ይቡስ ፡ ሶበ ፡ ጸማዕከ ፡
ወሰአልከኒ ።

፷፫ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘፈወስክዎሙ ፡ ለድውያን ፡
በእደዊከ ፡ ዘእገብር ፡ ለከ ፡ ኃይላተ ፡ ብዙ
ኃተ ፡ እምንእስከ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።

፷፬ ፤ ወእገብርሂ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወዘንተ ፡
ብሂሎ ፡ ባረኮ ፡ በእደዊሁ ፡ ቅዱሳት ።

፷፭ ፡ ወነፍሐ ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ንሣእ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፷፮ ፤ ዘአሰርከ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ እሱረ ፡
በሰማያት ።

፷፯ ፤ ወዘፈታሕከ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ ፍቱሐ ፡
በሰማያት ።

፷፰ ፤ ዘኪያከ ፡ ሰምዐ ፡ ኪያየ ፡ ሰምዐ ።

፷፱ ፤ ወሰምዓ ፡ ለዘፈነወኒ ።

፸ ፤ ዘለከ ፡ አበየ ፡ ሊተ ፡ አበየ ።

ክንፍ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡
ጐልማሳ ፡ መስሎ ፡ ታየው ።

፶፩ ፤ በሥጋ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ እንደ
ነበረ ፡ ሁኖ ።

፶፪ ፤ ክቡር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ አይቶት ፡
ፈጽሞ ፡ አደነቀ ።

፶፫ ፤ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ መልአኩንም ፡ ጌታ
ንም ፡ ተገልጸው ፡ አላያቸውምና ።

፶፬ ፤ ጌታችንም ፡ ወዳጄ ፡ እንዴት ፡ ሰነበትክ ፡
ቸር ፡ አለህን ፡ አለው ።

፶፭ ፤ ክቡር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ጌታዬ ፡
ሆይ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አለው ፤

፶፮ ፤ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ የምሆን ፡ እኔ
ኢየሱስ ፡ ነኝ ፡ አለው ።

፶፯ ፤ በናትህ ፡ ማኅፀን ፡ ሳለህ ፡ ፈጥሬ ፡ ያከበ
ርኩህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

፶፰ ፤ የኔ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ያደረግሁህ ፡ እኔ ፡
ነኝ ።

፶፱ ፤ በተወለድክ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ፩ ፡ አብ
ቅዱስ ፡ ፩ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለህ ፡ ታመሰግነኝ ፡
ዘንድ ፡ የምስጋና ፡ ሀብት ፡ ያሳደርኩብህ ፡
እኔ ፡ ነኝ ።

፷ ፤ በረኀብ ፡ ዘመን ፡ በቤት ፡ የሚያሻው ፡
ምግብ ፡ ሁሉ ፡ ቅቤውም ፡ የሥንዴውም ፡
ዱቄት ፡ በናት ፡ ባባትህ ፡ ቤት ፡ ይመላ ፡
ዘንድ ፡ በእጅህ ፡ ሀብተ ፡ በረከት ፡ ያሳደ
ርኩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

፷፩ ፤ ያንን ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ በተጣላህ ፡ ጊዜ ፡
በነፋስ ፡ አውታር ፡ የሰቀልሁት ፡ በመዓት
ጨንገር ፡ የገረፍኩት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

፷፪ ፤ ውኃ ፡ ጠምቶህ ፡ በለመንከኝ ፡ ጊዜ ፡ ከደ
ረቅ ፡ መሬት ፡ የጣፈጠ ፡ ውኃ ፡ ያመነጨ
ሁልህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

፷፫ ፤ ከልጅነትህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ
ብዙ ፡ ተአምራት ፡ እያደረግኩ ፡ ባንተ ፡
እጅ ፡ የታመሙትን ፡ ያዳንኋቸው ፡ እኔ ፡
ነኝ ።

፷፬ ፤ ወደፊትም ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ይህን ፡ ብሎ
ንጹሐት ፡ ክቡራት ፡ በሚሆኑ ፡ እጆቹ ፡
ባረከው ።

፷፭ ፤ ንሣእ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ የሹመት ፡
ሀብት ፡ አሳደረበት ።

፷፮ ፤ በምድር ፡ ያሰርከው ፡ በሰማይ ፡ የታሰረ ፡
ይሁን ።

፷፯ ፤ በምድርም ፡ የፈታኸው ፡ በሰማይ ፡ የተ
ፈታ ፡ ይሁን ።

፷፰ ፤ አንተን ፡ የሰማ ፡ እኔን ፡ መስማቱ ፡ ነው ።

፷፱ ፤ የላከኝ ፡ አባቴንም ፡ መስማቱ ፡ ነው ።

፸ ፤ አንተን ፡ እምቢ ፡ ያለ ፡ እኔን ፡ እምቢ ፡
ማለቱ ፡ ነው ።

፷፩ ፤ አበዮ ፡ ለዘፈነወኒ ። ወዘንተ ፡ ሥልጣንየ፡ ወሀብኩ ፡ ቅድመ ፡ ለሐዋርያት ።

፷፪ ፤ ወእምሐዋርያት ፡ ዘተወፈየ ፡ ጳጳስ ፡ ሤመከ ፡ ቅድመ ፡ ወወሀበከ ፡ መባሕተ ።

፷፫ ፤ ትእስር ፡ ወትፍታሕ ፡ ትትክል ፡ ወትምላሕ ።

፷፬ ፤ ወዘንተ ፡ ዘገበርኩ ፡ ለከ ፡ አኮ ፡ በመንኖ፡ ቃሉ ፡ ለጳጳስ ።

፷፭ ፤ አላ ፡ ከመ ፡ አርኢ ፡ ፍቅረ ፡ ዚአየ ፡ በላዕሌከ ።

፷፮ ፤ ናሁ ፡ ሰመይኩከ ፡ ስመ ፡ ሐዲስ ፡ በአፉሁ።

፷፯ ፤ ከመ ፡ እፈኑከ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ ኀበ ፡ ኢበጽሑ ፡ ሐዋርያትየ ፡ ቅዱሳን ።

፷፰ ፤ አንተኒ ፡ ኢትቀሐጽጽ ፡ እምኔሆሙ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ።

፷፱ ፤ እስመ ፡ ረሰይኩከ ፡ ሐዲስ ፡ ሐዋርያ ።

፸ ፤ ትጸውዕ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ መንግሌየ ።

፸፩ ፤ ወሚካኤል ፡ መልአኪየ ፡ ይኩንከ ፡ ረዳኤ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘሀለይከ ።

፸፪ ፤ ወኢይትፈለጥ፡እምኔከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

፸፫ ፤ ወውእቱ ፡ ይምራሕከ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ፍኖት ፡ ዘተሐውር ፡ ባቲ ።

፸፬ ፤ ወአንሂ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌከ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትከ ።

፸፭ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ወሀቦ ፡ ሰላመ ፡ ወዓርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ነቢሮ ፡ መልዕልተ አክናፊሁ ፡ ለሚካኤል ፡

፸፮ ፤ እንዘ ፡ ይኔጽሮ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ተሰወረ ፡ እምአዕይንቲሁ።

፸፯ ፤ ወቅዱስሰ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰገደ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወባረኮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፸፰ ፤ ወይቤ ፡ ይትባረክ ፡ ስምከ ፡ እግዚኦ ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ፡ ዘወሀብከኒ ፡ ዘንተ ኵሎ ፡ ጸጋ ፡ ዘኢድልወትየ ፡ ለኃጥእ ።

፸፱ ፤ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ተመልአ ፡ መንፈሰ ፡ ኃይል ።

፹ ፤ ወያበርህ ፡ ገጾ ፡ በሱራሄ ፡ መለኮት ፡ ዘተናገሮ ።

፹፩ ፤ ወእምዝ ፡ ተራከቦ ፡ ምስለ ፡ ሰብኡ ።

፹፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ኢመልኡ ፡ ንሑር ፡ ውስተ፡ አብያቲኒ ፡ እስመ ፡ መስየነ ፡ ብሔር ።

፹፫ ፡ ወሶበ ፡ ነጸርዎ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ ፡ ደንገፁ ፡ ጥቀ ፡ እምብርሃነ ፡ ገጹ ።

፹፬ ፤ ወኢክህሉ ፡ ርእየቶ ፡ ገሃደ ።

፹፭ ፤ ወውእቱሰ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ወይትሐሠይ ፡ በመንፈሱ ፡ በእንተ ፡ ዘረከበ ፡ ጸጋ ፡ አምላክ ።

፹፮ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ለወራዙት ፡ ንእቱ ፡ ውስተ ፡ አብያቲነ ።

፷፩ ፤ የላከኝ ፡ አባቴንም ፡ እንቢ ፡ ማለቱ ፡ ነው። ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ቀድሞ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰጥቻቸው ፡ ነበር ።

፷፪ ፤ ከሐዋርያትም ፡ የተቀበለ ፡ ጳጳሱ ፡ ቀድሞ ፡ ሹሞ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠህ ።

፷፫ ፤ ታስር ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ ትተክል ፡ ትነቅል ፡ ዘንድ ።

፷፬ ፤ ይህንም ፡ ያደረኩልህ ፡ የጳጳሱን ፡ ቃል ፡ በመናቅ ፡ አይደለም ።

፷፭ ፤ ባንተ ፡ የፍቅሬን ፡ ጽናት ፡ እገልጽ ፡ ዘንድ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፷፮ ፤ በሚካኤል ፡ ቃል ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ አወጣሁልህ ።

፷፯ ፤ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ አልደረሱበት ፡ ሕዝብ ፡ በመምህርነት ፡ እልክህ ፡ ዘንድ ።

፷፰ ፤ አንተም ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ከነሱ፡ አታንስም ።

፷፱ ፤ ሐዲስ ፡ ሐዋርያ ፡ አድርጌሃለሁና ።

፸ ፤ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ እያስተማርክ ፡ ታሳምን ፡ ዘንድ ።

፸፩ ፤ ሚካኤልም ፡ ባሰብከው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ረዳት ፡ ይሁንህ ።

፸፪ ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ካንተ ፡ አይለይ ።

፸፫ ፤ በምትሄድበት ፡ ጐዳና ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ መሪ ይሁንህ ።

፸፬ ፤ እኔም ፡ ባለ ፡ ዘመንህ ፡ አልለይህም ።

፸፭ ፤ ይህን ፡ ብሎ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥቶት ፡ በሚካኤል ፡ ክንፍ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ።

፸፮ ፤ ካይኖቹ ፡ እስኪርቅ ፡ ድረስ ፡ ክቡር ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እያየው ።

፸፯ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ።

፸፰ ፤ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ለኔ ፡ ለኃጥኡ ፡ የማይገባኝ ፡ ስሆን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ የሰጠኸኝ ፡ ስምህ ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡ የተመሰገነ ፡ ይሁን ።

፸፱ ፤ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሀብተ ፡ ኃይልን፡ የተመላ ፡ ሆነ ።

፹ ፤ በተናገረው ፡ በመለኮት ፡ ብርሃን ፡ ነጸብራቅ ፡ ፊቱ ፡ ብሩህ ፡ ሆነ ።

፹፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ።

፹፪ ፤ ጊዜው ፡ መሽቷልና ፡ ወደቤታችን ፡ እንግባ ፡ አላቸው ።

፹፫ ፡ እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ደነገፁ ።

፹፬ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ለማየት ፡ አልተቻላቸውም ።

፹፭ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ፈጣሪው ፡ የሰጠውን ፡ ሀብት ፡ ስላገኘ ፡ በልቡናው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

፹፮ ፤ ዳግመኛም ፡ ጓደኞቹን ፡ ወደቤታችን ፡ እንግባ ፡ አላቸው ።

፺፯ ፤ ወይቤልዎ ፡ እንዘ ፡ ይርእዱ ፡ እምኔሁ ፡ አርዌ ፡ ነአቱ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘነዓውነ ፡ እምእንስሳ ፡ ገዳም ።
፺፰ ፤ ወይቤሎሙ፡ቅዱስ ፡ ንዑኬ ፡ ንእቱ ፡ እም ይእዜሰ ፡ ኦልብነ ፡ መክፈልት ፡ ውስተ ፡ ንዒወ ፡ እንስሳ ፡ ገዳም ።
፺፱ ፤ ወባሕቱ ፡ ተደለውነ ፡ ውስተ ፡ ንዒወ ፡ እንስሳ ፡ ዘአብያት ።
፻ ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ አባግዕ ፡ ግዱፋን ፡ ከመ ኢይብልዕዎሙ ፡ አራዊት ፡ መሰጥ ።
፻፩ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ ፡ ቃለ ፡ ነገሩ ፡ መሰሎሙ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ንነሥእ፡ አባግዓ ፡ እምዓጸደ ፡ ወፍር ፡ ዘሀገር ።
፻፪ ፤ ወእያእመሩ ፡ ከመ ፡ ይቤሎሙ ፡ በእንተ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብእ ።
፻፫ ፤ ወኢነገሮሙ ፡ ከመ ፡ አስተርአዮ ፡ እግ ዚእነ ።
፻፬ ፤ ወሶቤሃ ፡ አተው ፡ ውስተ ፡ ማኅደሪሆሙ፡ ወቅዱስኒ ፡ አተወ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።
፻፭ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ያንከሩ ፡ ወእንዘ ፡ ይትብ ሃሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ርኢክሙኑ ፡ ብር ሃነ ፡ ገጹ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ።
፻፮ ፤ እም ፡ አመ ፡ ተፈልጠ ፡ እምኔነ ፡ ጊዜ ፡ ሠልስቱ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ።
፻፯ ፤ ሶበሂ ፡ መጽአ ፡ ኀቤነ ፡ ስዕነ ፡ ነጽሮት ፡ እምብዙኀ ፡ ብርሃን ፡ ዘውስተ ፡ ገጹ ።
፻፰ ፤ እንዳኢ ፡ ኢነአምር ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሁ ።
፻፱ ፤ ወነገረኒ ፡ ዘተናገረነ ፡ ዘኢልማድ ፡ ሎቱ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እምይዜሰ ፡ አልብነ ፡ መክፈልት ፡ ውስተ ፡ ንዒወ ፡ እንስሳ ፡ ዘገዳም ።
፻፲ ፤ አቡነሰ ፡ **ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ቤተ፡ ኩላ ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ይትፌሣህ ፡ ወይት ሐሠይ ፡ **በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ዘንደረ ፡ ላዕ ሌሁ ።
፻፲፩ ፤ ወይቤሉ ፡ እምይእዜሰ ፡ ይረትዕ ፡ ከመ ፡ ንበሎ ፡ አቡነ ።
፻፲፪ ፤ እስመ ፡ ተሰይመ ፡ ላዕሌነ ፡ እምአፈ ፡ ጳጳስ ፡ ቅድመ ፡ ወእምአፈ ፡ አምላክ ፡ ዳግመ ።
፻፲፫ ፤ ወጸቢሖ ፡ አስተጋብአ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ዘውስተ ፡ ቤት ፡ ወዘውስተ ፡ ገዳም ።
፻፲፬ ፤ ወአኅዘ ፡ ይዝሩ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን፡ ለዕቤራት ፡ ወለዕጓለ ፡ ማውታ ።
፻፲፭ ፤ ወዘይትፈቀድ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሀበ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።
፻፲፮ ፤ ከመዝ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡ ይዘሩ ፡ ንዋየ ፡ ሰሙነ ፡ መዋዕለ ።
፻፲፯ ፤ ወኢያትረፈ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋይ ፡ ዘአ ጥረይዎ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ወዘአጥረየ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ እስከኔሁ ።

፺፯ ፤ እነሱም ፡ እየፈሩ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ከዱር አውሬ ፡ ያገኘነው ፡ ሳይኖር ፡ እንደምን፡ እንገባለን ፡ አሉት ።
፺፰ ፤ እሱም ፡ እንግዲህስ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ማደን ፡ ክፍላችን ፡ አይደለም ፡ ኑ ፡ ወደቤ ታችን ፡ እንግባ ፡ አላቸው ።
፺፱ ፤ በቤት ፡ ያሉ ፡ እንስሳትን ፡ ለማደን ፡ ተዘ ጋጅተናል ፡ እንጂ ።
፻ ፤ እሊህም ፡ ጠባቂ ፡ አጥተው ፡ የጠፉ ፡ አባ ግዕ ፡ ናቸው ፡ የሚነጣጠቁ ፡ አራዊት ፡ እን ዳይበሏቸው ።
፻፩ ፤ እሊህም ፡ ሰዎች ፡ ነገሩን ፡ ሰምተው ፡ በሀ ገር ፡ ያሉ ፡ የተሰማሩትን ፡ አባግዕ ፡ እን ወስዳለን ፡ ያለ ፡ መሰሏቸው ።
፻፪ ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ስለሰዎቹ ፡ እንደሆነ ፡ ዐላወቁም ።
፻፫ ፤ ጌታችን ፡ እንደታየው ፡ እንደተነጋገረው ፡ አልነገራቸውምና ።
፻፬ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው፡ ገቡ ፡ እሱም ፡ ወደቤቱ ፡ ገባ ።
፻፭ ፤ ይህን ፡ ሰው ፡ የፊቱን ፡ ብርሃን ፡ አያች ሁን ፡ እየተባባሉ ፡ ያደንቁ ፡ ነበር ።
፻፮ ፤ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ከኛ ፡ ከተለየ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ አላየነውም ።
፻፯ ፤ ወደኛ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ ብርሃን ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ማየት ፡ ተሳነን ።
፻፰ ፤ በሱ ፡ ላይ ፡ የሆነውን ፡ እንጃ ፡ አናውቅም።
፻፱ ፤ እንግዲህስ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ማደን ፡ ክፍ ላችን ፡ አይደለም ፡ እያለ ፡ የተናገረንም ፡ ነገር ፡ ያለወትሮው ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያደ ንቁ ፡ ነበረ ።
፻፲ ፤ **አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ግን ፡ ባደ ረበት ፡ **በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ሌሊቱን፡ ሁሉ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ አደረ ።
፻፲፩ ፤ እንግዲህስ ፡ አባታችን ፡ ልንለው ፡ ይገ ባናል ፡ አሉ ።
፻፲፪ ፤ መጀመሪያ ፡ በጳጳስ ፡ ቃል ፡ ሁለተኛም ፡ በአምላክ ፡ ቃል ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተሾሟልና፡ አሉ ።
፻፲፫ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ በቤት ፡ በዱርም ፡ ያለ ገንዘቡን ፡ ሰብስቦ ።
፻፲፬ ፤ ለድኃ ፡ ልጅ ፡ ረጅ ፡ እናት ፡ አባት ፡ ለሌ ላቸው ፡ ይመጸውት ፡ ጀመር ።
፻፲፭ ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያሻውንም ፡ ለቤተ ክርስቲያን ፡ ሰጠ ።
፻፲፮ ፤ ገንዘቡን ፡ እንዲህ ፡ እየመጸወተ ፡ ስምንት ቀን ፡ ተቀመጠ ።
፻፲፯ ፤ እናት ፡ አባቱ ፡ ካቆዩት ፡ ገንዘብ ፡ እሱም፡ እስከዚያ ፡ ያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ምንም፡ አላስቀረ ።

፻፲፰ ፤ ወርእዮሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወኵሎሙ ፡
አዝማዲሁ ፡ ከመ ፡ ይዘሩ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡
ተጋብኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤልዎ ፡ ለምንት፡
ታጠፍእ ፡ ዘንተ ፡ ንዋየ ፡ በ፩ ፡ ጊዜ ።
፻፲፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
አኮ ፡ ዘአጠፍእ ፡ አላ ፡ አበዝኆ ፡ ከመ ፡
ይኩን ፡ ሊተ ፡ ትዕሥርተ ።
፻፳ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ተአምሩኑ ፡ ስምየ ።
፻፳፩ ፤ ወይቤልዎ ፡ እወ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ኮነ ፡
ስምከ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።**
፻፳፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አንሰ ፡ ሐዲስ ፡ ስመ ፡ ተሠ
የምኩ ፡ እመልአከ ፡ ሰማይ ።
፻፳፫ ፤ ወይቤለኒ ፡ ኢይኩን ፡ ስምከ ፡ **ፍሥሐ ፡
ጽዮን ፡** አላ ፡ ይኩን ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**
፻፳፬ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ ፡ ቃሎ ፡
ሐዋዘ ፡ ይቤልዎ ፡ ጥቀ ፡ አዳም ፡ ወጥቀ ፡
ሠናይ ፡ ዝንቱ ፡ ስም ።
፻፳፭ ፤ እምኢሜሃ ፡ ጸውዕዎ ፡ በዝ ፡ ስም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡** ወአኃዘ ፡ ይትሉ ፡ ፍኖተ ፡ ሐዋር
ያት ፡ ንጹሐን ።
፪ ፤ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መልእክተ ፡ **መንፈስ ፡
ቅዱስ ።**
፫ ፤ ወዓርገ ፡ **መስቀል ፡** ከመ ፡ ወልድ ፡ ለተ
ቀንዎ ።
፬ ፤ ወለተ.ቃትሎ ፡ ኵሎ ፡ እሚረ ፡ በእንተ ፡
ስመ ፡ **ክርስቶስ ።**
፭ ፤ ወኢያተከዞ ፡ ፍቅረ ፡ ዘመድ ፡ ወፍቅረ ፡
አርክ ፡ ወንዋይ ።
፮ ፤ ወወፅአ ፡ ፍጡነ ፡ ለሰቢከ ፡ ወንጌል ፡
ወኀደገ ፡ ቤቶ ፡ ርኅወ ፡ ወፀጸወ ፡ ኖኀቶ።
፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ **ኦ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡** ናሁ ፡ ኀደጉ ፡ ቤትየ ፡ ርኅወ ፡
ከመ ፡ ታርኁ ፡ ሊተ ፡ አብያተ ፡ መንግሥ
ሥትከ ፡ ዘበሰማያት ።
፰ ፤ ኦእግዚእየ ፡ እምይእዜሰ ፡ አልብየ ፡ ረዳኢ
ለምንዱብ ፡ ዘእንበሌከ ።
ወአልብየ ፡ መጽንኢ ፡ ለድኩም ፡ ዘእን
በሌከ ።
፱ ፤ አልብየ ፡ ሰዋቂ ፡ ለትንቱን ፡ ዘእንበሌከ ።
፲ ፤ ወአልብየ ፡ መንሥኢ ፡ ለወዱቅ ፡ ዘእን
በሌከ ፡ አልብየ ፡ ናዛዚ ፡ ለኅዙን ፡ ዘእን
በሌከ ።
፲፩ ፤ ወአልብየ ፡ ጸወን ፡ ለምስኪን ፡ ዘእንበሌከ።
፲፪ ፤ ዘንተ ፡ ወዘይመስሎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ወፅአ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**

፻፲፰ ፤ ያገሩም ፡ ሰዎች ፡ ዘመዶቹም ፡ ገንዘቡን ፡
ሲበትን ፡ አይተው ፡ ተሰብስበው ፡ መጥ
ተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ባንድ ፡
ጊዜ ፡ ለምን ፡ ታጠፋለህ ፡ አሉት ።
፻፲፱ ፤ **አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡** የሚ
ጠፋ ፡ አይደለም ፡ ዐሥር ፡ እጅ ፡ ይሆን
ልኝ ፡ ዘንድ ፡ አበዛለሁ ፡ እንጂ ።
፻፳ ፤ ዳግመኛም ፡ ስሜን ፡ ታውቃላችሁ ፡ አላ
ቸው ።
፻፳፩ ፤ ስምህ ፡ **ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡** መሆኑን ፡ እና
ውቃለን ፡ አሉት ።
፻፳፪ ፤ እኔስ ፡ ከመልአክ ፡ ሐዲስ ፡ ስም ፡ አውጥ
ቻለሁ ።
፻፳፫ ፤ ስምህ ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ይሁን ፡ እንጂ ፡
ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ አይሁን ፡ አለኝ ፡ አላ
ቸው ።
፻፳፬ ፤ እሊህም ፡ ሰዎች ፡ ነገሩን ፡ በሰሙት ፡ ጊዜ
ይህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡
ነው ፡ አሉ ።
፻፳፭ ፤ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
እየተባለ ፡ ሲጠራ ፡ ኖረ ።

ምዕራፍ ፡ ኻያ ፡ ስምንተኛ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ **አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡** ተነሥቶ ፡ የሐዋርያትን ፡ ሥራ ፡
ይከታተል ፡ ጀመረ ።
፪ ፤ ይኸውም ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ ነው ።
፫ ፤ እንደ ፡ ጌታ ፡ ለመቾንከር ፡ ወደ ፡ **መስቀል ፡**
ለመውጣት ።
፬ ፤ **በክርስቶስ ፡** ስም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሰማዕ
ትነት ፡ ለመሞት ።
፭ ፤ የወዳጅና ፡ የዘመድ ፡ ፍቅር ፡ የገንዘብም ፡
ፍቅር ፡ አላሳዘነውም ።
፮ ፤ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡ ትቶ ፡ ወንጌልን ፡
ለማስተማር ፡ ፈጥኖ ፡ ወጣ ።
፯ ፤ አቤቱ ፡ **ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** የመ
ንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በር ፡ ትከፍትልኝ ፡
ዘንድ ፡ እነሆ ፡ ቤቴን ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡
ተውኩልህ ፡ እያለ ።
፰ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህስ ፡ ለችግረኛው ፡
ለኔ ፡ ያላንተ ፡ ረዳት ፡ የለኝም ።
ለደካማው ፡ ለኔ ፡ ያላንተ ፡ የሚያጸናኝ ፡
የለኝም ።
፱ ፤ ለምፍገመገም ፡ ለኔ ፡ ያላንተ ፡ ደጋፊ ፡ የለ
ኝም ።
፲ ፤ ለወደቅኩ ፡ ለኔ ፡ ያላንተ ፡ የሚያሥነሣኝ ፡
የለኝም ። ላዘንኩ ፡ ለኔ ፡ ያላንተ ፡ የሚያ
ረጋጋኝ ፡ የለኝም ።
፲፩ ፡ ለድኃው ፡ ለኔ ፡ ያላንተ ፡ መጸጊያ ፡ የለኝም።
፲፪ ፤ ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡
አባታችን፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከቤቱ ፡
ወጥቶ ፡ ሄደ ።

፲፫ ፤ ከመ ፡ ገባሬዊ ፡ ኃያል ፡ ወከመ ፡ ሐራዊ ፡ መስተቃትል ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይቀድሞ ፡ ወኢዘይተልዎ ።

፲፬ ፤ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ምንተ ፡ ይበቍዖ ፡ ለሰብእ ፡ ለእመ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ረብሐ ፡ ወነፍሶ ፡ ሐጕለ ።

፲፭ ፡ ወምንተ ፡ እምኢወሀበ ፡ ሰብእ ፡ ቤዛሃ ፡ ለነፍሱ ።

፲፮ ፤ እንዘ ፡ ይዜክር ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ።

ማቴዎስ ፡ ምዕ ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ።

፲፯ ፤ ዘያፈቅራ ፡ ለነፍሱ ፡ ለይግድፋ ።

፲፰ ፤ ወዘሰ ፡ ገደፋ ፡ ለነፍሱ ፡ በእንቲአየ ፡ ይረክባ ።

ማቴዎስ ፡ ምዕ ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፴፱ ።

፲፱ ፤ ወሐረ ፡ ፍኖቶ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኃሠሥኩ ፡ እግዚኦ ፡ ገጸከ ።

፳ ፤ ገጸ ፡ ዚአከ ፡ አኃሥሥ ፡ እግዚኦ ።

፳፩ ፤ ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

መዝ ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፳፪ ፤ ተለውኩ ፡ ስምዓከ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢታስተኃፍረኒ ።

፳፫ ፤ ረዳኤ ፡ ኩነኒ ፡ ወኢትግድፈኒ ።

፳፬ ፤ ወኀበ ፡ በጽሐ ፡ ሀገር ፡ ይሰብክ ፡ ወይብል ፡ ነስሑ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እመኑ ፡ በወንጌል ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።

ማቴ ፡ ምዕ ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፳፭ ፤ ወተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አድያም ፡ ወውስተ ፡ ኵሉ ፡ አኅጉር ፡ ብዙኃት ።

፳፮ ፤ ወይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ሰብእ ፡ እምኵለሄ ፡ ወይትባረኩ ፡ እምኔሁ ።

፳፯ ፤ ወአለኒ ፡ ቦሙ ፡ ድውያነ ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ደዌ ሆሙ ፡ ያመጽኡ ፡ ወይገድፉ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ።

፳፰ ፤ ውእቱኒ ፡ ይፌውሶሙ ፡ ፍጡነ ፡ በኃይለ ፡ አምላኩ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕሌሁ ።

፳፱ ፤ ወርእዮሙ ፡ ሰብእ ፡ ዘይገብር ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተለውዎ ፡ በኵሉ ፡ ልቦሙ ።

፴ ፤ ወኀደጉ ፡ ኵሎ ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ እንተ ፡ ትመርሆ ፡ ውስተ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ ወኮኑ ፡ ፍጹማነ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ።

፴፩ ፤ ወሶበ ፡ ረትዓ ፡ ልቦሙ ፡ በአሚን ፡ ሥላሴ ፡ ይቤልዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሀለው ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ያመልኩ ፡ ጣዖተ ፡ በሀገር ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ከተታ ።

፲፫ ፤ የሚቀድመው ፡ የሚከተለው ፡ ሳይኖር ፡ ወደሠልፍ ፡ እንደሚገባ ፡ አርበኛ ፡ እንደተጉህ ፡ ገበሬ ፡ ሆኖ ።

፲፬ ፤ ለሰው ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ቢገዛ ፡ በነፍሱ ፡ እንዲጎዳ ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፡ እያለ ።

፲፭ ፤ ሰው ፡ ለነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ ባልሰጠ ፡ ነበር ።

፲፮ ፤ ጌታ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እያሰበ ።

ማቴዎስ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስተኛ ፡ ምዕ ፡ ቍ/ ፳፮

፲፯ ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ በገራኅተ ፡ መስቀል ፡ ይጣላት ።

፲፰ ፤ ስለኔ ፡ በገራኅተ ፡ መስቀል ፡ የጣላት ፡ ነፍሱን ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ በክብር ፡ ያገኛታል ።

ማቴዎስ ፡ ምዕ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ቍ ፡ ፴፱ ።

፲፱ ፤ አቤቱ ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ፈለግሁ ።

፳ ፤ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ እፈልጋለሁ ።

፳፩ ፤ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ከኔ ፡ አትመልስ ።

መዝ ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፳፪ ፤ አምልኮትህን ፡ ፈለግሁ ፡ አታሳፍረኝ ።

፳፫ ፤ ረዳት ፡ ሁነኝ ፡ እንጂ ፡ አትጣለኝ ።

፳፬ ፤ በደረሰበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ልትሰጥ ፡ ቀርባለችና ፡ ጌታ ፡ ባስተማራት ፡ በወንጌል ፡ እመኑ ፡ እያለ ፡ ያስተምራል ።

ማቴዎስ ፡ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፳፭ ፤ ዜና ፡ ተአምራቱ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ወጣ ፡ ተነገረ ፡ በብዙችም ፡ አገሮች ፡ ተሰማ ።

፳፮ ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየመጣ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ይባረካሉ ።

፳፯ ፤ ደዌያቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ሰዎችን ፡ እያመጡ ፡ ከእግሩ ፡ ሥር ፡ ያፈሱዋቸዋል ።

፳፰ ፤ እሱም ፡ አድሮበት ፡ ባለ ፡ በፈጣሪው ፡ ኃይል ፡ ፈጥኖ ፡ ያድናቸዋል ።

፳፱ ፤ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚያደርገውን ፡ ተአምራት ፡ አይተው ፡ በፍጹም ልቡናቸው ፡ አምነው ፡ ተከተሉት ።

፴ ፤ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ጣኦት ፡ የምትወስድ ፡ የኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ ሥራን ፡ ትተው ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ጸኑ ።

፴፩ ፤ ልቡናቸው ፡ በሃይማኖት ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ከተታ ፡ በምትባል ፡ ሀገር ፡ ጣኦት ፡ የሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ብለው ፡ ለአባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነገሩት ።

፴፪ ፤ ቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአዕዋም ።
፴፫ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአእባን ።
፴፬ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ በባሕር ።
፴፭ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይትሜረዩ ፡ በእሳት ፤
፴፮ ፤ እለ ፡ ያስተቃስሙ ፡ በብዙኀ ፡ ሥራያት ።
፴፯ ፤ ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ፋል ።
፴፰ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ መዓስባን ።
፴፱ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ገባርያን ፡ ኵርበት ።
፵ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ።
፵፩ ፤ ወብዙኀ ፡ እኪያት ፡ ይትገበራ ፡ በሀገሮሙ ፡ ዘዕጹብ ፡ ለሰሚዖቱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

፩ ፤ ወሰሚዖ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሆከቶ ፡ ልበ ፡ ቅንዓት ፡ ሰማያዊት ።
፪ ፤ ወስእነ ፡ ተዓግሦ ፡ ወተንሥአ ፡ ፍጡነ ።
፫ ፤ ወዓደወ ፡ ፈለገ ፡ ቸይ ፡ ወበጽሐ ፡ ምድረ ፡ ከተታ ።
፬ ፤ ወበከመ ፡ ነገርዎ ፡ ረከቦሙ ፡ ለሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ እንስሳ ።
፭ ፤ ወኢየአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፮ ፤ ወነጸሮሙ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ምግባረ ፡ ምኑነ ።
፯ ፤ ወአኃዘ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ወይምሐሮሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

፩ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ተምዑ ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ዐቢየ ፡ መዓተ ።
፪ ፤ ወፈቀዱ ፡ የሐጥዎ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ።
፫ ፤ ወውእቱሰ ፡ አንሃ ፡ መንፈሶ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወአስተጸንዓ ፡ ርእሶ ፡ በትዕግሥት ።
፬ ፤ ወሄጦሙ ፡ በነገረ ፡ የዋሃት ፡ እስመ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ይገብሩ ፡ በኢያእምሮቶሙ ፡
፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ምንተኑ ፡ ታመልኩ ።
፮ ፤ ወይቤልዎ ፡ ሀሎ ፡ ዓቢይ ፡ ዖም ፡ ዘናመልክ ፡ ንሕነ ፡ ወንሰግድ ፡ ሎቱ ።
፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምንተኑ ፡ ያወስአክሙ ፡ ዕበ ፡ ትሰግዱ ፡ ሎቱ ።
፰ ፤ ወይቤልዎ ፡ ቃለ ፡ ይትናገረነ ፡ እመልዕልቴሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አነ ፡ አምላክክሙ ፡ ወአነ ፡ ፈጠርኩክሙ ።
፱ ፤ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ንሕነሂ ፡ ንሰግድ ፡ ወንዘብሕ ፡ ሎቱ ፡ እምእንስሳ ፡ ዘፈቀደ ።
፲ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊተሂ ፡ ሰዱኒ ፡ ምስሌክሙ ፡ ከመ ፡ እስግድ ፡ ሎቱ ።

፴፪ ፤ ለዕንጨትም ፡ የሚሰግዱ ፡ አሉ ።
፴፫ ፤ ለድንጋይም ፡ የሚሰግዱ ፡ አሉ ።
፴፬ ፤ በባሕር ፡ የሚጠነቁሉ ፡ አሉ ።
፴፭ ፤ በእሳት ፡ የሚያሟርቱም ፡ አሉ ።
፴፮ ፤ ብዙ ፡ መድኃኒት ፡ የሚያጣፍጡ ፡ አሉ ።
፴፯ ፤ የሚጠነቁሉም ፡ አሉ ።
፴፰ ፤ ጠንቋዮችም ፡ አሉ ።
፴፱ ፤ ክታብ ፡ ሰፊዎችም ፡ አሉ ።
፵ ፤ የሚጠነቁሉም ፡ አሉ ።
፵፩ ፤ ለመስማት ፡ የማይቻል ፡ በሀገራቸው ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ኻያ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ልቡናውን ፡ አወከችው ፡ አነሣሣችው ።
፪ ፤ መታገሥ ፡ ቢሳነው ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ሔደ ።
፫ ፤ ቸይ ፡ የምትባል ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ ከተታ ፡ አውራጃ ፡ ደረሰ ።
፬ ፤ የዚያችም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንደነገሩት ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁነው ፡ አገኛቸው ።
፭ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አያውቁት ።
፮ ፤ እሱም ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ የተናቀ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ አይቶ ።
፯ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ይነግራቸው ፡ ይገሥጻቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ጀመር ።

ሠላሳ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡበት ።
፪ ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ሊውጡት ፡ ወደዱ ።
፫ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ታግሦ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ አስተማራቸው ።
፬ ፤ እያለዛዘበ ፡ አስተማራቸው ፡ ባለወቀት ፡ እንዲሠሩት ፡ ያውቃልና ።
፭ ፤ ምን ፡ ታመልካላችሁ ፡ አላቸው ።
፮ ፤ የምናመልከው ፡ የምንሰግድለት ፡ ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ አለ ፡ አሉት ።
፯ ፤ በሰገዳችሁለት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይመልስላችኋል ፡ አላቸው ።
፰ ፤ እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ይናገረናል ።
፱ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኛም ፡ እንሰግድለታለን ፡ የወደደውን ፡ እንሠዋለታለን ።
፲ አባታችንም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እሰግድለት ፡ ዘንድ ፡ እኔንም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ውሰዱኝ ፡ አላቸው ።

፴፪ ፤ ቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአዕዋም ።
፴፫ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአእባን ።
፴፬ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ በባሕር ።
፴፭ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይትሜረዩ ፡ በእሳት ፤
፴፮ ፤ እለ ፡ ያስተቃስሙ ፡ በብዙኅ ፡ ሥራያት ።
፴፯ ፤ ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ፋል ።
፴፰ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ መዓስባን ።
፴፱ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ገባርያነ ፡ ኩርበት ።
፵ ፤ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ።
፵፩ ፤ ወብዙኅ ፡ እከያት ፡ ይትገበሩ ፡ በሀገሮሙ ፡ ዘዕጹብ ፡ ለሰሚዖቱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

፩ ፤ ወሰሚዖ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሆከቶ ፡ ልበ ፡ ቅንዓት ፡ ሰማያዊት ።

፪ ፤ ወስእነ ፡ ተዓግሦ ፡ ወተንሥአ ፡ ፍጡነ ።

፫ ፤ ወዓደወ ፡ ፈለገ ፡ ቸይ ፡ ወበጽሐ ፡ ምድረ ፡ ከተታ ።
፬ ፤ ወበከመ ፡ ነገርዎ ፡ ረከቦሙ ፡ ለሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ እንስሳ ።
፭ ፤ ወኢየአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፮ ፤ ወነጸሮሙ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ምግባረ ፡ ምኑነ ።
፯ ፤ ወአኃዘ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ወይምሐሮሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

፩ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ተምዑ ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ዐቢየ ፡ መዓተ ።
፪ ፤ ወፈቀዱ ፡ የሐጥዎ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ።
፫ ፤ ወውእቱሰ ፡ አንሃ ፡ መንፈሶ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወአስተጻንዓ ፡ ርእሶ ፡ በትዕግሥት ።
፬ ፤ ወሄጠሙ ፡ በነገረ ፡ የዋሃት ፡ እስመ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ይገብሩ ፡ በኢያእምሮቶሙ ፡
፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ምንተኑ ፡ ታመልኩ ።
፮ ፤ ወይቤልዎ ፡ ሀሎ ፡ ዓቢይ ፡ ዖም ፡ ዘናመልክ ፡ ንሕነ ፡ ወንሰግድ ፡ ሎቱ ።
፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምንተኑ ፡ ያወስእክሙ ፡ ሶበ ፡ ትሰግዱ ፡ ሎቱ ።
፰ ፤ ወይቤልዎ ፡ ቃለ ፡ ይትናገረነ ፡ እመልዕልቴሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አነ ፡ አምላክክሙ ፡ ወአነ ፡ ፈጠርኩክሙ ።
፱ ፤ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ንሕነሂ ፡ ንሰግድ ፡ ወንዘብሕ ፡ ሎቱ ፡ እምእንስሳ ፡ ዘፈቀደ ።
፲ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊተሂ ፡ ሰዱኒ ፡ ምስሌክሙ ፡ ከመ ፡ እስግድ ፡ ሎቱ ።

፴፪ ፤ ለዕንጨትም ፡ የሚሰግዱ ፡ አሉ ።
፴፫ ፤ ለድንጋይም ፡ የሚሰግዱ ፡ አሉ ።
፴፬ ፤ በባሕር ፡ የሚጠነቁሉ ፡ አሉ ።
፴፭ ፤ በእሳት ፡ የሚያሟርቱም ፡ አሉ ።
፴፮ ፤ ብዙ ፡ መድኃኒት ፡ የሚያጣፍጡ ፡ አሉ ።
፴፯ ፤ የሚጠነቁሉም ፡ አሉ ።
፴፰ ፤ ጠንቋዮችም ፡ አሉ ።
፴፱ ፤ ክታብ ፡ ሰፊዎችም ፡ አሉ ።
፵ ፤ የሚጠነቁሉም ፡ አሉ ።
፵፩ ፤ ለመስማት ፡ የማይቻል ፡ በሀገራቸው ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ኻያ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ልቡናውን ፡ አወከችው ፡ አነሣሣችው ።
፪ ፤ መታገሥ ፡ ቢሳነው ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ሔደ ።
፫ ፤ ቸይ ፡ የምትባል ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ ከተታ ፡ አውራጃ ፡ ደረሰ ።
፬ ፤ የዚያችም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንደነገሩት ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁነው ፡ አገኛቸው ።
፭ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አያውቁት ።
፮ ፤ እሱም ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ የተናቀ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ አይቶ ።
፯ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ይነግራቸው ፡ ይገሥጻቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ጀመር ።

ሠላሳ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡበት ።
፪ ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ሊውጡት ፡ ወደዱ ።
፫ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ታግሦ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ አስተማራቸው ።
፬ ፤ እያለዛዘበ ፡ አስተማራቸው ፡ ባለወቀት ፡ እንዲሠሩት ፡ ያውቃልና ።
፭ ፤ ምን ፡ ታመልካላችሁ ፡ አላቸው ።
፮ ፤ የምናመልከው ፡ የምንሰግድለት ፡ ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ አለ ፡ አሉት ።
፯ ፤ በሰገዳችሁለት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይመልስላችኋል ፡ አላቸው ።

፰ ፤ እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ይናገረናል ።

፱ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኛም ፡ እንሰግድለታለን ፡ የወደደውን ፡ እንሠዋለታለን ።
፲ ፤ አባታችንም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስግድለት ፡ ዘንድ ፡ እኔንም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ውሰዱኝ ፡ አላቸው ።

፲፩ ፤ ወይቤልዎ ፡ አሆ ፡ ጌሠመ ፡ ንወስደከ ።
፲፪ ፤ ወበሳኒታ ፡ ወሰድዎ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ይመስሎሙ ፡ ዘይሰግድ ፡ ለአምላኮሙ ።
፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ቀርቡ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ያም ፡ ከልሐ ፡ ሰይጣን ፡ ዘላዕሌሃ ።
፲፬ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ ሰብአ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ምንተኑ ፡ አምጻእክሙ ፡ ኀቤየ ፡ ብእሴ ፡ ዘነኪር ፡ እምሕግየ ።
፲፭ ፤ ውእቱ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘየሐውር ፡ ማእከሌክሙ ።
፲፮ ፤ ወይቤልዎ ፡ ኪያከ ፡ ይብል ፡ ኢታምጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ እስመ ፡ ጸልዓከ ፡ አምላክነ ፡ እምርትቅ ።
፲፯ ፤ ወከመዝ ፡ የአምር ፡ ዘልፈ ፡ ዘቦቱ ፡ ኃጢአት ፡ ወይጸልዕ ፡ ይምጻእ ፡ ኀቤሁ ፡ አንተሂ ፡ ኀድግ ፡ ምዕረ ፡ ይእዜ ፡ እስከ ፡ ናስተብቍዖ ፡ ንሕነ ።
፲፰ ፤ ወእምድኅረ ፡ አስተብቋዕናሁ ፡ ትመጽእ ።
፲፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አኮ ፡ ኪያየ ፡ ዘይጸልዕ ።
፳ ፤ አላ ፡ እምተፈሥሐ ፡ ሶበ ፡ መጻእኩ ፡ እስግድ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሰባሕ ፡ መንግሥቱ ፡ በላዕሌየ ።
፳፩ ፤ እስመ ፡ መጻእኩ ፡ አነ ፡ እምርትቅ፡ብሔር።
፳፪ ፤ ወባሕቱ ፡ ኅሡ ፡ እምኔክሙ ፡ ዘይጸልዖ ።
፳፫ ፤ ወእምዝ ፡ ሖሩ ፡ መንገለ ፡ ያም ።
፳፬ ፤ ወካዕበ ፡ ጸርሐ ፡ ሰይጣን ፡ ወይቤ ፡ ኢይቤለክሙኑ ፡ ኢታምጽኡ ፡ ብእሴ ፡ ነኪረ ፡ እምሕግየ ፡ ውእቱ ፡ ዘሀሎ ፡ ማዕከሌክሙ ።
፳፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ አንተኑ ፡ ውእቱ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡ ወአልቦ ፡ ውስተ ፡ ሀገርነ ፡ ዘይሰመይ ፡ በዝንቱ ፡ ስም ።
፳፮ ፤ ወስምከኒ ፡ እንግዳ ፡ ውእቱ ።
፳፯ ፤ ወኢሰማዕነ ፡ ዘከመዝ ፡ ስም ፡ እምዓመ ፡ ኮነ ።
፳፰ ፤ ኅድግ ፡ ወኢትምጻእ ፡ ከመ ፡ ኢይትመዐዓነ ፡ አምላክነ ።
፳፱ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎሙ ፡ ኀደግዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ መጠነ ፡ ፫ ፡ ምዕራፍ ፡ ወሐሩ ፡ ከመ ፡ ይስግዱ ፡ ለያም ።
፴ ፤ ወርእዮ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምግባሮሙ ፡ ምኑነ ፡ ቆመ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ወሜጠ ፡ ገጾ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ወጸለየ ።
፴፩ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ርኢ ፡ እግዚኦ ፡ ትምይንቶ ፡ ለሰይጣን ፡ ዘይትሜየን ፡ በላዕለ ፡ ፍጥረትከ ።
፴፪ ፤ ለምንት ፡ አባሕኮ ፡ ለመስተቃርን ፡ ከመ ፡ ያኅስም ፡ ግብረ ፡ እደዊከ ።

፲፩ ፤ እሺ ፡ ነገ ፡ እንወስድሃለን ፡ አሉት ።
፲፪ ፤ በነጋው ፡ ለጣኦታቸው ፡ የሚሰግድ ፡ መስሏቸው ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰዱት ።
፲፫ ፤ ከዛፉ ፡ ዘንድ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በላይዋ ፡ ያደረ ፡ ሰይጣን ፡ ጮኸ ።
፲፬ ፤ እላንት ፡ የዚች ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ከኔ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ምን ፡ አመጣችሁብኝ ፡ እያለ ።
፲፭ ፤ በመካከላችሁ ፡ የሚሄድ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እያለ ።
፲፮ ፤ ፈጣሪያችን ፡ ጠልቶሃልና ፡ ከሩቅ ፡ አይቶ ፡ አንተን ፡ ወደኔ ፡ አታምጡብኝ ፡ አለ ፡ አሉት ።
፲፯ ፤ ዘወትር፡ እንደዚሁ ፡ ኃጢአት ፡ ያለበትን ፡ እያወቀ ፡ ወደሱ ፡ ሊመጣ ፡ አይወድም ፤ አንተም ፡ ዛሬ ፡ ቆይ ፡ ሂደን ፡ እስክንለምነው ፡ ድረስ ፡ አሉት ።
፲፰ ፤ ከለመነው ፡ በኋላ ፡ ትመጣለህ ።
፲፱ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የሚጠላው ፡ እኔን ፡ አይደለም ።
፳ ፤ ጌትነቱ ፡ በኔ ፡ ይገለጽ ፡ ዘንድ ፡ ልሰግድለት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ነበር ፡ እንጂ ።
፳፩ ፤ እኔ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ መጥቻለሁና ።
፳፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከናንት ፡ የሚጠላው ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ፈልጉ ፡ አላቸው ።
፳፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደዛፉ ፡ ቀረቡ ።
፳፬ ፤ ይህ ፡ ከመካከላችሁ ፡ ያለ ፡ ከኔ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ አታምጡብኝ ፡ አላልኋችሁምን ፡ እያለ ፡ ዳግመኛ ፡ ጮኸ ።
፳፭ ፤ ያገሩም ፡ ሰዎች ፡ በሀገራችን ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ የለም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አንተ ፡ ነህን ።
፳፮ ፤ ስምህም ፡ እንግዳ ፡ ነው ።
፳፯ ፤ ከሆነ ፡ ጀምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስም ፡ አልሰማንም ።
፳፰ ፤ ፈጣሪያችን ፡ እንዳይቆጣን ፡ ቆይ ፡ አትምጣ ፡ አሉት ።
፳፱ ፤ ይህን ፡ ብለው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሦስት ፡ ምዕራፍ ፡ ያህል ፡ ጐዳና ፡ ሲቀር ፡ ትተውት ፡ ሊሰግዱ ፡ ወደ ፡ ዛፉ ፡ ሄዱ ።
፴ ፤ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የተናቀ ፡ ሥራቸውን ፡ አይቶ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መልሶ ፡ ወደፈጣሪው ፡ አመለከተ ።
፴፩ ፤ አቤቱ ፡ በፍጥረትህ ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ የሰይጣንን ፡ ትንኮል ፡ ተመልከት ፡ እያለ ።
፴፪ ፤ ሥነ ፡ ፍጥረትህን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ተከራካሪያችንን ፡ ለምን ፡ አሠለጠንከው ።

፺፫ ይእዜኒ ፡ አስተበቍዓከ ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ታኅሥሮ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰይጣን ፡ ዕቡይ ፡ በእደ ዚአየ ።
፺፬ ወፈንዎ ፡ ለሚካኤል ፡ መልአከ ፡ ምክርከ ፡ ከመ ፡ ይርድአኒ ፡ በከመ ፡ ትቤለኒ ።

፺፭ ወለሰይጣንሰ ፡ ኢታብሖ ፡ ይሑር ፡ እም ዝንቱ ፡ ደም ፡ እስከ ፡ ያስተርኢ ፡ ኃፍረቱ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ዘነበረ ፡ እንዘ ፡ ያስሕቶሙ ።

፯ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ በብርሃን ፡ ሠረገላ ፡
ተቀምጦ ፡ ሄደ ፡፡
፰ ፡ የእናርእት ፡ አውራጃን ፡ ሁሉ ፡ አስተማረ ፡፡
፱ ፡ የጣዖቱን ፡ ቤት ፡ አፈረሰ ፡፡
፲ ፡ የታሰልና ፡ የዊጽን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡
ወደውራጌ ፡ ሄደ ፡፡

፲፩ ፤ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ወግር ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ቢለት ።

፲፪ ፤ ወይእቲ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለመሠርያን ።

፲፫ ፤ ወበህየ ፡ ይሠውዑ ፡ ሎሙ ፡ ደመ ፡ ላህም ፡ ወጠሊ ።

፲፬ ፤ ወይትኤመሩ ፡ ሎሙ ፡ አጋንንት ፡ በውስቴታ ።

፲፭ ፤ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ንጉሦሙ ፡ ዘይነብር ፡ ህየ ።

፲፮ ፤ ወኵሎሙ ፡ ማርያን ።

፲፯ ፤ ወመስተቃስማን ፤

፲፰ ፤ ወሰብአ ፡ ሐረስ ።

፲፱ ፤ ይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ወይውዕሉ ፡ ውስተ ፡ ኵርጓኔሁ ፡ ታሕተ ፡ ውእቱ ፡ ወግር ።

፳ ፤ በበ፲ቱ ፻ ፡ ወ፳፻ ፡ መሠርያን ።

፳፩ ፤ ምስለ ፡ አምኃሆሙ ፡ እንዘ ፡ በአተ ፡ ቃል ፡ እምአፉሁ ።

፳፪ ፤ እመ ፡ ነበበ ፡ ሠናየ ፡ ይረክቡ ፡ ሠናየ ።

፳፫ ፤ ወእመ ፡ ነበበ ፡ እኩየ ፡ ይረክቡ ፡ እኩየ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አንገሥዎ ፡ ላዕሌሆሙ ።

፳፬ ፤ ወርእዮሙ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ግብሮሙ ፡ አርገ ፡ ጽቡተ ፡ እንተ ፡ ካልዕ ፡ ገጽ ።

፳፭ ፤ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ይነብር ፡ ውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ መሠርያን ።

፳፮ ፤ ነቢሮ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ወርቅ ፡ ወተሰርጊዎ ፡ በአልባሰ ፡ ወርቅ ።

፳፯ ፤ ወጸፍዖ ፡ ገጾ ፡ ወአውደቆ ፡ እመንበሩ ፡ ወረገጾ ፡ ክሣዶ ።

፳፰ ፤ ወኀድአ ፡ እንግድአሁ ።

፳፱ ፤ ወይቤሎ ፡ አንተ ፡ እኩይ ፡ ወልዱ ፡ ለሰይጣን ፡ ወእኊሆሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ለምንት ፡ ታስሕት ፡ ሕዝበ ፡ ዘተሣየጠሙ ፡ **ክርስቶስ ፡** በደሙ ።

፴ ፤ ወውእቱሰ ፡ ንጉሠ ፡ መሠርያን ፡ ኃጥእ ፡ ዘይነብብ ።

፴፩ ፤ እስመ ፡ መሰሎ ፡ ዘነጠረ ፡ መብረቅ ፡ እምሰማይ ፡ ወአውደቆ ።

፴፪ ፤ ወኢነጸሮ ፡ ጊዜ ፡ ይበውእ ፡ ኀቤሁ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**

፴፫ ፤ ወአኃዝዎ ፡ ወአልጸቅዎ ፡ **ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ወይቤልዎ ፡ እምአይቴ ፡ መጻእከ ፡ ወበምንት ፡ ግብር ፡ በጻሕከ ፡ ዝየ ። ወመኑ ፡ አዕረገከ ፡ ወአብአከ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

፴፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎሙ ፡ ጸፍዕዎ ፡ ገጾ ፡ እስከ ፡ ይውኅዝ ፡ ደም ፡ እምአፉሁ ፡ ወእምአጽናፊሁ ።

፲፩ ፤ ቢለት ፡ ከምትባል ፡ ተራራ ፡ ደረሰ ።

፲፪ ፤ ይችውም ፡ ያስማተኞች ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ናት ።

፲፫ ፤ ፍየልና ፡ ላም ፡ ይሠውበታል ።

፲፬ ፤ በሱዋም ፡ አጋንንት ፡ ይላገጹላቸዋል ።

፲፭ ፤ ከዚያ ፡ የሚቀመጥ ፡ አንድ ፡ ንጉሣቸው ፡ ነበር ።

፲፮ ፤ ሟርተኞች ።

፲፯ ፤ መድኃኒት ፡ የሚያጣፍጡ ።

፲፰ ፤ ጠንቋዮች ።

፲፱ ፤ ከተራራው ፡ ሥር ፡ በሸንጎው ፡ ሲሰግዱለት ፡ ይውላሉ ።

፳ ፤ ሺህ ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ የሚያሟርቱ ።

፳፩ ፤ እጅ ፡ መንሻቸውን ፡ ይዘው ፡ ቃል ፡ እስኪናገራቸው ፡ ድረስ ፡ እየጠበቁ ።

፳፪ ፤ ደግ ፡ የተናገረ ፡ እንደሆነ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ያገኛሉ ።

፳፫ ፤ ክፉ ፡ ቢናገር ፡ ክፉ ፡ ይደረግባቸዋል ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አንግሠውት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

፳፬ ፤ **ክቡር ፡ አባታችንም ፡** ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ አይቶ ፡ በሌላ ፡ ጐዳና ፡ ተሰውሮ ፡ ወጣ ።

፳፭ ፤ ይህ ፡ የጠንቋዮች ፡ ንጉሥ ፡ ካለበት ፡ ደረሰ።

፳፮ ፤ በወርቅ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ፡ ለብሶ ፡ አገኘው ።

፳፯ ፤ ፊቱን ፡ ጸፍቶ ፡ ከዙፋኑ ፡ ጥሎ ፡ አንገቱን ፡ ረግጦ ።

፳፰ ፤ ደረቱን ፡ ረገጠው ።

፳፱ ፤ አንተ ፡ ክፉ ፡ የዲያብሎስ ፡ የግብር ፡ ልጁ ፡ የአጋንንት ፡ ወንድማቸው ፡ **ክርስቶስ ፡** በደሙ ፡ የዋጃቸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለምን ፡ ታስታለህ ፡ አለው ።

፴ ፤ ይህም ፡ የጠንቋዮች ፡ ንጉሥ ፡ የሚናገረውን ፡ አጣ ።

፴፩ ፤ መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ የጣለው ፡ መስሎት ፡ ነበርና ።

፴፪ ፤ **ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ወደሱ ፡ የገባ ፡ ጊዜ ፡ አላየውም ፡ ነበርና ።

፴፫ ፤ አሽከሮቹ ፡ **ክቡር ፡ አባታችንን ፡** ይዘው ፡ ከወዴት ፡ መጣህ ፡ በምን ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ ደረስክ ፡ ማን ፡ አውጥቶ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ አገባህ ።

፴፬ ፤ ይህን ፡ ብለው ፡ ፊቱን ፡ ጸፉት ፡ ደም ፡ ካፍንጫውም ፡ ካፉም ፡ እስኪወርድ ፡ ድረስ ።

፷፭ ፤ ወአምጽኡ ፡ አብትረ ፡ ሐጺን ፡ ግዙፋተ ፡ ወዘበጥዎ ፡ እስከ ፡ ይደቅ ፡ ዓፅሙ ።

፷፮ ፤ ወሞተ ፡ ሶቤሃ ።

፷፯ ፤ ወነሥኡ ፡ በድኖ ፡ ወገደፍዎ ፡ ታሕተ ፡ ውእቱ ፡ ወግር ።

፷፰ ፤ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ይብልዎ፡ አራዊተ፡ ገዳም ።

፷፱ ፤ ወመጽአ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወጸውዖ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተንሥእ፡ እንበለ ፡ ሙስና ።

፸ ፤ ወበጊዜሃ ፡ ተንሥአ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡ ከመ ፡ ዘንታሕ ፡ እምንዋም ።

፸፩ ፤ ወኀሠሠ ፡ ቍስሊሁ ፡ ወኢሐየዎ፡ እምደዌሁ ።

፸፪ ፤ ወኮነ ፡ ጥዑየ ፡ ከመ ፡ ዘኢለከፎ ፡ ሕማም ፡ ግሙራ ።

፸፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሑር ፡ ጽብዖ ፡ ለውእቱ ፡ መሠርይ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ትመውእ ።

፸፬ ፤ ወሖረ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ይትወረዘው ፡ በኃይለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወአርገ ፡ መልዕልተ ፡ ወግር ።

፸፭ ፤ ወረከቦ ፡ ለውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ መሠርያን ፡ ነቢሮ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ወርቅ ።

፸፮ ፤ ውእቱሰ ፡ መሠርይ ፡ ኢይኔጽር ፡ ጊዜ ፡ ይበውእ ፡ ኀቤሁ ፡ አቡነ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፸፯ ፤ ወባሕቱ ፡ ጊዜ ፡ ይጸፍዖ ፡ ገጾ ፡ ይሬእዮ ።

፸፰ ፤ ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ጸፍዖ ፡ ዳግመ ፡ አቡነ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፸፱ ፤ ወኢውደቀ ፡ እመንበሩ ፡ ወነሥአ ፡ መንበሮ ፡ ወቀጥቀጠ ፡ በዲቤሁ ።

፹ ፤ ወከልሐ ፡ ውእቱ ፡ መሠርይ ፡ እንዘ ፡ ይብሎሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ናሁ ፡ ይቀትለኒ ፡ ዘትማልም ፡ ብእሲ ፡ ወለምንት ፡ ተኃድጉኒ ፡ ባሕቲትየ ።

፹፩ ፤ ወቦኡ ፡ አግብርቲሁ ፡ እንዘ ፡ ይረውጹ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ።

፹፪ ፤ ወረከብዎ ፡ ለቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡እንዘ ፡ ይዘብጦ ፡ ለእግዚእሙ ።

፹፫ ፤ ወአኀዝዎ ፡ ፍጡነ ፡ ወአምጽኡ ፡ አስዋጠ፡ ሐጺን ፡ ወቀሠፍዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ይትረአይ ፡ ዓፅመ ፡ ገቦሁ ።

፹፬ ፤ ወተበህሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ፡ ይእዜሰ ፡ ኢንቅትሎ ፡ እስከ ፡ ንሕትቶ ፡ ቅድመ ።

፹፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ እምአይቴ ፡ ወአይቴ ፡ ብሔርከ ፡ ወምንት ፡ ግብርከ ።

፹፮ ፤ ኢቀተልናከኑ ፡ ትማልም ፡ መኑ ፡ አንሥአከዮም ። ይጸንዕኑ ፡ ሥራይከ ፡ እምሥራይነ።

፷፭ ፤ ወፍራም ፡ ወፍራም ፡ የብረት ፡ በትር ፡ አምጥተው ፡ አጥንቱ ፡ እስኪደቅ ፡ ድረስ፡ መቱት ።

፷፮ ፤ ያንጊዜ ፡ ሞተ ።

፷፯ ፤ በድኑን ፡ አንሥተው ፡ ከተራራው ፡ ሥር ፡ ጣሉት ።

፷፰ ፤ የዱር ፡ አራዊት ፡ ይብሉት ፡ ብለው ።

፷፱ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ መጥቶ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጉዳት ፡ የለብህም ፡ ተነሥ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

፸ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ፈጥኖ፡ እንዲነሣ ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣ ።

፸፩ ፤ ቁስሉን ፡ ዳሰ ፡ ከደዌው ፡ አዳነው ፤

፸፪ ፤ መከራ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳላገኘው ፡ ሆኖ ፡ዳነ።

፸፫ ፤ ይህንን ፡ ሚርተኛ ፡ አንተ ፡ ድል ፡ ታደርገዋለህና ፡ ሂደህ ፡ ተዋጋው ፡ አለው ።

፸፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ኀልምሶ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

፸፭ ፤ ይህን ፡ የጠንቋዮቹን ፡ ንጉሥ ፡ በወርቅ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘው ።

፸፮ ፤ ይህ ፡ የጠንቋዮቹ ፡ ንጉሥ ፡ ግን፡ አባታችን ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደሱ ፡ ሲገባ፡ አላየውም ።

፸፯ ፤ ፊቱን ፡ ሲመታው ፡ ያየዋል ፡ እንጂ ።

፸፰ ፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ንጉሣቸውን ፡ ፊቱን፡ ጸፍቶ ።

፸፱ ፤ ከዙፋኑ ፡ ጣልው ፡ አልጋውን ፡ አንሥቶ ፡ በላዩ ፡ ሰበረው ።

፹ ፤ ይኸም ፡ የጠንቋዮች ፡ ንጉሥ ፡ አሽከሮቹን፡ እነሆ ፡ የትናንትናው ፡ ሰው ፡ ሲገለኝ ፡ ብቻየን ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ትላላችሁ ፡ እያለ ፡ ጮኸ።

፹፩ ፤ ባሮቹም ፡ በወዲያና ፡ በወዲህ ፡ እየሮጡ ገቡ ።

፹፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡ ጌታቸውን ፡ ሲመታ ፡ አገኙት ።

፹፫ ፤ ፈጥነው ፡ ይዘው ፡ የብረት ፡ አለንጋ ፡ አምጥተው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ የጐኑ ፡ አጥንት ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ ገረፉት ።

፹፬ ፤ ዛሬስ ፡ አንግደለው ፡ እስኪ ፡ ቀድሞ ፡ እንመርምረው ፡ ተባባሉ ።

፹፭ ፤ ከወዴት ፡ መጣህ ፡ አገርህስ ፡ ወዴት ፡ ነው፡ ሥራህስ ፡ ምድርነው ።

፹፮ ፤ ትላንት ፡ አልገደልንህምን ፡ ዛሬ ፡ ማን ፡ አሥነሣህ፡ ከኛ ፡ መድኃኒት ፡ ያንተ ፡ መድኃኒት ፡ ይጸናል ፡ አሉት ።

፶፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በአማን ፡ ይጸንዕ ፡ አምላኪየ ፡ እምአምላክክሙ ።
፶፰ ፤ ወአንሰ ፡ ሥራየ ፡ ኢየአምር ።
፶፱ ፤ ባሕቱ ፡ እስዕር ፡ ሥራየክሙ ፡ መጸእኩ ።
፷ ፤ ወይቤልዎ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ ብሔርከ ፡
፷፩ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለከለባትኑ ፡ እነግር ፡ ብሔርየ።
፷፪ ፤ ባሕቱ ፡ ከለባት ፡ ይኄይሱ ፡ እምኔክሙ።
፷፫ ፤ እስመ ፡ የአምሩ ፡ እግዚአሙ ።
፷፬ ፤ ወሶበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ዘንተ ።
፷፭ ፤ ቀሠፍዎ ፡ ካዕበ ፡ እስከ ፡ ይትረዓይ ፡ ንዋየ ፡ ውስጡ ።
፷፮ ፤ ወተክዕወ ፡ ደሙ ፡ ከመ ፡ ውኂዘ፡ ማይ ፡
፷፯ ፤ ወኮና ፡ አባላቲሁ ፡ በበግማድ ፡ ግማደ።
፷፰ ፤ ወአልጸቀ ፡ ለመዊት ።
፷፱ ፤ ወነሥእዎ ፡ ወገደፍዎ ፡ ውስተ ፡ ጸድፍ።
፸ ፤ ወበጊዜሃ ፡ አንሥኦ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ከመ ፡ ቀዳሚ ።
፸፩ ፤ ወነበረ ፡ ከመዝ ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ጽባሕ ፡ እንዘ ይሣቀይ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ኵነኔ።
፸፪ ፤ ወኢጥዕመ ፡ እክለ ፡ ወማየ ፡ በእላንቱ ፡ አርባ ፡ መዋዕል ።
፸፫ ፤ ወበጽሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ መከራ ፡ ብዙኅ ።
፸፬ ፤ ረኃብ ፡ ወጽምዕ ፡ ዝብጠት ፡ ወተቀስፎ፡ እምኀበ ፡ እሉ ፡ እኩያን ።
፸፭ ፤ እንዘ ፡ ይፈቅድ ፡ ያግብአሙ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ መድኃኒት ።
፸፮ ፤ እመንቱሰ ፡ ዓበዩ ፡ ተግኅሦ ፡ እምፍናዊ ሆሙ ፡ እኩይ ።
፸፯ ፤ ወእምድኅረ ፡ ፵ ፡ ዕለት ፡ ሶበ ፡ ርእየ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ግዝፈተ ፡ ልቦሙ ፡ ወጽንዓተ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ እብን ፡ ዘኢይለመልም ፡ ጸለየ ፡ ኀበ እግዚአብሔር ።
፸፰ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአስተርአይከኒ ፡ በሀገርየ ።
፸፱ ፤ ወትቤለኒ ፡ ረሰይኩከ ፡ ሐዋርያ ፡ ሐዲሰ።
፹ ፤ ወእፌንወከ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብ ፡ ሐዲሳን ።
፹፩ ፤ አንሰ ፡ ኀበኒ ፡ ኦሐውር ፡ ወኀበኒ ፡ አኀድር በትእዛዝከ ፡ እነብር ።
፹፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ በጻሕኩ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብ ፡ እለ፡ ኢየአምሩከ ።
፹፫ ፤ ወአሕሰሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ብዙኃ ።
፹፬ ፤ ወአንሰ ፡ ተወከፍኩ ፡ ምንዳቤያተ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ፡ እንዘ ፡ ታጸንዓኒ ፡ አንተ።
፹፭ ፤ የምስ ፡ ሐመምኩ ፡ ፈድፋደ ።

፶፯ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በውነት ፡ ከናንተ ፡ ፈጣሪ ፡ የኔ ፡ ፈጣሪ ፡ ይጸናል ።
፶፰ ፤ እኔ ፡ መድኃኒት ፡ ዐላውቅም ።
፶፱ ፤ የእናንተን ፡ መድኃኒት ፡ ላጠፋ ፡ መጥቻለሁ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
፷ ፤ አገርህ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ አሉት ።
፷፩ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ አገሬን ፡ ለውሻ ፡ እናገራለሁን ።
፷፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ውሾች ፡ ከናንተ ፡ ይሻላሉ።
፷፫ ፤ ጌታቸውን ፡ ያውቃሉና ፡ አላቸው ።
፷፬ ፤ ይህን ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ።
፷፭ ፤ የውስጥ ፡ ዕቃው ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ፡ ሁለተኛ ፡ ገረፉት ።
፷፮ ፤ ደሙም ፡ እንደሚፈስ፡ ውኃ ፡ ወረደ ።
፷፯ ፤ አካሉም ፡ እንደሥጋ ፡ ተቆራረጠ ።
፷፰ ፤ ለመሞትም ፡ ደረሰ ።
፷፱ ፤ አንሥተው ፡ ወደገደል ፡ ጣሉት ።
፸ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እንደቀድሞ ፡ ፈጥኖ አነሣው ።
፸፩ ፤ እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከነሱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ መከራ እየተቀበለ ፡ ተቀመጠ ።
፸፪ ፤ በኒህም ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ እህል ፡ ውኃ፡ አል ቀመሰም ።
፸፫ ፤ ብዙ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት ።
፸፬ ፤ ከሊህ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ የደረሱበት ፡ ረኃብ ፡ ጽም ፡ መመታት ፡ መገረፍ ፡ ናቸው ።
፸፭ ፤ ወደደህንነት ፡ ጎዳና ፡ ሊመልሳቸው ፡ ወዶ ።
፸፮ ፤ እነሱ ፡ ግን ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ አንመለስም ፡ አሉ ።
፸፯ ፤ ከአርባ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን እንደ ፡ ደረቅ ፡ ደንጊያ ፡ የሕሊናቸውን ፡ ጽናት ፡ የልቡናቸውን ፡ መወፈር ፡ አይቶ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነ ።
፸፰ ፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሀገሬ ፡ ሳለሁ ፡ የታየኸኝ ፡ የተነጋገርከኝ ፡ አንተ ነህ ።
፸፱ ፤ አዲስ ፡ ሐዋርያ ፡ አድርጌሃለሁ ።
፹ ፤ ወደ ፡ አዲስ ፡ አማኞች ፡ እልክሃለሁ፡ ያልከኝ ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፹፩ ፤ እኔ ፡ በምሄድበትም፡ በማድርበትም ፡ በትእዛዝህ ፡ ጸንቼ ፡ እቀመጣለሁ ፡ እያለ፡ ለመነ ።
፹፪ ፤ ዛሬም ፡ አንተን ፡ ወደማያውቁ ፡ ሕዝብ፡ ደረስኩ ።
፹፫ ፤ ብዙ ፡ አከፉብኝ ።
፹፬ ፤ እኔም ፡ አንተ ፡ እያጸናኸኝ ፡ በስምህ ፡ ስለ ፡ ተጸራሁ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ።
፹፭ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ታመምኩ ።

፹፮ ፤ ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ ወተበተል ፡ በቀ
ልየ ፡ እምሕዝብ ፡ ውጹእን ፡ እምጽድቅ ።

መዝ ፡ ፵፱ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፹፯ ፤ አዝዛ ፡ ለምድር፡ ታብቍዕ ፡ አፉሃ ፡ ወተኃ
ጠሙ ፡ ከመ ፡ ዳታን ፡ ወአቤሮን ።
፹፰ ፤ ወከመ ፡ ትኢይንቶሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ቆሬ፡
ኀብልያሙ ፡ እሳት ፡ አርኢ ፡ ኃይለከ ፡
በላዕሌሆሙ ።
፹፱ ፤ ወነገረ ፡ ቃልከሰ ፡ ርሱን ፡ ይትቃወም ፡
ሊተ ፡ ለገብርከ ።
፺ ፤ ወፈጺሞ ፡ ዘንተ ፡ ጸሎቶ ፡ አርገ ፡ መልዕ
ልተ ፡ ወግር ።
፺፩ ፤ ወረከቦሙ ፡ ለመሠርያነ ፡ ኵሉ ፡ አህጉር ፡
ተጋቢኦሙ ፡ አሐተኒ ፡ እንዘ ፡ ይሰግዱ ፡
ለንጉሦሙ ።
፺፪ ፤ ወቆመ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡
በዊአ ፡ ማእከሎሙ ።
፺፫ ፤ ወከልሐ ፡ በዓቢይ ፡ ቃል ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
እኤዝዘኪ ፡ ምድር ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር
ወአኮ ፡ በቃለ ፡ ዚአየ ፡ ከመ ፡ ታብቅዊ ፡
አፉኪ ፡ ወኃጢዮሙ ፡ ለእሉ ፡ እኩያን ።
፺፬ ፤ ወበጊዜሃ ፡ አብቀወት ፡ ምድር ፡ አፉሃ ፡
ወውኅጠቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መሠርያን ፡
ምስለ ፡ ንጉሦሙ ፡ ረሲዕ ።
፺፭ ፤ ወወረዱ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ሕያዋኒሆሙ ።
፺፮ ፤ ወርእዮ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አዕኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፺፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተዓውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ ብር
ሃነ ፡ ገጽከ ፡ እግዚኦ ።
፺፰ ፤ ወወደይከ ፡ ዮም ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡
ልብየ ።

መዝ ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፺፱ ፤ አማን ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፡ አንተ ፡ ወን
ጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አንተ ።
፻ ፤ ወእንዘ ፡ ይብል ፡ ዘንተ ፡ አንሶሰወ ፡ መል
ዕልተ ፡ ወግር ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ማኅደሪሆሙ ፡
ለመሠርያን ።
፻፩ ፤ ወረከበ ፡ ግልፍዋተ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ።
፻፪ ፤ ወነሥአ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ እብነ ፡ ወቀጥቀጠሙ ።
፻፫ ፤ ወነሠተ ፡ ኵሎ ፡ መሥዋዕቲሆሙ ።
፻፬ ፤ ወመሲዮ ፡ ቆመ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ
ሃይማኖት ፡ ኀበ ፡ አኀቲ ፡ ዖም ፡ እምነ ፡
ዕፀዋም ፡ ዐቢያን ።
፻፭ ፤ ወእንዘ ፡ ይገብር ፡ ጸሎተ ፡ በህየ ፡ መጽኡ፡
ትእልፊት ፡ አእላፋት ፡ አጋንንት ፡ ዘኢይ
ትኌለቍ ፡ ብዝሆሙ ።
፻፮ ፤ ቅዱስኒ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አር
መመ ፡ እምገቢረ ፡ ጸሎት ፡ ከመ ፡ ይርአ
ዮሙ ፡ ለእሉ ።

፹፮ ፤ ከውነት ፡ ከወጡ ፡ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ፈር
ደህ ፡ አድነኝ ።

አርባ ፡ ሁለተኛ ፡ መዝሙር ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፹፯ ፤ እንደ ፡ አቤሮንና ፡ እንደዳታን ፡ ተከፍታ ፡
ትውጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ምድርን ፡ እዘዛት ።
፹፰ ፤ እንደቆሬ ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ እሳት ፡ ታቃ
ጥላቸው ፡ ዘንድ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ኃይልህን
ግለጥ ።
፹፱ ፤ የጋለ ፡ ቃልህ ፡ ግን ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ይከ
ራከርልኝ ፡ እያለ ፡ ጸለየ ።
፺ ፤ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ከጸለየ ፡ በኋላ ፡ ወደተ
ራራው ፡ ወጣ ።
፺፩ ፤ ከየሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ጠንቋ
ዮች ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ ለንጉሣቸው ፡
ሲሰግዱ ፡ አገኛቸው ።
፺፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡
ከመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ ቆመ ።
፺፫ ፤ አንቺ ፡ ምድር ፡ እኒህን ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች፡
ተከፍተሽ ፡ ትውጫቸው ፡ ዘንድ ፡ በኔ
ቃል ፡ ያይደለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
አዝዝሻለሁ ፡ እያለ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ።
፺፬ ፤ ወዲያው ፡ ተከፍታ ፡ ጠንቋዮቹን ፡ ሁሉ
ከከሃዲ ፡ ንጉሣቸው ፡ ጋራ ፡ ዋጠቻቸው ።
፺፭ ፤ እንደኖሩም ፡ ወደሲኦል ፡ ወረዱ ።
፺፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ።
፺፯ ፤ ገጸ ፡ ረድኤትህ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተገለጸ ።
፺፰ ፤ ዛሬ ፡ ልቡናዬን ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ።

አራተኛ ፡ መዝ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፺፱ ፤ በውነት ፡ የአማልክት ፡ ፈጣሪ ፡ አንተ
ነህ ፡ የነገሥታት ፡ ገዥ ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፻ ፤ በተራራው ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ወደጠንቋዮቹ፡
ማደሪያ ፡ ሁሉ ፡ ተመላለሰ ።
፻፩ ፤ በብርና ፡ በወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ጣዖቶች ፡
አገኘ ።
፻፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ቀጠቀጣቸው ።
፻፫ ፤ የሚሠውበትን ፡ ሁሉ ፡ አፈረሰ ።
፻፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ከመሸ ፡ በኋላ ፡ ከታ
ላላቆች ፡ ዛፎች ፡ በአንዲቱ ፡ ዛፍ ፡ አጠ
ገብ ፡ ቆሞ ፡ ጸለየ ።
፻፭ ፤ በዚያ ፡ ሲጸልይ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላ
ቸው ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ አጋንንት ፡ መጡ ።
፻፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡
የሚያደርጉትን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ዝም ፡ አለ ።

፻፯ ፡ ወከልሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይቤሉ ፡ ኢአከለ ከኑ ፡ ምድረ ፡ ሸዋ ፡ ዘኃደግነ ፡ ለከ ።
፻፰ ፡ ዝየኒ ፡ መጻእከ ፡ ከመ ፡ ትክላዕ ፡ አምልኮተነ ።

፻፱ ፡ ንሕነኒ ፡ ኢነኃድገከ ፡ ዘእንበለ ፡ ንቅትልከ ።
፻፲ ፡ ወነሥኡ ፡ አእባነ ፡ ወወገርዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ይደቅቅ ፡ ዐፅሙ ።

፻፲፩ ፡ ወእንዘ ፡ ይዌግርዎ ፡ ወረደ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ በነበልባለ ፡ እሳት ወዘበጦሙ ፡ በክነፊሁ ።
፻፲፪ ፡ ወረሰዮሙ ፡ ከመ ፡ ጸበለ ፡ ምድር ፡ ወኃልቁ ፡ ኵሎሙ ።
፻፲፫ ፡ ወአንሥኦ ፡ ለእቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወገሠሦ ፡ ወአሕየዎ ፡ እምሕማሙ ።

፻፲፬ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለምንተ ፡ ኢአተብከ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ጊዜ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤከ ፡ አጋንንት ።
፻፲፭ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምንተ ፡ ይሬስዩኒ ፡ ለእመ ፡ ቀተሉ ፡ ሥጋየ ለነፍስየሰ ፡ ኢይክሉ ፡ ቀቲሎታ ።

ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።

፻፲፮ ፡ ባሕቱ ፡ እትፌሣሕ ፡ በእንተ ፡ ዘያበዝኁ ፡ ሊተ ፡ ዕሤተ ፡ ምዝጋና ፡ በተጋድሎቶሙ ፡ ምስሌየ ።
፻፲፯ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አፍቁርየ ፡ ጽናዕ ፡ ወኃይል ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ገድላተ ፡ ጸላኢ ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ ኀቤከ ።

፻፲፰ ፡ እስመ ፡ ሀለወከ ፡ ትሚጥ ፡ ብዙኃነ ፡ ነፍሳተ ፡ እምኢያእምሮ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ አሚን ።
፻፲፱ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ መልአክ ፡ ኃለፈ ።
፻፳ ፡ ወበሳኒታ ፡ ሰምዓ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቃለ ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ናሁ ይትወለድ ፡ ለከ ፡ ወልድ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘስሙ ፡ አኖሬዎስ ።

፻፳፩ ፡ ወውእቱ ፡ ይጠፍዮሙ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ፡ መሠርያን ፡ ወይመይጦሙ ፡ ውስተ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ።
፻፳፪ ፡ ወይትሐነጽ ፡ ዓቢይ ፡ ምኔት ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ወይበዝኁ ፡ ደቂቅከ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ።
፻፳፫ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰሚዖ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ አርመመ ።
፻፳፬ ፡ ወእምዝ ፡ ነሥተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘአጋንንት ።
፻፳፭ ፡ ወአእመኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ።

፻፯ ፡ ሁሉም ፡ የተውንልህ ፡ የሸዋ ፡ አውራጃ ፡ አልበቃህምን ፡ ብለው ፡ ጮሁ ።
፻፰ ፡ ከዚህም ፡ እንዳያመልኩብን ፡ ልትከለክል ፡ መጣህ ።
፻፱ ፡ እኛም ፡ ሳንገልህ ፡ አንተውህም ፡ ብለው ።
፻፲ ፡ ደንጊያ ፡ አንሥተው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አጥንቱ ፡ እስኪደቅድረስ ፡ ወገሩት ።

፻፲፩ ፡ ሲወግሩት ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እየተንቦገቦገ ፡ ወርዶ ፡ በክንፉ ፡ መታቸው ።
፻፲፪ ፡ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ አደረጋቸው ፡ ሁሉም አለቁ ።
፻፲፫ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አንሥቶ ፡ ዳሰሰው ፡ ከመከራውም ፡ አዳነው ።
፻፲፬ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አጋንንት ፡ በመጡብህ ፡ ጊዜ ፡ በመስቀል ፡ አለማማተብህ ፡ ለምንድነው ፡ አለው ።
፻፲፭ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ሥጋየን ፡ ቢገድሉ ፡ ነፍሴን ፡ ለመግደል ፡ አይቻላቸውም ፡ ምን ፡ ያደርጉኛል ፡ አለው ።

ማቴ ፡ ዐሥረኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።

፻፲፮ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በመዋጋታቸው ፡ የምስጋና ፡ ዋጋዬን ፡ ስለአበዙልኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ እንጂ ።
፻፲፯ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጠላትህ ፡ እየተዋጋ ፡ በሚያመጣብህ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጸንተህ ፡ ተዋጋ ፡ ጽና ፡ በርታ ።
፻፲፰ ፡ ብዙን ፡ ሰዎች ፡ ከድንቁርና ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ትመልሳቸዋለህና ፡ አለው ።

፻፲፱ ፡ መልአኩ ፡ ይህን ፡ ነግሮት ፡ ሄደ ።
፻፳ ፡ በነጋው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ አኖሬዎስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይወለድልሀል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከሰማይ ፡ ሰማ ።

፻፳፩ ፡ እሱ ፡ ከአንተ ፡ የተረፉትን ፡ ጠንቋዮች ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመልሳቸዋል ።
፻፳፪ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ታላቅ ፡ ገዳም ፡ ይሠራል ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ በዷ ፡ ልጆችህ ፡ ይበዛሉ ።

፻፳፫ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።
፻፳፬ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለአጋንንት ፡ የሚሠውበትን ፡ ቦታ ፡ አፈረሰ ።
፻፳፭ ፡ ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አሳመናቸው ።

፻፷፮ ፤ እስመ ፡ ልማዱ ፡ ለዝንቱ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ኀበ ፡ በጽሐ ፡ ሀገር፡ ይሴአል ፡ እምሰብእ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ ምሕራማተ ፡ ዘያመልኩ ፡ ቦቱ።
፻፷፯ ፤ ወሶበ ፡ ነገርዎ ፡ የሐውር፡ ፍጡነ፡ ወይነሥቶ።
፻፷፰ ፤ ወእንዘ ፡ ከመዝ ፡ ይገብር ፡ በጽሐ ፡ ምድረ ዳሞት ፡ ኀበ ፡ ደብር ፡ ዘይሰመይ ፡ ዝባፌ ተን ።
፻፷፱ ፤ ወቦ ፡ ህየ ፡ ጣዖት ፡ ዘአእባን ፡ ወዘዕፀው ፡ በዘያሰግሉ ።

፻፸ ፤ ወይትገሀዱ ፡ ቦሙ ፡ አጋንንት ፡ በውስቴቱ ።
፻፸፩ ፤ ወይዘብሁ ፡ ሎሙ ፡ መምለክያኒሆሙ ፡ ወይወጽሑ ፡ ሎሙ ፡ ደመ ፡ እንስሳ ።
፻፸፪ ፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት እልክተ ፡ ግልፎዋተ ፡ ነሥአ ፡ እብነ ፡ ወቀጥቀጦሙ ፡ ወገንጸለ፡ መናብርቲሆሙ ።

፻፸፫ ፤ ወሶበ ፡ ዓርበ ፡ ፀሐይ ፡ ቆመ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለጸልዩ ፡ ታሕተ ፡ ዖም ።
፻፸፬ ፤ ወመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኃን ፡ አጋንንት ፡ እንዘ ፡ ይጸዓቁ ።
፻፸፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ በቃለ ፡ ከላህ ፡ ኢአከለከኑ፡ አድያማተ ፡ ሸዋ ፡ ዘኃደግነ ፡ ለከ።
፻፸፮ ፤ ዝየኒ ፡ መጻእከ ፡ ከመ ፡ ትክላዕ ፡ እምልኮትነ ።
፻፸፯ ፤ ወይእዜኒ፡ኢነኀድገከ ፡ በእንበለ ፡ ንቅትልከ።
፻፸፰ ፤ ወተገረሙ ፡ በአፍርሆቱ ፡ ወወገርዎ ፡ በአእባን ።
፻፸፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለምንት ፡ ትጸምዉ ፡ ከንቶ፡ እንዘ ፡ ድኩማን ፡ አንትሙ ።
፻፹ ፤ ወዓተበ ፡ ላዕሌሁ ፡ በማዕተበ ፡ ክርስቶስ፤
፻፹፩ ፤ ወተዘርው ፡ ከመ ፡ ጢስ ።
፻፹፪ ፤ ወበሳኒታ ፡ ተጋብኡ ፡ ሰብእ ፡ ብዙኃን፡ ዓበይተ ፡ ሀገር ።
፻፹፫ ፤ ከመ ፡ ይስግዱ ፡ ለአማልክቲሆሙ ።
፻፹፬ ፤ ወሰከብዎሙ ፡ ውዱቃነ ፡ ወግዱፋነ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ምድር ።
፻፹፭ ፤ ወደንገፁ ፡ ወተበሀሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ምንተ ፡ ኮኑ ፡ አማልክቲነ ፡ ዮም ፡ ወመኑ፡ ቀጥቀጦሙ ።
፻፹፮ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አነ፡ ሰበርክዎሙ ፡ በኃይለ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
፻፹፯ ፤ ዘኢክህሉ ፡ አድኅኖ ፡ ርእሶሙ ፡ እሉ ፡ ድኩማን ፡ እምእዴየ ፡ እፎኑ ፡ ይክሉ ፡ ረዲአ ፡ ለባዕዳን ፡
፻፹፰ ፤ ምንተ ፡ ይገብሩ ፡ ለክሙ ፡ እሉ ፡ አእባን፡ ዘአልቦሙ ፡ እስትንፋስ ።
፻፹፱ ፤ ወርእየሙ ፡ ኪያሁ ፡ ይቤልዎ ፡ እምአይቴ ፡ አንተ ።

፻፷፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በደረሰበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያመልኩበት ፡ የጣዖት ፡ ቤት ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ እያለ እየጠየቀ ፡ ማጥፋት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ።
፻፷፯ ፤ በነገሩትም ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ሄዶ ፡ ያጠፋዋል።
፻፷፰ ፤ እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ ሲሄድ ፡ በዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ወዳለ ፡ ዝባፌተን ፡ ከሚባል፡ ተራራ ፡ ደረሰ ።
፻፷፱ ፤ ከዚያም ፡ ያገር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያመልከው ፡ የዕንጨትና ፡ የድንጊያ ፡ ጣዖት የሚያስጠነቁሉበት ፡ አገኘ ፡ (አለ) ።
፻፸ ፤ በዚያም ፡ አጋንንት ፡ ይገለጹላቸዋል ።
፻፸፩ ፤ የሚያመልኳቸውም ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ እያፈሰሱ ፡ ይሠውላቸዋል ።
፻፸፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡ እሊህን ፡ ጣዖቶች ፡ አይቶ ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ቀጠቀጣቸው ፡ ቦታቸውንም ፡ አጠፋባቸው ። ወንበራቸውን ፡ ገለበጠባቸው ።
፻፸፫ ፤ ፀሐይ ፡ በገባም ፡ ጊዜ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ቁሞ ፡ ሲጸልይ ።

፻፸፬ ፤ ወደሱ ፡ አጋንንት ፡ በዝተው ፡ እየተጬናነቁ ፡ መጡ ።
፻፸፭ ፤ የተውንልህ ፡ የሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ አልበቃህምን ፡ ብለው ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ።
፻፸፮ ፤ ከዚህም ፡ ግዛታችንን ፡ ልትከለክል ፡ መጣህን ።
፻፸፯ ፤ ዛሬስ ፡ ሳንገልህ ፡ አንተውህም ፡ አሉት
፻፸፰ ፤ እሱን ፡ ለማስፈራራት ፡ ተገርመው ፡ በደንጊያ ፡ ወገሩት ።
፻፸፱ ፤ የማይቻላችሁ ፡ ስትሆኑ ፡ በከንቱ ፡ ለምን ትደክማላችሁ ፡ ብሎ ።
፻፹ ፤ በመስቀል ፡ አማተበባቸው ።
፻፹፩ ፤ እንደ ፡ ጢስ ፡ በነው ፡ ጠፉ ።
፻፹፪ ፤ በነጋው ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ።
፻፹፫ ፤ ለጣዖቶቻቸው ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ።
፻፹፬ ፤ ከምድር ፡ ወድቀው ፡ ወድቀው ፡ አገኙዋቸው ።
፻፹፭ ፤ ደንግጠው ፡ ጣዖቶቻችን ፡ ምን ፡ አገኛቸው፡ ማን ፡ ሰባበራቸው ፡ ተባባሉ።

፻፹፮ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በጌታዬ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ እኔ ፡ ሰበርኳቸው ፡ አላቸው ።
፻፹፯ ፤ ከኔ ፡ እጅ ፡ ራሳቸውን ፡ ማዳን ፡ ያልቻሉ እሊህ ፡ ደካሞች ፡ ሌላውን ፡ ማዳን ፡ እንደምን ፡ ይችላሉ ።
፻፹፰ ፤ ትንፋሽ ፡ የሌላቸው ፡ እኒህ ፡ ድንጋዮች ፡ ምን ፡ ያደርጉላችኋል ፡ አላቸው ።
፻፹፱ ፤ እሱን ፡ አይተው ፡ ከየት ፡ መጣህ፡ አሉት ።

፻፶ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አንሰ ፡ መጻእኩ ፡ እምሀገርየ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
፻፶፩ ፤ ከመ ፡ እንስት ፡ ኵሎ ፡ ምሕራማተ ፡ ዘታስሕቱ ፡ ቦሙ ።
፻፶፪ ፤ ወይቤልዎ ፡ እመሰ ፡ ፈነወከ ፡ እግዚእከ ፡ እስኩኬ ፡ ንሬኢ ፡ ለእመ ፡ ያድኅነከ ፡ እምእዴነ ።
፻፶፫ ፤ በከመ ፡ አጥፋዕከ ፡ አማልክቲከ ፡ ንሕነኒ ፡ ንገብር ፡ እኩየ ፡ ላዕሌከ ።
፻፶፬ ፤ ወአኃዝዎ ፡ ወዘበጥዎ ።
፻፶፭ ፤ ወአሕመምዎ ፡ ብዙኃ ፡ እስከ ፡ አልጸቀት ፡ ነፍሱ ፡ ለወፂእ ።
፻፶፮ ፤ ወመንፈቆሙ ፡ ይቤሉ ፡ ኢንቅትሎ ፡ ዘእንበለ ፡ ያእምር ፡ ንጉሥ ።
፻፶፯ ፤ እስመ ፡ ሰበረ ፡ አማልክተ ፡ ዘያመልኮሙ ።
፻፶፰ ፤ ወሞቅሕዎ ፡ በጽኑዕ ፡ ሙቃሔ ።
፻፶፱ ፤ ወወሰዶ ፡ ፩ እምኔሆሙ ፡ ዘስሙ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ ዘውእቱ ፡ መኰንነ ፡ አዳም ።
፻፷ ፤ ለውእቱሰ ፡ መኰንነ ፡ አዳም ፡ ቦቱ ፡ ወልድ ፡ ዘየሐንቆ ፡ ጋኔን ፡ ወይነጽሖ ።
፻፷፩ ፤ ወሶቤሃ ፡ እንዘ ፡ የአቱ ፡ መኰንን ፡ ሶበ ፡ አልጸቀ ፡ ለበዊአ ፡ ቤቱ ፡ ወፅአ ፡ ውእቱ ፡ ወልድ ፡ ለቀበላ ፡ አቡሁ ።
፻፷፪ ፤ ወሶቤሃ ፡ ነጽሖ ፡ ጋኔኑ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።
፻፷፫ ፤ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ።
፻፷፬ ፤ ወጸርሐ ፡ ጋኔን ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ምንት ፡ ብየ ፡ ምስሌከ ፡ ኦ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ።
፻፷፭ ፤ ወጸውዖ ፡ ስምከሰ ፡ ሐዲስ ፡ ኢይትከሃለኒ ።
፻፷፮ ፤ መኑ ፡ አብጽሐከ ፡ ዝየ ፡ ከመ ፡ ትሣቅየኒ ።
፻፷፯ ፤ ወኀደጉ ፡ ለከ ፡ ቅድመ ፡ ብዙኃተ ፡ አድያማተ ፡ ሸዋ ፡ ወኢያእክለከኑ ፡ እማንቱ ።
፻፷፰ ፤ ወሰደድከኒ ፡ እምኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ይእዜኒ ፡ ዝየ ፡ መጻእከ ።
፻፷፱ ፤ አሌ ፡ ሊተ ፡ አይቴ ፡ አጕይይ ፡ እምኔከ ፡ አ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ዘኢተአርፍ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ።
፻፸ ፤ አነ ፡ ወአንተ ፡ እንዘ ፡ ንትቃተል ፡ ንነብር እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞትከ ።
፻፸፩ ፤ ወእመኒ ፡ አበይከ ፡ አርምሞ ፡ ናሁ ፡ እበውእ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ንጉሥ ፡ ሞተሎሚ ወይወድየከ ፡ ውስተ ፡ ጠመ ፡ ግራር ።
፻፸፪ ፤ ወትትሐጎል ፡ በህየ ፡ ወአነ ፡ አዓርፍ ፡ እምኔከ ።
፻፸፫ ፤ ወሰሚዖ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ደንገፀ ፡ ወፈትሖ ፡ ፍጡነ ፡ እማእሰሩ ።
፻፸፬ ፤ ወሰገደ ፡ ቅድሜሁ ።
፻፸፭ ፤ ወይቤሎ ፡ አንተኑ ፡ አምላከ ፡ ሰማይ ፡ ዘይብልዎ ፡ እግዚአብሔር ።

፻፶ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እኔስ ፡ ከጌታዬ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታዝዤ ፡ ከሀገሬ ፡ መጣሁ ፡ አላቸው ።
፻፶፩ ፤ የምታስቱባቸው ፡ የጣዖቱን ፡ ቤት ፡ መስገጃችሁን ፡ አፈርስ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።
፻፶፪ ፤ ጌታህስ ፡ ተላከህ ፡ እስኪ ፡ ከኛ ፡ እጅ ፡ ሲያድንህ ፡ እናያለን ።
፻፶፫ ፤ ጣዖቶቻችንን ፡ እንዳጠፋህ ፡ አንተንም ፡ እናጠፋሃለን ፡ ብለው ።
፻፶፬ ፤ ይዘው ፡ ደበደቡት ።
፻፶፭ ፤ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ለመለየት ፡ እስክትለይ ፡ ድረስ ፡ መከራ ፡ አጸኑበት ።
፻፶፮ ፤ እኩሌቶቹ ፡ ንጉሡ ፡ ሳያውቅ ፡ እንግደለው ፡ አሉ ።
፻፶፯ ፤ ንጉሡ ፡ የሚያመልካቸውን ፡ ጣዖቶች ፡ ሰብሯልና ።
፻፶፰ ፤ አጽንተው ፡ አሰሩት ።
፻፶፱ ፤ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡ የሚሆን ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ወሰደው ።
፻፷ ፤ ለዚህም ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ጋኔን ፡ የሚጥለው ፡ ልጅ ፡ ነበረው ።
፻፷፩ ፤ ይህም ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ወደቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ሲመለስ ፡ ልጁ ፡ ሊቀበለው ፡ ወጣ ።
፻፷፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጋኔሉ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ጣለው ።
፻፷፫ ፤ ሁሉም ፡ ደነገጡ ።
፻፷፬ ፤ ፍሥሐ ፡ ጽዮንን ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ምን ፡ አለኝ ብሎ ፡ ሰይጣኑ ፡ ጮኸ ።
፻፷፭ ፤ አዲሱ ፡ ስምህንስ ፡ መጥራት ፡ አይቻለኝም ።
፻፷፮ ፤ መከራ ፡ ታጸናብኝ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ማን አመጣህ ።
፻፷፯ ፤ ቀድሞ ፡ የሸዋን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ተውኩልህ ፡ ስለዚህ ፡ አልበቃህምን ።
፻፷፰ ፤ በሄድኩበት ፡ እየተከተልክ ፡ ከየሀገሩ ፡ አስወጥተህ ፡ ሰደድከኝ ፡ ዛሬም ፡ ከዚህ ፡ መጣህ ።
፻፷፱ ፤ ባንድ ፡ አገር ፡ የማታርፍ ፡ አንተ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ካንተ ፡ ወዴት ፡ እሸሻለሁ ፡ ወዮ ልኝ ።
፻፸ ፤ እኔና ፡ አንተ ፡ እስክንሞት ፡ ስንዋጋ ፡ እንኖራለን ።
፻፸፩ ፤ ዝም ፡ ካላልክስ ፡ በሞተለሚ ፡ ልብ ፡ አድሬ ወደ ፡ ገደል ፡ ይጥልሃል ።
፻፸፪ ፤ ከዚያ ፡ ትሞታለህ ፡ እኔም ፡ ካንተ ፡ አርፋለሁ ፡ አለው ።
፻፸፫ ፤ ይህም ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ደንግጦ ፡ እስሩን ፡ ፈታው ።
፻፸፬ ፤ ከፊቱ ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣው ።
፻፸፭ ፤ እግዚአብሔር የሚሉት ፡ የሰማይ ፡ ፈጣሪ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ።

፻፸፮ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አንሰ ፡ ኢኮንኩ ፡ ኪያሁ ፡ ዳዕሙ ፡ ገብሩ ፡ አነ ፡ ዘአመልክ ።

፻፸፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ መሐረኒ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ፡ አ ፡ አባ ።

፻፸፰ ፤ ወፈውሶ ፡ ሊተ ፡ ለወልድየ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለእመ ተፈውሰ ፡ ለከ ፡ ወልድከ ፡ በእዴየ ፡ ተአምንኑ ፡ በአምላኪየ ።

፻፸፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ እወ ፡ አአምን ፡ ፍጹመ ።

፻፹ ፤ ወአንሥአ ፡ እዴሁ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡ ወአተበ ፡ ላዕለ ፡ ገጸ ፡ ሕፃን ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ በስመ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፃእ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እምላዕለ ፡ ወልድ ።

፻፹፩ ፤ ወወፅአ ፡ በጊዜሃ ፡ በአምሳለ ፡ ዓቢይ ፡ ቅርድ ።

፻፹፪ ፤ እንዘ ፡ ይኬልህ ፡ ወይብል ፡ ኢትልክፈኒ ፡ ወኢታውዕየኒ ፡ በእሳት ፡ ዘእዴከ ፡ በልየ ፡ እወፅእ ፡ ለከ ።

፻፹፫ ፤ ወአንከሩ ፡ እለ ፡ ርእዩ ፡ ወተፈሥሐ ፡ ውእቱ መኰንን ፡ ወአምነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ወምስለ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገረ ፡ አደሞ ፡ በላዕለ ፡ እደዊሁ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፹፬ ፤ ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ አጥመቆሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፻፹፭ ፤ ወሰመዮ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ለውእቱ ፡ መኰንን ።

፻፹፮ ፤ ወለብእሲቱ ፡ ሰመያ ፡ ወለተ ፡ ዋሕድ።

፻፹፯ ፤ ወለወልዱ ፡ ሰመዮ ፡ ተክለ ፡ ዋሕድ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ መጽኡ ፡ ዓበይተ ፡ ሀገር ፡ እለ ፡ አኀዝዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ወይቤልዎ ፡ ለመኰንን ፡ ዕቀቦ ፡ በጽኑዕ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘቀጥቀጠ ፡ አማልክቲነ ።

፪ ፤ እስከ ፡ ናበጽሖ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።

፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ ሠናይ ፡ እነ ፡ እዓቅቦ ።

፬ ፤ ወነበረ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሰብአ ፡ አደሞ ፡ ሕገ ሃይማኖት ፡ ኦርቶዶክሳዊት ።

፭ ፤ ወይፌውስ ፡ ድውያነ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ፡ ሀገር ።

፻፸፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡ እኔስ ፡ እሱን ፡ አይደለሁም ፡ የማመልከው፡ የሱ ፡ ባሪያ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ።

፻፸፯ ፤ አባቴ ፡ አምላክ ፡ የሚባለው ፡ ማነው ፡ ሕይወት ፡ የማገኝበትን ፡ ሥራ ፡ ንገረኝ ።

፻፸፰ ፤ ልጄንም ፡ አድንልኝ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ልጅህን ፡ ባድን ልህ ፡ በኔ ፡ አምላክ ፡ ታምናለህን ፡ አለው ።

፻፸፱ ፤ አዎን ፡ ፈጽሜ ፡ አምናለሁ ፡ አለው ።

፻፹ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡ አንተ ፡ ርኩስ ፡ሰይጣን ፡ በጌታዬ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ ከብላቴና ፡ ላይ ፡ ውጣ ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ አንሥቶ ፡ በሕፃኑ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ አማተበ ።

፻፹፩ ፤ ወዲያው ፡ ገመር ፡ ዝንጀሮ ፡ መስሎ ፡ ወጣ ።

፻፹፪ ፤ እኔው ፡ እወጣለሁ ፡ አትንካኝ ፡ በጅህ ፡ ባለ ፡ እሳት ፡ አታቃጥለኝ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ።

፻፹፫ ፤ ይህን ፡ ያዩ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ፡ ይህም ፡ አገረ፡ ገዥ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከነቤተሰቡ ፡ ከሀገሩም ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በክቡር ፡ አባታችን፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቃል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ስም ፡ አመነ ።

፻፹፬ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ በሦስቱ ፡ ስም ፡ አጠመቃቸው ።

፻፹፭ ፤ አገረ ፡ ገዥውን ፡ ስሙን ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ አለው ።

፻፹፮ ፤ ሚስቱንም ፡ ወለተ ፡ ዋሕድ ፡ አላት ።

፻፹፯ ፤ ልጁንም ፡ ተክለ ዋሕድ ፡ አለው ።

ሠላሳ ፡ ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ሃይማኖትን ፡ የያዙት ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሽማግሎች ፡ መጥተው ፡ አገረ ፡ ገዥውን ፡ ጣዖታችንን፡ ያጠፋ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ አጽንተህ ፡ ጠብቅ ፡ አሉት ።

፪ ፤ ከንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ እስክናደርሰው ።

፫ ፤ ይህም ፡ ሹም ፡ ደኅና ፡ አድርጌ ፡ እጠብቃለሁ ፡ አላቸው ።

፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ለዳሞት ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ ሃይማኖትን ፡ እያስተማረ ፡ ተቀመጠ ።

፭ ፤ በሀገራቸው ፡ የታመሙትንም ፡ እያዳነ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

፩ ፡ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ ፫ ፡ አውራኅ ፡ መጽኡ ፡ እሙንቱ ፡ መኳንንት ፡ ወይቤልዎ ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድ ፡ አምጽእ ፡ ብእሴ ፡ ዘአቀብነ ፡ ለከ ።
፪ ፡ ወነዓ ፡ ንስዶ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።
፫ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢይሁበክሙ ፡ ኪያሁ ፡ እስከ እመውት ፡ ምስሌሁ ።
፬ ፡ ወይቤልዎ ፡ እመ ፡ ኢወሀብከነ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ፪ኤክሙ ፡ ትትወደዩ ፡ ውስተ ፡ ጦመ ፡ ግራር ።
፭ ፡ ወትትኴነኑ ፡ ብዙኀ ።
፮ ፡ ወሖሩ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ ያስተዋድይዎ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወበጺሖሙ ፡ ሀየ ፡ ዜነውዎ ፡ ለንጉሥ ፡ እንዘ ይብሉ ።
አ ፡ እግዚእነ ረከብነ ብእሴ ፡ መልዕልተ፡ ዘባፈተን ፡ ሰቢሮ ፡ ኵሎ ፡ አማልክተ ፡ ዘትሰግድ ፡ ሎሙ ፡ አንተ ።
፯ ፡ ወአሰርናሆ ፡ እስከ ፡ ናመጽእ ፡ ለከ ፡ ወአዕቀብናሆ ፡ ለቀፈረ ፡ ውደም ።
፰ ፡ ወናሁ ፡ ቀዊሞ ፡ ሎቱ ፡ ወይቤለነ ፡ ኢይሁበክሙ ፡ ኪያሁ ፡ እስከ ፡ እመውት ፡ ምስሌሁ ።
፱ ፡ እንዳኢ ፡ ኢነአምር ፡ ለእመ ፡ ከሀዶሙ ፡ ለአማልክቲከ ፡ አ ፡ ንጉሥ ።
፲ ፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ ተምዓ ፡ ጥቀ ።
፲፩ ፡ ወፈነወ ፡ ኃያላነ ፡ ላዕካነ ፡ ከመ ፡ ያምጽእዎሙ ፡ ለ፪ኤሆሙ ፡ በሙቃሔ ፡ ጽኑዕ ።
፲፪ ፡ ወበጺሖሙ ፡ ልዑካን ፡ ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ለመኰንን ፡ አዳም ።
፲፫ ፡ ረከብዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ያወዕእ ፡ አጋንንተ ፡ ወይሜህሮሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሀገር ፡ ዕበያቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፲፬ ፡ ወአኀዝዎ ፡ ወአሰርዎ ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድሂ ምስሌሁ ፡ ወወሰድዎ ፡ ኅቡረ ።
፲፭ ፡ ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በፍኖት ፡ ይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፲፮ ፡ ስማዕ ፡ እንግርከ ፡ አብእሴ ፡ እግዚአብሔር ።
፲፯ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ፳ወ፭ ፡ ዓመት ፡ እምዘ ፡ ተአንበዘ ፡ ልቡ ፡ ለንጉሥ ፡ በእንተ ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘጼወዋ ፡ እምሀገረ ፡ ሸዋ ።
፲፰ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያውስባ ፡ በሕገ ፡ አማልክቲሁ ፡ ጠቢሐ ፡ መጋዝዕተ ፡ ብዙኃተ ።
፲፱ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ያምጽእዋ ፡ በክብር ፡ ከመ፡ ያስግዳ ፡ ለአማልክት ፡ እምቅድመ ፡ ያውስባ ።

ሠላሳ ፡ ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ መኳንንቱ መጥተው ፡ ገብረ ፡ ዋሕድን ፡ ጠብቅ ፡ ያልንህን ፡ ሰው ፡ አምጣ ።
፪ ፡ና ፡ ወደንጉሡ ፡ እንውሰደው ፡ አሉት ።
፫ ፡ እሱንስ ፡ አልሰጣችሁም ፡ አብሬ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
፬ ፡ እሱንስ ፡ ካልሰጠኸን ፡ ሁለታችሁንም ፡ ገደል ፡ እንድንሰዳችሁ ፡ ዕወቅ ።
፭ ፡ ብዙ ፡ መከራም ፡ ትቀበላላችሁ ፡ አሉት ።
፮ ፡ ሊያጣሉት ፡ ሊያኮስሱት ፡ ወደንጉሡ ፡ ፈጥነው ፡ ሄዱ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በደረሱ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ የምትሰግድላቸውን ፡ አማልክት ፡ የሰበረ ፡ ሰው ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ አግኝተን ።
፯ ፡ ወዳንተ ፡ እስክናመጣ ፡ ድረስ ፡ አስረን ጠብቅ ፡ ብለን ፡ ለቀፈረ ፡ ውድም ፡ ሰጠነው ።
፰ ፡ እነሆ ፡ ለሱ ፡ ጠበቃ ፡ ሁኖ ፡ ስጠን ፡ ብንለው ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ እሱንስ ፡ አልሰጣችሁም ፡ አለን ፡ ብለው ፡ አካሰሱት ።
፱ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ያንተን ፡ አማልክት ፡ ክዷቸውም ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ ፡ አናውቅም ፡ አሉት ።
፲ ፡ ንጉሡም ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ተቆጣ ።
፲፩ ፡ ሁለቱን ፡ አስራችሁ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ኃይለኞች ፡ አሽከሮቹን ፡ ላከ ።
፲፪ ፡ መልእክተኞች ፡ ከቀፈረ ፡ ውድም ፡ ቤት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ።
፲፫ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ጋኔን ፡ ሲያወጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱን ፡ (ቸርነቱን ፡) ለሀገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲያስተምር ፡ አገኙት ።
፲፬ ፡ እሱንም ፡ ገብረ ፡ ዋሕድንም ፡ አስረው ፡ አብረው ፡ ወሰዷቸው ።
፲፭ ፡ በጐዳና ፡ ሲሄዱ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንዲህ ፡ አለው።
፲፮ ፡ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ሰው ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ።
፲፯ ፡ ከሸዋ ፡ የተማረከች ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ነገር ፡ ንጉሡ ፡ አእምሮውን ፡ ካጣ ፡ እነሆ ፡ ኻያ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ ነው ።
፲፰ ፡ በጣዖቱ ፡ ሥርዓት ፡ ሊያገባት ፡ ወዶ ፡ ብዙ ፡ ሰንጋዎች ፡ አረደ ።
፲፱ ፡ ሊያገባት ፡ ለጣዖቱ ፡ ሊያሰግዳት ፡ አክብራችሁ ፡ አምጧት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፳ ፤ ወሶበ ፡ ቆመት ፡ ቅድመ ፡ አማልክት ፡ መጽአ ፡ መብረቅ ፡ እምሰማይ ፡ እንዘ ፡ ንሬኢ ፡ ኵልነ ፡ ወመሰጣ ፡ ግብተ ፡ ወአዕረጋ ፡ ሰማየ ።
፳፩ ፤ ወሞቱ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ እምግርማሁ ፡ ንጉሥኒ ፡ ኮነ ፡ እንቡዘ ፡ እምይእቲ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ዮም ።
፳፪ ፤ ለእመ ፡ አሕየውኮ ፡ እምእንባዜ ፡ እምኀድገነ ፡ ይመስለኒ ።
፳፫ ፤ ወእመአኮሰ ፡ ይቀትለኒ ።
፳፬ ፤ ወአክሞሰሰ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ወይቤ ፡ ትፈርህኑ ፡ ኵነኔ ፡ አ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ።
፳፭ ፤ ኢትፍራህ ፡ እስመ ፡ ኢየኀድገነ ፡ አምላክነ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለንጉሥ ።
፳፮ ፤ ወበእንተ ፡ ይእቲኒ ፡ ብእሲት ፡ ዘትቤለኒ ፡ ድኅረ ፡ እነግረከ ።
፳፯ ፤ እምከመ ፡ ርኢከ ፡ ስብሐተ ፡ **እግዚአብሔር** ።
፳፰ ፤ ወእንዘ ፡ ይትበሃሉ ፡ ዘንተ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ። ወነገርዎ ፡ ልዑካን ፡ በእንቲአሆሙ ።
፳፱ ፤ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ አምጽእዎሙ ፡ ኀቤየ ።
፴ ፤ ወአምጽእዎሙ ፡ ወአቀምዎሙ ፡ ቅድሜሁ ።
፴፩ ፤ ወይቤሎ ፡ ለማር ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ ብሔርከ ። አ ፡ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ዘታማስን ፡ ሀገረነ ።
፴፪ ፤ ወይቤሎ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ አ ፡ ሀርቱም ፡ ወእንቡዝ ፡ ሕሊና ። እንዘ ፡ ኢተአምር ፡ ኪያየ ፡ ትሴአለኒ ሀገርየ ።
፴፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ ብሔርከ ፡ ወምንት ፡ ውእቱ ፡ ፍጥረትከ ።
፴፬ ፤ ወይቤሎ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ አንሰ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ እምብሔረ ፡ ጽባሕ ።
፴፭ ፤ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ አብጽሐከ ፡ ዝየ ።
፴፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ማር ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ፈነወኒ ፡ ከመ ፡ አጥፍዕ ፡ ኵሎ ፡ አማልክተ ፡ ዘውስተ ፡ ሀገርከ ።
፴፯ ፤ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ ተምዓ ።
፴፰ ፤ ወይቤሎ ፡ ኪያከኑ ፡ ያምልኩ ፡ መጻእከ ፡ ዘታጠፍዕ ፡ አማልክተ ።
፴፱ ፤ አነ ፡ ወልደ ፡ እስለንደኒ ፡ አጠፍዕ ፡ ኪያከ ፡ ሶበ ፡ አጥፋዕከ ፡ አማልክተ ። ወእምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ሞተለሚ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ።
፵ ፤ ወይቤሎ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ ዕቡየ ፡ ልብ ፡ ወእቡየ ፡ ሕሊና ፡ ከላዕከ ፡ ከመ ፡ ኢያምጽኦ ፡ ኀቤየ ፡ ለዝ ፡ ብእሲ ።
፵፩ ፤ ወይቤሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ እወ ፡ ከላዕኩ ፡ እስመ ፡ ርኢኩ ፡ መንክረ ፡ ወመድምመ ፡

፳ ፤ ከጣዖቱ ፡ ፊት ፡ በቆመች ፡ ጊዜ ፡ መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ ድንገት ፡ መጥቶ ፡ ሁላችን ፡ እያየን ፡ ነጥቆ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አወጣት ።
፳፩ ፤ ከድንጋጤው ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ፡ ንጉሡም ፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አእምሮውን ፡ አጥቶ ፡ ኖረ ።
፳፪ ፤ ከዚህ ፡ አእምሮ ፡ ማጣት ፡ ብታድነው ፡ ይተወን ፡ ይመስለኛል ።
፳፫ ፤ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ይገለናል ፡ አለው ።
፳፬ ፤ **ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም** ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ መከራ ፡ ትፈራለህን ፡ አለ።
፳፭ ፤ ፈጣሪያችን ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አይጥለንምና ፡ አትፍራ ።
፳፮ ፤ ይችንም ፡ ያልከኝን ፡ ሴት ፡ ነገር ፡ ኋላ ፡ እነግርሃለሁ ።
፳፯ ፤ **የእግዚአብሔር** ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ካየህ ፡ በኋላ ።
፳፰ ፤ ይህን ፡ እየተነጋገሩ ፡ ሲሄዱ ፡ ከንጉሡ ፡ ደረሱ ። መልክተኞቹ ፡ ለንጉሡ ፡ መጡ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።
፳፱ ፤ ወደኔ ፡ አምጧቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።
፴ ፤ አምጥተው ፡ ከፊቱ ፡ አቆሙዋቸው ።
፴፩ ፤ **ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን** ፡ ሀገራችንን ፡ የምታጠፋ ፡ አንተ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ሀገርህ ፡ ታዲት ፡ ነው ፡ አለው ።
፴፪ ፤ **ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም** ፡ አንተ ፡ ጕስቋላ ፡ አእምሮህን ፡ ያጣህ ፡ እኔን ፡ ሳታውቅ ፡ አገሬን ፡ ትጠይቀኛለህ ፡ አለው ።
፴፫ ፤ ሞተለሚም ፡ አገርህ ፡ ወዴትነው ፡ ወገንህስ ፡ ምንድነው ፡ አለው ።
፴፬ ፤ **ክቡር ። አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም** ፡ እኔስ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጣሁ ፡ **የክርስቶስ** ፡ ወገን ፡ ነኝ ፡ አለው ።
፴፭ ፤ እሱም ፡ ከዚህ ፡ ማን ፡ አደረሰህ ፡ አለው ።
፴፮ ፤ **ብፁዕ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** በሀገርህ ፡ ያሉ ፡ ጣዖትን ፡ ሁሉ ፡ ላጠፋ ፡ **ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ልኮኛል ፡ አለው ።
፴፯ ፤ ንጉሡም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተቆጣ ።
፴፰ ፤ የኔን ፡ ጣዖት ፡ የምታጠፋ ፡ አንተን ፡ ሊያመልኩ ፡ መጥተሃልን ።
፴፱ ፤ የኔን ፡ አማልክት ፡ ባጠፋህ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የእስለደኔ ፡ ልጅ ፡ አንተንም ፡ አጠፋሃለሁ ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሞተለሚ ፡ ወደ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ተመልሶ ።
፵ ፤ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ አንተ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ቸልተኛ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ እንዳያመጡት ፡ የከለከልክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አለው ።
፵፩ ። አባቶቼ ፡ ያላዩት ፡ በጁ ፡ የተደረገ ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ አይቻለሁና ፡ አዎን ፡

ዘይትገበር ፡ በእደዊሁ ፡ ዘኢርእዩ ፡ አበውየ ፡ ወይቤሎ ፡ ምንተ ፡ እንዘ ፡ ይገብር ፡ ርኢከ ።

፵፪ ፡ ወይቤ ፡ ርኢኩ ፡ እንዘ ፡ ያወፅእ ፡ አጋንንተ ፡ ወይፌውስ ፡ ድውያነ ፡ ወይገብር ፡ ኃይለ ፡ ብዙኃ ።

፵፫ ፡ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ከላዕኩ ፡ አንሰ ።

፵፬ ፡ እንዘ ፡ ዕብል ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ እመውት ፡ ምስሌሁ ፡ ወለእመ ፡ ሐይወ ፡ አሐዩ ፡ ምስሌሁ ።

፵፭ ፡ ዘፈቀድከ ፡ ግበር ፡ አ ፡ ንጉሥ ።

፵፮ ፡ ወተምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ እስኩ ፡ ለእመ ተሐዩ ፡ በሕይወተ ፡ ባዕድ ፡ እሬእየከ ።

፵፯ ፡ ወአዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ ፪ተ ፡ ቀፎዋተ ።

፵፰ ፡ ወይደይዎሙ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወይሕትሙ ፡ አፉሆሙ ፡ ለአንዳ ፡ ላህም ፡ ርጡብ ፡ ወይውርውዎሙ ፡ ውስተ ፡ ጸድፍ ዓቢይ ፡ ዘይሰመይ ፡ ጠመ ፡ ግራር ።

፵፱ ፡ ወገብሩ ፡ ከማሁ ።

፶ ፡ ወሶበ ፡ ወረውዎሙ ፡ ውስተ ፡ ጸድፍ ፡ ወረደ ፡ ኀቤሆሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወጾሮሙ ፡ በአክናፊሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጽሑ ፡ ምድረ ።

፶፩ ፡ ወአውፅኦሙ ፡ ውስተ ፡ መርኅብ ፡ ዘእንበለ ፡ ያርኁ ፡ አፈ ፡ ቀፎዋት ።

፶፪ ፡ ወወፅኡ ፡ ፍጡነ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወቆሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ እምቅድመ ፡ ይትመየጡ ፡ እለ ፡ ወረውዎሙ ።

፶፫ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለተሞለሚ ፡ ተሐፈር ፡ አ ፡ ዕልው ፡ ነዋ ፡ ንሕነ ፡ ዘአዘዝከ ፡ ይውርውነ ፡ ውስተ ፡ ጸድፍ ።

፶፬ ፡ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ አውፅአከ ፡ እምጸድፍ ፡ ወእም ፡ ድንብዕኩል ።

፶፭ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አምላኪየ ፡ ከሃሊ ፡ አውፅአነ ፡ እምጸድፍ ።

፶፮ ፡ ወእንዘ ፡ ይትናገር ፡ ዘንተ ፡ መጽኡ ፡ እሙንቱ ፡ እደው ፡ እለ ፡ ወረውዎሙ ።

፶፯ ፡ ወሶበ ፡ ርእይዎሙ ፡ ደንገፁ ፡ ጥቀ ።

፶፰ ፡ ወይቤሉ ፡ ሠናየ ፡ አምነ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ።

፶፱ ፡ ንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በአምላከ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ።

፷ ፡ ዘአድኃነ ፡ ርእሶ ፡ ወነፍሰ ፡ ካልኡ ፡ እምነ ፡ ሞተ ፡ ጸድፍ ።

፷፩ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት እሙኑ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምዝ ፡ ትሬእዩ ፡ ድኅረ ።

ዮሐ ፡ ምዕ ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፶፩ ።

፷፪ ፡ ወይቤ ፡ ሞተለሚ ፡ እሉ ፡ ሰብእ ፡ ተማከሩ ፡ በፍኖት ፡ ከመ ፡ ይሂጡኒ ።

ክልክያለሁ ፡ አለው ፡ ምን ፡ ሲያደርግ ፡ አየህ ፡ አለው ።

፵፪ ፡ ጋኔን ፡ ሲያወጣ ፡ ድውይ ፡ ሲፈውስ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ሲያደርግ ፡ አየሁ ።

፵፫ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ክልክያለሁ ።

፵፬ ፡ ቢሞትም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እሞታለሁ ፡ ቢድንም ፡ እንደሱ ፡ እድናለሁ ።

፵፭ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አሁንም ፡ የወደድኸውን ፡ አድርግ ፡ አለው ።

፵፮ ፡ ንጉሡም ፡ ተቆጥቶ ፡ እስኪ ፡ እሱ ፡ ሲያድንህ ፡ አይሃለሁ ፡ ብሎ ።

፵፯ ፡ ሁለት ፡ ቀፎ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፵፰ ፡ ሁለቱንም ፡ በሁለት ፡ ቀፎ ፡ አድርጋችሁ ፡ የቀፎውን ፡ አፍ ፡ ዘግታችሁ ፡ በርጥብ ፡ ቁርበት ፡ ጠቅላችሁ ፡ ጠመ ፡ ግራር ፡ ወደ ሚባል ፡ ወደታላቁ ፡ ገደል ፡ ስደዱዋቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፵፱ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ።

፶ ፡ ወደገደል ፡ በሰደዱዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዞ ፡ መጥቶ ከምድር ፡ ሳይደርሱ ፡ በክንፉ ፡ ተቀበላቸው ።

፶፩ ፡ የቀፎውን ፡ አፍ ፡ ሳይከፍት ፡ ከነቀፎው ፡ አውጥቶ ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ አኖራቸው ።

፶፪ ፡ ፈጥነው ፡ ወጥተው ፡ ገደል ፡ የሰደዱዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሳይመለሱ ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ሂደው ቆሙ ።

፶፫ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሞተለሚን ፡ አንተ ፡ ከሃዲ ፡ ገደል ፡ ያስጣልከን ፡ እኛ ፡ እነሆ ፡ መጣን ፡ እፈር ፡ አለው ።

፶፬ ፡ ከገደልስ ፡ ከቀፎስ ፡ ማን ፡ አወጣችሁ ፡ አለው ።

፶፭ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሁሉ ፡ የሚቻለው ፡ ፈጣሪዬ ፡ ከገደል ፡ አወጣን ፡ አለው ።

፶፮ ፡ ይህን ፡ ሲነጋገሩ ፡ ገደል ፡ የሰደዱዋቸው ፡ ሰዎች ፡ መጡ ።

፶፯ ፡ ባይዋቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደነገጡ ።

፶፰ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ በውነት ፡ አምኑዋል ።

፶፱ ፡ እኛም ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ፈጣሪ ፡ አምነናል ።

፷ ፡ ከገደል ፡ ሞት ፡ ራሱንም ፡ ሌላውንም ፡ ያዳነ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ፈጣሪ ፡ አምነናል ፡ አሉ ።

፷፩ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ፈጽማችሁ ፡ እመኑ ፡ ኋላም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ታያላችሁ ፡ አላቸው ።

ዮሐ ፡ አንደኛ ፡ ምራፍ ፡ ቍ ፡ ፶፩ ።

፷፪ ፡ ሞተለሚም ፡ እሊህ ፡ ሰዎች ፡ ሊያታልሉኝ ፡ በጐዳና ፡ ተማክረውብኛል ።

፶፫ ፤ ወዘእንበለ ፡ ይውርውዎሙ ፡ መጽኡ ፡ ኀቤየ
ወአዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ እሎንተ ፡ ድንብዕኩ ፡
ላተ ፡ ዘወደይዎሙ ፡ በሙ ።

፶፬ ፤ ወተረክቡ ፡ እንዘ ፡ ኀቱም ፡ አፉሆሙ ፡
በከመ ፡ ቀዳሚ ።

፶፭ ፤ ወይቤ ፡ ሞተለሚ ፡ አምጽኡ ፡ ካልእተኒ ፡
፲ተ ፡ ድንኩዕላተ ።

፶፮ ፤ ወደዩ ፡ ኪያሆሙ ፡ ውስቴቶሙ ፡ እለ ፡ አጽ
ርው ፡ ገቢረ ፡ ትእዛዝየ ።

፶፯ ፤ ለውእቱሂ ፡ ብእሲ ፡ መሠርይ ።

፶፰ ፤ ወለቀፈረ ፡ ውድምሂ ፡ ደይዎሙ ፡ በከመ ፡
ቀዳሚ ፡ ወውርዎሙ ፡ ውስተ ፡ ጠመ ፡
ግራር ።

፶፱ ፤ ወከመዝ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለምእመናኒሁ ።

፷ ፤ ወይቤልዎ ፡ አሆ ።

፷፩ ፤ ወመጽኡ ፡ ምእመናነ ፡ ንጉሥ ፡ እምቅድ
ሜሁ ፡ ወአጸሩ ፡ ፲ተ ፡ ድንብዕኩላተ ፡
ወደይዎሙ ፡ ለዐሠርቱሆሙ ፡ ወአልያነ ፡
ንጉሥ ፡ እለ ፡ ይቤሎሙ ፡ አጽርው ፡ ገቢረ
ትእዛዝየ ።

፷፪ ፤ ለአቡነሂ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ወለገብረ ፡ ዋሕድሂ ፡ ወደይዎሙ ፡ ኀበ ፡
ዘቀዳሚ ።

፷፫ ፤ ወወደይዎሙ ፡ ይውርውዎሙ ፡ ውስተ ፡
ጸድፍ ።

፷፬ ፤ ወተለውዎሙ ፡ ተአይነ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙኃን ፡
ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ዘይከውን ።

፷፭ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ጸድፍ ፡
ወረውዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ቅድመ ።

፷፮ ፤ ወለመኰንን ፡ ዳግመ ።
ወለአሠርቱሆሙ ፡ ድኅረ ።
አሚሃ ፡ ወረደ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ከመ
ቀዳሚ ፡ ወጾሮሙ ፡ በክነፊሁ ፡ ወአውዕ
አሙ ፡ ውስተ ፡ መርኅብ ።

፷፯ ፤ ወካዕበ ፡ አውዕአሙ ፡ እምድንብዕኩል ።

፷፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ሑር ፡ እስተሐፍሮ ፡ ለዝኩ ፡
ረሲዕ ፡ እስከ ፡ የአምን ፡ በአምላክከ ።

፷፱ ፤ ወአሙንቱሰ ፡ ዕደው ፡ ዘወረውዎሙ ፡
ውስተ ፡ ጸድፍ ፡ መሰሎሙ ።

፸ ፤ ወአርአዩ ፡ ከመ ፡ መሰጠሙ ፡ መልአከ ፡
እግዚአብሔር ።

፸፩ ፤ ወኍልቍሙ ፡ እሙንቱ ፡ ለምእመናነ ፡
ንጉሥ ፡ ፰ወ፬ ።

፸፪ ፤ ወቆመ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አንጻረ ፡ ዴዴሁ ፡ ለንጉሥ ፡ እንዘ ፡ የአኵቶ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡
ተአምረ ።

፸፫ ፤ እልክቱኒ ፡ ሰብእ ፡ እሊአሁ ፡ አኃዙ ፡ ይስ
ግዱ ፡ ቅድሜሁ ።

፶፫ ፤ ገደል ፡ ጣሉ ፡ ያልኳቸውን ፡ ሳይጥሉ ፡
ወደኔ ፡ መጥተዋል ። በውስጣቸው ፡ አድ
ርገው ፡ የጣሉባቸውን ፡ ቀፎዎች ፡ አምጡ
ብሎ ፡ አዘዘ ።

፶፬ ፤ አፉ ፡ ቸው ፡ ቀድሞ ፡ እንደተዘጋ ፡ ተገኙ ።

፶፭ ፤ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ዐሥር ፡ ቀፎ ፡ አምጡ ፡ ብሎ
አዘዘ ።

፶፮ ፤ ትእዛዜን ፡ ያፈረሱ ፡ እነዚያንም ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ጨምሯቸው ።

፶፯ ፤ ያን ፡ መድኃኒተኛም ።

፶፰ ፤ ቀፈረ ፡ ውድምን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ በቀፎ ፡
አድርጋችሁ ፡ ወደገደል ፡ ጣሏቸው ።

፶፱ ፤ የታመኑ ፡ አሽከሮችን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ።

፷ ፤ እሺ ፡ በጀ ፡ አሉት ።

፷፩ ፤ እነሆም ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የታመኑ ፡
አሽከሮቹ ፡ ወጥተው ፡ ዐሥር ፡ ቀፎ ፡ አሽ
ከመው ፡ ንጉሡ ፡ ትእዛዜን ፡ አፈረሱ ፡ ያላ
ቸውን ፡ ዐሥሩ ፡ ሎሌዎችን ፡ በዐሥሩ ፡
ቀፎ ፡ ጨምረው ።

፷፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ገብረ ፡ ዋሕድንም ፡
በቀድሞው ፡ ቀፎዋቸው ፡ ጨምረው ።

፷፫ ፤ ወደገደል ፡ ሊጥሏቸው ፡ ሲወስዷቸው ።

፷፬ ፤ የሚደረገውን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ የን
ጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ ተከተሏቸው ።

፷፭ ፤ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ
ጣሉት ።
ክቡር ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡

፷፮ ፤ ቀጥሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድን ።
ከሱም ፡ በኋላ ፡ ዐሥሩን ፡ ጣሏቸው ።
ያንጊዜም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወርዶ ፡
እንደቀድሞ ፡ በክንፉ ፡ ተቀብሎ ፡ ከሜዳ ፡
አውጥቶ ፡ ጣላቸው ።

፷፯ ፤ ዳግመኛም ፡ ከቀፎ ፡ አወጣቸው ።

፷፰ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
በፈጣሪህ ፡ እስኪያምን ፡ ድረስ ፡ ሂደህ ፡
ይኽን ፡ ከሃዲ ፡ አሳፍረው ፡ አለው ።

፷፱ ፤ እሊህም ፡ ገደል ፡ የሰደዷቸው ፡ ሰዎች ፡
የወደቁ ፡ መሰላቸው ፡ እንጂ ።

፸ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንዳወጣቸው ፡
ዐላወቁም ።

፸፩ ፤ እነዚህም ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የታመኑ ፡
ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ ነው ።

፸፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
በንጉሡ ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡
ተአምር ፡ ያደረገልኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ አመሰገነ ።

፸፫ ፤ እሊህም ፡ የንጉሡ ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡
ሰዎች ፡ ከፊቱ ፡ ወድቀው ፡ ሰገዱ ።

፹፬ ፤ ወይቤሉ ፡ ነአምን ፡ በአምላክከ ፡ አ ፡
አቡነ ፡ ቅዱስ ።

፹፭ ፤ ለእመ ፡ አንተኑ ፡ አምላክ ፡ ንግረነ ፡ ጥዩቀ ።

፹፮ ፤ ወእመ ፡ አኮ ፡ ሰብእ ፡ መሐረነ ፡ ጽድቀ ።

፹፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ አንሰ ፡ ኢኮንኩ ፡ አምላክ ፡ አላ ፡
ገብረ ፡ አምላክ ፡ አነ ።

፹፰ ፤ አምላክሰ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፹፱ ፤ በሥላሴሁ ፡ ዘይሁብ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓ
ለም ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ።

፺ ፤ ወይቤልዎ ፡ ንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በስሙ ፡ ከመ ፡
ንሕየው ፡ ለዓለም ።

፺፩ ፤ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይተል
ውዎ ፡ ማኅበራኒሁ ።

፺፪ ፤ ወይቤሎ ፡ ተኃፈር ፡ አ ፡ ረሲዕ ፡ እስመ ፡ ናሁ
መጻእኩ ፡ በኃይለ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ አስተኃፍርከ ።

፺፫ ፤ ወደንገፀ ፡ ንጉሥ ፡ ወኃጥአ ፡ ዘይነብብ ፤

፺፬ ፤ ወመጽኡ ፡ ፪ወ፬ እደው ፡ ወአልያኒሁ
ለንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ቀዳሚሰ ፡ ዘኢ
ወረውዎሙ ፡ መሰለነ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡
ንጉሥ ።

፺፭ ፤ ንሕነ ፡ ንቤ ፡ እስመ ፡ መኰንን ፡ ተሀብ
የሙ ፡ በብዙህ ፡ ንዋይ

፺፮ ፤ ወይእዜሰ ፡ ወረውናሆሙ ፡ ንሕነ ፡ ለእሙ
ንቱ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡
ዘአስሐቶሙ ።

፺፯ ፤ ወእንዘ ፡ ይትበሀሉ ፡ ዘንተ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡
ዴዴ ፡ ንጉሥ ።

፺፰ ፤ ወረከቡ ፡ ህየ ፡ ፪ተወ፪ተ ፡ ድንብዕኩላተ ፡
ሕቱማት ፡ አፉሆሙ ፡ በከመ ፡ ቀዳሚ ።

፺፱ ፤ ወደንገፁ ፡ ወቦኡ ፡ ፍጡነ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።

፻ ፤ ወረከብዎሙ ፡ ለ፪ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ እደው ፡
እንዘ ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ።

፻፩ ፤ ወ፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ማር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ኮነ ፡ ይዛለፎ ፡ ለንጉሥ ፡ በእንተ ፡ እከዩ ።

፻፪ ፤ ወቆሙ ፡ እሙንቱ ፡ ወዓልያኒሁ ፡ እንዘ ፡
መንክራነ ፡ ጥቀ ።

፻፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አንትሙኑ ፡ ኀበርክሙ ፡
ምስለ ፡ እሉ ፡ ሐሳውያን ።

፻፬ ፤ ለምንት ፡ ኢወረውክምዎሙ ፡ ውስተ ፡
ጸድፍ ።

፻፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ምእመናኒሁ ፡ አ ፡
ንጉሥ ፡ ወረውናሆሙ ፡ ፍጡነ ፡ በከመ ፡
አዘዝከነ ።

፻፮ ፤ ወኢሐሰውናከ ፡ ተስእሎሙ ፡ ለሠራዊትከ ።

፹፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ በአምላክህ ፡
እናምናለን ።

፹፭ ፤ አንተ ፡ አምላክ ፡ እንደሆንክ ፡ አስረድተህ ፡
ንገረን ።

፹፮ ፤ ሰውም ፡ እንደሆንክ ፡ የምንጸድቅበትን ፡
አስተምረን ፡ አሉት ።

፹፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
እኔስ ፡ አምላክ ፡ አይደለሁም ፡ የአምላክ ፡
ባሪያ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።

፹፰ ፤ አምላክስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

፹፱ ፤ በሦስትነቱ ፡ ለሚያምኑበት ፡ የዘለዓለም ፡
ሕይወት ፡ የሚሰጥ ።

፺ ፤ እንኪያስ ፡ እኛም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡
እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ በስሙ ፡ አምነናል ፡ አሉ ።

፺፩ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖትም ፡ ወገኖቹን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ
ንጉሡ ፡ ገባ ።

፺፪ ፤ አንተ ፡ ከሃዲ ፡ እፈር ።
በጌታዬ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃይል ፡
ላሳፍርህ ፡ መጥቻለሁና ፡ አለው ።

፺፫ ፤ ንጉሡም ፡ ደንግጦ ፡ የሚናገረውን ፡ አጣ ።

፺፬ ፤ እነዚያም ፡ ሃያ ፡ አራቱ ፡ ሎሌዎች ፡ መጥ
ተው ፡ ቀድሞስ ፡ ንጉሥ ፡ እንድተናገረ ፡
ገደል ፡ ያልጣሏቸው ፡ መስሎን ፡ ነበረ ።

፺፭ ፤ እኛም ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡
ሰጥቶ ፡ ዋጅቷቸዋል ፡ ብለን ፡ ነበር ፡ አሉ ።

፺፮ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ እኛ ፡ እኝህን ፡ ክፉ ፡ አድራጊ
ዎች ፡ ብለን ፡ ካሳታቸው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡
ጣልናቸው ።

፺፯ ፤ ይህን ፡ እየተባባሉ ፡ ከንጉሡ ፡ ደጅ ፡ ደረሱ ።

፺፰ ፤ አፋቸው ፡ እንደቀድሞ ፡ ተዘግቶ ፡ ዐሥራ ፡
ሁለት ፡ ቀፎዎች ፡ አገኙ ።

፺፱ ፤ ደንግጠው ፡ ወደንጉሡ ፡ ገቡ ።

፻ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡
ቁመው ፡ አገኙዋቸው ።

፻፩ ፤ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ብፁዕ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ንጉሡን ፡ ስለ ፡ ክፋቱ ፡ ይዘልፈው ፡ ነበር ።

፻፪ ፤ እኒህም ፡ ሌሎቹ ፡ እጅግ ፡ እያደነቁ ፡ ቆሙ ።

፻፫ ፤ እላንተም ፡ ከሊህ ፡ ከሐሰተኞች ፡ ጋራ ፡
አንድ ፡ ሆናችሁን ።

፻፬ ፤ ገደል ፡ ለምን ፡ አልጣላችኋቸውም ፡ አላ
ቸው ።

፻፭ ፤ እኒህም ፡ የታመኑት ፡ አሽከሮቹ ፡ ንጉሥ ፡
ሆይ ፡ እኛስ ፡ አንተ ፡ እንዳዘዝከን ፡ ፈጥነን
ጣልናቸው ።

፻፮ ፤ ሐሰትም ፡ እንዳልተናገርህ ፡ ሠራዊትህን ፡
ጠይቃቸው ።

፻፯ ፤ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብአ ፡ ዓይነ ፡ ሀለዉ ፡ ምስሌነ ፡ ዘርእዩ ፡ እንዘ ፡ ንዌርዎሙ ፡ ባሕቱ ፡ ይእዜ ፡ ርኢነ ፡ መንክረ ።
፻፰ ፤ ናሁ ፡ ድንብዕኩላት ፡ ንቡራት ፡ ውስተ ፡ ዶዶከ ፡ ወኅቱማን ፡ አፉሆሙ ፡ በከመ ፡ ቀዳሚ ።

፻፱ ፤ ወእደውኒ ፡ እለ ፡ ወረውናሆሙ ፡ ወደይነ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ነዮሙ ፡ ቅድሜከ ፡ ይቀውሙ ።
፻፲ ፤ ምንተ ፡ ትብል ፡ አ ፡ ንጉሥ ።
፻፲፩ ፤ መኑ ፡ አድኃኖሙ ፡ ለእሉ ፡ ዘእንበለ ፡ አምላኩ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ እንግዳ ።

፻፲፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ ንሕነ ፡ አመነ ፡ በአምላኩ ፡ ዘያድኅን ፡ እምቀትል ።
፻፲፫ ፤ ወኢንሰግድ ፡ ለአማልክቲከ ፡ ርኩሳን ።

፻፲፬ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አ ፡ ደቂቅየ ፡ እመኑ ፡ ቦቱ ፡ ፈድፋደ ።
፻፲፭ ፤ አኮ ፡ ዘያድኅን ፡ እምቀትለዝ ፡ ዓለም ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ እምሲኦልኒ ፡ ያድኅን ።

፻፲፮ ፤ ወጸርሑ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይቤሉ ፡ አመነ ፡ በአምላክከ ፡ ቅዱስ ።
፻፲፯ ፤ ወተምዓ ፡ ንጉሥ ፡ ላዕለ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወፀረፈ ፡ ላዕሌሁ ፡ ብዙኃ ።
፻፲፰ ፤ ወይቤሎ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ዘሰደዱከ ፡ እምሀገርከ ፡ ይመስለከኑ ፡ ትንግሥ ፡ ዝየ ።

፻፲፱ ፤ ወነሥአ ፡ ኵናተ ፡ በእዴሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ይርግዞ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወተአፅፈ ፡ ኵናት ፡ ወተጠብለለ ፡ ውስተ እዴሁ ።
፻፳ ወረግዓ ፡ ከመ ፡ ሰምዕ ።

፻፳፩ ፤ ወርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ ጉቡአን ፡ ከልሑ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አመነ ፡ በአምላከ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይክል ፡ አድኅኖ ።
፻፳፪ ፤ ወአዘዞሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለሐራሁ ፡ ይርግዝዎሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ጉቡአን ።
፻፳፫ ፤ ወወፅኡ ፡ ሐራ ፡ ወረገዝዎሙ ፡ ቅድሜሁ ።

፻፳፬ ፤ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ፫፻ ፡ ወ፵፻ ፡ ወ፹ ፡ ነፍስ ።

፻፳፭ ፤ ወውኅዘ ፡ ደም ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ በማልበረዶ ።
፻፳፮ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ቅቱላን ፡ በእንተ ክርስቶስ ፡ ነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ ዘኢይማስን ።
፻፳፯ ፤ በረከቶሙ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ።
፻፳፰ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፻፯ ፤ ስንጥላቸው ፡ ያዩ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ጕብኝዎች ፡ ነበሩና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ አየን ።
፻፰ ፤ እነሆ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ቀፎች ፡ እንደቀድሞ ፡ አፋቸው ፡ እንደተዘጋ ፡ ከደጅህ ፡ ላይ ፡ አሉ ።

፻፱ ፤ በውስጣቸውም ፡ ጨምረን ፡ የጣልናቸው ፡ ሰዎች ፡ እነሆ ፡ ከፊትህ ፡ ቆመዋል ።
፻፲ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ትላለህ ።
፻፲፩ ፤ የዚህ ፡ የእንግዳ ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ቢያድናቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ አዳናቸው ።
፻፲፪ ፤ እኛም ፡ ዛሬ ፡ ከሞት ፡ በሚያድን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ አምነናል ።
፻፲፫ ፤ ርኩሳን ፡ ለሚሆኑ ፡ ላንተ ፡ አማልክት ፡ አንሰግድም ፡ አሉት ።
፻፲፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልጆቼ ፡ ፈጽማችሁ ፡ እመኑበት ።

፻፲፭ ፤ የሚያድነው ፡ ከሞተ ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ከሞተ ፡ ነፍስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
፻፲፮ ፤ ክቡር ፡ ሆይ ፡ ሁላችንም ፡ ባንተ ፡ አምላክ ፡ አምነናል ፡ ብለው ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ።
፻፲፯ ፤ ንጉሡም ፡ በክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ተቆጥቶ ፡ ብዙ ፡ ተናገረ ።

፻፲፰ ፤ አንት ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ከሀገርህ ፡ አስወጥተው የሰደዱህ ፡ ከዚህ ፡ ትነግሥ ፡ መስሎሃልን ፡ አለው ።
፻፲፱ ፤ ጦር ፡ በጁ ፡ አንሥቶ ፡ ክቡር ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሊወጋው ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ ጦሩ ፡ ተመልሶ ፡ በጁ ፡ ላይ ፡ ተጠመጠመ ።
፻፳ ፤ እንደሰም ፡ ከላዩ ፡ ተጣበቀ ።

፻፳፩ ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ ማዳን ፡ በሚቻለው ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ አምላክ አምነናል ፡ እያሉ ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ።
፻፳፪ ፤ ንጉሡም ፡ ጭፍሮቹን ፡ እሊህ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ሁሉ ፡ ውጉዋቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።
፻፳፫ ፤ ጭፍሮቹም ፡ ወጥተው ፡ ከፊቱ ፡ ወግተው ፡ ገደሏቸው ።
፻፳፬ ፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ሦስት ፡ እልፍ ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ ሰማንያ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።
፻፳፭ ፤ በከተማው ፡ ደማቸው ፡ እንደውኃ ፡ ፈሰሰ ።
፻፳፮ ፤ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ እሊህም ፡ ቅዱሳን ፡ የማያልፍ ፡ ክብር ፡ ተቀበሉ ።
፻፳፯ ፤ በረከታቸው ፡ ከሁላችን ፡ ይደረግ ።
፻፳፰ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።

፻፷፱ ፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ይእስርዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እደዊሁ ወእገሪሁ ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድሂ ።

፻፸ ፤ እስከ ፡ ይመክር ፡ በዘይቀትሎሙ ።

፻፸፩ ፤ ወገብሩ ፡ ሳዕሌሆሙ ፡ ከመዝ ።

፻፸፪ ፤ ወጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አስተርአዮ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፸፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ኢትፍራህ ፡ አ ፡ ፍቁርየ ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት ።

፻፸፬ ፤ ናሁ ፡ ታገብእ ፤ ብዙኃነ ፡ ነፍሳተ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽናዕ ፡ ወኑይል ።

፻፸፭ ፤ እስመ ፡ ተውህበ ፡ ለከ ፡ ሥልጣነ ፡ መዊእ።

፻፸፮ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ፈትሆ እማእሰሩ ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድሂ ።

፻፸፯ ፤ ወጸቢሖ ፡ ለአከ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ከመ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፸፰ ፤ ወረከብዎ ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ቀዊሞ ፡ ወይበርህ ።

፻፸፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ ላዕካነ ፡ ነዓ ፡ ይጼውዓከ ፡ ንጉሥ ።

፻፹ ፤ ወወፅአ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ።

፻፹፩ ፤ ወቆመ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ።
ወይቤሎሙ ፡ንጉሥ ፡ ለላዕካኒሁ ፡ መኑ ፡ ፈትሆሙ ፡ እማእሰሪሆሙ ።

፻፹፪ ፤ ወይቤልዎ ፡ እንዳኢ ፡ ኢነአምር ፡ ባሕቱ ፡ ረከብናሁ ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ቀዊሞ ።

፻፹፫ ፤ ወፍቱሐት ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ እማእሰር ፡ ወገብረ ፡ ዋሕድሂ ፡ ምስሌሁ ።

፻፹፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ መኑ ፡ ፈትሐከ ።

፻፹፭ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡አ ፡ ኅርቱም ፡ ዘኢምስጠ ፡ ልቡ ፡ እስከ ማዕዜኑ ፡ ትሴእለኒ ፡ ኃይለ ፡ እምላኪየ ።

፻፹፮ ፤ ትማልም ፡ መኑ ፡ አድኃነኒ ፡ እምእዴከ ።

፻፹፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ትማልምሰ ፡ ድኅንከ በሥራይከ ።

፻፹፰ ፤ ወነሥአ ፡ ኩናተ ፡ በጼጋመ ፡ እዴሁ ፡ ወየማነ ፡ እዴሁሰ ፡ ጥብልልት ፡ ይእቲ ፡ በኵናት ፡ ዘትማልም ።

፻፹፱ ፤ ወፈቀደ ፡ ይርግዞ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡ ወሶቤሃ ፡ ጠግዓት ፡ ኩናት ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

፻፺ ፤ ወየብሰ ፡ መዝራዕቱ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ እብን።

፻፷፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ክቡር ፡ አባታችንን እጁንም ፡ እግሩንም ፡ አስራችሁ ፡ ገብረ ዋሕድንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ በእስር ፡ ቤት አቆዩዋቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፻፸ ፤ የሚገልበትን ፡ ምክንያት ፡ እስኪ ፡ መክር፡ ድረስ ።

፻፸፩ ፤ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ።

፻፸፪ ፤ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ።

፻፸፫ ፡ ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አትፍራ ።

፻፸፬ ፤ ብዙዎቹን ፡ ሰዎች ፡ እነሆ ፡ ወደ ፡ አምልኮተ እግዚአብሔር ፡ ትመልሳቸዋለህ ፡ ጽና በርታ ፡ አለው ።

፻፸፭ ፤ ድል ፡ የምታደርግበት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶሃልና ።

፻፸፮ ፤ ይህን ፡ ብሎ ፡ እሱንም ፡ ገብረ ፡ ዋሕድንም፡ ከስራታቸው ፡ ፈታቸው ።

፻፸፯ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ተክለ ፡ ሃይማኖትን አምጡት ፡ ብሎ ፡ ወደእስር ፡ ቤት ፡ ላከ ።

፻፸፰ ፤ ሬቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እያበራ ፡ ቁሞ ፡ ሲጸልይ ፡ አገኙት ፡

፻፸፱ ፤ መልእክተኞቹም ፡ ንጉሥ ፡ ይጠራሃል ፡ አሉት ።

፻፹ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡ ከልጁ ፡ ከገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ጋራ ፡ ሂዶ ።

፻፹፩ ፤ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ ቆመ ።
ንጉሥም ፡ መልክተኞቹን ፡ ከእስራታቸው ማን ፡ ፈታቸው ፡ አላቸው ።

፻፹፪ ፤ ቁሞ ፡ ሲጸልይ ፡ አገኘነው ፡ እንጂ ፡ የፈታቸውን ፡ አናውቅም ፡ አሉት ።

፻፹፫ ፤ እጆቹም ፡ እግሮቹም ፡ ተፈተው ፡ ገብረ ፡ዋሕድም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሁኖ ፡ አገኘነው ፡ አሉት።

፻፹፬ ፤ ማን ፡ ፈታህ ፡ አለው ።

፻፹፭ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ አእምሮህን ፡ ያጣህ ፡ አንተ ፡ ጐስቋላ ፡ የፈጣሪዬን ፡ ኃይል ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ፡ ትጠይቀኛለህ ፡ አለው ።

፻፹፮ ፤ ትላንት ፡ ከእጅህ ፡ ያዳነኝ ፡ ማነው ።

፻፹፯ ፤ ትላንትስ ፡ በመድኃኒትህ ፡ ዳንክ ፡ ብሎ ።

፻፹፰ ፤ በግራ ፡ እጁ ፡ ጦሩን ፡ አነሣ ።
ቀኝ ፡ እጁ ፡ ግን ፡ ትላንት ፡ በያዛት ፡ ጦር ፡ ተጠቅልላለችና ።

፻፹፱ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን፡ ሊወጋ ፡ ወዶ ፡ ጦሩ ፡ ከእጁ ፡ ጋር፡ተጣበቀች።

፻፺ ፤ ክንዱ ፡ ሰለለ ፡ ደረቀ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ሆነ ።

፻፶፩ ፤ ወአውየወ ፡ ወይቤ ፡ ዝንቱ ፡ መሰርይ ፡ እምአይቴ ፡ መጽአ ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ኪያየ ፡ ወይንሣእ ፡ መንግሥትየ ፡ ወያማስን ፡ ሀገርየ ።

፻፶፪ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ እቅትልከ ፡ ዘመጻእኩ ።

፻፶፫ ፤ አላ ፡ ከመ ፡ አኀዩከ ፡ ሀገረከሂ ፡ እሕንጽ ፡ በሃይማኖት ።

፻፶፬ ፤ መንግሥትከ ፡ ይመስለኒ ፡ ከመ ፡ ጽንጕን ፡ መርህብ ፡ ዘይከይድዎ ፡ ከለባት ።

፻፶፭ ፤ ኅጽግሰ ፡ መንግሥተከ ፡ ጸበለ ፡ ምድርኒ ፡ እምበትከ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ለከ ።

፻፶፮ ፤ እመን ፡ በአምላኪየ ፡ ወየሐይወከ ፡ ወኢታአውዩ ።

፻፶፯ ፤ ወእመ ፡ አኮ ፡ በሎሙ ፡ ለአማልክቲከ ፡ ፈውሱኒ ፡ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ዓይኑ ፡ እምአማልክት ፡ ዘይፈውስ ፡ እምሕማም ።

፻፶፰ ፤ ወቆመ ፡ ሰይጣን ፡ እምርጉቅ ፡ ወከልሐ ፡ሎቱ ፡ ወይቤ ፡ አሞተለሚ ፡ እምከመ ፡ ቀተልኮ ፡ ለዝንቱ ፡ መሠርይ ፡ አነ ፡ እፌውሰከ ።

፻፶፱ ፤ ውእቱኒ ፡ አዘዘ ፡ ይቅትልዎ ።

፻፷ ፤ ወይቤልዎ ፡ ሐራሁ ፡ በምንት ፡ ይትቀተል ፡ ዝመሠርይ ።

፻፷፩ ፤ ኵናትኒ ፡ ኢይክሎ ፡ ወጸድፍ ፡ ኢይትሜጥዎ ።

፻፷፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ በሉኬ ፡ አመክሩኒ ፡ ወአስተፋጥኑ ፡ ሊተ ፡ ቀቲሎቶ ።

፻፷፫ ፤ እስመ ፡ ሐመምኩ ፡ ፈድፋደ ።

፻፷፬ ፤ ወይቤልዎ ፡ ይደዩ ፡ ሐብለ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡ ይሕንቅዎ ፡ ወይቅትልዎ ፡ ውስተ ፡ ያም ነዊሀ ፡ ወይሙት ፡ በህየ ።

፻፷፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ግበሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍጡነ ፡ በከመ ፡ ትቤሉኒ ።

፻፷፮ ፤ ወአውፅእዎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወወደዩ ፡ ሐብለ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡ ወሐነቅዎ ፡ ወወሰድዎ ፡ ይስቅልዎ ።

፻፷፯ ፤ ወተለውዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊተ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ሞቶ ።

፻፷፰ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ኀበ ፡ ያም ፡ አርገ ፡ ብእሲ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአሠረ ፡ ሐብለ ፡ ኀበ ፡ ያም ፡ ወአልዐሎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምድር ፡ መጠነ ፡ ፶ ፡ በእመት ፡ ወኅደጎ ፡ በህየ ፡ ይሙት ፡ በጻዕር ።

፻፷፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይወርድ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ እሳሬ ፡ ኃብል ወድቀ ፡ እምላዕለ ፡ ያም ፡ ወተቀጥቀጠ ፡ አዕፅምቲሁ ፡ ወሞተ ፡ በጊዜሃ ፡ እኩየ ፡ ሞተ ።

፻፶፩ ፤ እኔንም ፡ ገድሎ ፡ መንግሥቴን ፡ ይቀማኝ ዘንድ ፡ አገሬንም ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሟርተኛ ፡ ከየት ፡ መጣ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ።

፻፶፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እኔ ፡ የመጣሁ ፡ ልገልህ ፡ አይደለም ።

፻፶፫ ፤ አንተንም ፡ ላድን ፡ ሀገርህንም ፡ በሃይማኖት ፡ ላንጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፻፶፬ ፤ መንግሥትህም ፡ ውሾች ፡ እንደሚረግጡት ፡ እንደ ፡ ዐደባባይ ፡ ጭቃ ፡ ይመስለኛል ።

፻፶፭ ፤ መንግሥትህንስ ፡ ተውና ፡ ከቤትህ ፡ የምድር ፡ ትቢያ ፡ ስንኳ ፡ አልሻም ።

፻፶፮ ፤ አትጨክህ ፡ በፈጣሪህ ፡ እመን ፡ ያድንሃል ።

፻፶፯ ፤ ይኸም ፡ ባይሆን ፡ ያንተን ፡ አማልክት ፡ አድኑኝ ፡ በላቸው ፡ አለው ፡ ከአማልክት በሽታ ፡ የሚያድን ፡ የቱ ፡ ነው ፡ አለ ።

፻፶፰ ፤ ሰይጣንም ፡ ከሩቅ ፡ ቁሞ ፡ ሞተለሚን ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ብትገድለው ፡ እኔ ፡ አድንህ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

፻፶፱ ፤ እሱም ፡ ግደሉት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፻፷ ፤ ጭፍሮቹም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በምን ፡ ይሞታል ።

፻፷፩ ፤ ጦርም ፡ አይገለው ፡ ገደልም ፡ አይቀበለው ፡ አሉት ።

፻፷፪ ፤ ንጉሡም ፡ ፈጥኖ ፡ የሚሞትበትን ፡ በሉ ምከሩኝ ፡ አላቸው ።

፻፷፫ ፤ በጭንቅ ፡ ታምሜያለሁና ።

፻፷፬ ፤ ገመድ ፡ ካንገቱ ፡ አግብተው ፡ ከታላቅ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ አንቀው ፡ ይስቀሉት ፡ በዚያ ፡ ይሞታል ፡ አሉት ።

፻፷፭ ፤ እንደነገራችሁኝ ፡ ፈጥናችሁ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

፻፷፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አወጥተው ፡ ካንገቱ ፡ ገመድ ፡ አግብተው ፡ አንቀው ፡ ሊሰቅሉት ፡ ወሰዱት ።

፻፷፯ ፤ የንጉሡም ፡ ሠራዊት ፡ ሞቱን ፡ እናያለን ፡ ብለው ፡ ተከትለውት ፡ ሄዱ ።

፻፷፰ ፤ ከዛፉ ፡ ዘንድ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ በላዩ ፡ ገመድ አስሮ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከምድር ፡ ሃምሳ ፡ ክንድ ያህል ፡ ርቆ ፡ በዚያ ፡ ተጻዕሮ ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ ተወው ።

፻፷፱ ፤ ይህም ፡ ገመድ ፡ ያሰረው ፡ ሰው ፡ ሲወርድ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አጥንቱ ተሰባብሮ ፡ ክፉ ፡ ሞት ፡ ፈጥኖ ፡ ሞተ ።

፻፹ ፡ ያምሰ ፡ አጽንነ ፡ ርእሶ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ረድ ፡ እምላዕሌየ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ።

፻፹፩ ፤ ወወረደ ፡ ወቆመ ፡ በእገሪሁ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፹፪ ፤ ወንብልኒ ፡ ወፅአ ፡ እምክሣዱ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈትሖ ፡ መኑሂ ።

፻፹፫ ፤ ወገብአ ፡ ያም ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ህላዌሁ ።

፻፹፬ ፤ ወርእዮሙ ፡ ጉቡአን ፡ ዘንተ ፡ ተአምረ ፡ ጸርሑ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አመነ ፡ በአምላከ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ያም ፡ ወኵናት ።

፻፹፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እመኑ ፡ ፈድፋደ ፡ እ ምዝ ፡ ዘየዓቢ ፡ ትሬእዩ ፡ ድኅረ ።

፻፹፮ ፤ ወይቤሉ ፡ ኵሎሙ ፡ አመነ ፡ በዘከመዝ አምላክ ፡ ዘይክል ፡ ኵሎ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይ ሰዐኖ ።

፻፹፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አንሥኡ ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ከመ ፡ ትርአዩ ፡ ዘእቤለክሙ ፡ እምዝ ፡ ዘየዓቢ ፡ ትሬእዩ ።

፻፹፰ ፤ ወአንሥኡ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወርእዩ ፡ መላ እክተ ፡ ብርሃን ፡ ጾዊሮሙ ፡ አክሊላተ ፡ ብሩሃተ ።

፻፹፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ ምንትኑዝ ፡ አ ፡ አቡነ ።

፻፺ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ናሁ ፡ ይኤዝዝ ፡ ንጉሥ ፡ ይቅትሉክሙ ፡ ወመላእክት ፡ ይጸንሑ ፡ ለከልሎ ፡ ነፍሳቲክሙ ፡ በአክሊላተ ፡ ብር ሃን ።

፻፺፩ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ዘንተ ፡ እሉ ፡ ጉቡአን ፡ ሰብእ ፡ ተፈሥሐ ፡ ጥቀ ፡ ወጸንዑ ፡ በአሚነ ፡ ክር ስቶስ ።

፻፺፪ ፤ ወነገርዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ወይቤልዎ ፡ ዕፅኒ ፡ ኢክህሎ ፡ ለውእቱ ፡ መሠርይ ።

፻፺፫ ፤ ለአሣሬ ፡ ሐብልኒ ፡ እንዘ ፡ ይወርድ ፡ ወጸፎ ያም ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወተቀጥቀጠ ፡ ወሞተ ።

፻፺፬ ፤ ወኵሎሙ ፡ ሠራዊትከ ፡ አምኑ ፡ በአምላኩ ለዝንቱ ፡ መሠርይ ።

፻፺፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ ማርያን ፡ ለንጉሥ ፡ አዝዝ ፡ ይቅትሉ ፡ ሰብአ ፡ ዘአምኑ ፡ በአምላኩ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ ንመክር ፡ በዘን ቀትሎ ፡ ኪያሁ ።

፻፺፮ ፤ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ይቅትሉ ፡ ኵሎ ፡ እደ ፡ ወአንስተ ፡ ዘአምኑ ።

፻፹ ፤ ዛፉ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ከላዬ ፡ ውረድልኝ ፡ እንደሚል ፡ ራሱን ፡ ወደምድር ፡ አዘነበለ ።

፻፹፩ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ወርዶ ፡ በእግሩ ፡ ቆመ ።

፻፹፪ ፤ ገመዱም ፡ ማንም ፡ ሳይፈታው ፡ ካንገቱ ፡ ወጣ ።

፻፹፫ ፤ ዛፉም ፡ ተመልሶ ፡ ቀድሞ ፡ እንደነበረ ፡ ሆነ

፻፹፬ ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ተአምራት አይተው ፡ ጦርና ፡ ዛፍ ፡ ለሚታዘዙለት ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አምላክ ፡ እምነናል፡ ብለው ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ።

፻፹፭ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡ ፈጽማችሁ ፡ እመኑ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ኋላ ታያላችሁ ።

፻፹፮ ፤ ሁሉም ፡ በሚቻለው ፡ የሚሳነው ፡ በሌለ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አምላክ ፡ እምነናል ፡ አሉ ።

፻፹፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ አቅንታችሁ ፡ ወደሰማይ ፡ ተመልከቱ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ኋላ ፡ ታያላችሁ ።

፻፹፰ ፤ አቅንተው ፡ ተመለከቱ ፡ መላእክት ፡ የብ ርሃን ፡ አክሊል ፡ ይዘው ፡ አዩዋቸው ።

፻፹፱ ፤ አባታችን ፡ ይህ ፡ የምናየው ፡ ምንድነው ፡ አሉት ።

፻፺ ፤ እነሆ ፡ ንጉሥ ፡ እናንተን ፡ ግደሏቸው ፡ ብሎ ፡ ያዛል ፡ መላእክትም ፡ በብርሃን ፡ አክ ሊል ፡ ነፍሳችሁን ፡ ለመጋረድ ፡ ይዘው ፡ ይጠብቃሉ ።

፻፺፩ ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ በሃይማኖትም፡ ጸኑ።

፻፺፪ ፤ ሂደው ፡ ንጉሡን ፡ ይህን ፡ ሰራየኛ ፡ ሰው ፡ ዕንጨትም ፡ አልቻለው ።

፻፺፫ ፤ ገመድ ፡ አሳሪውንም ፡ ሲወርድ ፡ ዛፍ ፡ ጣለው ፡ ተቀጥቅጦ ፡ ሞተ ።

፻፺፬ ፤ ሠራዊትህም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ አም ላክ ፡ አመኑ ።

፻፺፭ ፤ ጠንቋዮችም ፡ ንጉሡን ፡ እሱን ፡ የምንገ ልበት ፡ እስክንመክር ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ሰው አምላክ ፡ ያመነውን ፡ ሁሉ ፡ ግደሉ ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ፡ አሉት ።

፻፺፮ ፤ ንጉሡም ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ያመነ ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ሁሉ ፡ ግደሉ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፻፹፯ ፤ ወወፅኡ ፡ ሐራ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይጸውሩ ፡ አስይፍተ ፡ ምሉሐነ ፡ ወቀተሉ ፡ ኵሎ ።

፻፹፰ ፤ ወኮነ ፡ ኍልቈሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ በይ እቲ ፡ ዕለት ፡ ፲፼ ፡ ወ፹፻ ፡ ወ፭ወ፲ ፡ እደው ዘእንበለ ፡ አንስት ፡ ወደቅ ።

፻፹፱ ፤ ወፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ ፡ ለሰኔ ።

፻፺ ፤ ኃይለ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ይሱቀነ ፡ እምትን ታኔ ።

፻፺፩ ፤ ወያንጽሐነ ፡ እምግማኔ ።

፻፺፪ ፤ ለኵልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

፻፺፫ ፤ ወፈድፋደሰ ፡ ለሀገሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ።

፻፺፬ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

(ዘ ሐ ሙ ስ ፡) ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

፩ ፤ ወኮነ ፡ ክምረ ፡ ክምር ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ ትማልም ፡ ወዮም ።

፪ ፤ ወነገርዎ፡ ሰብኡ ፡ ለንጉሥ ፡ ወይቤልዎ ፡ ናሁ ፡ ኃልቁ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊትከ ፡ እንዘ ፡ ተኃሥሥ ፡ ፩ደ ፡ ብእሴ ።

፫ ፤ ምስለ ፡ መኑ ፡ ትትቃተል ፡ ሶበ ፡ ይትነ ሥኡ ፡ ላዕሌከ ፡ ፀር ።

፬ ፤ ውእቱሰ ፡ ርጉም ፡ ሞተለሚ ፡ ናሁ ፡ ሀሎ ፡ ይጼዓር ፡ በደዌ ።

፭ ፤ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ቅዱስ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ለሞተለሚ ።

፮ ፤ ለምንት ፡ ከመዝ ፡ ትጼዓር ፡ አ ፡ ንጉሥ ።

፯ ፤ እምኢፈወስከኑ ፡ ዝብእሲ ፡ ሶበ ፡ ተአምነ ፡ በአምላኩ ።

፰ ፤ ወይቤሉ ፡ እምነተሰ ፡ እምአመንኩ ።

፱ ፤ ባሕቱ ፡ እፈርሆ ፡ ከመ ፡ ኢይንሥአኒ ፡ መንግሥትየ ።

፲ ፤ ወይቤሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ኢሰማዕከኑ ፡ እንዘ ፡ ይብለከ ፡ ቅድመ ፡ ጸበለ ፡ ሣዕርኒ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እምቤትከ ።

፲፩ ፤ ኢትኅዝን ፡ በእንተዝሰ ፡ ነገር ፡ አነ ፡ እፌጽም ፡ ለከ ፡ ኀቤሁ ።

፲፪ ፤ ወይቤልዎ ፡ ማርያን ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድ ፡ አንተ ፡ አምጻእከ ፡ ላዕሌነ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ እኩየ ።

፲፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ከመዝሰ ፡ ኢይ ኩን ፡ ለንጉሥ ፡ ኢትክልዕዎ ፡ ተፈውሶ ።

፲፬ ፤ ለክሙሰ ፡ ናስተፋትነክሙ ፡ ምስሌሁ ።

፲፭ ፤ ለእመ ፡ አንትሙ ፡ ሞእክምዎ ፡ ንቀትል ፡ ኪያሁ ።

፲፮ ፤ ወእመ ፡ ውእቱ ፡ ሞአክሙ ፡ ንቀትል ፡ ኪያክሙ ።

፻፹፯ ፤ የንጉሡም ፡ ጭፍሮች ፡ ከንጉሡ ፡ ታዘው ሰይፍ ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዘው ፡ **በክርስቶስ ፡** ያመኑትን ፡ ሁሉ ፡ ገደሏቸው ።

፻፹፰ ፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ከልጅና ፡ ከሴት ፡ በቀር ፡ ቍጥራቸው ፡ ሰባት ፡ እልፍ ፡ ፹ሺህ ፡ ፭ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

፻፹፱ ፤ በሰኔ ፡ በ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሰማዕትነት ፡ ተቀበሉ ።

፻፺ ፤ የሃይማኖታቸው ፡ ጽናት ፡ ከመውደቅ ፡ ይደግፈን ።

፻፺፩ ፤ ከኃጢአት ፡ ያንጻን ።

፻፺፪ ፤ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ የሆን ፡ ሁላችንን ።

፻፺፫ ፤ ይልቁንም ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ።

፻፺፬ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።

(ዘ ሐ ሙ ስ ፡) ሠላሳ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ትላንትም ፡ ዛሬም ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ በድኖቻቸው ፡ እንደነዶ ፡ ክምር ፡ ሆነ ።

፪ ፤ ሰዎቹ ፡ ሂደው ፡ ለንጉሡ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስትሻ ፡ ሠራዊትህ ፡ ሁሉ ፡ አለቁ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

፫ ፤ ጠላቶች ፡ በተነሡብህ ፡ ጊዜ ፡ ከማን ፡ ጋራ ማንን ፡ ይዘህ ፡ ትዋጋለህ ።

፬ ፤ የተረገመ ፡ እሱ ፡ ሞተለሚ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ በደዌ ፡ ተይዞ ፡ ይጨነቅ ፡ ነበረ ።

፭ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ወደሱ ፡ ገብቶ ፡ ሞተለሚን ፡ አለው ።

፮ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ትጨነ ቃለህ ።

፯ ፤ በፈጣሪው ፡ ብታምን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ባላዳ ነህም ፡ ነበር ።

፰ ፤ ማመኑንስ ፡ ባመንኩ ፡ ነበር ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መንግሥቴን ፡ እንዳይወስድ ብኝ ፡ እፈራለሁ ፡ እንጂ ፡ አለው ።

፲ ፤ ገብረ ፡ ዋሕድም ፡ ቀድሞ ፡ ስንኳ ፡ ከቤትህ ፡ የሣር ፡ ትቢያ ፡ አልሻም ፡ ሲል ፡ አልሰማ ህምን ።

፲፩ ፤ ስለዚህስ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ እጨርስልሃለሁ ፡ አትፍራ ፡ አለው ።

፲፪ ፤ ማርያንም ፡ ገብረ ፡ ዋሕድን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያመጣብህን ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አሉት ።

፲፫ ፤ ገብረ ፡ ዋሕድም ፡ እንዲህስ ፡ አትበሉ ፡ አይሆንም ፡ ንጉሡን ፡ መዳን ፡ አትከልክ ሉት ።

፲፬ ፤ እናንተን ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እናፈታትና ችኋለን ።

፲፭ ፤ እናንተ ፡ ያቸነፋችሁት ፡ እንደሆነ ፡ እሱን ፡ እንገላለን ።

፲፮ ፤ እሱ ፡ ያቸነፋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እናንተን ፡ እንገላለን ፡ አላቸው ።

፲፯ ፤ ወአደሞ ፡ ዝነገር ፡ ለንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ሠናየ ፡ መክርክኒ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ።

፲፰ ፤ አምጽኦ ፡ ሊተ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ ይፈውሰኒ ።

፲፱ ፤ ወወፅአ ፡ ወረከቦ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ሃይማኖት እንዘ ፡ ይቀብር ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ መሃይምናን ።

፳ ፤ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ወዘከመ ፡ መከረ ፡ ለሊሁ ።

፳፩ ፤ ወአክሞሰሰ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይቤሎ ፡ ለገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ኮነ ሠናየ ፡ ምክርከ ፡ በነቢየ ፡ ከመ ፡ ምክረ ፡ ኩሲ ።

፳፪ ፤ ባሕቱ ፡ ለምንት ፡ አስተርአይኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ማርያን ።

፳፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ አኮ ፡ ዘአስተርአይክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ማርያን ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸሞሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ እቤ ፡ ዘንተ ።

፳፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ወሰዶ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአብአ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።

፳፭ ፤ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ሞተለሚ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይቤሎ ፡ አ ብእሲ ፡ ፈውሰኒ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ ንገብር ፡ ድኅረ ።

፳፮ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስኩ ፡ ቅድመ ፡ በሎሙ ፡ ለማርያኒከ ፡ ፈውሱኒ ።

፳፯ ፤ ወአመ ፡ ስእኑ ፡ ፈውሶተከ ፡ አነ ፡ እፌውሰከ ፡ በስመ ፡ አምላኪየ ።

፳፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለማርያን ፡ ለምንት ፡ ኢትፈውሱኒ ፡ አንትሙ ።

፳፱ ፤ እስመ ፡ አነ ፡ ሀሎኩ ፡ እትበአስ ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲአክሙ ፡ ዮም ።

፴ ፤ ለእመ ፡ ትፌውሱኒ ፡ ፈውሱኒ ፡ እመ ፡ አኮሰ እቀትለክሙ ።

፴፩ ፤ ወይቤልዎ ፡ ማርያን ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ አሕመመከ ፡ በሥራዩ ፡ በምንት ፡ ንክል ፡ ፈውሶተከ ።

፴፪ ፤ እስመ ፡ ኢየኀብር ፡ ሥራይ ፡ ምስለ ፡ ሥራይ ፡ ወኪን ፡ ምስለ ፡ ኪን ።

፴፫ ፤ ባሕቱ ፡ ሎቱሰ ፡ አብሐነ ፡ ንቅትሎ ።

፴፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ በምንትኑ ፡ ኢትክሉ ፡ ቀቲሎቶ ።

፴፭ ፤ ወባሕቱ ፡ ፈውሱ ፡ ንጉሠ ፡ በከመ ፡ ይቤለክሙ ።

፴፮ ፤ ወይቤሉ ፡ ማርያን ፡ ኢንክል ፡ ፈውሶቶ ፡ እስመ ፡ ሥራይክሙ ፡ ይጸንዓኒ ።

፲፯ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ቀፈረውድም ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ መከርከኝ ፡ አለው ።

፲፰ ፤ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈጥነህ ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ።

፲፱ ፤ ሒዶ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ከቀሩት ፡ ምእመናን ፡ ጋራ ፡ ዓፅመ ፡ ሰማዕታትን ፡ ሲያስቀብር ፡ አገኘው ።

፳ ፤ እኔም ፡ እንዲህ ፡ መከርኩ ፡ ንጉሡም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

፳፩ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ገብረ ፡ ዋሕድን ፡ ምክርህ ፡ እንደ ፡ ኩሲ ፡ ምክር ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ደግ ፡ ነው ።

፳፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማርያኖች ጋራ ፡ ለምን ፡ አስተካከልከው ።

፳፫ ፤ ገብረ ፡ ዋሕድም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማርያኖች ፡ ጋራ ፡ ያስተካከልኩት ፡ አይደለም ፡ ኃጢአታቸው ፡ ይፈጸምባቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ አልኩ ፡ እንጂ ።

፳፬ ፤ ይህን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ወስዶ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ አገባው ።

፳፭ ፤ ሞተለሚም ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ፡ ሃይማኖትን ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ አድነኝ ፡ ቀፈረ ፡ ውድም ፡ እንደነገረኝ ፡ ኋላ ፡ እናደርጋለን ፡ አለው ።

፳፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እስኪ ፡ ቀድሞ ፡ ማርያኖችህን ፡ አድኑኝ ፡ በላቸው ።

፳፯ ፤ አንተን ፡ ማዳን ፡ ቢሳናቸው ፡ እኔ ፡ በፈጣሪዬ ፡ ስም ፡ አድንሃለሁ ፡ አለው ።

፳፰ ፤ ንጉሡም ፡ ማርያንን ፡ እናንተ ፡ ለምን ፡ አታድኑኝም ፡ አላቸው ።

፳፱ ፤ እኔ ፡ ስለናንተ ፡ ዘወትር ፡ እጣላለሁና ።

፴ ፤ ብታድኑኝ ፡ አድኑኝ ፡ ባታድኑኝ ፡ እናንተን ፡ እገላችኋለሁ ፡ አላቸው ።

፴፩ ፤ ማርያንም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ መድኃኒት ፡ አድርጎብሃል ፡ እኛ ፡ በምን ፡ ማዳን ፡ ይቻለናል ።

፴፪ ፤ ያንዱ ፡ መድኃኒት ፡ ካንዱ ፡ መድኃኒት ፡ ያንዱ ፡ ብልሃት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አይደለምና ።

፴፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሱን ፡ እንግደለው ፡ አሰናብተን ፡ ፍቀድልን ።

፴፬ ፤ ገብረ ፡ ዋሕድም ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ልትገሉት ፡ አትችሉም ።

፴፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ አድኑኝ ፡ እንዳላችሁ አድኑት ፡ አላቸው ።

፴፮ ፤ ማርያንም ፡ መድኃኒታችሁ ፡ ከመድኃኒታችን ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ ማዳን ፡ አይቻለንም፡ አሉ።

፴፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ዝሰ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ውእቱ ፡
እምግብርክሙ ፡ ይትዓወቅ ፡ ደኃሪትክሙ ።

፴፰ ፤ አነ ፡ እሐይዎ ፡ በስመ ፡ አምላኪየ ፡ ናቅም ፡
ነገረ ፡ ማእከሌየ ፡ ወማእከሌክሙ ።
፴፱ ፤ ንጉሥ ፡ ይርግዝክሙ ፡ በኲናት ፡ ሰማየ ።

፵ ፤ ወለእመ ፡ ኢተክህሎ ፡ ረጊዝ ፡ ወአጠው
ቅሙ ፡ ኲናተ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

፵፩ ፤ አነ ፡ እፌውሶ ።
፵፪ ፤ ወለእመ ፡ ኢፈወስክዎ ፡ ይቀትል ፡ ኪያየ ።
፵፫ ፤ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ ርቱዕ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ከመዝ ፡
ይኩን ፡ ነዓ ፡ ፈውሰኒ ፡ ቅድመ ።

፵፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት
መሐል ፡ በአማልክቲከ ፡ ከመ ፡ ትግበር ፡
ዘንተ ።
፵፭ ፤ ወመሐለ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘንተ ፡ በከመ ፡
ይቤሎ ።
፵፮ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ አንተኒ ፡ ዑቅ ፡
ርእሰከ ፡ ለእመ ፡ ኢፈወስከኒ ፡ እቀትለከ ፡
ወኢይሄሱ ፡ ቃልየ ።
፵፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ቅትለኒ ፡ አንሰ ፡ ኢይምህር፡ ለርእስየ።

፵፰ ፤ ወገሠሦ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ በስመ ፡ እግዚእየ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘአነ ፡ እሰብከ ፡ በስሙ ፡
ሕያው ፡ እምደዌከ ።
፵፱ ፤ ወበጊዜሃ ፡ ሐይወ ፡ እምደዌሁ ።
፶ ፤ ወወድቀ ፡ ፀጕ ፡ ኵያንው ፡ እምደዌሁ ።

፶፩ ፤ ወዘየብሰኒ ፡ መዝራዕቱ ፡ ጥዕየ ፡ ፍጹመ ።
፶፪ ፤ ወሐይወ ፡ እምእንባዚሁ ።
፶፫ ፤ ወእምዝ ፡ ይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ አፍጥን ፡ ገቢረ ፡ ዘተአደምነ ፡
ቅድመ ።

፶፬ ፤ ወይቤ ፡ እሆ ።
፶፭ ፤ ወአዘዘ ፡ ሞተለሚ ፡ ከመ ፡ ይስሐሉ ፡ ኲናተ ፡
ዘወዓለት ፡ ጥብልልተ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

፶፮ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ኅድግ ፡ ዘንተ ፡ ወያምጽኡ ፡ ካልአ ፡
ከመ ፡ ኢያመክንዩ ፡ ማርያን ፤ ወኢይ
በሉ ፡ ገብረ ፡ ቦቱ ፡ ሥራየ ።

፶፯ ፤ ወአዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ ካልአ ።
፶፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለማርያን ፡ በሉኬ ፡ ተሐረዩ ፡
እለ ፡ ተአምሩ ፡ ኪነ ።
፶፱ ፤ ወጸውዑ ፡ ማርያን ፡ ስመ ፡ እምላኪሆሙ ፡ ወተ
ቃሰሙ ።

፴፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ይህስ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ከሥራ
ችሁ ፡ የተነሣ ፡ ፍጻሜያችሁ ፡ ይታወቃል ፡
አላቸው ።
፴፰ ፤ እኔ ፡ በፈጣሪዬ ፡ ስም ፡ አድነዋለሁ ፡ በና
ንተም ፡ በኔም ፡ መካከል ፡ ነገር ፡ እንወስን ።
፴፱ ፤ ንጉሥ ፡ እኔን ፡ እንደወጋ ፡ እናንተንም ፡
ይውጋችሁ ።
፵ ፤ መውጋት ፡ ባይቻለው ፡ ጦሩን ፡ በጁ ፡ አጣ
ብቃችሁ ፡ መከራ ፡ ብታጸኑበት ።

፵፩ ፤ እኔ ፡ አድነዋለሁ ።
፵፪ ፤ ባላድነው ፡ እኔን ፡ ይግደለኝ ፡ አላቸው ።
፵፫ ፤ ንጉሡም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ የቀና ፡ ነው ፡ እን
ደዚሁ ፡ ይሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡
እኔን ፡ አድነኝ ፡ አለ ።
፵፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ይህን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በአምላኮችህ ፡
ማል ፡ አለው ።
፵፭ ፤ እንዳለው ፡ እንዲያደርግ ፡ ማለ ።

፵፮ ፤ ዳግመኛም ፡ ንጉሡ ፡ አንተም ፡ ለራስህ
ዕወቅ ፡ ያላዳንከኝ ፡ እንደሆነ ፡ እገልሃለሁ ፡
የተናገርኩትን ፡ አላስቀርም ፡ አለው ።
፵፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ግደለኝ ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ አላዝንም ፡ አለው ።

፵፰ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
በስሙ ፡ የማስተምር ፡ በጌታዬ ፡ በኢየሱስ
ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከደዌህ ፡ ዳን ፡ ብሎ ፡
ዳሰሰው ።
፵፱ ፤ ከደዌው ፡ ፈጥኖ ፡ ዳነ ።
፶ ፤ ሁለቱም ፡ ጦሮች ፡ ከጁ ፡ ተለይተው ፡
ወደቁ ።
፶፩ ፤ የሰለለ ፡ ክንዱም ፡ ፈጽሞ ፡ ዳነ ።
፶፪ ፤ አእምሮውም ፡ ተመለሰለት ።
፶፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ
ሃይማኖት ፡ ቀድሞ ፡ የተነጋገርነውን ፡
ፈጥነህ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

፶፬ ፤ እሺ ፡ በጄ ፡ ብሎ ።
፶፭ ፤ ሞተለሚ ፡ ከጁ ፡ ጋራ ፡ ተጣብቃ ፡ የዋለ
ችውን ፡ ጦር ፡ ስላችሁ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡
አዘዘ ።
፶፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ይህን ፡ ትተህ ፡ ሌላ ፡ አምጡ ፡ ብለህ፡
እዘዝ መድኃኒት አደረገበት ብለው ማርያን
ምክንያት ፡ እንዳያደርጉ ።

፶፯ ፤ ሌላ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።
፶፰ ፤ ማርያንንም ፡ በሉ ፡ ጥበብ ፡ የምታውቁ ፡
ተመራረጡ ፡ አላቸው ።
፶፱ ፤ ማርያንም ፡ የአምላካቸውን ፡ ስም ፡ ጠርተው
መድኃኒታቸውን ፡ ያዘጋጁ ፡ ጀመር ።

፴ ፤ ወተኀረዩ ፡ ፫ቲ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወቆሙ ፡ አንጻረ ፡ ንጉሥ ።
፴፩ ፤ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሜ ለቆሙ ፡ ነቢሮ ።

፩ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፴፯ ።

፴፪ ፤ ወኵሎሙ ፡ ጉቡአን ፡ ያንክሩ ።
፴፫ ፤ ወተንሥአ ፡ ሞተለሚ ፡ እመንበሩ ፡ ወአስ ተጸንአ ፡ መዝራዕቶ ፡ ወቀልቀለ ፡ ኲናቶ ።
፴፬ ፤ ወረገዞ ፡ ለካህን ፡ ጣዖት ፡ ውስተ ፡ ሰንብዑ።
፴፭ ፤ ወወፅአት ፡ በሬራ ፡ እንተ ፡ ዘባኑ ።
፴፮ ፤ ወወግአቶ ፡ ለካልዑ ፡ ወእምድኅረ ፡ ካልዑ ፡ ለሣልሱ ።
፴፯ ፤ ወወድቁ ፡ ፫ቲሆሙ ፡ በ፩ ፡ ጊዜ ፡ ወሞቱ ።
፴፰ ፤ እሙንቱሂ ፡ መላህቅቲሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ማርያን ፡ ዘታሕተ ፡ መንግሥቱ ።
፴፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ መኳንንቲሁ ፡ ለንጉሥ ።
፵ ፤ ኢይኩን ፡ ሞቶሙ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ።
፵፩ ፤ ወአስተጋብአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ማርያን ፡ ወአስተፋተኖሙ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ።
፵፪ ፤ ለእመ ፡ ሞእዎ ፡ ይሙት ፡ ለሊሁ ።
፵፫ ፤ ወለእመ ፡ ተሞኡ ፡ ማርያን ፡ ይሙቱ ።
፵፬ ፤ ወአስተጋብአ ፡ ንጉሥ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ማር ርያን ፡ ወተምዓ ፡ ላዕሌሆሙ ።
፵፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ አድሙ ፡ አብያጺ ክሙ ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ጽባሕ ።
፵፮ ፤ ወተማከሩ ፡ በዘትመውእዎ ፡ ለዝ ብእሲ ።
፵፯ ፤ ወንዐ ፡ ትትፋተኑ ፡ ወይቤልዎ ፡ በረዓድ ፡ ማርያን ፡ አዝዝ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ ያስተጋ ብኡ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ።
፵፰ ፤ ወያንድዱ ፡ እሳተ ፡ እስከ ፡ ይትሌዓል ፡ ነዱ ፡ ውስተ ፡ አየር ።
፵፱ ፤ ወንእርግ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወንሐሊ ፡ ለከ ።
፶ ፤ ወበዝንቱ ፡ ለእመ ፡ ሞአነ ፡ ነፍስነ ፡ ውስተ እዴከ ።
፶፩ ፤ ወሑሩ ፡ ያስተጋብኡ ፡ ካልዓኒሆሙ ።
፶፪ ፤ ወወፅአ ፡ ዓዋዲ ፡ እምኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይ ብል ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ ዘታሕተ ፡ መንግሥ ትየ ፡ ዘኢያመጽእ ፡ ዕፀወ ፡ ዘይት ፡ መጠነ ጾዐረ ፡ ብእሲ ፡ ይትበረበር ፡ ቤቱ ፡ ወይትሐየ የድ ፡ ንዋዩ ።
፶፫ ፤ ወይውርውዎ ፡ ውስተ ፡ ጠመ ፡ ግራር ።
፶፬ ፤ ወአስተጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ወአለጹ ፡ ዕፀወ ።
፶፭ ፤ እስከ ፡ የአክል ፡ መጠነ ፡ ደብር ።
፶፮ ፤ ወተጋብኡ ፡ ማርያንሂ ፡ ወመስተቃስማን ፡ ኵሎሙ ፡ መሠርያን ።
፶፯ ፤ ወዓዲ ፡ ሠራዊትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ በአርብአ ጽባሕ ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ዘይከውን ።

፴ ፤ ከነሡ ፡ ሦስቱ ፡ ተመርጠው ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።
፴፩ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ከወዲያ ፡ ተቀምጦ ፡ ይዘብትባቸዋል ።

አንደኛ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፴፯ ።

፴፪ ፤ የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ያደንቃሉ ።
፴፫ ፤ ሞተለሚም ፡ ከዙፋኑ ፡ ተነሥቶ ፡ ክንዱን ፡ አጽንቶ ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ።
፴፬ ፤ አንዱን ፡ ካህነ ፡ ጣዖት ፡ ሳምባውን፡ ወጋው።
፴፭ ፤ በጀርባው ፡ ዘልቃ ፡ ወጣች ።
፴፮ ፤ ሁለተኛውን ፡ ወጋችው ፡ ከሁለተኛውም ፡ ወጥታ ፡ ሦስተኛውን ፡ ወጋችው ።
፴፯ ፤ ሦስቱም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወድቀው ፡ ሞቱ ።
፴፰ ፤ እሊህም ፡ በግዛቱ ፡ ያሉ ፡ የማርያን ፡ አለ ቆችም ፡ ሞቱ ።
፴፱ ፤ መኳንንቱም ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ አሉት ።
፵ ፤ ሞታቸው ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አይሁን ።
፵፩ ፤ ማርያኑን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበህ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ አፈታትናቸው ።
፵፪ ፤ እነሱ ፡ ቢያሸንፉት ፡ እሱ ፡ ይሙት ።
፵፫ ፤ እሱ ፡ ቢያሸንፋቸው ፡ እነሱ ፡ ይሙቱ ።
፵፬ ፤ ንጉሡም ፡ የቀሩትን ፡ ማርያን ፡ ጠርቶ ፡ ተቆጣቸው ።
፵፭ ፤ ሄዳችሁ ፡ ወገኖቻችሁን ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቅጠሩዋቸው ።
፵፮ ፤ ይህን ፡ ሰው ፡ ድል ፡ የምታደርጉበትን ፡ ተማከሩችሁ ።
፵፯ ፤ መጥታችሁ ፡ ተፈታተኑ ፡ ማርያንም ፡ ፈር ተው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ሰብስቡ ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ፡ አሉት ።
፵፰ ፤ ልሳኑ ፡ ወደሰማይ ፡ እንስኪደርስ ፡ እሳት ፡ ያንድዱ ።
፵፱ ፤ ከላዩ ፡ ወጥተን ፡ እንዘፍንልሀለን ።
፶ ፤ በዚህ ፡ ቢያቸንፈን ፡ ሰውነታችን ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ናት ፡ ብለው ።
፶፩ ፤ ወገኖቻቸውን ፡ ሊሰበስቡ ፡ ሄዱ ።
፶፪ ፤ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በኔ ፡ ግዛት ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ ወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ያላመጣ ፡ ቤቱ ፡ ይዘረፍ ፡ ከብቱ ፡ ይወረስ ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ ወጣ ፡ ተነገረ ።
፶፫ ፤ እሱን ፡ ወደገደል ፡ ይጣሉት ፡ በል ።
፶፬ ፤ ያገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዕንጨቱን ፡ ሰብስበው ከመሩ ።
፶፭ ፤ ተራራ ፡ እስኪያህል ፡ ድረስ ።
፶፮ ፤ ማርያንም ፡ ባለመድኃኒቶቹም ፡ ሟርተኞ ቹም ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ።
፶፯ ፤ ዳግመኛ ፡ ሠራዊቱም ፡ አርባው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሚያደርገውን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ተሰ በሰቡ ።

፹፰ ፤ ወእሚሃ ፡ ይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፹፱ ፤ አብእሲ ፡ መኑ ፡ ስምከ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምኅበ ፡ አቡየ ወእምየ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ስምየ ።

፺ ፤ ወእምኅበ ፡ መልአክሰ ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፺፩ ፤ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ፍካሬሁ ፡ ለዝ ፡ ስም ።

፺፪ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ፍካሬሁሰ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስምየ ።

፺፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ምንት ፡ ይትፌቀር ስምከ ።

፺፬ ፤ አርአያከኒ ፡ ፍሡሕ ።

፺፭ ፤ ወነገርከኒ ፡ ብሩህ ፡ ወስምከ ፡ ጥዑም ።

፺፮ ፤ ምንተ ፡ ይመስል ፡ አብ ፡ ዘወለደከ ፡ ወምንተ ፡ ትመስል ፡ እም ፡ ዘወለደት ፡ ኪያከ ።

፺፯ ፤ ብዕዕት ፡ ከርሥ ፡ እንተ ፡ ጾረተከ ።

፺፰ ፤ ወብፁዓት ፡ አጥባት ፡ እለ ፡ ሐፀናከ ።

፺፱ ፤ ወብፅዕት ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ተወለድከ ።

፻ ፤ ርኢ ፡ ኪያየ ፡ አርአያየ ፡ ኅሱም ።

፻፩ ፤ ወስምየ ፡ የዓኪ ፡ እምኔሁ ።

፻፪ ፤ አስተበቍዓከ ፡ አ ፡ ፍሡሕ ፡ ተሀበኒ ፡ ውእተ ስመ ፡ ዘሰመዩከ ፡ አቡከ ፡ ወእምከ ።

፻፫ ፤ እነሂ ፡ እሁብከ ፡ ፲ተ፡፻ተ ፡ ልጥረ ፡ ወርቅ ።

፻፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እመ ፡ ወሀብከኒ ፡ መንፈቀ ፡ መንግሥትከ ፡ ኢይሁበከ ፡ ስምየ ።

፻፭ ፤ ወእመሰ ፡ አመንከ ፡ በስመ ፡ እምላኪየ ፡ እንበለ ፡ ሤጥ ፡ እሁበከ ።

፻፮ ፤ አውሥአ ፡ ወይቤሎ ፡ ሞተለሚ ፡ ሶበ ፡ ሞእኮሙ ፡ ለማርያን ፡ አአምን ፡ በአምላክከ ።

፻፯ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አነሂ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ እሁብከ ።

፻፰ ፤ አውሥአ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አዘዝ ፡ ይቅብሩ ፡ ኵሎ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡ በእንተ ፡ ስመ ፡ አምላኪየ ፡ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ኵሎ ፡ ሠራዊቶ ፡ ይቅብሩ ፡ ሥጋ ፡ ቅዱሳን ፡ ቅዱሳኒ ፡ ወፅአ ፡ እምኀቤሁ ፡ ወቀበርዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕት በመልበርዲ ።

፹፰ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሞተለሚ ፡ ክቡር ፡ አባታችን፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

፹፱ ፤ አንተ ፡ ሰው ፡ ስምህ ፡ ማነው ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እናቴ ፡ አባቴ ፡ ያወጡልኝ ፡ ስም ፍሥሐ፡ ጽዮን ፡ ነው ።

፺ ፤ ከመልአክ ፡ ግን ፡ ያወጣሁት ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

፺፩ ፤ ሞተለሚም ፡ የዚህ ፡ ስም ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድነው ፡ አለው ።

፺፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ትርጓሜውስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አለው ።

፺፫ ፤ ሞተለሚም ፡ ስምህ ፡ ምን ፡ ይወደድ ።

፺፬ ፤ መልክህም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ።

፺፭ ፤ ነገርህም ፡ የጎላ ፡ የተረዳ ፡ ስምህም ፡ ያማረ ነው ።

፺፮ ፤ የወለደህ ፡ አባት ፡ ምን ፡ ይመስል ፡ አንተን ፡ የወለደች ፡ እናት ፡ ምን ፡ ትመስል ።

፺፯ ፤ አንተን ፡ የተሸከመች ፡ ማኅፀን ፡ ንዕድ ፡ ክብርት ፡ ናት ።

፺፰ ፤ አንተንም ፡ ያሳደጉ ፡ ጡቶች ፡ ንዑዳት ፡ ክቡራት ፡ ናቸው ።

፺፱ ፤ የተወለድክበትም ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡ ናት ።

፻ ፤ እኔን ፡ ተመልከት ፡ መልኬ ፡ ጥፉ ፡ ነው ።

፻፩ ፤ ስሜም ፡ ከመልኬ ፡ የከፋ ፡ ነው ።

፻፪ ፤ ፍሡሕ ፡ እናት ፡ አባትህ ፡ ያወጡልህን ፡ ስም ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ።

፻፫ ፤ እኔም ፡ ሺህ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ።

፻፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የመንግሥትህንም ፡ እኩሌታ ፡ ብትሰጠኝ ፡ ስሜን ፡ አልሰጥህም ።

፻፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በፈጣሪዬ ፡ ስም ፡ ብታምን ፡ ያለዋጋ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ።

፻፮ ፤ ሞተለሚም ፡ መለሰለት ፡ ማርያንን ፡ ባቸነፍካቸው ፡ ጊዜ ፡ በአምላክህ ፡ አምናለሁ ፡ አለው ።

፻፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ መለሰ ፡ እኔም ፡ ያንጊዜ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ።

፻፰ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ መለሰ ፡ ስለአምላኪዩ ፡ ስም ፡ የሞቱትን ፡ የሊህን ፡ ቅዱሳን ፡ ሥጋቸውን ፡ ቅበሩ ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ። ንጉሡም ፡ ሠራዊቱን ፡ ሰማዕት ፡ የሆኑትን ፡ የቅዱሳኑን ፡ ሥጋ ፡ ቅበሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡ ሰማዕት ፡ የሆኑትንም ፡ ቅዱሳን ፡ መልበርዴ ፡ በሚባል ፡ ሥፍራ ፡ ቀበሯቸው ።

፻፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ኵሎሙ ፡ ጉቡአን ፡
ማርያን ፡ ወሥራዊት ፡ ይጽንሑ ፡ ውስተ ፡
ዴዴክ ፡ እስመ ፡ አደምኮሙ ፡ ከመ ፡ ይብ
ጽሑ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ።
፻፲ ፤ ወይቤ ፡ ሞተለሚ ፡ አምጽኡ ፡ ካህናተ ፡
እለ ፡ ጼወውናሆሙ ፡ ቅድመ ፡ እምብሔረ ፡
ሸዋ ፡ ውንብዎ ፡ ለዝብእሲ ፡ ወአምጽእዎሙ
ወወሀብዎ ፡ ለቅዱስ ።
፻፲፩ ፤ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ካህናት ፡ **ለአቡነ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡** ሰገዱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወተን
ሥኡ ፡ ወአምኅዎ ፡ ወነገርዎ ፡ ኵሎ ፡ ዘበ
ጽሐ ፡ ላዕሌሆሙ ።
፻፲፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለምንት ፡ ኢያፍጠን
ክሙ ፡ መጺእ ፡ ኀቤየ ፡ ወሚመ ፡ ኢያእ
መርክሙኑ ፡ ምጽአትየ ። ወይቤልዎ ፡ እወ ፡
አእመርነ ፡ ጥዩቀ ፡ ወሰማዕነ ፡ መንክራቲከ ፡
ወከመ ፡ ኢንምጻእ ፡ ኀቤከ ፡ ካልዑነ ፡ እለ
የዓቅቡነ ።
፻፲፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ሰገድክሙኑ ፡ ለአማ
ልክት ፡ ወይቤልዎ ፡ እወ ፡ ሰገድነ ፡ ዘእን
በለ ፡ ፈቃድነ ፡ በሥቃሒ ፡ ወበመቅሠፍት ።
፻፲፬ ፤ ወይቤሎሙ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
ጽንሑኒ ፡ እነ ፡ እገብር ፡ ለክሙ ፡ ሰላመ ፡
ምስለ ፡ **እግዚአብሔር ፡** አምላኪየ ።
፻፲፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ሞተለሚ ፡ ለመኳንንቲሁ ፡
ኍልቍዎሙ ፡ ለማርያን ፡ ወወፅኡ ፡ መኳን
ንት ፡ ወኈልቍዎሙ ።
፻፲፮ ፤ ወተረክቡ ፡ ፍቅዶሙ ፡ ከመዝ ፡ ፬ቱ ፡ ፻ት ፡
ማርያን ፡ ወ፪፻ ፡ መስተቃስማን ፡ ወ፫፻ ፡
መሠርያን ፡ ወ፻ ፡ አንስት ፡ እምሰብአ ፡
ሐረስ ።
፻፲፯ ፤ ወኮነ ፡ ኍልቈሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡
ዓመፃ፡ ፲ተ፡፻ተ ፡ ወቦኡ ፡ መኳንንት ፡ ወነ
ገርዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ዘንተ ።
፻፲፰ ፤ ወፈነዎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለእሙንቱ ፡ መኳ
ንንት ፡ ኀበ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
እንዘ ፡ ይብል ፡ ናሁአ ፡ አስተጋባእኩአ ፡
ወአስተዳሎኩአ ፡ ኵሎአ ፡ ማርያንአ ፡ ዘይ
ገብሩአ ፡ ኃይለአ ፡ ኢታስተኃፍረኒአ ፡ ወኢ
ይማዑከአ ፡ አንተአ ፡ ማእሙአ ፡ እስመአ ፡
አንሰአ ፡ አፈቅርአ ፡ ከመአ ፡ አንተአ ፡
ትማዕአ ፡ ሊተአ ፡ ወኢትትመዋዕአ ፡
ብየአ ።
፻፲፱ ፤ ወነገርዎ ፡ **ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
ዘንተ ፡ ቃለ ፡ ንጉሥ ፡ ወሰሚዖ ፡ ቅዱስ ፡
አክሞሰሰ ፡ ወይቤሎሙ ፡ በልዎ ፡ ለንጉሥ ።

፻፱ ፤ ንጉሡንም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ እነሆ ፡
ማርያንና ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡
በደጅህ ፡ ይጠባበቃሉ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡
እንዲመጡ ፡ ቀጥረሀቸዋልና ።
፻፲ ፤ ሞተለሚም ፡ አስቀድመን ፡ ከሸዋ ፡ አው
ራጃ ፡ የማረክናቸውን ፡ ካህናት ፡ አምጥ
ታችሁ ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ስጡት ፡ አለ ፡
አምጥተው ፡ **ለክቡር ፡ አባታችን ፡** ሰጡት ።
፻፲፩ ፤ ካህናቱም ፡ **ክቡር ፡ አባታችንን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖትን ፡** ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ከጫማው ፡
ወድቀው ፡ ሰገዱለትና ፡ ተነሥተው ፡ እጅ ፡
ነሡት ፡ የደረሰባቸውንም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡
ነገሩት ።
፻፲፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ካህናቱን ፡ ፈጥናችሁ ፡
ወደኔ ፡ ሳትመጡ ፡ ለምን ፡ ቀራችሁ ፡
ወይስ ፡ መምጣቴን ፡ አላወቃችሁምን ፡
አላቸው ። ካህናቱም ፡ መምጣትክን ፡ በው
ነት ፡ አውቀናል ፡ ተአምራትህንም ፡ ሰም
ተናል ፡ ወዳንተ ፡ እንዳንመጣ ፡ ግን ፡ የሚ
ጠብቁን ፡ ዘበኞች ፡ ከለከሉን ፡ አሉ ።
፻፲፫ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ለጣዖት ፡ ሰገዳችሁን ፡
አላቸው ፡ ካህናቱም ፡ አዎን ፡ ሰገድን ፡
ያለፈቃዳችን ፡ በዕሥራት ፡ በግርፋት ፡
አስጨነቁን ፡ አሉት ።
፻፲፬ ፤ **አባታችን ፡ ክቡር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ከፈጣሪዬ ፡ ከእግዚአብሔር ፡** ጋራ ፡ እኔ ፡
አስታርቃችኋለሁ ፡ ቆዩኝ ፡ አላቸው ።
፻፲፭ ፤ ሞተለሚም ፡ መኳንንቱን ፡ እስኪውጡና ፡
ቍጠሯቸው ፡ አላቸው ፡ መኳንንቱም ፡
ወጥተው ፡ ቈጠሩዋቸው ።
፻፲፮ ፤ ቍጥራቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ፡
አራት ፡ መቶ ፡ ዛር ፡ አንጋሾች ፡ ሁለት ፡
መቶ ፡ ሟርተኞች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሥር ፡
ምሰው ፡ ቅጠል ፡ በጥሰው ፡ የሚያጠፉ ፡
ጨሌ ፡ ዛጐል ፡ ጠጠር ፡ ከሚጥሉ ፡ ወገን
መቶ ሴቶች ፡ ነበሩ ።
፻፲፯ ፤ የነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ዓመፀኞች ፡ ቍጥራቸው ፡
ሺህ ፡ ነበረ ፡ መኳንንቱም ፡ ከቤት ፡ ገብ
ተው ፡ ቍጥራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡
ለንጉሡ ፡ ነገሩት ።
፻፲፰ ፤ ንጉሡም ፡ እለዚህን ፡ መኳንንት ፡ ወደ ፡
ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላካ
ቸው ፡ እነሆ ፡ ተአምራት ፡ የሚያደርጉ ፡
ማርያን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቤ ፡ አዘጋጅቻለሁና ፡
እንዳታሳፍረኝ ፡ አንተ ፡ አሸንፋቸው ፡ እንጂ
እንዳያቸንፉህ ፡ እኔም ፡ አንተ ፡ ብታቸንፍ ፡
እወዳለሁና ፡ አቸንፍልኝ ፡ እንጂ ፡ እንዳ
ትቸነፍብኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ።
፻፲፱ ፤ መላክተኞቹም ፡ **ለክቡር ፡ አባታችን ፡** ይህን
የንጉሡን ፡ ቃል ፡ ነገሩት ፡ ክቡር ፡ አባታ
ችንም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ፍግግ ፡ ብሎ ፡
ስቆ ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።

፻፴ ፤ ኢትኅዝን ፡ ለእመ ፡ ሞኡኪ ፡ ማርያንአ ፡ ቅትልአ ፡ ኪያየአ ፡ **ወክርስቶስአ ፡ አምላኪየአ** ፡ ይኩንአ ፡ ከመአ ፡ ዘኢተሠገወአ ፡ **እማርያምአ** ፡ ወይኩንአ ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ እማርያንአ ፡ ወይኩንአ ፡ ከመ ፡ ኢኮነአ ፡ ፈጣሬአ ፡ ኵሉአ ።

፻፴፩ ፤ ወነገርዎ ፡ ላእካን ፡ ለንጉሥ ፡ ዘከመ ፡ ይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለማርያን ፡ ግበሩ ፡ በከመ ፡ ልማድ ክሙ ።

፻፴፪ ፤ ወአንደዱ ፡ እሳተ ፡ ማርያን ፡ ላዕለ ፡ ዕፀው ፡ እሎዳን ፡ ወተለዓለ ፡ ነዱ ፡ እስከ ፡ አየር ፡ ወወፅአ ፡ ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወቆመ አንጻረ ፡ እሳት ።

፻፴፫ ፤ ወሰብአ ፡ ሀገርኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ተጋብኡ ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ዘይከውን ፡ ወኮነ ፡ ጸዕቅ ፡ ዓቢይ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እስከ ፡ ይከይዱ ፡ ቢጾሙ ።

፻፴፬ ፤ ወቦኡ ፡ ማርያን ፡ ወኵሎሙ ፡ ምሁራኒ ፡ እከይ ፡ ማእከለ ፡ እሳት ፡ ወቆሙ ፡ ህየ ፡ እንዘ ፡ ይጼውዑ ፡ ስመ ፡ አማልክቲሆሙ ፡ ርኩሳን ፡ ወአኃዙ ፡ ይዝፍኑ ፡ ሎቱ ፡ ለንጉሥ ።

፻፴፭ ፤ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ርኢኬ ፡ ኦ ሞተለሚ ፡ አማልክቲከ ፡ ዘይረድኡከ ፡ በውስተ ፡ ጸብዕ ፡ ወይመውእዎሙ ፡ ለጸላዕትከ ።

፻፴፮ ፤ ኢያስሕትከ ፡ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ዘመጽአ ፡ በዝመዋዕል ፡ ወኢታማስን ፡ አማልክተ ፡ አቡከ ፡ ሞተቄል ፡ ወእምከ ፡ እስለደኔ ፡ በመዋዕለ፡ ትካት ፡ ዘረከቡ ፡ ኃይለ ፡ በእሉ ፡ አማልክት ።

፻፴፯ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ይጠፍኡ ፡ በአደዊሆሙ ፡ ወያጽሕሱ ፡ በእገሪሆሙ ፡ ላዕለ እሳት ፡ ወርእየ ፡ ኪያሆሙ ፡ ሞተለሚ ፡ ወይቤሎ ፡ **ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**

፻፴፰ ፤ ኦ ፡ ፍሡሕ ፡ ናሁ ፡ ማርያን ፡ ወጠኑ ፡ አርእዮ ኃይል ፡ ወአንተ ፡ ምንተ ፡ እንከ ፡ ትገብር ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ተአገሥ ፡ እስከ ፡ ትሬኢ ስብሐተ ፡ **እግዚአብሔር ።**

፻፴፱ ፤ ወይቤሎ ፡ እስኩ ፡ ኢታስተኃፍረኒ ፡ ኦ ፡ ፍሡሕ ፡ ወአዘዞሙ ፡ አቡነ ፡ ለ፲ወ፪ ፡ ካህናት ፡ ይቁሙ ፡ ከቢቦሙ ፡ እሳተ ፡ ከመ ፡ ዐረፍት ፡ ከመ ፡ ኢይጒየዩ ፡ እሉ ፡ እኩያን ፡ ወሠረረ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ወቆመ ፡ ማእከሌሆሙ ።

፻፴ ፤ አትዘንልኝ ፡ ማርያን ፡ ቢያሸንፉኝ ፡ እኔን ግደል ፡ **አምላኪየ ፡ ክርስቶስም ፡ ከድንግል ፡ ማርያም** ፡ ሥጋን ፡ እንደለበሰ ፡ የ፴፪ቱ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ እንዳይደለ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

፻፴፩ ፤ መላክተኞቹም ፡ ለንጉሡ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ያለውን ፡ ነገሩት ። ንጉሡም ፡ ማርያንን ፡ እንደልማዳችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ ሥሩ ፡ አላቸው ።

፻፴፪ ፤ ማርያንም ፡ በተከመሩት ፡ ዕንጨቶች ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ አነደዱ ፡ ነበልባሉም ፡ እስከ ፡ አየር ፡ ወጣ ፡ ንጉሡም ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ወጣና ፡ በእሳቱ ፡ አንጻር ፡ ቆመ ።

፻፴፫ ፤ የሀገር ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ የሚደረገውን ፡ ለማየት ፡ ተሰበሰቡ ፡ አንዱም ፡ ባንዱ ፡ በባልንጀራቸው ፡ ላይ ፡ እስከመቆም ፡ ደርሰው ፡ ታላቅ ፡ መጨናነቅ ፡ ሆነባቸው ።

፻፴፬ ፤ ማርያንም ፡ የተንኮል ፡ መምህሮች ፡ የሆኑትም ፡ ሁሉ ፡ ከእሳቱ ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ከዚያው ፡ ቁመው ፡ የርኩሳን ፡ አምላካቸውን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ ለንጉሡ ፡ ይዘፍኑለት ፡ ጀመሩ ።

፻፴፭ ፤ ሞተለሚ ፡ ሆይ ፡ በጦርነት ፡ የሚረዱህን ፡ ጠላቶችህን ፡ ድል ፡ የሚነሱዋቸውን ፡ አምላኮችህን ፡ እያቸው ፡ ተመልከታቸው ፡ እያሉ ።

፻፴፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ የመጣ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ እንዳያስትህና ፡ ያባታህ ፡ የሞተቄልን ፡ የናትህ ፡ የእስለንደኔን ፡ አምላኮች ፡ በወትሮው ፡ ዘመን ፡ በእነዚህ ፡ አምላኮች ፡ ክብር ፡ ያገኙባቸውን ፡ እንዳታጠፋ ፡ ተጠንቀቅ ።

፻፴፯ ፤ ይህንንም ፡ እያሉ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ በእግራቸው ፡ ያሸበሽቡ ፡ በእጃቸው ፡ ያጨበጭቡ ፡ ነበሩ ፡ ሞተለሚም ፡ እሳቸውን ፡ ዓይቶ ፡ **ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን** ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

፻፴፰ ፤ ደስ ፡ ያለህ ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ ማርያን ፡ ተአምራትን ፡ ማሳየት ፡ ጀመሩ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ ተአምራት ፡ ትሠራለህ ፡ አለው ፡ **ክቡር ፡ አባታችንም ፡ የእግዚአብሔርን** ፡ ጌትነት ፡ ክብር ፡ እስክታይ ፡ ድረስ ፡ ታገሥ ብሎ ፡ መለሰለት ።

፻፴፱ ፤ ንጉሡም ፡ ደስ ፡ ያለህ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ እስኪ ፡ እንዳታሳፍረኝ ፡ አለው ፡ **ክቡር ፡ አባታችንም** ፡ እለዚህ ፡ ተንኮለኞች ፡ እንዳይሸሹ ፡ እንደግድግዳ ፡ ሁናችሁ ፡ እሳቱን ፡ ከባችሁ ፡ ቁሙ ፡ ብሎ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ካህናት ፡ አዘዛቸውና ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ከእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በመካከላቸው ፡ ቆመ ።

፻፴ ፤ ወከልሐ ፡ በዓቢይ ፡ ቃል ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
በስመ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ተኃፈር ፡ ሰይጣን ፡
ይውዕዩ ፡ በዝንቱ ፡ እሳት ፡ ላእካኒከ ፡ ርኩ
ሳን ።

፻፴፩ ፤ ወእምሰሚዐ ፡ ድምፀ ፡ ቃሉ ፡ ኃደጎሙ ፡
ሰይጣን ፡ ለእሉ ፡ መሠርያን፡ ወውዕዩ፡ ወኮኑ፡
ሐመደ ።

፻፴፪ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ደንገፀ ፡ ንጉሥ ፡ ወርእዱ ፡
ሠራዊቱ ፡ ርእዮሙ ፡ ተአምረ ፡ ዘገብረ ፡
አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኮነ ፡ ግርማ ፡
ዓቢየ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
አኅጉረ ፡ ዳሞት ።

፻፴፫ ፤ ወአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ቆመ ፡ ነዊሃ ፡ ሰዓተ ፡
ማእከለ ፡ እሳት ፡ ወጸለየ ፡ ጸሎተ ፡ ፫ ፡ ደቂቅ
ወካዕበ ፡ ጸለየ ፡ ፲ወ፱ ፡ መዝሙራተ ፡ ወዓዲ ፡
ሐለየ ፡ ማኅሌተ ፡ ድርሳን ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
አድኅነነ ፡ ሕዝበከ ፡ ወባርከነ ፡ ርስተከ ፡
ኅበነ ፡ ኃይለ ፡ ወመዊአ ፡ ለአግብርቲከ ።

፻፴፬ ፤ ወዘንተ ፡ ማኅሌተ ፡ ሐለየ ፡ እስከ ፡ ተፍጻ
ሜቱ ፡ ወእስከ ፡ ይእዜ ፡ ሀሎ ፡ ይትቀነይዎ ፡
ካህናተ ፡ ወንጌል ፡ እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡
ዋዜማ ።

፻፴፭ ፤ ንጉሥኒ ፡ ሐለየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ሞአ ፡ ወማርያን ፡ ተሞኡ ፡
ካህናትኒ ፡ እንዘ ፡ ይዘፍኑ ፡ በማኅሌተ ፡
አቡሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አድኅነነ ፡
ሕዝከ ፡ ወባርከነ ፡ ርስተከ ።

፻፴፮ ፤ ወሠራዊቱ ፡ እንዘ ፡ ይዘፍኑ ፡ በማኅሌተ ፡
እግዚአሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ሞአ ፡ ወማርያን ፡ ተሞኡ ፡ ወገ
ብረ ፡ ሞተለሚ ፡ ብዙኃ ፡ ወከሀ ፡ በይእቲ፡
ሰዓት ፡ በእንተ ፡ ዘርእየ ፡ ተአምር ።

፻፴፯ ፤ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ጸሎተ ፡ ወፅአ ፡ አቡነ ፡
ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምእሳት ፡
እንዘ ፡ ይበርህ ፡ ገጹ ፡ እምፀሐይ ፡ ወአ
ልቦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጼና ፡ ዘእሳት ፡ ወሰገደ
ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊቱ ፡ ታሕተ ፡
እገሪሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ወከልሑ ፡ ኵሎሙ ፡
ከመ ፡ ዘ፩ ፡ አፍ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አመነ ፡
በአምላክከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘአጥ
ፍአ ፡ ማርያነ ፡ ወአድኃነ ፡ ገብሮ ፡ እምነ
በልባለ ፡ እሳት ።

፻፴፰ ፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ አበ ፡ ዘአ
በስኩ ፡ ለከ ፡ በኢያእምሮትየ ፡ እምይእ
ዜሰ ፡ አመንኩ ፡ በአምላክከ ፡ ዘይክል ፡
ኵሎ ፡ ወእገብር ፡ በከመ ፡ ትቤለኒ ።

፻፴ ፤ አሰምቶ ፡ ተናገረ ፡ በሦስቱ ፡ ሥላሴ፡ ሰይጣን
እፈር ፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ ርኩሳን ፡ የሆኑ ፡ አገ
ልጋዮችህም ፡ በዚህ ፡ እሳት ፡ ይቃጠሉ ፡
አለ ።

፻፴፩ ፤ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ፡
እለዚህን ፡ መሠርያን ፡ ሰይጣኑ፡ ጥሏቸው ፡
ሄዶ ፡ ተቃጠሉና ፡ አመድ ፡ ሆኑ ።

፻፴፪ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ደነገጠ፡ ሠራዊቱም፡
ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ያደረገውን ፡ ይህንን ፡ ተአምር ፡ አይተው ፡
ተንቀጠቀጡ ፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ በዳሞት ፡
አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ግርማ ፡ ሆነ ፡
ወረደ ።

፻፴፫ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ በእሳቱ ፡ መካከል ፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆመ ፡ የሠለስቱ ፡ ደቂቅን ፡
ጸሎት ፡ ፲፱ ፡ መዝሙራት ፡ ጸለየ ፡ ዳግመ
ኛም ፡ ሕዝቦችህን ፡ አድነን ፡ እርስቶችህ
ንም ፡ ባርከን ፡ ለባሮችህም ፡ ለኛ ፡ ድል
መንሣትን ፡ ገቢረ ፡ ተአምራትን ፡ ስጠን ፡
እያለ ፡ የድርሳኑን ፡ ማኅሌት ፡ እያደረገ ፡
ዘፈን ፡ ደግሞ ፡ ዘፈነ ።

፻፴፬ ፤ ይህንንም ፡ ማኅሌት ፡ እስከመጨረሻው ፡
ድረስ ፡ አደረገ ፡ ይኸውም ፡ እስካሁን ፡
አለ ፡ ዋዜማ ፡ ተቆሞ ፡ ካበቃ ፡ በኋላ ፡ የወ
ንጌል ፡ ካህናት ፡ ያገለግሉበታል ።

፻፴፭ ፤ ንጉሡም ፡ ዘፈነ ፡ ማኅሌት ፡ አደረገ ተክለ
ሃይማኖት ፡ ድል ፡ ነሣ ፡ ማርያን ፡ ግን ፡
ገድል ፡ ተነሡ ፡ ካህናቱም ፡ ያባታቸውን ፡
ማኅሌት ፡ ያደርጉ ፡ ጀመሩ ፡ ሕዝቦችህንም ፡
አድነን ፡ ማደሪያዎችህን ፡ እኛን፡ አክብረን፡
እያሉ ።

፻፴፮ ፤ የንጉሡም ፡ ሠራዊት ፡ የጌታቸውን ፡ ማኅ
ሌት ፡ ይዘፍኑ ፡ ጀመሩ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ድል ፡ ነሣ ፡ ማርያን ፡ ግን ፡ ድል ፡ ተነሡ ፤
ሞተለሚም ፡ ስለአየው ፡ ተአምራት ፡ በዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዕልልታ ፡ ግርግርታ ፡
ቀረርቶ ፡ ፍከራ ፡ አደረገ ።

፻፴፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ጸሎቱን ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ከፀሐይ ፡
ይልቅ ፡ እየበራ ፡ ከእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ ወጣ ፡
የእሳቱ ፡ ሽታ ፡ ከቶ ፡ በላዩ ፡ አልነበረም ።
ንጉሡም ፡ ከሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ለክ
ቡር ፡ አባታችን ፡ ከእግሩ ፡ ሰገዱ ፡ ሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ እንዳንድ ፡ አፍ ፡ ተናጋሪ ፡ ባንድ ፡
ቃል ፡ ሁነው ፡ አሰምተው ፡ ተናገሩ ፡ ባሪያ
ውን ፡ ከሚነድ ፡ እሳት ፡ ባዳነ ፡ ማርያን
ንም ፡ ባጠፋ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈጣሪ
አምነናል ፡ አሉ ።

፻፴፰ ፤ ንጉሡም ፡ አባቴ ፡ ያለዕውቀት ፡ የበደል
ኩህን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
ግን ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክህ ፡ አመ
ንኩ ፡ እንዳልከኝም ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ።

፻፴፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ኢትፍራህ ፡ ወልድየ ፡
ናሁ ፡ ጸውዓከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡
ርስቱ ፤ ዘለዓለም ።

፻፵ ፤ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ይፃእ ፡ ዓዋዴ ፡ እንዘ ፡
ይብል ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘውስተ ፡ መንግሥ
ትየ ፡ እመሂ ፡ መኰንን ፡ አው ፡ መስፍን ፡
አው ፡ ነዳይ ፡ አው ፡ ባዕል ፡ ዘሰገደ ፡ ለጣዖት ፤
ወዘተረክበ ፡ ማሪት ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ይት
ሐየድ ፡ ንዋዩ ፡ ወይትኰነን ፡ ነፍሱ ፡ ወይ
ውርውዎ ፡ ውስተ ፡ ጸድፍ ፡ ዘይሰመይ ፡
ጦመ ፡ ግራር ፡ ወይሙት ፡ በህየ ፡ እኩየ ፡
ሞተ ፡ ወይእመን ፡ ኵሉ ፡ በአምላከ ፡ ተክለ
ሃይማኖት ።

፻፵፩ ፤ ወፅአ ፡ ዓዋዲ ፡ ወነገረ ፡ ቃለ ፡ ንጉሥ ፡
ለኵሉ ፡ ተዓይነ ፡ ዳሞት ። ወይቤሎ ፡ ሞተ
ለሚ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተንሥእ ፡ ወአጥ
ምቀኒ ፡ በስመ ፡ አምላክከ ።

፻፵፪ ፤ ወተንሥአ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ወቀደሰ ፡ ማየ ፡ ወአጥመቆ ፡ ምስለ ፡
ኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወኮነ ፡ ኍልቈሙ ፡
ለእለ ፡ ተጠምቁ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ፲ቱ ፡ ፼ ፡
ወ፳፻ ፡ ፺ወ፱ ፡ ነፍስ ።

፻፵፫ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለሞ
ተለሚ ፡ ይኩን ፡ ስምከ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡
በከመ ፡ አሰፈውኩከ ፡ ቅድመ ፡ ወካዕበ ፡
ይቤሎ ፡ ኢትጥዓም ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡
ትትሜጠ ፡ ቍርባነ ።

፻፵፬ ፤ ወኢተክህሎ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ይሥራዕ ፡
ቍርባነ ፡ እስመ ፡ መስየ ፡ ፀሐይ ፡ ወቤተ ፡
ሞተለሚ ፡ እንዘ ፡ ኢይጥዕም ፡ እክለ ፡
ምንተኒ ።

፻፵፭ ፤ ወበሳኒታ ፡ ጸውዖሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ለእሙንቱ ፡ ካህናት ፡ ወይቤሎሙ ፡
አምጽኡ ፡ ታቦተ ፡ ንጉሥ ፡ አመ ፡ ጼወ
ወክሙ ፡ ወይቤልዎ ፡ እወ ፡ አምጽአ ፡ ወባ
ሕቱ ፡ ነገሩነ ፡ ከመ ፡ ገብሮ ፡ ትርአሰ ፡
መልዕልተ ፡ እራሱ ።

፻፵፮ ፤ ወለአከ ፡ ቅዱስ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡
ይፈኑ ፡ ሎቱ ፡ ታቦተ ፡ ዘአምጽአ ፡ እም
ጼዋዌ ፡ ወነሥአ ፡ እምትርዓሱ ፡ ወፈነወ ፡
ሎቱ ።

፻፵፯ ፤ ወርእየ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ውስተ
ታቦት ፡ ረከበ ፡ መልክአ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡
ዝታቦት ፡ በስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ወሜጠ ፡ ዘባኖ ፡ ወነጸረ ፡ ካዕበ ፡ ዘይብል
ዝንቱ ፡ ታቦት ፡ ዘአብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡
ነገሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወተቀደሰ ፡ በእደ ።

፻፴፱ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ወደማታልፍ ፡ ርስቱ
ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እነሆ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ጠርቶሃልና ፡ አትፍራ ፡ ልጄ ፡
ሆይ ፡ አለው ።

፻፵ ፤ ንጉሡም ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ይውጣ ፡ ብሎ ፡
አዘዘ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ አገረ ፡ ገዥም ፡ ቢሆን ፡ ራስ ፡ ቢት
ወደድም ፡ ቢሆን ፡ ድሀም ፡ ባለጸጋም ፡ ቢሆን
ለጣዖት ፡ የሰገደ ፡ ማሪት ፡ በቤቱ ፡ የተገኘ
በት ፡ ቢኖር ፡ ገንዘቡ ፡ ይወረስ ፡ ሰውነቱም
በሞት ፡ በእስራት ፡ ይቀጣ ፡ ጦመ ፡ ግራር ፡
በሚባል ፡ ገደል ፡ ይጣሉት ፡ ከዚያም ፡
ተጣጥሮ ፡ ይሙት ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በተ
ክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈጣሪ ፡ ይመን ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፻፵፩ ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪውም ፡ ወጥቶ ፡ የንጉሡንም ፡
ቃል ፡ ለዳሞት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ነገረ ፡
ሞተለሚም ፡ ተነሥተህ ፡ በአምላክህ ፡
ስም ፡ አጥምቀኝ ፡ አለው ።

፻፵፪ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተነሥቶ ፡ ውኃውን ፡
ባርኮ ፡ ንጉሡን ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ አጠ
መቃቸው ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የተጠመቁት ፡
ቍጥራቸው ፡ ዐሥር ፡ እልፍ ፡ ሁለት ፡ ሺህ
ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

፻፵፫ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ሞተለሚን ፡ ቀድሞ ፡ ተስፋ ፡ እንደሰጠሁህ ፡
ስምህ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ይሁን ፡ ሥጋውን ፡
ደሙንም ፡ ሳትቀበል ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አት
ቅመስ ፡ አለው ።

፻፵፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ መሥዋዕት ፡
መሥራት ፡ አልተቻለውም ፡ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡
ነበርና ፡ ሞተለሚም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡
ከምግብ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሳይቀምስ ፡
አደረ ።

፻፵፭ ፤ በበነጋው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ እለዚያን ፡ ካህናት ፡ ጠራቸው ፡
ንጉሡ ፡ በማረካችሁ ፡ ጊዜ ፡ ታቦት ፡ አመ
ጣን ፡ ወይስ ፡ አላመጣንም ፡ ብሎ ፡ ጠየቃ
ቸው ፡ አዎን ፡ አምጥቷል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ካል
ጋው ፡ ላይ ፡ ትራስ ፡ አድርጎታል ፡ ብለው ፡
ነገሩት ።

፻፵፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ወደንጉሡ ፡ ላከበት ።
በምርኮ ፡ ጊዜ ፡ ያመጣኸውን ፡ ታቦት ፡ ላክ
ልኝ ፡ በሉት ፡ አለ ፡ ንጉሡም ፡ ከራስጌው ፡
አንሥቶ ፡ ላከለት ።

፻፵፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ይህነን ፡ ታቦት ፡ ዓይቶ ፡ ይህ ፡ ታቦት ፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ የከበረ ፡ ነው ፡
ከሚለው ፡ ዘንድ ፡ ገጹን ፡ ተመልክቶ ፡
አዞሮ ፡ ደግሞ ፡ ጀርባውን ፡ ቢያየው ፡
ይህ ፡ ታቦት ፡ በጳጳሱ ፡ በከማቴ ፡ ብርሃን ፡
በአባ ፡ ሰላማ ፡ እጅ ፡ የተባረከ ፡ የኢትዮ
ጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የአብርሃ ፡ የአጽብሐ ፡
ታቦት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ቅርጽ ፡ አይቶ ።

፻፴፰ ፤ ወዘንተ ፡ ርእዮ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ በከየ ፡ ጥቀ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሚእ
ግበር ፡ እግዚእ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ታቦት፡
ዘነበረ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ርኩሳን ፡ ወበ
ምንት ፡ እሠርእ ፡ ሥጋከ ፡ ቅዱሰ ፡ ወደ
መከ ፡ ክቡረ ፡ ይከውነኒሁ ፡ እቀድስ ፡
ዳግመ ፡ ዘተቀደሰ ፡ በእደ ፡ ጳጳስ ።

፻፴፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይብል ፡ ከመዝ ፡ ወይበኪ ፡
ብዙኃ ፡ መጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ፡ዘብል፡
ኢትብኪ ፡ አ ፡ ፍቁርየ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አኮኑ ፡ አመ ፡ ፈነውኩከ ፡ ትስ
ዕር ፡ ጣዖታተ ፡ ወትቀድስ ፡ ታቦተ ፡
ወትሢም፡ካህናተ፡ወዲያቆናተ ።

፻፵ ፤ ወይእዜኒ ፡ ቀድስ ፡ ታቦተ ፡ ወኢትፍራህ፡
እስመ ፡ አነ ፡ ረሰይኩከ ፡ ብርሃነ ፡ ዓለም፡
ከማየ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ብሔረ፡ጽልመት ።

፻፵፩ ፤ አኮ፡ከመ፡ካልአን ፡ ጳጳሳት ፡ ዘይሰይምዎሙ፡
ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወለከሰ ፡ አነ ፡ ሤም
ኩከ ፡ በአፈ ፡ ዚአየ ፡ እንዘ ፡ እሁበከ ፡
ሥልጣነ ፡ መባሕት ።

፻፵፪ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ አርመመ ፡ ቃል ፡ ወሰ
ሚዖ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሐለየ፡
መጠነ ፡ አሐቲ ፡ ሰዓት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ይከውነኒሁ ፡ ቅዳሴ ፡ ታቦት ፡ ወሢመተ
ክህነት ፡ ዘእንበለ ፡ ቅብዓ ፡ሜሮን ፡ ምንተ
እገብር ፡ አነ ፡ ነዳይ ፡ ዘአልብየ ፡ ቅብዓ ፡
ሜሮን ።

፻፵፫ ፤ ወእንዘ ፡ ይቴክዝ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር፡
አስተርአዮ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡
መላእክት ፡ ቀዊሞ ፡ ውስተ ፡ የማኑ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ ናሁ ፡ አምጻእኩ ፡ ለከ ፡ ቅብዓ ፡
ሜሮን ፡ ወመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ንሥእ ፡
ይቤለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግበር ፡ በከመ ፡
እዘዘከ ፡ ለሊሁ ።

፻፵፬ ፤ ወተፈሥሐ ፡ አቡነ፡ቅዱስ፡ ተክለ፡ሃይማኖት፡
ወተሐሰየ ፡ በመንፈስ ፡ ወገብረ ፡ ቅዳሴ፡
ወቀደሰ ፡ ታቦተ ፡ ወሤመ ፡ ቀሳውስተ ፡
ወዲያቆናተ ።

፻፵፭ ፤ ወለእሙንቱ ፡ ካህናት ፡ ጺውዋን ፡ እለ ፡
ሰገዱ ፡ ለጣዖት ፡ ቅድመ ፡ ቀደሶሙ ፡
ወሤሞሙ ፡ ዳግመ ፡ ወሰመዮሙ ፡ ለኵ
ሎሙ ፡ በበአስማቲሆሙ ፡ ለአሮን ፡ ሰመዮ
ጴጥሮስ ፡ ወለኢዮብ ፡ እንድርያስ ፡ ወለ
ኢሳይያስ ፡ ቶማስ ፡ ወከመዝ ፡ ሰመዮሙ፡
ለ፲ወ፪ ፡ በአስማተ ፡ ፲ወ፪ ፡ ሐዋርያት ።

፻፵፮ ፤ ወአመ ፡ ተፈጸመ ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ወፅአ
ወእስከ ፡ አዲሁ ፡ ኢጥዕመ ፡ እክለ ፡ ንጉሥ
በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኃደረ ፡ ጽውመ ።

፻፴፰ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ይህንን ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ አለቀሰ ፡ አን
ዲህ፡ሲል፡አቤቱ፡ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በረከሱት ፡
ቤት ፡ ስለነበረው ፡ ታቦት ፡ ምን ፡ ባደርግ
ይሻለኛል ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋህንና ፡ ክቡር ፡
ደምህንስ ፡ በምን ፡ እሠራለሁ ፡ ወይስ ፡
በጳጳሱ ፡ እጅ ፡ የተባረከውን ፡ ታቦት ፡
ዳግመኛ ፡ መባረክ ፡ ይሆንልኛልን ።

፻፴፱ ፤ ይህንንም ፡ እያለ ፡ ሲያዝን ፡ ሲቆረቆር ፡
ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጣዖቶችን ፡
ልትሽር ፡ ታቦቱን ፡ ልታከብር ፡ ካህናት
ንና ፡ ዲያቆናትን ፡ ልትሾም ፡ እኔ ፡ ልኬ
ሃለሁና ፡ አትዘን ፡ አለው ።

፻፵ ፤ አሁንም ፡ ታቦቱን ፡ አክብረው ፡ መባረኩ
ንም ፡ አትፍራ ፡ በዚች ፡ በጨለማዪቱ ፡
ሀገር ፡ እንደኔ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ አድር
ጌሀለሁና ።

፻፵፩ ፤ ሹመትህም ፡ እንደ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡
እንደሚሾሟቸው ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ፡ጳጳሳት ፡
አይደለም ፡ ላንተ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ፍጹም ፡
ሥልጣን ፡ ሰጥቼ ፡ በአንደበቴ፡ሾሜሃለሁ ።

፻፵፪ ፤ የመጣውም ፡ ቃል ፡ ይህንን ፡ ተናግሮ ፡
ዝም ፡ አለ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖትም ፡አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በል
ቡናው ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበረ ፡ እንዲህ
እያለ ፡ ክህነት ፡ መስጠትና ፡ ታቦት ፡
መባረክ ፡ ያለቅብዓ ፡ ሜሮን ፡ ይሆናልን፡
ቅብዓ ፡ ሜሮን ፡ የሌለኝ ፡ ደኃ ፡ እኔ ፡ ምን፡
አደርጋለሁ ፡ አለ ።

፻፵፫ ፤ ስለዚያም ፡ ነገር ፡ ሲያዝን ፡ ሲቆረቆር፡
የመላእክት ፡ አለቃ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
በስተቀኙ ፡ ቁሞ ፡ ታየው ፡ እነሆ ፡ ቅብዓ፡
ሜሮንና ፡ ቅዳሴ ፡ መጽሐፍ ፡ አመጣሁልህ
ንሣእ ፡ ተቀበል ፡ እግዚአብሔርንም ፡
እንዳዘዝኩህ ፡ አድርግ ፡ ብሎሃል ፡ አለው።

፻፵፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም
ደስ ፡ ተሰኘ ፡ በሰውነቱም ፡ ሐሴት ፡አደ
ረገ ፡ ታቦቱንም ፡ ባረከ ።

፻፵፭ ፤ ለጣዖት ፡ ሰግደው ፡ የነበሩትንም ፡እነዚ
ያን ፡ ካህናት ፡ አስቀድሞ ፡ ቡራኬ ፡ በዳ
ግመኛው ፡ ቅስና ፡ ዲቁና ፡ ሰጣቸው፡ሁሉን
በየስማቸው ፡ ጠራቸው ፡ አሮንን ፡ ጴጥ
ሮስ ፡ አለው ፡ ኢዮብን ፡ እንድርያስ ፡ ኢሳ
ይያስን፡ቶማስ ፡ አላቸው ፡ እንደዚህ ፡ አድ
ርጎ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ በ፲፪ቱ ፡ ሐዋር
ያት ፡ ስም ፡ ጠራቸው ።

፻፵፮ ፤ የቡራኬው ፡ ጸሎት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
ክቡር ፡ አባታችን ፡ ወጣ ፡ እስከዚያ ፡
ድረስ ፡ ንጉሡ ፡ ገና ፡ እህል ፡ አልቀመሰም ፡
ነበር ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ አክፍሎ ፡ ነበርና ።

፻፶፯ ፤ ወጸቢሖ ፡ ለአከ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኢትሡርዕኑ ፡
ቍርባነ ፡ እስመ ፡ ተመንደብኩ ፡ ፈድፋደ፡
ናሁ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል ፡ እምዘ ፡ ጥዕምኩ ፡
እክለ ።
ወይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለላእካን ፡ በልዎ ፡
ለንጉሥ ፡ ኢትፍራህ ፡ ወልድየ ፡ እምነ ፡
ጾም ፡ እስመ ፡ ጾም ፡ ትፈውስ ፡ ቁስለ ፡
ነፍስ ፡ ወታጸምም ፡ ፍትወተ ፡ ዘሥጋ ፡
ወእሰርዕ ፡ ለከ ፡ ፍጡነ ፡ ቍርባነ ።
፻፶፰ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኃለፉ ፡ ላእካን ፡ ይቤሎ ፡
አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካ
ኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ምንተ ፡ እግበር፡
እስመ ፡ ዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ውእቱ ፡ የዑም ፡ እሠ
ርዕኑ ፡ ቍርባነ ፡ ወእገብር ፡ ምስሐ ፡ በጽ
ባሕ ፡ እንዘ ፡ እፈቅድ ፡ አብ ፡ ሰብአ ፡ ውስተ
ዓቢይ ፡ ክርስቲያን እስእርኑ ፡ ሕገ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ እስርኑ ፡ ሕገ ፡ ክርስቲያን ።
፻፶፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥራዕ ፡
ሎሙ ፡ ቍርባነ ፡ ጊዜ ፡ ፫ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወአ
ንብብ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቅዳሴ ፡ እስከ ፡ ይቤ
ሎሙ ፡ አርእስተ ፡ ግጻዌ ፡ ዐቢያን ፡ እስመ፡
ብዙኃን ፡ ሕዝብ ፡ ሀለዉ ፡ ዘያ
በጽሑከ ፡ እስከ ፡ ዕርበተ ፡ ፀሐይ ።
፻፷ ፤ ወለአከ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ኀበ፡
ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ነዓ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ
ትትመጠው ፡ ቍርባነ ፡ ወመጽአ ፡ ንጉሥ፡
ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊቱ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡
ወይቤልዎ ፡ አፍጥን ፡ ሥርዓተ ፡ ቍርባን፡
እስመ ፡ ሐመምነ ፡ ፈድፋደ ፡ በጽንዓ ፡
ረኃብ ።
፻፷፩ ፤ ወገብረ ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ በኅብስተ ፡
ሰማይ ፡ ወበጽዋዐ ፡ ወይን ፡ ጽሩይ ፡ ወመ
ጠዎሙ ፡ ለንጉሥ ፡ ወለሠራዊቱ ፡ ሥጋሁ
ወደሞ ፡ ለክርስቶስ ።
፻፷፪ ፤ ወኮኑ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወኵሎሙ ፡
ሊቃነ ፡ መላእክት ፡ ይሜግብዎ ፡ በየማኑ፡
ወበፀጋሙ ፡ በአምሳለ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት፡
ወእልቆሞሳት ፡ ውእቱሰ ፡ በአምሳለ፡ ጳጳስ።
፻፷፫ ፤ ወፈጺሞ ፡ መልእክተ ፡ ቍርባን ፡ ወወፅአ፡
ጊዜ ፡ ፲ወ፪ ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ፡ ዘዓርብ ፡
ወኮነ ፡ ሕይወት ፡ ውስተ፡ ኵሉ ፡ ብሔረ ፡
ዳሞት፡በአሚነ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።
፻፷፬ ፤ ወተፈሥሐ ፡ ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሠራ
ዊቱ ፡ ወይቤሎ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ንሣእ ፡ ፲ተ ፪ተ ፡ ልጥረ ፡ ወርቀ፡
ለዘፈቀድከ ፡ ይኩንከ ፡ በእንተ ፡ ዘወሀ
ብከኒ፡ ስመከ፡ ወበእንተ፡ ዘመሐርከኒ፡ ሕገከ።
፻፷፭ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አንሰ ፡ እፈቅድ ፡ ኪያከ
ወአኮ ፡ ንዋይከ ፡ እስመ ፡ ንዋይ ፡ ሥርወ

፻፶፯ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ወደክቡር ፡ አባታችን ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላከ ፡ እነሆ ፡ እህል ፡
ውኃ ፡ ከቀመስኩ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ነውና ፡
በረኃብ ፡ እጅግ ፡ ደክምኩ ፡ ቍርባኑን ፡
አትሠራምን ፡ ብሎ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም፡
መልክተኞችን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡
ለንጉሡም ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፡ ልጄ ፡ ሆይ፡
ከጾም ፡ የተነሣ ፡ አትፍራ ፡ ጾም ፡ የነፍስን፡
ቁስል ፡ ታጠፋለችና ፡ የሥጋንም ፡ ፈቃድ፡
ታደክማለች ፡ እኔም፡ ቍርባኑን ፡ ፈጥኜ፡
እሠራለሁ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።
፻፶፰ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም፡
የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤ
ልን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ እንግዲህ ፡ እንዴት
አደርጋለሁ ፡ ዛሬ ፡ ቀኑ ፡ ዓርብ ፡ ነው ፡
በነግህ ፡ ቍርባን ፡ ሠርቼ ፡ በጧት ፡ ምሳ ፡
አብልቼ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደደገኛይቱ ፡ ክር
ስትና ፡ ማግባት ፡ ስፈልግ ፡ ይልቁን ፡
የክርስቲያንን ፡ ሕግ፡ አፈርሳለሁን፡ አለው።
፻፶፱ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ አባታችንን ፡ እንዲህ
አለው ፡ ፀሐይ ፡ እስክትገባ፡ ድረስ፡ የሚያ
ቆዩህ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉና ፡ ቅዳሴውን
በሦስት ፡ ሰዓት ፡ አድርግለት ፡ የታላላቆ
ቹም ፡ የግጻዌ ፡ አርእስት ፡ እስኪደርሱ፡
ድረስ፡ሥርዓት፡ ቅዳሴውን፡ አድርስ፡ አለው ።
፻፷ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ወደ ፡
ንጉሡ ፡ ላከበት ፡ ቍርባኑን ፡ እንድትቀ
በል ፡ ፈጥነህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ንጉሡም ፡ ከሠ
ራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ መጣ ፡ ንጉሡና ፡
ሠራዊቱ ፡ አባታችንን ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡
ከረኃብ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ደክሞ
ናልና ፡ ቅዳሴውን ፡ ቶሎ ፡ አድርግልን ።
፻፷፩ ፤ አባታችንም ፡ ቍርባኑን ፡ ከሰማይ ፡ በወ
ረደለት ፡ ኅብስትና ፡ ጽሩይ ፡ ወይን ፡ አደ
ረገ ፡ ለንጉሡና ፡ ለሠራ ዊቱም ፡ የክር
ስቶስን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ አቀበላቸው ።
፻፷፪ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤልና ፡ የመላእክት ፡ አለቆች
ሁሉ፡ እንደ፡ ቆሞስና ፡ እንደ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡
ሆነው ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ ይረዱት ፡ ነበር ።
፻፷፫ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ የመሥዋዕቱን ፡
ሥራ ፡ ጨርሶ ፡ ዓርብ ፡ ከቀኑ ፡ በዐሥራ፡
ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ጊዜ ፡ ከመቅደስ ፡ ወጣ ።
የእግዚአብሔርንም ፡ ልጅ ፡ በማሳመን ፡
በዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ፡ ሕይወት፡ተሰጠ ።
፻፷፬ ፤ ንጉሡም፡ከሠራዊቱ ፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ ደስ፡ተሰኘ፡
ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
ሕግን ፡ ስለ ፡ አስተማረ ፡ ስምህንም ፡ ስለ ፡
ሰጠኸኝ ፡ ለወደድከው ፡ ጉዳይ ፡ እንዲሆንህ ፡
ሺህ ፡ ምዝን ፡ ወርቅ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።
፻፷፭ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ መለሰ ፡ እኔ ፡ አንተን ፡
እወዳለሁ ፡ ገንዘብኽን ፡ እይደለም ፡ የኃጢአት፡

እከይ ፡ ውእቱ ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅ
ርዎ ፡ ይረክቦሙ ፡ እኩይ ፡ ወኢይትቀነዩ ፡
ለሠናይ ፡ ወኢይትከሃሎሙ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ፡
በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢትክሉ ፡ ተቀ
ንዩ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፬ ፡ ሉቃስ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ፡
ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ።

፻፷፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ አኮ ፡ ንዋይየ ፡ ባሕቲቱ
አላ ፡ ነፍስየኒ ፡ ወሥጋየኒ ፡ ወኵሉ ፡ ዘብየ፡
ዘአኮ ፡ ውእቱ ፡ ወአስተብቍዖ ፡ ብዙኃ ፡
ከመ ፡ ይትመጠው ፡ እምኔሁ ፡ ወእምድ
ኅረ ፡ ብዙኅ ፡ ስኢል ፡ ተመጠወ ፡ እምኔሁ፡
ዘረወ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡
ወኢያቤተ ፡ ምንተኒ ።

መዝ ፡ ፻፲፩ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፻፷፯ ፤ ወጸንዓ ፡ በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ንጉሥ ፡
ወበዕለተ ፡ ተመጠወ ፡ ቍርባነ ፡ ኮነ ፡ ይሁብ
ለቀሳውስት ፡ ፲ ወ፪ተ ፡ ልጥረ ፡ ወርቅ ፡
ወለዲያቆናት ፡ ፮ተ ፡ እንዘ ፡ ይኩነኒ ፡
ለስርየተ ፡ ኃጢአትየ ፡ ዘገበርክዎ ፡ በኢ
ያእምሮትየ ፡ አንትሙኒ ፡ ትግሁ ፡ ለዓቂበ ፡
ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለአምላኪየ ።

ምዕራፍ ፡ ፵ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡
ይሕንጽ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ውስተ
ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ መንግሥቱ ፡ ወይቤ ፡ እሆ ፡
ወሐነጸ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ቅድመ
ኅበ ፡ ጠፍዑ ፡ ማርያን ፡ ወዳግመ ፡ ኅበ ፡
ተቀትሉ ፡ ሰማዕታት ።

፪ ፤ ወአንበሮ ፡ ህየ ፡ ለታቦተ ፡ ኢየሱስ ፡ ወሰ
መያ ፡ ለይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካነ፡
ኢየሱስ ፡ ወለካልዕታሂ ፡ መካነ ፡ ማርያም ፡
ወለመኳንንቲሁኒ ፡ አዘዞሙ ፡ ይሕንጹ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በበብሔሮሙ ።
፫ ፤ ወተሐንጸ ፡ ብዙኃት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ዳሞት ፡
በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ወነበረ ፡ አቡነ ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮ ፡ ለን
ጉሥ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ወሐዋርያት፡
ወትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወሕይወተ ፡ ዘይ
መጽእ ።
፬ ፤ ወንጉሥሰ ፡ ይብሎ ፡ ዘልፈ ፡ አመንኩ ፡
በኵሉ ፡ ዘትቤለኒ ፡ ወባሕቱ ፡ ትንሣኤ ፡
ሙታንሰ ፡ ሐሰተ ፡ ይመስለኒ ፡ ወይቤሎ፡

ሥሩ ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ ነውና ፡ ገን
ዘብ ፡ የሚወዱትን ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ ያገኛቸ
ዋል ፡ ከቶ ፡ ለበጐ፡ አይጥሩም ፡ ትሩፋትም ፡
ሊሠሩ ፡ አይቻላቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ስት
ወዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማገልገል ፡ አይቻ
ላችሁም ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ እንደ
ተናገረ ። ማቴ ፡ ስባት ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ ሉቃ
ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት፡ ሁለተኛ
ቆሮ ፡ ስድስት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ።

፻፷፮ ፤ ንጉሡም ፡ ለአባታችን ፡ መለሰለት ፡ ገን
ዘብ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሥጋዬም ፡ ነፍ
ሴም ፡ ያለኝም ፡ ሁሉ ፡ የአንተ ፡ ገንዘብ ፡
ነው ፡ አለው ፡ እንዲቀበለውም ፡ ብዙ ፡
ለመነው ። ከብዙም ፡ ልመናም ፡ በኋላ ፡
ወርቁን ፡ ከሱ ፡ ተቀብሎ ፡ ለድኆች ፡ ለችግረ
ኞች ፡ ሰጣቸው ፡ ከገንዘቡም ፡ ምንም ፡ አላስ
ቀረ ።

መዝ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ቍ ፡ ዘጠኝ ።

፻፷፯ ፤ ንጉሡም ፡ በወንጌል ፡ ሃይማኖት ፡ ጸና ፡
ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ በተቀበለ ፡ ቀን ፡
ቍጥር ፡ ለቀሳውስቱ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡
ለዲያቆናቱ ፡ ስድስት ፡ ምዝን ፡ ወርቅ ፡
ይሰጥ ፡ ነበር ፡ በውቀት ፡ ያለውቀት ፡ ለሠ
ራሁት ፡ ኃጢአት ፡ ስርየት ፡ ይሁነኝ ፡
ብሎ ፡ ቀሳውስቱንና ፡ ዲያቆናቱንም ፡ የፈ
ጣሪዬን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ለመጠበቅ
ትጉ ፡ እያለ ፡ ይመክራቸው ፡ ነበረ ።

አርባ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ በመንግሥትህ ፡ ሀገር ፡ ሁሉ
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ ብሎ ፡ ንጉሡን
አዘዘው ፡ ንጉሡም ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ መጀ
መሪያ ፡ ማርያን ፡ ከጠፉበት ፡ ሁለተኛ ፡
ሰማዕታት ፡ ያለቁበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡
ሠራ ።
፪ ፤ የኢየሱስን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ አኖረው ፡
ደብሪቱንም ፡ መካነ ፡ ኢየሱስ ፡ ብሎ ፡
ጠራት ፡ ሁለተኛዪቱን ም ፡ መካነ ፡ ማርያም ፡
አላት ፡ መኳንንቱንም ፡ በየሀገራችሁ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው።
፫ ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በዳሞት ፡ አውራጃ ፡
ሁሉ ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡
ተሠራ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ለንጉሡ ፡ የነቢያትን ፡ የሐዋርያትን ፡ መጻ
ሕፍት ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ሕይወት ፡
ከመ ፡ መላእክት ፡ ሲያስተምረው ፡ ቆየ ።

፬ ፤ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ያልኸኝን ፡ ሁሉ ፡
አምናለሁ ፡ የሙታን ፡ መነሣት ፡ ግን ፡
ሐሰት ፡ ይመስለኛል ፡ ይለዋል ፡ አባታችን፡

አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ይክል ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አንሥኦቶሙ ፡ ለምውታን ፡
ወዓቅሞቶሙ ፡ ቅድመ ፡ ስብሐቲሁ ።
፭ ፤ ወካዕበ ፡ በእሑቲ ፡ ዕለት ፡ ይቤሎ ፡ ንጉሥ፡
ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ እፎ ፡ ይትነሥኡ ፡ ምው
ታን ፡ እምድኅረ ፡ በልየ ፡ አዕፅምቲሆሙ
ወኮነ ፡ ሐመደ ።
፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ፡ ኢተአምንሁ ፡ ከመ ፡
ተንሥአ ፡ ክርስቶስ ፡ እሙታን፡ወይቤሎ ።
ንጉሥ ፡ አአምን ፡ ኪያሁሰ ፡ እስመ ፡ እሬኢ፡
ዘይገብር ፡ ኃይለ ፡ በላዕሌከ ።
፯ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ በዘርዐ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ለም
ውታን ፡ እመሰ ፡ ኢይትነሥኡ ፡ ሙታን ፡
ክርስቶስኒ ፡ ኢተንሥአ ፡ እሙታን ፡ ወእ
መሰ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢተንሥአ ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ
ሃይማኖትነ ፡ ወከንቶ ፡ ተአመነ ፡ ቦቱ ፡
ንሕነ ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ሐሰት ።
ቆሮ ፡ ፩ ፡ ምዕ ፡ ፲፭ ፡ ቊ ፡ ፲፬-፲፭ ።
፰ ፤ ብዙኃ ፡ ስማዕ ፡ አቂሞ ፡ እመጻሕፍተ ፡
ነቢያት ፡ ወሐዋርያት ፡ አይድኦ ፡ ወኢአ
ምነ ፡ በልቡ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለአቡነ ፡
ትንሣኤ ፡ ሙታንሰ፡በዘአአምን ፡ እነግረከ
ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ንግረኒ ፡ ወይቤሎ ፡
ናሁ ፡ ፳ወ፫ ፡ ዓመት ፡ እምዘሞቱ ፡ በአ
ሐቲ ፡ ዕለት ፡ ፲ቱ ፡ ፱፡ሰብእ ፡ እምሠራዊትየ ፡
ወ፫ቱ፱ ፡ እምነ ፡ ማርያን ፡ እምከመ ፡ አንሣ
እኮሙ ፡ ለእሉ ፡ አአምን ፡ ፍጡነ ።
፱ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ በምንት ፡ ኮነ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቶሙ
ለዘመጠነዝ ፡ ሰብእ ፡ በአሐቲ ፡ እለት ።
ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቶሙሰ ፡
ኢትሴአለኒ ፡ ባሕቱ ፡ አንሥአሙ ፡ ከመ ፡
እሙንቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ርእይየ ፡
ኪያሆሙ ።
፲ ፤ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ለእመ ፡ ኢነገርከኒ ፡
አንተ ፡ አነ ፡ እነግረከ ፡ ወይቤሎ ፡ በል
እስኩ ፡ ንግረኒ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ጼወውከ ፡ ብእሲተ ፡ እምብ
ሔረ ፡ ሸዋ ፡ ወፈቀድከ ፡ አውስቦታ ።
፲፩ ፤ ወአዘዝከ ፡ ከመ ፡ ይትገበር ፡ ግእዝ ፡ ወአደ
ምከ ፡ ሠራዊተከ ፡ ከመ ፡ ትረስዮ ፡ ንግ
ሥተ ፡ ኵሉ ፡ ደወለ ፡ መንግሥትከ ፡
ወታስግዳ ፡ ለአማልክቲከ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ
ክሙ ፡ ቀዊመክሙ ፡ ወትእጽሩ ፡ አንተሂ ፡

ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ዘወትር ፡ ሙታንን ፡
አሥነሥቶ፡ በፊቱ ፡ ለማቆም ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ይቻለዋል ፡ ይለው ፡ ነበር ።
፭ ፤ ከዕለታት ፡ ባንዲቱ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ንጉሡ፡
ክቡር ፡ አባታችንን፡ሙታን ፡ አጥንታቸው ፡
ካረጀ ፡ ከበሰበሰ ፡ ዓመድ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡
እንደምን ፡ ይነሣሉ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።
፮ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ም ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን፡
ተለይቶ ፡ እንደተነሣ ፡ አታምንምን ፡ አለው
ንጉሡም ፡ እሱን ፡ ስንኳ ፡ አምናለሁ ፡ ባንተ
አድሮ ፡ የሚሠራውን ፡ ተአምራት ፡ አያ
ለሁና ።
፯ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡
እንዲህ ፡ አለው ፡ ለሙታን ፡ ትንሣኤ ፡
መሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ሙታን ፡ ካልተ
ነሡ ፡ ክርስቶስ ፡ አልተነሣማ ፡ ክርስቶ
ስም ፡ ካልተነሣ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ከንቱ ፡
ነዋ ፡ በከንቱ ፡ አምነናል ፡ እኛም ፡ የሐ
ሰት ፡ ምስክር ፡ ሆነናል ።
አንደኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ምዕራፍ ፡ ቊ ፡ ፲፬-፲፭።
፰ ፤ ከነቢያትና ፡ ከሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡
እየጠቀሰ ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ አምጥቶ ፡ ነገ
ረው ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ በልቡ ፡ አላመነም፡
ንጉሡም ፡ አባታችንን ፡ የሙታንስ ፡ ትን
ሣኤ ፡ በማመን ፡ ገንዘብ ፡ የማምንበትን ፡
እኔ ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለው ። ክቡር ፡ አባ
ታችንም ፡ በል ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፡ ሺህ ፡
ሰዎች ፡ ከሠራዊቴ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡
ከማርያን ፡ ባንዲት ፡ ቀን ፡ ሞቱ ፡ ከሞቱም ፡
እነሆ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመታቸው ፡ ነው ፡
እነዚህን ፡ ብታሥነሣልኝ ፡ ፈጥኜ ፡ አምን
ሃለሁ ፡ አለው ።
፱ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡
አለው ፡ ይህን ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡ ባን
ዲት ፡ ቀን ፡ የሞቱበት ፡ ምክንያት ፡ ምን
ድነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ንጉሡም ፡ አባ
ታችንን ፡ እነሱን ፡ አይቼ ፡ የሙታንን ፡
ትንሣኤ ፡ እንዳምን ፡ አሥነሣቸው ፡ እንጂ
የሞታቸውንስ ፡ ምክንያት ፡ አትጠይቀኝ ፡
አለው ።
፲ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ አንተ ፡ ባትነግረኝ፡
እኔ ፡ እነግርሀ ፡ የለም ፡ አለው ፤ ንጉሡም፡
በል ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፡ ክቡር ፡
አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ከሸዋ ፡
አውራጃ ፡ ሴት ፡ ማርከህ ፡ ልታገባት ፡
ብትወድ ።
፲፩ ፤ ለአምላኮችህ ፡ አስግደህ ፡ በመንግሥትህ
አውራጃ ፡ ታነግሣት፡ ዘንድ ፡ ሠራዊትህን፡
ሁሉ ፡ ቀጠርህ ፡ የጋብቻውም ፡ ሥርዓት ፡
እንዲፈጸም ፡ አዘዝክ ፡ አንተም ፡ የተሰበ
ሰቡትም ፡ ሠራዊትህ ፡ ቆማችሁ ፡ ስትመ

ወጉቡአኒከ ፡ ግብተ ፡ በረቀ ፡ መብረቅ ፡
እምሰማይ ፡ ወመሰጠ ፡ እምአዕይንቲከሙ።
፲፪ ፤ ወበዝንቱ ፡ ግርማ ፡ ሞቱ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ
ወአንተ ፡ ኮንከ ፡ እንበዘ ፡ ልብ ፡ እምይ
እቲ ፡ ዕለት ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አህየውኩከ ፡
በስመ ፡ አምላኪየ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡
አቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቦኑ ፡ መኑ ፡ ነገ
ረከ ፡ ዘንተ ፡ ወይቤሎ ፡ አምላኪየ ፡ ዘየአ
ምር ፡ ኵሎ ።

፲፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ተአምርኑ ፡ ሀገረ ፡ ለይእቲ ፡
ብእሲት ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ነድግሰ ፡
ሀገራ ፡ ላቲኒ ፡ አእምራ ፡ እምየ ፡ ይእቲ ፡
ወላዲትየ ፡ ወደንገፀ ፡ ሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡
ወሰገደ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለቅዱስ ።

፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ሊተሰ ፡ መሰለኒ ፡ ዘአዕረገዋ ፡
ሰማያተ ፡ በአይቴ ፡ ወለደተከ ፡ በሰማይኑ፡
ወሚመ ፡ በምድር ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡
በሰማይሰ ፡ ኢይወልዱ ፡ ኢይትዋለዱ ፡
አላ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይከውኑ ፡ ሊተሰ ፡ ወለደተኒ ፡ በሀገራ ።

ማቴ ፡ ምዕ ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፴ ።

፲፭ ፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ አስተበቍዓከ ፡ አ ፡
አቡየ ፡ ቅዱስ ፡ ንግረኒ ፡ ጥዩቀ ፡ ቅድመ ፡
ዜወውናሃ ፡ ወለደተከ ፡ አው ፡ እምድኅረ ፡
ግብኢታ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አ ቡነ ፡ ተክለ
ሃይማኖት ፡ ዳዕሙ ፡ እምድኅረ ፡ ግብኢታ ፡
ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ በአማን ፡ አንተ ፡ ወልዳ ፡
ለይእቲ ፡ ቅድስት ።

፲፮ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አርእየኒ ፡ መቃብሪሆሙ ፡ ለእሙንቱ ፡
ሙታን ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ በአይቴ ፡
አእምር ፡ መቃብሪሆሙ ፡ እመኒ ፡ በል
ዕዎሙ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ኢየአምር ፡
ወለእመኒ ፡ በልዕዎሙ ፡ አራዊት ፡ ወወ
ፅአ ፡ ቅዱስ ፡ እምኀቤሁ ፡ ወቆመ ፡ በመ
ርህበ ፡ መልበርዲ ፡ ወሰገደ ፡ በብረኪሁ ፡
ወጸለየ ።
፲፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ዘአምጻእኮ ፡ ለሰብእ ፡ እምኀበ ፡
ኢሀሎ ፡ ወካዕበ ፡ ትሬስዮ ፡ ከመ ፡ ዘኢ
ሀሎ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአንሣእኮ ፡ ለአ
ልዓዛር ፡ እመቃብር ፡ በጽዋዒ ፡ ቃልከ ።
፲፰ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአንሣእካ ፡ ለወለተ
ኢያኤሮስ ፡ ሶበ ፡ ትቤላ ፡ ተንሥኢ ፡
ጣቢታ ።
ማቴ ፡ ፱ ፡ ፳፭ ። ማር ፡ ፭ ፡ ፵፩-፵፪፡ ሉቃ፡ ፰፡ ፶፩

ለከቱ ፡ ሳላችሁ ፡ ድንገት ፡ መብረቅ ፡ ከሰ
ማይ ፡ በርቆ ፡ ከፊታችሁ ፡ ነጠቃችሁ ።
፲፪ ፤ በዚህ ፡ ግርማ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ፡
አንተም ፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምረህ ፡ በአም
ላኬ ፡ ስም ፡ እኔ ፡ እስከፈወስኩህ ፡ ድረስ፦
ልበ ፡ ተላላ ፡ ዝንጉ ፡ ሁነህ ፡ ኖርክ ፡ አለው፡
ንጉሡም ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠህ ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ በውኑ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ማን፡
ነገረህ ፡ አለው ፡ ክ ቡ ር ፡ አ ባ ታ ች ን ም
ሁሉን ፡ የሚያውቅ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነዋ ፡ አለው።
፲፫ ፤ ንጉሡም ፡ የዚያችን ፡ የሴት ፡ አገሯን
ታውቀዋለህን ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታች
ንም ፡ ሀገሯንስ ፡ ተዎውና ፡ እሷን ፡ ራሷን
አውቃታለሁ ፡ የወለደችኝ ፡ እናቴ ፡ ናት ፡
አለው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ፡ ተንሥቶ ፡
ለአባታችን ፡ ሰገደለት ፡ ከጫማው ፡ ወደቀ።
፲፬ ፤ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ለኔስ ፡ ወደሰማይ ፡
ያወጧት ፡ መስሎኝ ፡ ነበረ ፡ በወዴት ፡
ሳለች ፡ ወለደችህ ፡ በሰማይስ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡
በምድር ፡ ነው ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታ
ችንም ፡ በሰማይስ ፡ አያገቡም ፡ አይወለ
ዱም ፡ አይዋለዱም እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡
መላእክት ፡ ይሆናሉ ፡ እንጂ ፡ እኔንስ ፡
በሀገሯ ፡ ነው ፡ የወለደችኝ ፡ አለው ።

ማቴ ፡ ሃያ ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፴ ።

፲፭ ፤ ንጉሡም፡ ክቡር ፡ አባታችንን ፡ አባቴ ፡
ሆይ ፡ እለምንሃለሁ ፡ እውነቱን ፡ ንገረኝ ፡
ቀድሞ ፡ ሳንማርካት ፡ ወለደችህን ፡ ወይስ ፡
ከተመለሰች ፡ በኋላ ፡ ወለደችህ ፡ አለው ፡
ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ከተመለሰች ፡ በኋላ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ ንጉሡም ፡ በው
ነት ፡ የዚያች ፡ የተመረጠች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
አንተ ፡ ነህ ፡ አለው ።
፲፮ ፤ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ንጉሡን ፡
የሊህን ፡ የሞቱትን ፡ መቃብራቸውን ፡
አሳየኝ ፡ አለው ፡ ንጉሡም ፡ መቃብራቸ
ውን ፡ ወዴት ፡ አውቀዋለሁ ፡ የሰማይ ፡
አዕዋፍም ፡ የምድር ፡ አራዊትም ፡ በልቷ
ቸው ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፡ አለ ፡ ክቡር፡
አባታችንም ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቶ ፡
በመልበርዴ ፡ ሜዳ ፡ ቁሞ ፡ በጉልበቱ ፡
ሰግዶ ፡ አመለከተ ።
፲፯ ፤ ሰውን ፡ ካለመኖር ፡ ወደመኖር ፡ ያመጣ
ኸው ፡ ያለውንም ፡ እንደሌለ ፡ የምታደ
ርገው ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ
አልዓዛርን ፡ ከመቃብር ፡ በቃልህ
ጠርተህ ፡ ያሥነሣኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፲፰ ፤ የኢያኤሮስን ፡ ልጅ ፡ ያሥነሣሃት ፡ አንተ ፡
ነህ ፡ ተነሽ ፡ ጣቢታ ፡ ብለህ ፡ በጠራሃት ፡
ጊዜ ።
ማቴ ፡ ፱ ፡ ፳፭ ፡ ማር ፡ ፭ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ፡ ሉቃ
፰ ፡ ፶፭ ።

፲፱ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአንሣእኮ ፡ ለወልደ ፡ መበለት ፡ በሀገረ ፡ ናይን ፡ እጊዚኦ ፡ ንፍቆ ፡ በብሂለ ፡ ወሬዛ ፡ ተንሥእ ።

ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።

፳ ፤ ወይእዜኒ ፡ አንሥኦሙ ፡ ለምውታን ፡ በኃይልከ ፡ ከመ ፡ ይእመኑ ፡ ብከ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወይጽናዕ ፡ ልቦሙ ፡ በፍቅረ ፡ ዚአከ ።

፳፩ ፤ ወእንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ከመዝ ፡ መጽአ ፡ ቃል፡ እምሰማይ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኦ ፡ ፍፍርየ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ኵሎ ፡ ዘሰአልከኒ ፡ እገብር ፡ ለከ ፡ ጸውዕ ፡ ሙታነ ፡ በቃልከ፡ ወይትነሥኡ ፡ ለከ ፡ ከመ ፡ ይትአመር ፡ ጽንዓ ፡ ፍቅርየ ፡ በላእሌከ ።

፳፪ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ጸርሐ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኵልክሙ ፡ ነፍሳት ፡ ዘሀሎክሙ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ መርህብ ፡ ተንሥኡ ፡ በኃይለ ፡ አምላኪየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፳፫ ፤ ወሶቤሃ ፡ ተንሥኡ ፡ ፲ወ፪ ፡ እደው ፡ ወቆሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ፡ ባርከነ ፡ ኦ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡ ሞትነ ፡ በእንተ ፡ እምከ ፡ ወናሁ ፡ ተንሣእነ ፡ በኃይለ፡ ጸሎትከ ።

፳፬ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ አይቴ ፡ ነበርክሙ ፡ ወይቤልዎ ፡ ነበርነ ፡ እንዘ ፡ ንሣቀይ ፡ በውስተ ፡ ሲኦል ፡ ወጸውዖ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ለንጉሥ ። ወይቤሎ ፡ ርኢ ፡ እልክተ ፡ እደወ ፡ እለ ፡ ተንሥኡ ፡ እሙታን፡ ወርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ ደንገፀ ፡ ወስዕነ ፡ ተናግሮ ።

፳፭ ፤ ወኵሎሙ ፡ ጉቡአን ፡ ፈርሁ ፡ ወደንገፁ፡ ወይቤሉ ፡ ሰብእኑ ፡ ዝብእሲ ፡ ወሚመ፡ አምላክ ፡ ወተስእሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለእለ ፡ ተንሥኡ ፡ ሰብኡ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ሀሎኑ ፡ ኩነኔ ፡ እምድኅረ ፡ ሞት ።

፳፮ ፤ ወይቤልዎ ፡ ኦ ፡ ንጉሥ ፡ ምንተ ፡ ንነግረከ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔረ ፡ ጽልመት ፡ ወብካይ ፡ ፲ቱ፻ ፡ ዘከመዝ ፡ ፀሐይ ፡ ሶበ፡ ቦኡ ፡ ኅበ ፡ ውእቱ ፡ መካነ ፡ ጽልመት ፡ እምኢክህሉ ፡ ያብርሁ ፡ ለ፩ ፡ ብእሲ ፡ ህየ ፡ ነበርነ ።

፳፯ ፤ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ አንሥጠጠ ፡ ኵለንታሁ ፡ ወፈርሃ ፡ ጥቀ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ በድን እስከ ፡ ገሠሦ ፡ ቅዱስ፡ ወአጽንዖ ፡ ወይቤ ፡

፲፱ ፤ ናይን ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ የነበረውን ፡ የመበለት ፡ ልጅ ፡ ቃሬዛውን ፡ ይዘህ ፡ አንተ ፡ ጐልማሳ ፡ ሆይ ፡ ተነሥ ፡ በማለት ፡ ያሥነሣኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።

፳ ፤ አሁንም ፡ ሙታንን ፡ በከሃሊነትህ ፡ አንሣቸው ፡ ሕዝብህ ፡ የሙታንን ፡ ትንሣኤ፡ አምነው ፡ ልባቸው ፡ በፍቅርህ ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፡ እያለ ፡ አመለከተ ።

፳፩ ፤ እንዲህም ፡ ሲያመለክት ፡ ከሰማይ ፡ ቃል፡ መጣ ። ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ሆይ ፡ የለመንከኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ሙታንን ፡ በቃልህ ፡ ጥራ ፡ የፍቅሬ ፡ ጽናት ፡ ባንተ ላይ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ይነሡልሃል ፡ አለው ።

፳፪ ፤ ያን ፡ ጊዜም፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ፡ ነፍሳት ፡ ሁላችሁ ፡ በዚች ፡ ሜዳ ፡ የተቀበራችሁ ፡ በፈጣሪዬ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ ተነሡ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ።

፳፫ ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች፡ ተነሥተው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ባርከን ፡ በእናትህ ፡ ምክንያት ፡ ሞተን ፡ ስለነበርን ፡ እነሆ ፡ በጸሎትህ ፡ ኃይል ፡ ተነሣን ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ።

፳፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ወዴት ፡ ነበራችሁ፡ አላቸው ፡ በሲኦል ፡ መከራ ፡ ስንቀበል ፡ ነበርን ፡ አሉት ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ንጉሡን ፡ ጠርቶ ፡ ከሙታን ፡ ተለይተው፡ የተነሡትን ፡ እይ ፡ አለው ፡ ንጉሡም ፡ ዓይቶ ፡ ደነገጠ ፡ መናገርም ፡ ተሣነው ።

፳፭ ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ፈጽመው ፡ ፈሩ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አምላክ ፡ ነው አሉ ፡ ንጉሡም ፡ የተነሡትም ፡ ጠየቃቸው ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ኩነኔ ፡ አለን ፡ አላቸው ።

፳፮ ፤ ንጉሡንም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የዚህንማ ፡ የጨለማውን ፡ ሀገርና፡ የመከራውን ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንነግርሃለን፡ እንደዚህ ፡ ዓለም ፡ ፀሐይ ፡ ያሉ ፡ እልፍ ፡ ፀሐዮች ፡ ከዚያ ፡ ከጨለማው ፡ ሥፍራ ፡ ቢገቡ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ ሊያበሩ ፡ ባልቻሉም ፡ ነበር ፡ እኛም ፡ ከዚያ፡ነበርን።

፳፯ ፤ ንጉሡም ፡ ሰምቶ ፡ ሰውነቱ ፡ ተንዋወጠ፡ ሁለንተናው ፡ ስግጥጥ ፡ ስግጥጥ ፡ ይል፡ ጀመር ፡ እጅግም ፡ ፈራ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ዳሰ ፡ እስኪያጸናው ፡ ድረስ ፡ እንደ፡ በድን ፡ ሆነ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡

ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይኬ
ሰብእ ፡ ዝ ፡ ኵሉ ፡ ይጸንሖ ።
፳፰ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለእሙ
ንቱ ፡ እደው ፡ በምንት ፡ ግብር ፡ መጻእ
ክሙ ፡ ዝየ ፡ ወይቤልዎ ፡ እንዘ ፡ ሀሎነ ፡
ማእከለ ፡ ጽልመት ፡ ዘእሳት ፡ መጽአ ፡
ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ አውፅአነ ፡
ወአብጽሐነ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት፡
ወርኢናሁ ፡ ለዝብእሲ ፡ ቀዊሞ ፡ ከመ ፡
ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ቅድመ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥ ።
፳፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለሚካኤል ፡ ኅበ ፡
እሎንተ ፡ ነፍሳተ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ወሰሚዖ ፡ ቃሎ ፡ አወፈየነ ፡ ሎቱ ፡ ወው
እቱ ፡ ጸውዓነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኵልክሙ፡
ነፍሳት ፡ እለ ፡ ሀሎክሙ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡
መርህብ ፡ ተንሥኡ ፡ ፃዑ ፡ ወንዑ ፡ ኅቤየ፡
ወመጻእነ ፡ ኅቤሁ ፡ ወቆምነ ፡ ቅድሜሁ ፡
ወሀሎነ ፡ በከመ ፡ ትሬእየነ ።
፴ ፤ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ለንጉሥ ፡ አ ፍሥሐ፡ ጽዮን ፡ አእመርከኑ ፡
ከመ ፡ ሀሎ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወይቤሎ ፡
እወ ፡ አመንኩ ፡ ወአእመርኩ ፡ ከመ ፡
አምላክከ ፡ ይክል ፡ ቀቲለ ፡ ወአሕይዎ ፡
ወአልቦ ፡ ግብር ፡ ዘይስአኖ ።

ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፮ ።

፴፩ ፤ ወባሕቱ ፡ ምንተ ፡ ትኤዝዘኒ ፡ እግበር ፡
ከመ ፡ እድኅን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኵነኔ ፡
በሰማዕኩ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ እምይእ
ዜሰ ፡ አልብከ ፡ ኵነኔ ፡ እስመ ፡ ዘየአምን ፡
በወልድ ፡ ቦ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ሕቱም፡
ውእቱ ፡ በስመ ፡ ዚአሁ ።

ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፮ ።

፴፪ ፤ ወባሕቱ ፡ አንተ ፡ ነገረ ፡ እኤዝዘከ ፡ ኅበ ፡
ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወለ
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወትረክብ ፡ መዝ
ገበ ፡ ዘሰማያት ፡ እስመ ፡ ሃይማኖት ፡
ወምጽዋት ፡ ይሰሪ ፡ ኃጢአተ ።

ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ፡

፴፫ ፤ ወሀበ ፡ ንጉሥ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ብዙኀ ፡ ንዋየ ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡
መንግሥቱ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ሎቱ ፡ ምጽ
ዋተ ፡ ውእቱኒ ፡ ነሢአ ፡ እምኔሁ ፡ ዘረወ ፡
በከመ ፡ ይቤሎ ፡ ወእምዝ ፡ አጥመቆሙ ፡
ለእሉ ፡ እደው ፡ እለ ፡ ተንሥኡ ፡ እሙታን፡
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡

ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ዓይቶ ፡ ወይ
ሰው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እኮ ፡ ይቆየዋልን ፡ አለ።
፳፰ ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ እሊህን ፡ ሰዎች ፡ በምን
ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ መጣችሁ ፡ አላቸው ፡
በእሳት ፡ ጨለማ ፡ መሃከል ፡ ሳለን ፡ የመ
ላእክት ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል ፡ መጥቶ ፡
አወጣን ፡ የክብር ፡ ባለቤቱ ፡ ከሚሆን ፡
ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ አደረሰን ፡ ይህንንም ፡
ሰው ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ምሰሶ ፡ ከዚያ ፡
በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቁሞ ፡ ዓየነው ።
፳፱ ፤ ንጉሡም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ እሊህን ፡
ነፍሳት ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስጥ ፡ አለው
እሱም ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ ለሱ ፡ ሰጠን ፡
እሱም ፡ በዚች ፡ ሜዳ ፡ ያላችሁ ፡ ሁላችሁ ፡
ነፍሳት ፡ ተነሡ ፡ ውጡ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡
ጠራን ፡ ወደሱ ፡ መጥተን ፡ በፊቱ ፡ ቆምን፡
ይኸው ፡ እንደምታየን ፡ አለን ፡ አሉት ።

፴፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ንጉሡን ፡ ፍሥሐ ፡
ጽዮን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ መኖሩን ፡ አወ
ቅህን ፡ እሱም ፡ አዎን ፡ አመንኩ ፡ አም
ላክህም ፡ መግደልና ፡ ማዳን ፡ እንዲችል፡
የሚሳነውም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ አመንኩ።

ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፮ ።

፴፩ ፤ ከዚህ ፡ ከሰማሁት ፡ ቅጣት ፡ እድን ፡
ዘንድ ፡ እንድሠራው ፡ የምታዘኝ ፡ ምንድ
ነው ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ንጉ
ሡን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ቅጣት ፡ የለብ
ህም ፡ በወልድ ፡ ያመነ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይ
ወት ፡ አለውና ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ክር
ስቲያን ፡ ተብሏልና ።

ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፮ ።

፴፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ አዝሃለሁ ፡
እድናለሁ ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ የሰጡት፡ ምጽ
ዋት ፡ ኃጢአትን ፡ ያስተሠርያልና ፡ ለድ
ሆችና ፡ ለችግረኞች ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያ
ንም ፡ ምጽዋት ፡ ስጥ ፡ ይህን ፡ ብታደርግ ፡
በሰማይ ፡ ድልብ ፡ ታከማቻለህ ።

ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ።

፴፫ ፤ ንጉሡም ፡ ለክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ምጽዋት ፡ ስጥልኝ ፡ ብሎ ፡
እስከ ፡ መንግሥቱ ፡ እኩሌታ ፡ ድረስ ፡
ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠ ፡ እሱም ፡ ከንጉሡ
ተቀብሎ ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፡ ገንዘቡ
ንም ፡ ለድሆች ፡ ለችግረኞች ፡ በተነ
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ከሙ
ታን ፡ ተለይተው ፡ የተነሡትን ፡ እሊ
ያን ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡
በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡

ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ወፈነዎሙ ፡ ይስብኩ ፡ ትንሣኤ ፡ እሙታን ፡ ለኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ዳሞት ።

ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

፴፩ ፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለአቡነ ፡ እምይእዜሰ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ መሐረኒ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡ ልብከ ፡ ዘይሠምር ፡ ቦቱ ፡ አምላክከ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አምላኪየሰ ፡ ይፈቅድ ፡ ፍኖተ ፡ ንጹሐ ፡ ወሕሊና ፡ ሠናየ ።

፴፪ ፤ ኅትት ፡ ማርያን ፡ እለንተ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ መንግሥትከ ፡ ወአጥፍአሙ ፡ ኩና ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ከመ ፡ አቡሁ ፡ ወቀም ፡ ላቲ ፡ ለእሙ ፡ ከመ ፡ ምታ ፡ ወትከውን ፡ ወልዶ ፡ ለልዑል ፡ ወትነግሥ ፡ በጽድቅ ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር።

፴፫ ፤ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ያምጽኡ ፡ ፍጡነ ፡ ኵሎ ፡ ማርያነ ፡ ዘተረክቡ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ መንግሥቱ ፡ ወአምጽእዎሙ ፡ ፍጡነ ፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ አውዕይዎሙ ፡ በእሳት ፡ ወአውዐይዎሙ ፡ ወአጥፍእ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወተስእሎ ፡ ማሪት ፡ እምኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ዳሞት ፡ በስብከቱ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፴፬ ፤ ወሤሞሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለእሙንቱ ፡ ፲ወ፪ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ ይስብኩ ፡ ወንጌለ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐወርተ ፡ ዳሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቶሙ ፡ ወለገብረ ፡ ዋሕድኒ ፡ ሴሞ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኖሙ ፡ አበ ፡ ሀየንቴሁ ፡ ወነበረ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሔረ ፡ ዳሞት ፡ መጠነ ፡ ፲ወ፪ ፡ ዓመት ።

፴፭ ፤ ወመልአ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኵሉ ፡ በሐውርቲሃ ፡ እስከ ፡ ምድረ ፡ ባርያ ፡ ወእስከ ፡ ፈለገ ፡ ግዮን ፡ ወእስከ ፡ ፈለገ ፡ ሆመል ፡ ወኵሎን ፡ አህጉር ፡ እለ ፡ ይትጋወራ ፡ ምስለ ፡ ዳሞት ፡ እምና ፡ በክርስቶስ ፡ በእደዊሁ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ምዕራፍ ፡ ፵፩ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ወዐርገ ፡ መልዕልተ ፡ ዝባፈተን ፡ በሀየ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ቅድስተ ፡ ወጾመ ፡ እንዘ ፡ ኢይጥዕም ፡ ምንተኒ ፡ ወበዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የሐምል ፡ ሐምለ ፡ ገዳም ፡ ዘእንበለ ፡ ይሕሪ ፡ መሪረ ፡ ወጥዑመ ፡ ወይብልዕ ፡ ጥሬዮ ፡ በበሰናብት ፡ ወማየሰ ፡

አጠመቃቸውና ፡ ለዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ።

ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

፴፩ ፤ ንጉሡም ፡ አባታችንን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰውነቴ ፡ በጅህ ፡ የተጨበጠች ፡ በእግርህ ፡ የተረገጠች ፡ ናትና ፡ አምላክህ ፡ የሚወደውን ፡ በልቡናህ ፡ ያለውን ፡ በጎ ፡ ትምህርት ፡ አስተምረኝ ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ አምላኬስ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ንጹሕ ፡ አኗኗር ፡ ይወዳል ።

፴፪ ፤ እሊህን ፡ ማርያንን ፡ በመንግሥትህ ፡ አውራጃ ፡ ያሉትን ፡ መኖራቸውን ፡ ጠይቀህ ፡ አጥፋቸው ፡ ለድኃ ፡ አደጉም ፡ ልጅ ፡ እንደአባቱ ፡ ሁንለት ፡ ለናቱም ፡ እንደ ፡ ባሏ ፡ ረዳት ፡ ሁናት ፡ ይህነን ፡ ብታደርግ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ትባላለህ ፡ በሰማይና ፡ በምድርም ፡ በውነት ፡ ትነግሣለህ ።

፴፫ ፤ ንጉሡም ፡ በነገሥኩበት ፡ አገር ፡ የተገኙትን ፡ ማርያንን ፡ ሁሉ ፡ በቶሎ ፡ አምጡልኝ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ፈጥነው ፡ አመጡለት ፡ በእሳት ፡ አቃጥሏቸው ፡ አለ ፡ አቃለት ፡ በእሳት ፡ አቃጥሏቸው ፡ አለ ፡ አቃለት ፡ በክቡር ፡ አባታችን ፡ ስብከት ፡ ጠሉለት ፡ በክቡር ፡ አባታችን ፡ ስብከት ፡ ከዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ዛር ፡ ጠንቋይ ፡ መጠየቅ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ጠፋ ።

፴፬ ፤ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ እለዚያን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ካህናት ፡ ሾማቸው ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ በዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡ ስለኔ ፡ አባት ፡ ይሁናችሁ ፡ ብሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድን ፡ ሾመላቸው ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ኖረ ።

፴፭ ፤ ከአውራጃዋ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ጥቁር ፡ ምድርና ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ እስከ ፡ ወሞ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ የክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡ መላ ፡ ለዳሞት ፡ አውራጃ ፡ አቅራቢያ ፡ የሆነ ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ፡ በክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እጅ ፡ በክርስቶስ ፡ አመነ ።

ምዕራፍ ፡ አርባ ፡ አንደኛ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ዝባፈተን ፡ በሚባል ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ በዚያው ፡ ሥፍራ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሳይቀምስ ፡ ከአጽዋማት ፡ ልዩ ፡ የምትሆን ፡ አርባ ፡ ጾምን ፡ ዓርብ ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መራራ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የሚጣፍጥ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሳይመርጥ ፡

ኢይሰቲ ፡ ፍጹመ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡
ዘመነ ፡ ጾም ።

፪ ፤ ወበዕለተ ፡ ፋሲካ ፡ ጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡
እንተ ፡ ይእቲ ፡ ትንሣኤሁ ፡ እምርት ፡ መጽአ
ኀቤሁ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እንዘ ፡ ሚካኤል ፡ በየማኑ ፡ ወገብርኤል ፡
በፀጋሙ ፡ ወማርያም ፡ እሙ ፡ ፲ወ፪ ፡ ሐዋ
ርያቲሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ወብዙኃን ፡ ሐራ ፡
ሰማይ ፡ ይትልውዎ ።

፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡ ፍቁርየ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ሰላመ ፡ አቡየ ፡ ወሰላመ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሃሉ ፡ ምስሌከ ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም ፡ ተፈሣሕ ፡ ወተሐሠይ ፡ እስመ ፡
ስምከ ፡ ተጽሕፈ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማ
ያት ፡ ወእንዘ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ ብከ ፡ እስመ ፡
አባዕከ ፡ ሊተ ፡ ብዙኃ ፡ ምሕርካ ።

ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

፬ ፤ ወበከመ ፡ አስተፍሣሕከኒ ፡ አንተ ፡ አነሂ ፡
መጺእኩ ፡ ከመ ፡ አስተፍሥሕከ ፡ ዮም ፡ ቅድ
ስናሆሙ ፡ ለነቢያትየ ፡ ወእሴቶሙ ፡ ለሐ
ዋርያትየ፡የሃሉ ፡ ዘልፈ ፡ ምስሌከ ፡ ወከመ ፡
ጊዮርጊስ ፡ ዘልዳ ፡ ሞገስየ ፡ ይትከዓው ፡
ውስተ ፡ ስምከ ።

መዝሙር ፡ ፹፰ ፡ ፪ ።

፭ ፤ ወኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ተዝካረከ ፡ እመሂ ፡
በኀብስት ፡ አው ፡ በዕጣን ፡ ወበቍርባን ፡
እስከ ፡ ጽዋዓ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ ይኅልፍ ፡ ምስ
ሌከ ፡ በግህደት ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ ወለኵሉ ፡ ዘይጼውዕ ፡ ስመከ ፡
በዕለተ ፡ ምንዳቤሁ ፡ አነ ፡ አድኅኖ ፡ እመ
ንሱት ።

ማቴ ፡ ፲ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ።

፮ ፤ ወኀበ ፡ ተሰምየ ፡ ስምከ ፡ እመሂ ፡ በገዳም ፡
ወእመሂ ፡ በአብያት ፡ ህየ ፡ ይኩን ፡ ሣህል ፡
ወምሕረት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፯ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ወሀቦ ፡ ቆጽለ ፡ ገነት ፡
ወጽዋዓኒ ፡ ዘእማየ ፡ ሕይወት ፡ ወይቤሎ ፡
ንሣእ ፡ ዘንተ ፡ ብላዕ ፡ ወስተይ ፡ በልዓ ፡
ወሰትየ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ነፍሱ ፡ ወመሰሎ ፡
ከመ ፡ ዘኢጾመ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ ፡ ወጠፍአ ፡
እምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኵሉ ፡ ሕገ ፡ ሥጋ ፡
እምኔሁ ።

የምድረ ፡ በዳ ፡ ቅጠል ፡ እየለቀመ ፡ እሑ
ድና ፡ ቅዳሜ ፡ ይመገብ ፡ ነበረ ፡ ወኀ፡
ቢሆን ፡ የጾሙ ፡ ወራት ፡ እስኪፈጸም ፡
ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡ አይጠጣም ፡ ነበረ ።
፪ ፤ በፋሲካም ፡ ዕለት ፡ ይችውም ፡ የታወቀች ፡
ጌታ ፡ የተነሣባት ፡ የምትሆን ፡ ናት ፡ መን
ፈቀ ፡ ሌሊት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ሚካኤልን ፡ በቀኙ ፡
ገብርኤልን ፡ በግራው ፡ አድርጎ ፡ እናቱን ፡
ማርያምን ፡ ፲፪ቱ ፡ ሐዋርያትን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡
ይዞ ፡ ብዙዎቹንም ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡
አስከትሎ ፡ ወደሱ ፡ መጣ ።
፫ ፤ እንዲህ ፡ አለው ፡ ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ የባ
ሕርይ ፡ አባቴ ፡ የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ሕይ
ወቴ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍቅር ፡ አንድ
ነት ፡ ለዘላለም ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፡ ስምህ
በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተጽፏልና ፡ ደስ ፡
ይበልህ ፡ ሐሤትን ፡ አድርግ ፡ እኔም ፡ ባንተ ፡
ደስ ፡ ተሰኘሁ ፡ ሐሤትንም ፡ አደረግሁ ፡
ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አግብተህልኛልና ።

ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

፬ ፤ አንተም ፡ ደስ ፡ እንዳሰኘኸኝ ፡ እኔም ፡
ደግሞ ፡ ደስ ፡ ላሰኝህ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡
መጣሁ ፡ የነቢያቶቼ ፡ ቅድስናቸው ፡ የሐ
ዋርያቶቼ ፡ ክብራቸው ፡ በረከታቸው ፡ ዘወ
ትር ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፡ የኔ ፡ የባለሟ
ልነት ፡ ሞገስ ፡ በስምህ፡ እንደ፡ልዳዊ ፡ ጊዮ
ርጊስ ፡ ይሁን ።

መዝሙር ፡ ፹፰ ፡ ፲

፭ ፤ በዓልህን ፡ የሚያከብር ፡ ስምህን ፡ የሚያ
ስጠራ ፡ ሁሉ ፡ በእንጀራም ፡ ቢሆን ፡ በዕ
ጣንም ፡ ቢሆን ፡ በመሥዋዕትም ፡ ቢሆን ፡
እስከ ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡ ድረስ ፡ ባንተ ፡ ስም ፡
እንግዳ ፡ ቢቀበል ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በግልጽ ፡
ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይለፍ ፡ በመከ
ራም ፡ ቀን ፡ ስምህን ፡ የጠራውን ፡ ሁሉ ፡
እኔ ፡ ከጥፋት ፡ አድነዋለሁ ።

ማቴ ፡ ፲ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ።

፮ ፤ ስምህም ፡ በተጠራበት ፡ በገዳምም ፡ ቢሆን ፡
በዓለምም ፡ ቢሆን ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡
ለዘለዓለም ፡ ይቅርታና ፡ ቸርነት ፡ ከዚያ ፡
ይኑር ፡ በውነት ፡ ያለሐሰት ።
፯ ፤ ይህነንም ፡ ተናግሮ ፡ የገነት ፡ ቅጠል ፡ የሕ
ይወት ፡ ውኃ ፡ ጽዋ ፡ ሰጠው ፡ ንሣ ፡ ይህንን
ብላ ፡ ይህንም ፡ ጠጣ ፡ አለው ፡ በላ ፡ ጠጣ ፡
ሰውነቱም ፡ ደስ ፡ ተሰኘች ፡ አንድ ፡ ቀንስ ፡
ስንኳ ፡ እንዳልጾመ ፡ መሰለው ፡ ከዚያችም ፡
ቀን ፡ ወዲህ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ጠፋለት

፳ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ እምይእዜሰ ሑር ፡ ምድረ ፡ አምሐራ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ በጸሎት ፡ ሚካኤል ፡ ዘግሼት ፡ ወንበር ፡ ህየ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ እነግረከ ፡ ወሚካኤል ፡ መልአከ ፡ ምክርየ ፡ የሃሉ ፡ ምስሌከ ፡ ወሰዓሞ ፡ አፉሁ ፡ ወአንበረ ፡ እዴሁ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ወባረኮ ፡ ወዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ በዓቢይ ፡ ስብሐት ።

፳፩ ፤ ወይቤ ፡ አቡነ፡ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይትባረክ ፡ እግዚኦ ፡ ስመ ፡ ስብሐቲከ ፡ ዘወሀብከኒ ፡ ዘመጠንዝ ፡ ጸጋ ፡ ለኃጥእ ፡ ገብርከ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፪ ።

፩ ፤ ወተፈጺሞን ፡ እማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ሖረ ፡ ቅዱስ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ወይቤሎ ፡ ጽናዕ ፡ በሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወትጋህ ፡ ለዓቂበ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንሰ ፡ አሐውር ፡ ኀበ ፡ አዘዘኒ ፡ አምላኪየ ።

፪ ፤ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ በከየ ፡ ብካየ ፡ ብዙኀ ፡ ወይቤ ፡ አ ፡ አቡነ ፡ ለመኑ ፡ ተኃድግ ፡ ሀገረከ ፡ ዘሐነጽካ ፡ በሃይማኖትከ ፡ ወአድኃንካ ፡ እምእደ ፡ ሰይጣን ፡ በጸሎትከ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይትከሃለኒ ፡ እትዓደው ፡ እምትእዛዘ ፡ እግዚእየ ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ አስተጋብአሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ምስለ ፡ ሊቃውንት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኩኑ ፡ ውሩያነ ፡ ወቅኑያነ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ አርአያ ፡ መርዔቱ ፡ ወረዓየ፡ሕዝበ ፡ በጽድቅ ፡ ወበኵሉ ፡ ተግሣጽ ፡ መንፈሳዊት ከመ ፡ ኢይትኃሠሥ ፡ ደሞ ፡ እምኔክሙ።

፬ ፤ ናሁ ፡ አንሰ ፡ እሑር ፡ ኀበ ፡ ዘፈነወኒ ፡ አምላኪየ ፡ ወአንትሙሰ ፡ ጽንዑ ፡ ወሀልዉ ፡ ዝየ ፡ ወዕቀቡ ፡ ሊተ ፡ ደቂቅየ ፡ በፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢታማስንዎሙ፡ እስመ ፡ ዘአግብአሙ ፡ እግዚአብሔር ። ኀቤሁ ፡ በአርአዮ ፡ ኃይላት ፡ ወመንክራት ፡

፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ካህናት ፡ ንሕነሰ ፡ ነሐውር ፡ ምስሌከ ፡ ወኢንትፈለጥ ፡ እምኔከ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ተሰፋነ ፡ እምታሕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሐሰ ፡ ለክሙ ፡ ትሑሩ ፡ ምስሌየ ፡ አላ ፡

፳ ፤ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ የግሼቱ ፡ አባ ፡ በጸሎት ፡ ሚካኤል ፡ ወዳለበት ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ምድር ፡ ሂድ ውጣ ፡ ብዬ ፡ እስክነግርህ ፡ ድረስ ፡ ከዚያው ፡ ተቀመጥ ፡ የምክሬም ፡ መልአክ፡ ሚካኤልም ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አፉን ፡ ሳመው ፡ እጁንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ ባረከውና ፡ በፍጹም ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ዐረገ ።

፳፩ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ለኔ ፡ ለኃጢአተኛው ፡ ባሪያህ ይኸንን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ የሰጠኸኝ ፡ አቤቱ ፡ ምስጉን ፡ የሆነ ፡ ስምህ ፡ የከበረ ፡ ይሁን ፡ አለ ።

አርባ ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የተነጋገሩባቸው ፡ ዕለታት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ከንጉሡ ፡ ከፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ዘንድ ፡ ሂዶ ፡ እኔ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወደ አዘዘኝ ፡ እሄዳለሁና ፡ ክርስቶስን ፡ በማመን ፡ ጸንተህ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ በመጠበቅ ፡ ተግተህ ፡ ኑር ፡ አለው ።

፪ ፤ ንጉሡም ፡ ይህንን ፡ ሰምቶ ፡ ብዙውን ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሰ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ በጸሎትህ ፡ ከሰይጣን ፡ እጅ ፡ ያዳንሃትን ፡ በሃይማኖትህ ፡፡ ያነጽሐትን ፡ አገርህን ፡ ለማን ፡ ትተዋለህ ፡ አለው ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ከፈጣሪዬ ፡ ትእዛዝ ፡ ትተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኛልን ፡ አይቻለኝም ፡ አለው ።

፫ ፤ ክቡር፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ዳግመኛ ፡ ካህናቱን ፡ ሁሉ ፡ ካለቃቸው ፡ ከገብረ ዋሕድ ፡ ጋራ ፡ ሰብስቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ለክርስቶስ፡ መንጋዎች ፡ ለምእመናን ፡ የበጎ ፡ አብነት ፡ እንድትሆኗቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡የምትገዙ ፡ ቅኖች ፡ ሁኑ ፡ ሕዝቡንም ፡ በውነት ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ሁሉ ፡ ጠብቋቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ደማቸውን ፡ ከናንተ ፡ እንዳይሻ ።

፬ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወዳዘዘኝ ፡ ሥፍራ፡ እሄዳለሁ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ልጆቼንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ጠብቁልኝ ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅን ፡ ተአምራት ፡ በማድረግ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የሰበሰባቸውን ፡ ሕዝቡን ፡ አትበትኗቸው ።

፭ ፤ እነዚያም ፡ ካህናት ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ እኛስ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እንሄዳለን ፡ ከፈጣሪያችን ፡ ከእግዚአብሔር ብታች ፡ ተስፋችን ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ካንተ ፡ አንለይም ፡ አሉ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ከዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ እንጂ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ መሄድ ፡ አይሆንላችሁም ፡ ሕዝቦቼን ፡

ንብሩ ፡ ዝየ ፡ ወዕቀቡ ፡ መርዔትየ ፡ ወበዝ
ንቱ ፡ ይሠምር ፡ ልብየ ።

፮ ፡ ወገብረ ፡ ዋሕድኒ ፡ ኮነ ፡ ይበኪ ፡ ፈድፋደ ፡
እምኵሎሙ ፡ እስመ ፡ ቀዳማይ ፡ ወልዱ ፡
ውእቱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምኵሎሙ ፡
ሰብእ ፡ ዳሞት ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ኢት
ብኪ ፡ ወልድየ ፡ እላ ፡ ጽናዕ ፡ በሃይማኖት ፡
ርትዕት ፡ በዘመሐርኩከ ፡ ወአጽንዖሙ ፡
ለአብያጺከ ፡ መሃይምናን ።

፯ ፡ ወይቤሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ከመ ፡ ምንት ፡
እከውን ፡ ኃጢአየ ፡ ኪያከ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ቀጸላ
ርእስየ ፡ ወብርሃን ፡ ለአዕይንትየ ፡ ወጽንዓ ፡
ኃይልየ ፡ ወስርጋዌ ፡ ኵሎን መልክእየ ፡
እመውት ፡ አንሰ ፡ በእግርከ ፡ ከሙ ፡ ትቅ
ብረኒ ፡ አንተ ።

፰ ፡ ወይቤሎ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ለምንት ፡ ትሰ
ብረኒ ፡ ልብየ ፡ ሶበ ፡ አኃድገከ ፡ በሥጋየ ፡
ወበመንፈስየ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌከ ፡ ዘልፈ ፡
ወበብዙኃ ፡ ጣዕመ ፡ ቃሉ ፡ አኃድጎ ፡ ብካየ።
ወአስተፋነውዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ንጉሥ ፡ ወሠ
ራዊቱ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ንኡ
ሶሙ ፡ ወዓቢዮሙ ፡ እንዘ ፡ ይበክዩ ፡ መሪረ።

፱ ፡ ወይቤሎ ፡ ሶበሰ ፡ ኀደገኒ ፡ በሥጋከ ፡ ኢትኅ
ድገነ ፡ በመንፈስከ ፡ ወተዘከረነ ፡ በጸሎትከ ፡
አ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ተመየጡ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይዘከረነ ፡ ለኵልነ ፡ ወሰ
ዓሙ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወተመይጡ ፡
ሀገሮሙ ።

፲ ፡ ወቅዱስኒ ፡ ሖረ ፡ ፍኖቶ ፡ ተጽዒኖ ፡ ዲበ ፡
ሠረገላ ፡ ብርሃን ፡ እንተ ፡ ነበ ፡ መጽአ ፡
ፍኖት ፡ ወኃደረ ፡ ነበ ፡ መሃይምናኒሁ ፡
ዘመሐሮሙ ፡ ቅድመ ፡ ወርእዮሙ ፡ ኪያሁ ።
ሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ወተአምኅዎ ፡ ወይቤልዎ ፡
ለምንት ፡ ዘመጠነዝ ፡ ጐንደይከ ፡ ዘእንበለ ፡
ትምጻእ ፡ ኀቤነ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ይትከሀለ
ኒኑ ፡ በፈቃድየ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚ
አብሔር ።

፲፩ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ አኀሰመኑ ፡ ጸላዒ ፡
ላዕሌክሙ ፡ ዳግመ ፡ ወይቤልዎ ፡ አልቦ ፡
ዳህነ ፡ ሀሎነ ፡ በጸሎትከ ፡ ወባሕቱ ፡ ሐዳ
ጣን ፡ ድውያን ፡ ሀለዉ ፡ በሀገርነ ፡ ወይቤ
ሎሙ ፡ አምጽእዎሙ ፡ ኀቤየ ፡ ወአምጽኡ ፡
ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ዱያነ ፡ ዘተረክቡ ፡ ውስተ ፡
ሀገር ፡ ወገሠሦሙ ፡ ወአሕየዎሙ ፡ ወኮነ ፡
ሕይወት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔሮሙ ።

፲፪ ፡ ወእምድኅረ ፡ ሐወጸ ፡ ኵሎ ፡ መሃይምናነ ፡
ዘሰበከ ፡ ሎሙ ፡ ቅድመ ፡ በጽሐ ፡ ውስተ ፡
ሀገረ ፡ ዞረሬ ፡ ወረከበ ፡ በህየ ፡ ፡ ብእሲተ ፡

ጠብቁልኝ ፡ የኔም ፡ ልቡናዬ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡
ይፈቅዳል ።

፮ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድም ፡ ከዳሞት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በፊት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የወለደው ፡
የመጀመሪያ ፡ ልጁ ፡ ነውና ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡
አብዝቶ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ፡ ክቡር ፡ አባታ
ችንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ አታ
ልቅስ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ባስተማርኩህ ፡
በቀናችው ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተህ ፡ ያመኑትን፡
ባልንጀሮችህን ፡ አጽናቸው ፡ አለው ።

፯ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡
የዓይኖቼ ፡ ብርሃን ፡ የጉልበቴ ፡ ብርታት ፡
የመልኮቼ ፡ ሁሉ ፡ ጌጥ ፡ የራሴ ፡ ቀጸላ ፡
ከለላዬ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አንተን ፡ አጥቼ ፡
እንዴት ፡ እሆናለሁ ፡ እኔስ ፡ አንተ ፡ እን
ድትቀብረኝ ፡ እግርህ ፡ በታች ፡ አሁኑኑ ፡
እሞታለሁ ፡ አለ ።

፰ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡
ልጄ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ልቤን ፡ ትከፍልብኛ
ለህ ፡ በሥጋዬ ፡ ብለይህ ፡ በልቤ ፡ በመን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘወትር ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡
እኖራለሁ ፡ በነገሩም ፡ ጣዕም ፡ ብዛት ፡
ልቅሶውን ፡ አስተወው ፡ ክቡር ፡ አባታ
ችንም ፡ ንጉሡና ፡ ሠራዊቱ ፡ የሀገርም ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ታናናሾቹም ፡ ታላላቆቹም ፡
ሁሉ ፡ መሪር ፡ ዕንባ ፡ እያለቀሱ ፡ ሸኙት ።

፱ ፡ በሥጋ ፡ ብትለየን ፡ በልብህ ፡ አትለየን ፡
በጸሎትህም ፡ አስበን ፡ አሉት ፡ እሱም ፡
እንዲህ ፡ አላቸው ። እግዚአብሔር ፡ ሁላ
ችንን ፡ ያስበን ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ፡ እጁን ፡
እግሩንም ፡ ስመው ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ተመ
ለሱ ።

፲ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ በብርሃን ፡ ሠረገላ ፡
ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ መንገድ ፡ ተመ
ልሶ ፡ ሄደ ፡ ቀድሞ ፡ አስተምሯቸው ፡ ካመ
ኑት ፡ ሰዎች ፡ ቤት ፡ አደረ ፡ እነሱም ፡ እሱን ፡
ዓይተው ፡ ሰገዱለት ፡ ወደኛ ፡ ሳትመጣ ፡
ይህነን ፡ ያህል ፡ ቀን ፡ ለምን ፡ ቆየህ ፡ እያሉ ፡
ሳሙት፡ እሱም ፡ ያለ፡ እግዚአብሔር ፡ፈቃድ
በኔ ፡ ፈቃድ ፡ ይቻለኛልን ፡ አላቸው ።

፲፩ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ጠላታችሁ ፡
ሰይጣን ፡ ዳግመኛ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠራባ
ችሁን ፡ አለ ፡ የለም ፡ ባንተ ፡ ጸሎት ፡ እኛ ፡
ደህና ፡ ነን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ በሽ
ተኞች ፡ በሀገራችን ፡ አሉ ፡ አሉት ፡ ወደኔ ፡
አምጧቸው ፡ አለ ፡ በሀገር ፡ የተገኙትን ፡
ድውያን ፡ ሁሉ ፡ አመጡለት ፡ ዳሶ ፡ አዳና
ቸው ። በሀገራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ጤና ፡ ሆነ ።

፲፪ ፡ ቀድሞ ፡ ወንጌልን ፡ ሰብኮላቸው ፡ ያመኑ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከጐበኘ ፡ በኋላ ፡ ዞረሬ
ከምትባል ፡ ሀገር ፡ ደረሰ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምራ፡

ዘማዊት ፡ ዘኮነ ፡ ይሬእያ ፡ እምትካት ፡ እንዘ፡
ትዜሙ ፡ ወይቤላ ፡ አ ፡ ብእሲቶ ፡ እስከ፡ ማዕ
ዜኑ ፡ ትዜምዊ ፡ ኢያእክለኪኑ ፡ ዝንቱ ፡
ኃሣር ።
፲፫ ፡ ወትቤሎ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ **አ፡ አቡየ ፡
ቅዱስ** ፡ ኢይትከሃለኒ ፡ እኅድግ ፡ ዘንተ ፡
ወባሕቱ ፡ ይነድድ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ልብየ፡
ወሀሎ ፡ ጋኔን ፡ ዘያዜምወኒ ፡ ዘእንበለ ፡
ፈቃድየ ፡ አ፡ ብእሴ ፡ **እግዚአብሔር** ፡በዘት
ክል ፡ ርድአኒ ፡ ወባልሐኒ ፡ እምዝንቱ ፡ ጻማ።

፲፬ ፡ ወአተበ ፡ ገጻ ፡ በትእምርተ ፡ **መስቀል** ፡
እንዘ ፡ ይብል ፡ ፃዕ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እም
ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ወወፅአ ፡ ሰይጣን ፡
እምኔሃ ፡ በአምሳለ ፡ ብእሲት ፡ ዓመት ፡
ኀስምት ፡ ጥቀ ፡ ወጽፉር ፡ ስእርተ ፡ ርእሱ ፡
እንዘ ፡ ይኬልህ ፡ ወይብል ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡
አይቴ ፡ እጐይይ ፡ እምኔከ ፡ እስመ ፡ ተመ
ንደብኩ ፡ በዠለሄ ፡ ወኅጣዕኩ ፡ ኀበ ፡ እመ
ስጥ ።
፲፭ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ጠፍአ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ ወእ
ምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነት ፡ ጽንዕተ ፡ ይእቲ ፡
ብእሲት ፡ ውስተ ፡ ፈሪሃ ፡ **እግዚአብሔር** ።

፲፮ ፡ ወተጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወዐ
ዝማዲሁኒ ፡ ወይቤሉ ፡ ስብሐት ፡ **ለእግዚ
አብሔር** ፡ ዘአርአየነ ፡ ገጸከ ፡ ወአስምዓነ ፡
ቃለከ፡አይቴ ፡ እማንቱ ፡ አዕይንተ ፡ አቡከ ፡
ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ከመ ፡ ይርአያ ፡ ዘንተ ፡ ሀብተ ፡
ጸጋ ፡ ዘተውህበ ፡ ለከ ፡ አይቴ ፡ ውእቶን ፡
አዕይንተ ፡ እምከ ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ ከመ ፡
ይርአያ ፡ ዘኮንከ ፡ ነቢየ ፡ ወሐዋርያ ፡ ወሰ
ባኬ ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፲፯ ፡ ወርእዮሙ ፡ ኃይለ ፡ ዘይትልዎ ፡ እምጽኡ ፡
ኵሎ ፡ ዱያነ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወአ
ንበርዎሙ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ እንዘ ፡
ይብሉ ፡ አኅይዎሙ ፡ አባ ፡ በጸሎትከ ።

፲፰ ፡ ወዓተበ ፡ **ቅዱስ** ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወአኅየ
ዎሙ ፡ ወአተው ፡ በፍሥሐ ፡ ውስተ ፡ አብ
ያቲሆሙ ፡ ወተፈሥሑ ፡ አዝማዲሁ ፡ ወሰ
ብሕዎ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ዘወሀቦ ፡ ዘመ
ጠንዝ ፡ ጸጋ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፫ ።

፩ ፡ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት** ፡ ከመ ፡ ይሖር ፡ ምድረ ፡ እምሐራ ፡
ወእንዘ ፡ የሐውር ፡ ረከቦ ፡ ለ፩ ፡ መነኮስ ፡
ወዓተበ ፡ ገጾ ፡ እምርኁቅ ፡ ወጸለየ ፡ ጸሎተ፡
ወንጌል ፡ ወውእቱ ፡ መነኮስ ፡ ጸለየ ፡ ከማሁ፡

ስትሴስን ፡ ያያት ፡ የነበረች ፡ ሴሰኛ ፡ ሴት ፡
በዚያ ፡ አገኛት ፡ ሴትዮ ፡ ይህ ፡ ጉስቍልና ፡
አይበቃሽምን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡
ትሴስኛለሽ ፡ አላት ።
፲፫ ፡ ሴቲቱም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፡**ክቡር ፡ አባቴ**
ሆይ ፡ ይህንን ፡ መሰሰኑን ፡ ለመተው ፡
አይቻለኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡
እሳት ፡ ይነዳል፡ ያደረብኝ ፡ መንፈስ ፡
ዝሙት ፡ አለ ፡ ሥራውን ፡ ያለፈቃዴ ፡ ያሠ
ራኛል ፡ **የእግዚአብሔር** ፡ሰው ፡ ሆይ ፡ በሚ
ቻልህ ፡ ርዳኝ ፡ ከዚህም ፡ ጉስቍልና ፡ አድ
ነኝ ፡ አለችው ።
፲፬ ፡ ፊቷን ፡ **በመስቀል** ፡ አምሳያ ፡ አማተበና ፡
አንተ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ከዚች ፡ ሴት ፡
ላይ ፡ ውጣ ፡ አለው ፡ ሰይጣኑም ፡ በጥፉ ፡
ሴት ፡ ባሪያ ፡ አምሳል ፡ የራሱ ፡ ጠጉር ፡
የተጎነጎነ ፡ ሆኖ ፡ እየጮኸ ፡ እየተንጸረጸረ ፡
በሁሉ ፡ ወገን ፡ ተቸግሬአለሁና ፡ ወዮልኝ ፡
የማመልጥበት ፡ አጣሁ ፡ ካንተ ፡ ወዴት ፡
እሸሻለሁ ፡ እያለ ፡ ከሴቲቱ ፡ ወጣ ።

፲፭ ፡ ይህነንም ፡ ተናግሮ ፡ እንደጢስ ፡ ተኖ ፡
እንደትቢያ ፡ በኖ ፡ ጠፋ ፡ ይቺም ፡ ሴት ፡
ከዚያን ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ **እግዚአብሔርን** ፡
በመፍራት ፡ ጸንታ ፡ ኖረች ።
፲፮ ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘመዶቹም ፡ እንዲህ ፡
አሉ ፡ ፊትህን ፡ ላሳየን ፡ ድምፅህን ፡ ላሰማን
ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግ
ባው ፡ አሉ ፡ ይህንንስ ፡ ላንተ ፡ የተሰጠ
ህን ፡ የጸጋ ፡ ሀብት ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ያባትህ ፡
የጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ዓይኖቹ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፡
ለመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የሚያበቃ ፡
የወንጌል ፡ መምህር፡አዲስ ፡ ሐዋርያ ፡ የተ
ባልከው ፡ ነቢይ ፡ የሆንከው ፡ አንተን ፡
ያዩ ፡ ዘንድ ፡ የእናትህ ፡ **የእግዚእ፡ሐረያ** ፡
ዓይኖቿ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፡ እያሉ ፡ አደነቁ ።
፲፯ ፡ የሚከተለውንም ፡ ኃይል ፡ አይተው ፡ በሀ
ገርም ፡ ያሉትን ፡ ድውያን ፡ ሰብስበው ፡
ከእግሩ ፡ በታች ፡ አፈሰሷቸው ፡ **ክቡር ፡
አባታችን** ፡ ሆይ ፡ በጸሎትህ ፡ አድናቸው ፡
እያሉ ፡ ለመኑት ።
፲፰ ፡**ክቡር ፡ አባታችንም** ፡ አማትቦ ፡ አዳናቸ
ውና ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወደቤታቸው ፡ ገቡ ፡
ዘመዶቹም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይህንን ፡
ያህል ፡ ክብር ፡ የሰጠውን ፡ **እግዚአብሔ
ርን** ፡ አመሰገኑት ።

አርባ ፡ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡**ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት** ፡ ወደእማራ ፡ ምድር ፡ ሊሄድ ፡
ተነሣ ፡ ሲሄድም ፡ አንዱን ፡ መነኩሴ ፡
አገኘው ፡ ገና ፡ ከሩቅ ፡ ሳለ ፡ ፊቱን ፡ አማ
ትቦ ፡ የወንጌሉን ፡ ጸሎት ፡ ጸለየ ፡ ያም ፡

እስመ ፡ ልማዶሙ ፡ ለመነኰሳት ፡ ከመ፡ገ ፡
ውእቱ ፡ ይጸልዩ ፡ እምቅድመ ፡ ይትራከቡ ፡
ወእምድኅሬሁ ፡ ይትአምኁ ፡ ወበዝ ፡ ትእ
ምርተ ፡ ጸልዮ ፡ **ቅዱስ** ፡ ተአምኆ ፡ ለው
እቱ ፡ መነኰስ ።

፪ ፡ ወይቤሎ ፡ ዳህንኑ ፡ አባ ፡ ወይቤሎ ፡ ዳህን
በጸሎትከ ፡ ወይቤሎ ፡ **ቅዱስ** ፡እምአይቴ ፡
መጻእከ ፡ ወይቤሎ ፡ እምብሔረ ፡ አምሐራ ፡
እምደብረ ፡ አቡነ ፡ በጸሎተ ፡ **ሚካኤል** ፡
ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አይቴ ፡ ተሐውር ፡ ወይ
ቤሎ ፡ መነኰስ ፡ ኢየአምር ፡ ብሔረ ፡ ኀበ ፡
አይ ፡ አሐውር ፡ ወባሕቱ ፡ ኀበ ፡ አብጽ
ሐኒ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ አሐውር ።

፫ ፡ ወይቤሎ ፡ **ቅዱስ** ፡ ለምንት ፡ ተሐውር ፡ ዘኢ
ተአምር ፡ መካኖ ፡ አንሰ ፡ እብል ፡ ኀቤየ ፡
ፈነወከ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ተመየጥ ፡ እን
ከሰ ፡ ተማልአኒ ፡ ንሑር ፡ ሀገረከ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ መነኰስ ፡ ኢየሐውር ፡ በምንት ፡
ግብር ፡ ይፈንወኒ ፡ ኀቤከ ።

፬ ፡ ወይቤሎ ፡ **ቅዱስ** ፡ ከመ ፡ ትሚጥ ፡ ኪያየ ፡
ኃጥእ ፡ እምኢያእምሮ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡
ወትምርሐኒ ፡ መካነከ ፡ ከመ ፡ እትምሐር ፡
ህየ ፡ ሥርዓተ ፡ ወሕገ ፡ ወይቤሎ ፡ መነኰስ ፡
አንሰ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ለሐዊር ፡ ምስሌከ ፡
